
1
ጭጉ መሠረት
ወንጌሉን
የማሰራጨት ዘዴ
የጠራይ ኪዝን

ማውጫ

ትምህርት 1:- መጽሐፍ ቅዱስን ማስተዋወቅ 1
ትምህርት 2:- «በመጀመሪያ እግዚአብሔር...» 13
ትምህርት 3:- «በመጀመሪያ እግዚአብሔር...» 24
ትምህርት 4:- ሰይጣንና መላእክቱ 29
ትምህርት 5:- እግዚአብሔር ከምንም ነገር ሁሉንም ነገር ፈጠረ። 40
ትምህርት 6:- የእግዚአብሔር ተፈጥሮና ባሕርይ በመፍጠር ሥራው ውስጥ ተገልጧል። 45
ትምህርት 7:- የሰው ልጅ ልዩ አፈጣጠርና በምድር ላይ የተሰጠው ልዩ ሥልጣን 60
ትምህርት 8:- እግዚአብሔር አዳምን በኤደን አኖረው 75
ትምህርት 9:- እግዚአብሔር ሔዋንን ፈጠረ 91
ትምህርት 10:- እስካሁን ድረስ ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ሰይጣንና ስለ ሰው የተሰጡትን ትምህርቶች ከልስ 96
ትምህርት 11:- አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ሳይታዘዙ ቀሩ። 103
ትምህርት 12:- የእግዚአብሔር የተስፋ ቃልና ርግማን። 119
ትምህርት 13:- የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታና የእግዚአብሔር ፍርድ...130
ትምህርት 14:- እግዚአብሔር ቃየንንና መሥዋዕቱን ሳይቀበል ቀረ፤ አቤልንና መሥዋዕቱን ግን ተቀበለ። 138
ትምህርት 15:- የቃየን ዝርያዎችና ሴት፥ ሄኖክና ኖኅ። 158
ትምህርት 16:- እግዚአብሔር ዓለምን እቀጣለሁ አለ። ነገር ግን ኖኅንና ወደ መርከቡ የሚገቡትን ሁሉ ለማዳን ቃል ገባ። 167
ትምህርት 17:-የእግዚአብሔር ፍርድ በዓለም ላይና የእግዚአብሔር ታዳጊነት ለኖኅና በመርከቡ ውስጥ ለነበሩ ሁሉ። 178
ትምህርት 18:- እግዚአብሔር የባቢሎንን ግንብ ለመገንባት የተሰበሰቡ ዓመፀኞችን በተናቸው። 187
ትምህርት 19:- እግዚአብሔር አብራምን መረጠው፥ ጠራው፥ መራው። 193
ትምህርት 20:- እግዚአብሔር ለሥራ ቃል ኪዳን ገባላት፥ የአብራምን ተስፋም አደሰ። 199
ትምህርት 21:- እግዚአብሔር ሰዶምና ገሞራን ደመሰሰ። 205

ጽኑ መሠረት

ጸሐፊው፡- ትሬቨር ምክኢልዌን

ተርጓሚው፡- ጌቱ ግዛው

ክፍል ሁለት

አንደኛ መጽሐፍ

LAPSLEY / BROOKS FOUNDATION, INC.
1701 N. GREENVILLE AVE. ST. 810
RICHARDSON, TEXAS 75081, USA

Copyright © 1996 by SIM, Addis Ababa, Ethiopia: Originally published in English under the title of BUILDING ON FIRM FOUNDATIONS, Copyright © 1988 by New Tribes Mission, Sanford, U.S.A. All rights reserved.

ማውጫ

ትምህርት 1:- መጽሐፍ ቅዱስን ማስተዋወቅ 1
ትምህርት 2:- «በመጀመሪያ እግዚአብሔር...» 13
ትምህርት 3:- «በመጀመሪያ እግዚአብሔር...» 24
ትምህርት 4:- ሰይጣንና መላእክቱ 29
ትምህርት 5:- እግዚአብሔር ከምንም ነገር ሁሉንም ነገር ፈጠረ። 40
ትምህርት 6:- የእግዚአብሔር ተፈጥሮና ባሕርይ በመፍጠር ሥራው ውስጥ ተገልጧል። 45
ትምህርት 7:- የሰው ልጅ ልዩ አፈጣጠርና በምድር ላይ የተሰጠው ልዩ ሥልጣን 60
ትምህርት 8:- እግዚአብሔር አዳምን በኤደን አኖረው 75
ትምህርት 9:- እግዚአብሔር ሔዋንን ፈጠረ 91
ትምህርት 10:- እስካሁን ድረስ ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ሰይጣንና ስለ ሰው የተሰጡትን ትምህርቶች ከልስ 96
ትምህርት 11:- አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ሳይታዘዙ ቀሩ። 103
ትምህርት 12:- የእግዚአብሔር የተስፋ ቃልና ርግማን። 119
ትምህርት 13:- የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታና የእግዚአብሔር ፍርድ...130
ትምህርት 14:- እግዚአብሔር ቃየንንና መሥዋዕቱን ሳይቀበል ቀረ፤ አቤልንና መሥዋዕቱን ግን ተቀበለ። 138
ትምህርት 15:- የቃየን ዝርያዎችና ሴት፥ ሄኖክና ኖኅ። 158
ትምህርት 16:- እግዚአብሔር ዓለምን እቀጣለሁ አለ። ነገር ግን ኖኅንና ወደ መርከቡ የሚገቡትን ሁሉ ለማዳን ቃል ገባ። 167
ትምህርት 17:-የእግዚአብሔር ፍርድ በዓለም ላይና የእግዚአብሔር ታዳጊነት ለኖኅና በመርከቡ ውስጥ ለነበሩ ሁሉ። 178
ትምህርት 18:- እግዚአብሔር የባቢሎንን ግንብ ለመገንባት የተሰበሰቡ ዓመፀኞችን በተናቸው። 187
ትምህርት 19:- እግዚአብሔር አብራምን መረጠው፥ ጠራው፥ መራው። 193
ትምህርት 20:- እግዚአብሔር ለሥራ ቃል ኪዳን ገባላት፥ የአብራምን ተስፋም አደሰ። 199
ትምህርት 21:- እግዚአብሔር ሰዶምና ገሞራን ደመሰሰ። 205

ትምህርት 1

አጠቃላይ ርእስ፡- መጽሐፍ ቅዱስን ማስተዋወቅ

የትምህርቱ አስተዋጽኦና መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. የእግዚአብሔርን መልእክት ልንነግራችሁ መጥተናል።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ለ. እግዚአብሔር በመጽሐፉ ውስጥ የተናገራቸውን ሁሉ እናምናለን።

ሐ. የእግዚአብሔር መልእክት በመላው ዓለም ከሚገኙ መልእክቶች ሁሉ የላቀ ነው።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

መ. በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር መልእክቱን ለመረጣቸው ሰዎች ሰጣቸው።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ሠ. መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ብዙ የተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሟል።

ረ. እኛም መጽሐፍ ቅዱስን ልናስተምራችሁ እየተረጐምነው ነው።

ሰ. በራሳችሁ ቋንቋ ልታነቡት እንድትችሉ እናስተምራችኋለን።

ከቅድመ የወንጌል ትምህርት ውስጥ የተውጣጡ የክለሳ ጥያቄዎች

መምህር ሆይ፡- በቅድመ የወንጌል ትምህርት ከፍለ ጊዜ ሕዝቡን የጠየቅካቸውን ከእግዚአብሔርና ከሌሎች መንፈሳዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች አስታውሳቸው። የወንጌል ማስተማር ሥራህን ስትጀምር በቅድመ የወንጌል ትምህርት ከፍለ ጊዜ ጥለኸው በነበረው መሠረት ላይ በአምንታዊ መንገድ መገንባትህን ትያያዛለህ።

ሀ) መልስ ያላገኙላቸውን ወይም እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ እምነቶች ያሳዩባቸውን ጥያቄዎች በተናጠል አስታውሳቸው።

ለ) በቅድመ የወንጌል ሥራ ክፍለ ትምህርት ጊዜ ሰዎች የተለያዩ እምነቶች እንዳላቸው የነገርካቸውን ጉዳዮች አስታውሳቸው።

ሐ) ጥያቄዎችን አቅርበህ እነርሱ መልስ እንድትሰጥባቸው ቢገፋፉህም አንተ ግን መልስ ያልሰጠህባቸውን ጊዜያት አስታውሳቸው።

መ) ስለ መንፈሳዊ ጉዳዮች በዓለምና በእነርሱ አእምሮ ጭምር ያለውን ግራ የሚያጋባና የተምታታ ጉዳይ አስታውሳቸው።

የቅድመ ወንጌል ትምህርት አገልግሎትህ ለሕዝቡ እጅግ አሉታዊ ሆኖ ታይቶ ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም ለተጠየቅካቸው ጥያቄዎች ምንም መልስ አልሰጠኻቸውምና ነው። አሁን ግን መልሶችን መስጠት ልትጀምር ነው፤ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን ታስተዋውቃቸው ዘንድ ግድ ይሆናል።

ያም ሆኖ ግን በዚህ በመጀመሪያ ትምህርት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለመሆኑ የማረጋገጥ ዕቅድ የለንም። ወንጌላውያን፥ ወንጌልን ላልሰሙ የተለያዩ ሕዝቦች መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ተሽቀዳድመው ለማረጋገጥ የሞከሩባቸውን ትምህርቶች ተመልክቼአለሁ። ገና በመጀመሪያ ትምህርታቸው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ለማረጋገጥ በብሉይ ኪዳን የተነገሩ ትንቢቶች በአዲስ ኪዳን እንዴት እንደተፈጸሙ ይጠቅሳሉ። ግን የእግዚአብሔርን ቃል ጨርሶ ሰምተው ለማያውቁ ሕዝቦች ይህ ምን ትርጉም ይሰጣል? አስቀድመን እስካላስተማርናቸው ድረስ በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን መካከል ስላለው የጊዜ ቅደም ተከተልና ደግሞም በትንቢቶቹ ውስጥ ስለምናነሣቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች የሚያውቁት አንዳችም ነገር አይኖርም። በመሆኑም አድማጮቹ «ይህ ወንጌላዊ የሚጠቅሳቸው እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው?» በማለት ግራ ይጋባሉ። የዚህ ዓይነቱ አቀራረብ እውነትን አጉልቶ ለማሳየት የማይችል ከመሆኑም ሌላ፥

ከታወቀው በመነሣት ወደ ኦልታወቀው የሚያደርሰውን መሠረታዊ የማስተማርያ መመሪያ የሚቃረን ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለመሆኑ የማረጋገጡን ተግባር በራሱ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንዲገለጽ መተው እጅግ የተሻለ ነው። ስፐርጅን የተባለው የእግዚአብሔር ሰው ስለ መጽሐፍ ቅዱስ መከላከያ እንዲያቀርብ በተጠየቀ ጊዜ፥ «ምን? ለአንበሳ ተከላከልለት ነው የምትሉኝ? ፈታችሁ ልቀቁት! እራሱ ለራሱ ይከላከላል» ብሏል።

እኛም የእግዚአብሔር መንፈስ በቃሉ እንደሚጠቀም በተገባልን የተስፋ ቃል ላይ ሙሉ በሙሉ በመተማመን የእግዚአብሔር ቃል በራሱ እንዲሠራ «ልንተወው» ይገባል። የእግዚአብሔር ኃይል በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ተሰውሮ ይገኛል። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል የመሆኑ ማረጋገጫ የሚገኘው በራሱ በቃሉ ውስጥ ነው፤ ስለሆነም ቃሉ በብሉይና በአዲስ ኪዳን ታሪኮች ውስጥ ቀስ በቀስ፥ ነገር ግን ግልጽ በሆነ ሁኔታ ይረጋገጣል።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

ሀ. የእግዚአብሔርን መልእክት ልንነግራችሁ መጥተናል።

ዋና አሳብ፡ - እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

እኛ በመካከላችሁ የተገኘነው የእግዚአብሔርን መልእክት እንድታውቁና እስካሁን ስንጠይቃችሁ ለነበሩት ጥያቄዎች እርሱ የሚሰጠውን መልስ ሙሉ በሙሉ በመረዳት እንድታምኑበት ለማስቻል ነው።

እስካሁን ድረስ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ፥ የት እንደሚኖር፥ ምን እንደሚመስል ወይም ምን እንደሚያስብ ላታውቁ ትችላላችሁ። ሆኖም እንነግራችሁ ዘንድ ወደ እናንተ የላከንን የእግዚአብሔርን መልእክት በምትሰሙበት ጊዜ ለእነዚህ ጥያቄዎች በሙሉ የእግዚአብሔር መልሶች ምን እንደሆኑ ትረዳላችሁ። የእግዚአብሔር መልእክትና ልናውቃቸው የሚገቡ መልሶች በሙሉ በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ተብሎ በሚጠራው መጽሐፍ ውስጥ ተጽፈዋል።

ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ሞትና ስለ ሌሎች ጉዳዮች ለጠየቅናችሁ ጥያቄዎች ቀደም ብለን መልስ ያልሰጠንበት ምክንያት፥ የእኛ ወደዚህ አመጣጥ የግል አስተሳሰባችንን ወይም ሌሎች ሰዎች የሚያስቡትን ልንነግራችሁ ባለመሆኑም ነው። ወደ እናንተ የመጣነው እግዚአብሔር ምን እንደሚል ልንነግራችሁ ብቻ ነው።

የቀደሙት አባቶቻችንም (አበው) ቢሆን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈውን የእግዚአብሔርን ቃል እስኪሰሙ ድረስ፥ የእነዚህን ለእናንተ ያቀረብናቸውን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ አያውቁም ነበር።

በአገራችንና በመላው ዓለም የሚገኙ ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር የተናገራቸውን ቃላት ለመስማትና ለማመን ፈቃደኞች ባለ መሆናቸው እውነቱን አያውቁም።

መምህር ሆይ፡- በምታስተምረው ሕዝብ ቋንቋ የተዘጋጀ መጽሐፍ ቅዱስ ከሌለ በአማርኛ የተጻፈ መጽሐፍ ቅዱስ ይዘህ ወደ ስብሰባው መሄድ እንዳለብህ አትዘንጋ።

ሀ) ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ስትናገር መጽሐፉን ከፍ አድርገህ ያዘው ወይም ወደ መጽሐፍ ቅዱሱ በማመልከት ተናገር።

ለ) ከአንድ ቅጂ በላይ የሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ማሳየትህ፥ በዓለም ላይ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች መኖራቸውን ሕዝቡ እንዲገነዘብ ያስችላል። እንደዚሁም የእግዚአብሔር ቃል ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች እንደተተረጐመ በምትገልጥበት ጊዜ፥ በማስረጃነት በተለያዩ ቋንቋዎች የተጻፉ መጽሐፍ ቅዱሶች ይዘህ መቅረቡ ይረዳሃል።

ሐ) ሕዝቡ መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ የማይችሉ ቢሆኑም እንኳ እርስ በርሳቸው እየተቀባበሉ እንዲያዩትና ከፍተው አገላብጠው እንዲመለከቱት አድርግ። ከዚህ በፊት እንዳሳየሃቸው ሌሎች መጻሕፍትና ሥዕሎች ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስም ከወረቀት የተሠራ እውነተኛ መጽሐፍ መሆኑን እንዲያውቁት ያስፈልጋል። ስለ መጽሐፉ በፍርሃት ላይ የተመሠረተ እምነት ሊያድርባቸው አይገባም።

ለ. እግዚአብሔር በመጽሐፉ ውስጥ የተናገራቸውን ነገሮች ሁሉ እናምናለን።

የእግዚአብሔርን መጽሐፍ አንብበናል፤ እግዚአብሔር የተናገራቸውን ነገሮች ሁሉ ደግሞ እናምናለን። ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ሰዎችና ስለ መናፍስት ለጠየቅናችሁ ጥያቄዎች በሙሉ እግዚአብሔር የራሱን መልሶች አስተምሮናል።

መምህር ሆይ፡- በምታስተምርበት ጊዜ በዚህ ምስክርነት የሚያምኑትን ባለቤትህን፥ ሌሎች የቡድኑ አባላትንና የወንጌላዊያንን ልጆች በሙሉ በአጠገብህ እንዲገኙ አድርግ።

የወንጌል አገልጋዮችን በስም እየጠራህ «በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፉት የእግዚአብሔር ቃል መሆናቸውን ታምናለህን?» ብለህ መጠየቅ ያስፈልግህ ይሆናል። ለዚህ ጥያቄ መልስ እንዲሰጡና ከፈለጉም አጭር ምስክርነት እንዲያቀርቡ እንኳ ፍቀድላቸው። በዚህ ደረጃ የሚሰጡ ምስክርነቶች ከሚከተሉት ነጥቦች ማለፍ የለባቸውም፡-

ሀ) የእግዚአብሔርን መልእክት እንዴት ለማወቅ እንደቻሉና ሲጠይቋቸው ለነበረው ጥያቄዎች የእግዚአብሔርን መልሶች እንዴት ለመረዳት እንደበቁ፥

ለ) በዚህ በእግዚአብሔር መልእክት ሙሉ በሙሉ ያመኑበት መሆኑን፥

ሐ) በበኩልህም ይህ መልእክት ለሰዎች ሁሉ መድረስ እንዳለበት እግዚአብሔር እንዴት እንዳስተማረህና አንተም ወደዚህ የመጣኸው ይህን መልእክት እንዲሰሙ፥ እንዲረዱና የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያምኑ እንደሆነ።

ማስታወሻ፡- በዚህ ምስክርነትህ ስለ ኃጢአት፥ ስለ ደኅንነት፥ ስለ አዳኙ ወይም ከገሃነም ስለ መዳን አትናገር። እነዚህ ሕዝቦች እግዚአብሔር ግን እንደሆነ፥ እነርሱ ደግሞ የጠፉ እንደሆኑና መዳን እንደሚያስፈልጋቸው እንኳ ገና አያውቁም፤ ስለዚህ ይህንን በማስመልከት ብትናገር የምትናገረው ምን እንደሆነ አይገባቸውም።

ሐ. የእግዚአብሔር መልእክት በመላው ዓለም ከሚገኙ መልእክቶች ሁሉ እጅግ የላቀ ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል። እግዚአብሔር ከሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ለምሳሌ የቀበሌአችሁ ሊቀመንበር «በጣም አስፈላጊ መልእክት ስላለኝ ልነግራችሁ ይገባልና ተሰብሰቡ» ቢላችሁ፥ የሚለውን ነገር ለመስማትና ለመረዳት ትሰበሰባላችሁ አይደል?

መምህር ሆይ፡- እጅግ ጠቃሚ የሆነ መልእክት ሊያመጣላቸው ይችላል ብለህ የምታስበውን ሌላ መሪ ወይም የመንግሥት ተወካይ... ወዘተ በምሳሌነት መምረጥ ትችላለህ።

ጠላቶቻችሁ ጥቃት ሊፈጽሙባችሁ እየተዘጋጁ መሆናቸውን ብታውቁ፥ ይህን ጉዳይ ለመሰለል የመረጣችኋቸው ሰላዮች ቢኖሩና የተሰጣቸውን ተግባር አከናውነው የሰለላቸውን ዘገባ ለማሰማት ቢቀርቡ፥ ፈጥናችሁ በመሰብሰብ በጥንቃቄ ታዳምጣላችሁ። የሚያመጡት ዘገባ እጅግ ጠቃሚ መልእክት ነው። አይደለምን?

መምህር ሆይ፡- አንድን መልእክት መስማት ለሕዝቡ እጅግ አስፈላጊ የሚሆንበትን አንድ አሳማኝ ሁኔታ በአእምሮህ አሰላስል። ምናልባት በዚያን አጋጣሚ ሰዎቹ ከጐረቤቶቻቸው ጋር እየተጣሉ ይሆናል ወይም እንደዚህ ዓይነቱን ሁኔታ ስላሳለፉበት ጊዜ የሚያስታውሳቸው ሊሆን ይችላል።

የሰላዮቹ መልእክቶች እጅግ ጠቃሚ እንደሚሆኑ አያጠራጥርም፤ ምክንያቱም ሁላችሁንም በጠላቶቻችሁ ከመገደል የሚያድኑ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው። እግዚአብሔር በመጽሐፉ ውስጥ ያስቀመጠው መልእክት ግን ከዚህ በላቀ ሁኔታ እጅግ አስፈላጊ ነው። በመላው ዓለም ከሚገኙ መልእክቶች ሁሉ የሚበልጥ ነው።

ስለማንኛውም ነገር እውነቱን ሊነግረን የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔር ማን እንደሆነና መልእክቱ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምን እንደሆነ እስካሁንም አልተረዳችሁ ይሆናል፤ ነገር ግን በበለጠ እየሰማችሁት እየተረዳችሁት ስትሄዱ ከእግዚአብሔር የበለጠ ማንም እንደሌለና ለእናንተ እንድንነግራችሁ የላከን ይህ መልእክቱ በሕይወትህ ሁሉ ከምትሰሚቸው ማናቸውም መልእክቶች የበለጠ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ትረዳላችሁ።

መምህር ሆይ፡- በዚህ ባሉበት ደረጃ ሊረዱት የማይችሉትን ምክንያቶች ሳትሰጥ የእግዚአብሔርን መልእክት ጠቃሚነትና እግዚአብሔር የሚላቸውን ለመረዳት ምን ያህል በጥንቃቄ ማዳመጥ እንደሚገባቸው አስረግጠህ ለመግለጥ ሞክር።

እናንተ ሴቶች በቤት ውስጥ የምትንከባከቧቸው ልጆች አሏችሁ፤ በቤት ውስጥና (በማሳዎቻችሁ) የምትሠሯቸው በርካታ ተግባራት አሉባችሁ። እናንተ ወንዶችም ብዙ የጉልበት ሥራ አለባችሁ። እናንተ ወጣቶች ደግሞ መጫወትና መዋኘት ትፈልጋላችሁ። እኛ እዚህ ተሰብስበን ሳለን እናንተ ግን በሥራ ወይም በጨዋታ የተጠመዳችሁ ከሆነ እግዚአብሔር የሚናገረውን መስማት ትችላላችሁን? አትችሉም! ስለዚህ ከእኛ ጋር ልትቀመጡና ጊዜ ሰጥታችሁ እግዚአብሔር ለእናንተ ያለውን መልእክት ልትሰሙ ያስፈልጋል። ይህን ካላደረጋችሁ የምታገኙበትና ለዘላለም የምትጸጸቱበት ቀን ይመጣል።

መምህር ሆይ፡- መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ወደ እያንዳንዱ ሰው የላከው መልእክት እንደሆነ አስቀድመህ ግለጽላቸው። ይህም፡- ሽማግሌ፥ ወጣት፥ ወንዶች፥ ሴቶችንና ልጆችን ሁሉ የሚጨምር ነው። የተለያዩ ዓይነት ሰዎችን በተናጠልና በቀጥታ አመልክት።

መ. በመጀመሪያ እግዚአብሔር መልእክቱን ለመረጣቸው ሰዎች ሰጣቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

እግዚአብሔር በአንድ መጽሐፍ ውስጥ ቃሉቹን ጽፎ በመላ ዓለም ለሚገኙ ሕዝቦች እንዲያነቡት ሊሰጣቸው ይችል ነበር፤ ነገር ግን በዚያ መንገድ ሊያደርገው አልመረጠም። በምትኩ ሰዎችን መረጠና መልእክቱን በአእምሮአቸው አስቀመጠ።

እግዚአብሔር መልእክቱን ለአንድ ሰው ብቻ አልሰጠም። እግዚአብሔር የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ለማጻፍ በግምት በ40 የተለያዩ ምርጥ ሰዎች ተጠቅሟል። እነዚህም ሰዎች የእግዚአብሔር ነቢያት በመባል ይታወቃሉ።

ነቢያት የእግዚአብሔርን መልእክት ልክ እርሱ በነገራቸው መንገድ ተናገሩ፥ ደግሞም ጻፉ። ይህ አንድ የአገር መሪ የሚነግርህ አንድ መልእክት ሲኖር እንደሚሆነው ዓይነት ነው። ወደ አንተ በመምጣት መልእክቱን በግምባር አይነግርህም አይደለም? መልአክቱን ለሌሎች ሰዎች ይሰጥና መልእክተኞቹ የመሪውን መልእክት ያደርሱልሃል። እግዚአብሔር መልእክቱን የሚያደርሱለትን ቃለ አቀባዮቹን የመረጠው በተመሳሳይ መንገድ ነው። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን በመወከል የእግዚአብሔርን መልእክት ተናገሩ፤ ደግሞም ጻፉ።

እነዚህ ሰዎች የኖሩት በአንድ ዘመን አልነበረም። አብዛኛዎቹ እርስ በርስ የሚተዋወቁ እንኳ አልነበሩም።

የመጀመሪያው ሰው በጻፈበት ጊዜና የመጨረሻው ሰው በጻፈበት ጊዜ መካከል 1600 ዓመታት አልፈዋል።

መምህር ሆይ፡- መጽሐፍ ቅዱስህን በመክፈት የተለያዩ ሰዎች የጻፏቸውን አንዳንድ መጻሕፍት አሳያቸው። በቀላሉ ለማሳየት ትችል ዘንድ በአንዳንዶቹ መጻሕፍት ውስጥ ግልጽ ምልክት ማድረግ ይረዳል።

እግዚአብሔር እንዲጽፉ የመረጣቸው ሰዎች ከአንዱ በስተቀር ሁሉም አይሁዳውያን ነበሩ። የአይሁዳውያን ምድር እስራኤል ናት። እግዚአብሔር የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍትን እንዲጽፉ የመረጣቸው ሰዎች የእኛ አገር ሰዎች አልነበሩም።

ከዚህ በኋላ ስለ አይሁዳውያንና እግዚአብሔር እነርሱን መርጦ መልእክቱን ለዓለም እንዲያደርሱ እንዴት እንደተጠቀመባቸው በርከት ያሉ ነገሮችን እንማራለን። እነዚህ ጉዳዮች በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፈዋል።

መምህር ሆይ፡- በዓለም ካርታ ላይ የእስራኤልን ምድር አሳያቸው። በቅድመ የወንጌል ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያሳየሃቸውን አንዳንድ የእስራኤልን ካርታዎች እንደገና አሳያቸው። በሚገባ ካሳየሃቸው በኋላ በዓለም ካርታ ላይ እስራኤልን እንዲያሳዩ ጠይቃቸው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች በሙሉ፡- ከራሳቸው ቋንቋ በስተቀር ሌላ ቋንቋ ለምሳሌ፥ አማርኛ ወይም እንግሊዘኛ ወይም ግዕዝ የሚናገሩ አልነበሩም። የእግዚአብሔርንም መልእክት በሌላ ቋንቋ አልጻፉም።

መምህር ሆይ፡- በብራና ጥቅል ላይ የሚጽፍ የአንድ አይሁዳዊ ነቢይ ሥዕል አሳያቸው።

ሠ. መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ብዙ የተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሟል።

እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን እንዲጽፉ የመረጣቸው ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በእስራኤል ምድር ይነገር በነበረው በገዛ ቋንቋቸው ጻፉት። ከጊዜ በኋላ ከእስራኤል ምድር ጐረቤት በነበሩ አገሮች ይኖሩ የነበሩ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላትን በማንበብ በራሳቸው ቋንቋዎች ጻፏቸው። የእግዚአብሔር ቃል በአሁኑ ወቅት በብዙ የዓለም ቋንቋዎች ተተርጉሞ ተጽፏል። እንደዚሁም መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛና ደግሞም በአገራችን በሚገኙ በበርካታ ዋና ዋና ቋንቋዎች ተተርጉሟል።

መምህር ሆይ፡-

ሀ) አንዳንዶች ወንጌላዊያን የእግዚአብሔር ቃል ከእስራኤል ተነሥቶ የቀደምት አባቶቻቸው ወደኖሩበት አውሮፓ- የእንግሊዝ ደሴቶች፥ ጀርመን ወዘተ እንዴት እንደተስፋፋ በመቀጠልም በአውስትራልያ፥ ኒውዚላንድና አሜሪካ ስለመሰራጨቱ፥ ከዚያም በተለያዩ የወንጌል አገልጋዮች አማካይነት ቃሉ ወደ በርካታ የተለያዩ አገሮች ስለ መድረሱና በመጨረሻም በአንተ በኩል ለአሁን ለምታስተምራቸው ሕዝቦች እንዴት እንደደረሰ የሚገልጽ አጭር ታሪካዊ ዘገባ ማቅረብ የሚጠቅም ሆኖ አግኝተውታል። ታዲያ አንተም ይህን የምታደርግ ከሆነ ረጅምና አላስፈላጊ የሆኑ ዝርዝር ሐተታዎችን አስወግድ። በዚህ አጭር የታሪክ ትምህርት ውስጥ የዓለም ካርታህ ሊረዳህ ይችላል።

ለ) የትርጉም ሂደትን ለማመልከት፥ በጥቁር ሰሌዳ ላይ አንድ ዐረፍተ ነገር በእንግሊዝኛ ከጻፍክ በኋላ ቀጥሎ ትርጉሙን በሕዝቡ ቋንቋ በመጻፍ አሳያቸው። በቀላሉና በአጭሩ ግለጽላቸው።

ረ. መጽሐፍ ቅዱስን ልናስተምራችሁ እየተረጐምነው ነው።

እግዚአብሔር የተናገረውን ወደ ቋንቋችሁ እየመለስነው ነው። የእናንተን ቋንቋ በሚገባ ተረድተን የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ለመተርጐም እንችል ዘንድ ልትረዱን ያስፈልጋል። ከዚያ በኋላ ስለ መልእክቱ ይዘት እናስተምራችኋለን።

እግዚአብሔር እንድታውቁት የሚፈልጋቸው ነገሮች ብዙ ስለሆኑ፥ ሁሉንም እናስተምራችሁ ዘንድ የሚወስድብን ጊዜ ረጅም ይሆናል። የእግዚአብሔርን ቃል የምናስተምራችሁ ጥቂት በጥቂቱ ነው።

እስኪ ቤታችሁን የምትገነቡት እንዴት እንደሆነ ንገሩኝ? አዎን በመጀመሪያ ትላልቅ ዋና ምሰሶዎችን ትተክላላችሁ፤ ቀጥሎ ቤቱ ወደ ፍጻሜ እስኪደርስ ድረስ ጥቂት በጥቂቱ ትገነባላችሁ። በመሬት ላይ ምሰሶ በቅድሚያ ሳትተክሉ ጣሪያውን ልትሠሩ ትችላላችሁን? በእርግጥ አትችሉም፤ ጣሪያውን የሚደግፍ አንዳችም ነገር የለምና!

ይህ እንዴት እንደምናስተምራችሁ የሚገልጽ ነው። በመጀመሪያ ከዋናዎቹ ምሰሶዎች እንጀምራለን። እነዚህ እንደ ምሰሶ የሚቆጠሩት እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተናገራቸውና በመጀመሪያ ልታውቋቸው የሚገቡ ናቸው። እነዚህን ጉዳዮች በመጀመሪያ ካልተረዳችሁ እግዚአብሔር ሊያስተምራችሁ የሚፈልጋቸውን ሌሎች ነገሮች ለመረዳት አትችሉም።

መምህር ሆይ፡- የምታስተምርባቸውን መንገዶችና እንዴት ረጅም ጊዜ እንደሚወስድ የምትገልጽበት ሌላው መግለጫ የእርሻ ማሳዎቻቸውን እንደ ምሳሌ በመውሰድ፥ መሬቱን ከማለስለስ ጀምሮ ዘር መዝራት፥ አረምን ለማስወገድና ምርቶቻቸውን ለመሰብሰብ የሚወስደውን የጊዜ ሂደት በመግለጽ ነው።

በየለቱ ምግብ ትመገባላችሁን? ያንን የምታደርጉት ለምንድን ነው? አምን ምግብ በየለቱ የምትመገቡት ስለሚርባችሁ ነው። ሕፃናቶቻችሁ ብርቱና ጤነኛ እንዲሆኑ ምግብ በየለቱ መመገብ ያስፈልጋቸዋል።

በእግዚአብሔር ቃል አንጻርም እንደዚሁ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በተደጋጋሚ ካዳመጣችሁ፥ በዚህ ሕይወትም ሆነ በምትሞቱበት ጊዜ እንኳ ትልቅ ጠቀሜታ የሚኖራቸውን በርካታ አስደናቂ ነገሮች በፍጥነት ትማራላችሁ።

ሰ. በራሳችሁ ቋንቋ ልታነቡት እንድትችሉ እናስተምራች ኋለን።

የእግዚአብሔርን ቃል በራሳችሁ ቋንቋ ለመማር ለምትፈልጉ ደግሞ እናስተምራችኋለን። ይህን ማድረግ ቀላል ባይሆንም፤ ነገር ግን በየዕለቱ የምትመጡ ከሆነና እንድናስተምራችሁ የምትፈቅዱ ከሆነ እንዴት ማንበብ እንዳለባችሁ በፍጥነት ትማራላችሁ።

ጥያቄዎች

1. በእናንተ መካከል የተገኘነው ለምንድን ነው? የእግዚአብሔርን መልእክት ልንነግራችሁ ነው።

2. በመላው ዓለም ከሁሉ የላቀው ጠቃሚ መልእክት የትኛው ነው? የእግዚአብሔር መልእክት ነው።

3. የእግዚአብሔር መልእክት በመላው ዓለም ከሁሉ የላቀው ጠቃሚ መልእክት የሆነው ለምንድን ነው? ምክንያቱም ሰዎች ስለ ዓለም አጀማመር፥ ሰዎች ሁሉ ከየት እንደመጡ፥ በምንሞትበት ጊዜ ወዴት እንደምንሄድ፥ ለምን እንደምንሞትና ስለ ሌሎች በርካታ ጉዳዮች እጅግ የተለያየ አስተሳሰብ ያላቸው ሲሆን፥ዳሩ ግን ስለማናቸውም ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ነው። ሰዎች እውነትን የሚያውቁት የእግዚአብሔርን መልእክት ከሰሙና ከተረዱ በኋላ ብቻ ነው።

4. የእግዚአብሔር መልእክት የተጻፈው በየት ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው።

5. እግዚአብሔር ቃሉን እንዲጽፉ ያደረጋቸው እነማንን ነው? በእግዚአብሔር የተመረጡ ሰዎችን ነው።

6. እነዚህ ሰዎች ማን ተብለው ይጠራሉ? ነቢያት።

7. እነዚህ ሰዎች በሙሉ የእግዚአብሔርን ቃል የጻፉትና የኖሩት በአንድ ወቅት ነውን? አይደለም። አብዛኛዎቹ የኖሩት በተለያዩ ጊዜያት ነበር። የእግዚአብሔር ቃል በሙሉ ተጽፎ እስኪጠቃለል ድረስ 1600 ዓመታት ፈጅተዋል።

8. እነዚህ ሰዎች የእኔ ወይም የእናንተ ቅድመ አባቶች ናቸውን? አይደሉም።

9. እነማን ነበሩ? ከአንዱ በስተቀር በሙሉ አይሁዳውያን ነበሩ።

10. የእግዚአብሔርን ቃል የጻፉት በአማርኛ ነበርን? አልነበረም።

11. እግዚአብሔር የመጽሐፉን መልእክት የሰጠው ለማን ነበር? በሁሉም ስፍራ ለሚኖሩ ለሁሉም ሰዎች ነበር።

12. እውነትን ሊነግረን የሚችለው ብቸኛው ማን ነው? እግዚአብሔር ነው።

ትምህርት 2

የትምህርት ክፍል፡- ዘፍጥረት 1፡1 «በመጀመሪያ እግዚአብሔር . . . »

አጠቃላይ ርእስ፡- ከመጀመሪያ በፊት ይኖር የነበረ እግዚአብሔር ብቻ ነበር።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. በመጀመሪያ (1፡1)

1. በዙሪያችን ከምንመለከታቸው ነገሮች አንደኛዎቹም ከመጀመሪያ በፊት አልነበሩም።

2. ማንኛውም ሰው ከመጀመሪያ በፊት አልነበረም።

3. ማንኛውም መናፍስት ከመጀመሪያ በፊት አልነበሩም።

ለ. በመጀመሪያ የነበረው እግዚአብሔር ብቻ ነበር (1፡1)

1. እግዚአብሔር ከሁሉም የሚበልጥ ታላቅ ነው።

. እግዚአብሔር ከሁሉ በላይና ሉዓላዊ ነው።

2. ስለ ፍጥረት መጀመሪያ ሊነግረን የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው።

3. እግዚአብሔር ብቻ ዘላለማዊ ነው።

4. እግዚአብሔር በማንም ሆነ በምንም ላይ ሳይደገፍ፥ ሙሉ በሙሉ እራሱን ችሎ የሚኖር ነው።

. እግዚአብሔር ከሁሉ በላይና ሉዓላዊ ነው።

5. እግዚአብሔር ከሁሉ በላይና ሉዓላዊ ነው።

የትምህርት 1 ጥያቄዎችን ከልስ።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

መምህር ሆይ፡- የዘፍጥረት መጽሐፍ የቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ሲሆን ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ደግሞ የዘፍጥረት መጽሐፍ

መሠረት ነው። ስለ ተፈጥሮና ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ መሠረታዊ መገለጥ የሚገኘው በዚህ ምዕራፍ ስለሆነ በጥድፊያ አትለፈው።

በዚህ በትምህርታችን የመጀመሪያ ደረጃ የእግዚአብሔርን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት መሠረት ማስተዋወቅ እንጀምራለን። የእግዚአብሔርን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በቅዱሳት መጻሕፍትና አስተዋይ አእምሮ ሊረዳው በሚችል መግለጫ በመደገፍ ደረጃ በደረጃ እናቀርበዋለን። በቅድምያ የእግዚአብሔርን መሠረታዊ ባሕርያት ካስተዋውቅናችሁ በኋላ፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማስተማራችንን በቀጠልን ቁጥር አትኩሮት እናደርግበታለን።

በመጀመሪያ፥ ከዘፍጥረት 1፡1 በመነሣት ሁሉም ነገሮች የተጀመሩበት ጊዜ እንደ ነበር እናሳያለን። ቀጥሎም ከዚህ ከመጀመሪያ በፊት ፀሐይ፥ጨረቃ ወይም ከዋክብት ወይም ሰዎች ወይም መናፍስት እንዳልነበሩ በማስረገጥ እናመለክታለን።

ሁለተኛ፥ከዘፍጥረት 1፡1 በመጀመሪያ እግዚአብሔር ብቻ እንደ ነበረ እናሳያለን። በመቀጠልም የሚከተሉትን የተጨመቁ ፍሬ አሳቦች እናወጣለን።

ሀ) በመጀመሪያ የነበረው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ እርሱ ከነገሮች ሁሉ፥ ከመናፍስትና ከሰዎች በላይ ነው። እግዚአብሔር ከሁሉ በላይና ሉዓላዊ ነው ለሚለው የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳብ መሠረቶችን እየጣልን ነው።

ለ) በመጀመሪያ የነበረው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ በመጀመሪያ ስለ ተፈጸመው ነገር ሊነግረን የሚችል እርሱ ብቻ ነው።

ሐ) ከነገሮች ሁሉ በፊት መጀመሪያ የነበረው እግዚአብሔር ስለ ነበር እርሱ ዘላለማዊ ነው።

መ) ምንም ነገር ሕልውናውን ካላገኘበት ጊዜ አስቀድሞ እንኳ እግዚአብሔር ከመጀመሪያ በፊት አንሥቶ ይኖር ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ከምንም ሆነ ከማንም ሙሉ በሙሉ ተለይቶ እራሱን ችሎ የሚኖር ነው።

በዚህ መሠረት ከሁሉ በላይና በፍጥረታት ሁሉ ላይ ሉዓላዊ የሆነውን እግዚአብሔርን ከፍ በማድረግ ትምህርቱን እናጠቃልላለን።

ሀ. መጀመሪያ

እግዚአብሔር በመጽሐፉ የጻፈልን የመጀመሪያ ቃል «በመጀመሪያ ....» የሚል ነው። እግዚአብሔር ይህን ቃል የጻፈልን ለሁሉም ነገር መጀመሪያ እንዳለው እንድናውቅ ነው። ለማየት የምንችለው ማንኛውም ነገርና ልናየው ባንችልም ስለመኖሩ የምናምንበት ማንኛውም ነገር መጀመሪያ አለው።

1. በዙሪያችን የምናያቸው ማናቸውም ነገሮች ከመጀመሪያው በፊት አልነበሩም።

ከመጀመሪያ በፊት ምድር አልነበረችም። ተራራዎች፥ ወንዞች፥ ዓለቶችና ዛፎች አልነበሩም። የምትታጠቡበትና ለመጠጥ የሚሆን ውኃ የምታገኙበት ወንዝ አልነበረም። ባሕሮች አልነበሩም። ሰማይ፥ ፀሐይ፥ ጨረቃና ከዋክብት ገና አልተፈጠሩም ነበር።

መምህር ሆይ፡- ሊያዩት የሚችሉትን ነገር በተናጠል እየጠራህ አስረዳ። በእርግጥ ገብቶአቸው እንደሆነ ለመረዳት ጥያቄዎችን ጠይቅ።

2. ማንኛውም ሰው ከመጀመሪያ በፊት አልነበረም።

ምድር፥ ፀሐይ፥ ጨረቃና ከዋክብት ከመጀመሪያ በፊት እንዳልነበሩ አስቀድመን ጠቅሰናል። ከመጀመሪያ በፊት ሰዎች ነበሩ ብላችሁ ታስባላችሁን? የእናንተ አገር ሕዝቦችም ሆኑ የእኛ አገር ሕዝቦች መኖር የጀመሩት ከመጀመሪያ በፊት ነበርን?

መምህር ሆይ፡- ጥያቄውን በሚገባ በትክክል ባይመልሱት ምንም አይደለም። እውነትን እስክታስተምራቸው ድረስ መልስ ሊሰጡ የሚችሉት ከዚህ ቀደም በነበራቸው መረዳት መጠን ብቻ ነው።

የሰው ልጆች ያለ ፀሐይ፥ ያለ መሬት፥ ያለ ውኃና ያለ ምግብ ሊኖሩ አይችሉም። ከመጀመሪያ በፊት እነዚህ ነገሮች ስላልነበሩ የሰው ልጅም ከመጀመሪያ በፊት አልነበረም።

የእኔ ቅድመ አባቶች ከመጀመሪያ በፊት አልነበሩም። እንደዚሁም የእናንተም ቅድመ አባቶች ከመጀመሪያ በፊት መኖር አልጀመሩም ነበር። በየትኛውም አገር ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ቅድመ አባቶችም ቢሆኑ ከመጀመሪያ በፊት መኖር አልጀመሩም ነበር።

መምህር ሆይ፡- አድማጮችህ የሚያውቋቸውን የተለያዩ ነገዶችና ዝርያዎች በመጥራት መጀመሪያ ተብሎ ከተጠራው ከዚህ ጊዜ በፊት ማናቸውም እንዳልነበሩ አስረግጠህ ንገራቸው። ይህንን ከእነርሱ ጋር በመነጋገር በአንድነት እንዲወያዩበት አድርግ።

3. ማንኛቸውም መናፍስት ከመጀመሪያ በፊት አልነበሩም።

የምታምኑባቸው ማንኛቸውም መናፍስት ከመጀመሪያ በፊት አልነበሩም። አዝርዕቶቻችሁን እንዲያሳድጉላችሁ፥ ከሕመማችሁ እንዲፈውሷችሁና ሀብትን እንዲሰጧችሁ የምትማጸኗቸው መናፍስት ሁሉ ከዚያ በፊት አልነበሩም።

መምህር ሆይ፡-

ሀ) በሚያምኑባቸው መናፍስት ባላቸው እምነት አንተም እንደምትስማማ አድርገው እንዳያስቡ መናፍስቱን በስማቸው አትጥራ። በዚያ ፈንታ «የምታምኑባቸው መናስፍት» እያልክ በደፈናው ተናገር። መናፍስቱን እነርሱ በሚጠሩበት ስማቸው ከጠራህ የመጠሪያ ስማቸው የሚያመለክተውን ነገር የምትቀበልና የምታምን ያስመስላል።

ለ) የሚያምኑባቸው መናፍስት ሕልውና እነርሱ እንደሚያውቁት አይደለም። እኛ ግን እነዚያ መናፍስት እራሳቸውን በመለዋወጥ የዛፎች፥ የዓለቶች፥ የሙታን ወዘተ መናፍስት በመሆን ሕዝቡን የሚያሳስቱ የአጋንንት ኃይላት እንደሆኑ እናውቃለን (1ኛ ቆሮንቶስ 10፡19-20)።

ሐ) ሕዝቡ የራሳቸውን የመናፍስት ዓለም ባህላዊ መረዳት መግለጣቸውን ይቀጥላሉ። በዚህ ደረጃ ልታርማቸው አትሞክር።

መ) በተጨማሪ በዚህ ደረጃ በቅዱሳት መጻሕፍት የተጠቀሱትን መናፍስት ስም አትጥቀስ (ለምሳሌ፡- መላእክትና ሰይጣን)። (ስለ እነርሱ በትምህርት 4 ላይ ታስተምራቸዋለህ።)

ሠ) ስለ እነርሱ የመናፍስት ዓለም ጠቅለል ባለ መልክ ንገራቸው።

ረ) ማንኛቸውም መናፍስት ሆኑ ወይም ሌሎች ፍጡራን ከመጀመሪያ በፊት እንዳልነበሩ ለማስረዳት የሚያስፈልገውን ያህል ጊዜ ውሰድ። ይህን ማድረግ ያለብህ ስለ እግዚአብሔር ስትናገር ብቻውን ዘላለማዊ የሆነ እና ሉዓላዊ የሆነ የሕይወት ሁሉ ምንጭ እርሱ መሆኑ ታውቆ፥ በሕዝቡ መካከል ከፍ ብሎና ከብሮ እንዲታይ ነው።

ሰ) ማንኛቸውም የፍጥረት አካል ወይም ሰው፥ ወይም መናፍስት ከመጀመሪያ በፊት አንሥቶ እንደነበሩ አድርገው ያስቡት የነበረውን አስተሳሰብ ከሕሊናቸው ካስወገድክ በኋላ (ከመጀመሪያ በፊት የነበረውን ፍጹም ባዶነትና ገላጣነት የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ በመስጠት)፥ በትረካህ ውስጥ እግዚአብሔርን የምታስተዋውቅበት አመቺው ጊዜ ይህ ይሆናል። ይህንን ከማድገርህ በፊት ግን የገለጽከውን ነገር በሙሉ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ ስለ መጀመሪያዎቹ ሦስት ነጥቦች አጭር ክለሳ አቅርብ።

ለ. በመጀመሪያ የነበረው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

የቅደም ተከተል ሠንጠረዥ፡- «እግዚአብሔር አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ» የሚሉትን ቃላት አሳይ።

አሁን እንደገና በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ የተጻፉትን የመጀመሪያ ቃላት እናነባለን። እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡- «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ...» ምንም ነገር ባልነበረበት፥ ማንኛውም ሰው ሆነ መናፍስት ባልነበሩበት በመጀመሪያ ብቻውን የሚኖር አንድ አካል ብቻ ነበር፤ ያም ብቸኛ አካል እግዚአብሔር ነበር።

ምድር፥ ውቅያኖስ፥ ፀሐይ፥ ጨረቃ፥ ከዋክብት፥ እንስሳ፥ ሕዝቦች ወይም መናፍስት ባልነበሩበት ጊዜ እግዚአብሔር ነበር።

1. እግዚአብሔር ከሁሉም በላይና ታላቅ ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሁሉ በላይና ሉዓላዊ ነው።

ከግንኛውም ነገር ጅግራ በፊት እግዚአብሔር ብቻ ነበር፤ ስለዚህ እርሱ ከምድር፥ ከውቅያኖስ ከጨረቃ፥ ከፀሐይ፥ ከከዋክብት፥ ከሰዎች ሁሉ፥ ከመናፍስት ሁሉና ከእንስሳት ሁሉ በላይ ታላቅ ነው።

2. ስለ መጀመሪያው ሊነግረን የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ግናቸውም ነገሮች ከመጀመራቸው በፊት የነበረ እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ ስለዚህ በመጀመሪያ ስለሆነው ነገር በእርግጥ ሊነግረን የሚችል እርሱ ብቻ ነው።

መምህር ሆይ፡- የጠቀስከውን የመጨረሻ ነጥብ ለማስረዳት ከአድማጮችህ አብዛኛዎቹ ከመወለዳቸው በፊት የደረሱትን አንዳንድ ክሥተቶች በምሳሌነት በመጥቀስ፥ዳሩ ግን ስለ እነዚህ ሁኔታዎች የቀደሙት ወላጆቻቸው ያውቁ እንደነበረ አስታውሳቸው። ለምሳሌ፡- ሕዝቡ ከብዙ ዓመታት በፊት በጐረቤት ከሚገኙ ሕዝቦች ጋር የተዋጉበትን ጊዜ ነግረውህ ይሆናል። ከእነዚህ አዛውንት መካከል በዚያ የነበረ ምናልባትም በዚህ የነገድ ጦርነት ውስጥ የተካፈለ ሊኖር ይችላል። ስለዚህ ሕዝቡን እንዲህ በማለት ልትጠይቅ ትችላለህ፡- «በዚያ የጦርነት ጊዜ ምን እንደተፈጸመ በእርግጥ ማወቅ ከፈለግሁ ከእነዚህ ትናንሽ ልጆች መካከል አንዱን ወይም ሴቶችን መጠየቅ አለብኝን? የለብኝም! ታዲያ ጥሩ መረጃ እንዲሰጠኝ ልጠይቀው የሚገባ ሰው ማን ይመስላችኋል? በወቅቱ የነበረን ሰው መጠየቅ ከሁሉ የተሻለ አይደለምን?» በመቀጠል ደግሞ በቅርቡ ስለተፈጸመና አንድ ወይም ሁለት ሰው ስላየው አንድ ድርጊት ተናገር። ለምሳሌ ከዚህ ሕዝብ መካከል የተቀሩት ያላዩትን አንድ ትልቅ ከተማ ወይም የአገሪቱን ዋና ከተማ ያዩ ሰዎች ጥቂቶች ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ስፍራ ምን እንደሚመስል ሊናገሩ የሚችሉ እነርሱ ብቻ ናቸው።

3. እግዚአብሔር ብቻ ዘላለማዊ ነው።

እግዚአብሔር መጀመሪያ አልነበረውም። እግዚአብሔር ሁልጊዜ ነበር። እርሱ ፍጡር አይደለም። እርሱ በመወለድ አልተገኘም። እራሱን አልሠራም፤ ሁልጊዜ ነበር፤ ሁልጊዜም ያው ነው። እግዚአብሔር ሊሞት አይችልም።

መምህር ሆይ፡- እርግጥ እንደ ፖለዋኖሶች ያሉት ነገዶች እግዚአብሔር አልተወለደም ወይም እርሱን የሠራው የለም በምንለው አሳብ ይስማማሉ፤ ነገር ግን በድንገት መኖር የጀመረ ይመስላቸዋል። ስለዚህ ልንጠይቀው የሚገባ ትክክለኛ ጥያቄ፡- «እግዚአብሔር ያልነበረበት ጊዜ ነበርን?» የሚለው ይሆናል።

4. እግዚአብሔር በማንም ሆነ በምንም ላይ ሳይደገፍ ሙሉ በሙሉ እራሱን ችሎ የሚኖር ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሁሉ በላይና ሉዓላዊ ነው።

ወደዚህ ዓለም በመወለድ እንድንመጣም ሆነ፥ በሕፃንነታችን ተገቢውን እንክብካቤ እንድናገኝ ወላጆች አስፈልገውናል፤ እግዚአብሔር ግን የማንም ድጋፍ አያስፈልገውም።

እግዚአብሔር ከመጀመሪያ በፊት ይኖር ነበር። እርሱ ከምድር፥ ከፀሐይ፥ ከጨረቃ፥ ከከዋክብት ወይም ከማናቸውም ነገሮች በፊት ይኖር ነበር።

ምድርና በእርሷ ያሉት ሁሉ ለእግዚአብሔር አያስፈልጉትም። ፀሐይ፥ ጨረቃ፥ ወይም ከዋክብት አያስፈልጉትም። የሚተነፍሰው አየር፥ የሚበላው ምግብ ወይም የሚጠጣው ውኃ አያስፈልገውም። እግዚአብሔር ለማየት ይችል ዘንድ የፀሐይ ወይም የጨረቃ ብርሃን አያስፈልገውም። እግዚአብሔር ያለምንም ብርሃን ለማየት ይችላል። እግዚአብሔር ይሠራ ዘንድ ቀን፥ በእንቅልፍ ያርፍ ዘንድ ሌሊት አያስፈልገውም። ለእርሱ ቀንና ሌሊት የለም።

እግዚአብሔር በራሱ ኃይል የሚኖር ነው። ማንም ይረዳው ዘንድ ወይም በማያቋርጥ ሕልውና ይኖር ዘንድ እንዲታገዝ አያስፈልገውም።

አይራብም፤ አይጠማም ወይም አይደክምም።

እኛስ ያለ ፀሐይ፥ ያለ ዝናብ፥ ያለ ምድርና አዝርዕትን ለማልማት ከሚያስፈልጉ ሌሎች ነገሮች ሁሉ ተለይተን ልንኖር እንችላለን? በእርሻ ቦታ ስትውሉ ወይም በአደን ተግባር ስትወጡ ራብና ጥማት ይሰማችሁ የለ? በዚህ ጊዜ የሚያስፈልጋችሁ ነገር ምንድን ነው? የምንመላለስበት ምድር፥ የምንተነፍሰው አየር፥ የምንበላው ምግብና የምንጠጣው ውኃ ያስፈልገናል።

መምህር ሆይ፡- መልእክትህን የሚያዳምጡ አብዛኛዎቹ ሰዎች የሚመገቧቸውን ዋና የምግብ ዓይነቶች በመጥቀስ ያለ እነዚህ ምግቦች ለመኖር ይችሉ እንደሆነ ጠይቃቸው።

እግዚአብሔር ግን እንደ ሰው አይደለም። እግዚአብሔር እንደ እንስሳትና እንደ አዕዋፋት፥ እንደ ተሳቢ እንስሳትም አይደለም። እግዚአብሔር ከነገሮች ሁሉ ጅማሬ በፊት ስለኖረ በማንኛውም ነገር ሆነ በማንኛውም ሰው አይደገፍም።

5. እግዚአብሔር የሁሉ በላይና ሉዓላዊ ነው።

መምህር ሆይ፡- የሚከተሉትን ነጥቦች (ቁሶችን፥ ሰዎችን፥ መናፍስትንና እንስሳትን) በአንዳንድ ነገሶች ዘንድ በሚኖራቸው አስፈላጊነት ቅደም ተከተል መሠረት አስቀምጫለሁ። አንተም፥ እንደ አድማጮችህ መረዳት ደረጃ በመሰለህ ቅደም ተከተል ልታስቀምጣቸው ትችላለህ።

እግዚአብሔር ከሁሉም በላይ ታላቅ ነው።

እግዚአብሔር ከፀሐይ፥ ከጨረቃ፥ ከከዋክብትና በምድር ላይ ከሚገኙ ከማናቸውም ነገሮች ይበልጣል። እርሱ ከፀሐይ ከጨረቃ፥ ከከዋክብትና ከምድር በፊት ነበር።

እርሱ ከሰዎች ሁሉ በላይ ታላቅ ነው። ከሰዎች ሁሉ በፊት ይኖር ነበር። እኛ የሚያስፈልጉን ሁሉ አያስፈልጉትም ነበር።

እግዚአብሔር ከመናፍስት ሁሉ በላይ ታላቅ ነው። ከመናፍስት ሁሉ በፊት ይኖር ነበር።

መምህር ሆይ፡-

ሀ) እግዚአብሔር የመኖሪያ ስፍራ የማያስፈልገውና ሕዝቡ የመናፍስት ዓለም ይደገፉባቸዋል ብለው ከሚያስቡት ከማናቸውም ነገሮች በተለየ ሁኔታ እራሱን ችሎ የሚኖር እንደሆነ ግልጽ አድርግ። እግዚአብሔር ከፍ ብሎ የሚገኝና ከነገሮች ሁሉ ነፃ ሆኖ ሙሉ በሙሉ እራሱን ችሎ የሚኖር እንደሆነ በማስተማር ከፍ እያደረግህ አክብረውና እነዚህ ሕዝቦች በመናፍስትና በእግዚአብሔር መካከል ንጽጽር እንዲያደርጉ አነሣሣቸው። ይህንን በግልጽ ማድረግ ሲጀምሩ ስለ መናፍስት እውነቱን ለመናገር ታላቅ ነፃነት ይኖርሃል።

ለ. መናፍስት የሚኖሩት በዛፎች፥ በዓለቶች፥ በወንዞች ውስጥ እንደሆነና አንዳንድ ምግቦችንም እንደሚበሉ አድርገው ሕዝቡ እንደሚያምኑ አስታውስ።

ሐ) ሕዝቡ መናፍስት ይኖሩበታል ብለው በሚያምኑባቸው ቦታዎች ውስጥ እንደሚኖሩ እንደምታምን አድርገው እንዲያስቡ በሚያመላክት ሁኔታ አታስተምር። ቅዱሳት መጻሕፍት፥ ሰይጣንና አጋንንቶቹ ዝቅተኛውን የአካባቢ አየር ክፍል በመኖሪያነት እንደያዙ የሚናገሩ ይመስላሉ (ኤፌሶን 2፡2)።

መ) ሕዝቡ መናፍስት ይበላሉ፤ ምግብ ያስፈልጋቸዋል ብለው ያምናሉ። አንተ ግን ይህን የምትቀበል አስመስለህ አታስተምር። ሕዝቡ የሚያምኑባቸው መናፍስት የአጋንንት ኃይላት ስለሆኑ ቁሳዊ ነገሮች ባያስፈልጋቸውም፥ ሕዝቡ ግን ያስፈልጋቸዋል የሚል እምነት አላቸው።

ሠ) ስለዚህ «የእናንተ መናፍስት የሚኖሩባቸው ዛፎችና ዓለቶች ምግብና ልብሶች ያስፈልጋቸዋል፤ እግዚአብሔር ግን ከእነዚህ ነገሮች የትኛውም አያስፈልገውም» በማለት አታንጻጽር። ይህን ካደረግህ አድማጮችህ አንተም ደግሞ መናፍስት ሕዝቡን የሚጠይቁትን ነገሮች

እንደሚያስፈልጋቸው የተቀበልክና ስለመናፍስት የሚያምኑት ነገር ትክክል እንደሆነ አድርገው እንዲቆጥሩት ታበረታታቸዋለህ።

ረ) እምነታቸውን በቀጥታ እየተቃወምክ ወይም እየተሳለቅህበት በሚመስል መንገድ መናገር የለብህም። በዚህ ምትክ መናፍስት በመኖሪያነት ያስፈልጋቸዋል ብለው የሚያምኑባቸው ማንኛዎቹም ቦታዎች ለእግዚአብሔር ጨርሶ እንደማያስፈልገው በጣም ግልጽ አድርግላቸው።

ሰ) ከመካከላቸው አንዱ እነዚህ ነገሮች ለመናፍስት እንደሚያስፈልጓቸው መናገር ቢጀምር አትከራከር። ከእግዚአብሔር መጽሐፍ ስለ መናፍስት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንማራለን ብለህ ንገረው።

እግዚአብሔር ከእነርሱ በፊት ስለኖረ ከእንስሳት ሁሉ በላይ ነው። እንስሳት የሚያስፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ አያስፈልገውም።

መምህር ሆይ፡-

ሀ) እያስተማርከው ላለው ሕዝብ በተለይ ልዩ ጠቀሜታ ያላቸውን አዕዋፋትንና እንስሳትን ጥቀስ። አዕዋፍ፥ በምድር የሚኖሩ እንስሳትና ተሳቢ ፍጥረታት ለመኖር ምን እንደሚያስፈልጋቸው ጠይቃቸው፤ እነዚህን ነገሮች ሳያገኙ ለመኖር ይችሉ እንደሆነ ጠይቃቸው።

እግዚአብሔር ከማንኛውም ነገር በፊት ይኖር እንደነበር መረዳታቸውን አረጋግጥ።

ጥያቄዎች

1) አካባቢህን ተመልከት። መጀመሪያ የሌለው ምን ነገር ልትመለከት ትችላለህ? ምንም ነገር የለም። ሁሉም ነገሮች መጀመሪያ አላቸው።

2. ከመጀመሪያ በፊት ይኖር የነበረ ብቸኛ ማን ነው? እግዚአብሔር ነው።

3. እግዚአብሔር መኖር የጀመረው መቼ ነበር? እግዚአብሔር ጨርሶ ጅማሬ አልነበረውም።

4. እግዚአብሔርን የፈጠረው አለን? የለም።

5. እግዚአብሔር እንደ እኛ ተወልዷልን? አልተወለደም።

6. እግዚአብሔር እራሱን ፈጥሯልን? አልፈጠረም።

7. እግዚአብሔር ያልነበረበት ጊዜ ነበረን? ፈጽሞ አልነበረም።

8. እኛ ምግብ፥ ውኃ፥ አየር፥ መሬትና ፀሐይ ያስፈለገናል፥ እግዚአብሔር ግን ምን ያስፈልገዋል? እግዚአብሔር ምንም አያስፈልገውም።

9. ታዲያ እግዚአብሔር የሚኖረው እንዴት ነው? እግዚአብሔር የሚኖረው በራሱ ኃይል ነው።

10. ከመሬት፥ ከፀሐይ፥ ከጨረቃ፥ ከከዋክብት፥ ከሕዝብ ሁሉና ከመናፍስት ሁሉ ግን ይበልጣል? እግዚአብሔር።

ትምህርት 3

የትምህርት ክፍል፡- ኦሪት ዘፍጥረት 1፡1 «በመጀመሪያ እግዚአብሔር . . .»

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር በዘላለም ውስጥ

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊው ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. እግዚአብሔር መንፈስ ነው።

ለ. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ ይገኛል።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝ ነው።

. እግዚአብሔር ከሁሉ በላይና ሉዓላዊ ነው።

ሐ. እግዚአብሔር ሥላሴ ነው።

የትምህርት 2 ጥያቄዎችን ከልስ።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማዳበር

ሀ. እግዚአብሔር መንፈስ ነው።

ለእግዚአብሔር እንደ እኛ ሰዎች መሬትና ሌሎችም ነገሮች የማያስፈልጉበት ምክንያት፡- እግዚአብሔር እንደ እኛ ዓይነት አካል ስለሌለው ነው። እግዚአብሔር እንደ ሰዎች፥ እንስሳት ወፎችና ተሳቢ ፍጥረታት ሥጋና አጥንት የለውም። ስለ እግዚአብሔር ከመጽሐፉ የበለጠ እየተማርክ ስትሄድ እግዚአብሔር መንፈስ መሆኑን ትረዳለህ።

ታዲያ እግዚአብሔር ምድር፥ ፀሐይ ጨረቃ ወይም ከዋክብት ባልነበሩበት ጊዜ ከመጀመሪያ ጀምሮ የሚኖረው የት ይመስልሃል?

እግዚአብሔር አሁን የት ያለ ይመስልሃል?

ለ. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ ይገኛል።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝ ነው።

እግዚአብሔር እርሱ እስካልነገረን ድረስ በየት እንዳለ ልናውቅ አንችልም፤ እንደዚሁም ደግሞ ልናየው አንችልም። በዚህ መጽሐፍ

ውስጥ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ እንደሚገኝ በተደጋጋሚ ትማራላችሁ። እግዚአብሔር ፀሐይ፥ ጨረቃና ከዋክብት ባሉበት አለ። በምድር ላይ በሁሉ ስፍራ አለ። እግዚአብሔር አሁን በዚህ በመካከላችን አለ፤ ሁላችንንም ሊያየን ይችላል። ደግሞ በቤቶቻችሁ ውስጥ፥ በእርሻ ስፍራዎቻችሁ፥ በዱር ውስጥ፥ ከወንዝ በታችና በውቅያኖስ ውስጥ አለ። በከፍተኛ ተራራማ ስፍራዎች፥ ደግሞም በጕረቤት አገሮችም ዘንድ አለ።

እናንተስ በአንድ ጊዜ በተለያዩ ስፍራዎች ለመሆን ትችላላችሁን? በቤታችሁ ውስጥ በምትሆኑበት ጊዜ በዱር ውስጥ ደግሞ ልትሆኑ ትችላላችሁን? ማገዶ ለማምጣት ወጥታችሁ ሳለ በዚያው ጊዜ ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ደግሞ በቤት ውስጥ ልትሆኑ ትችላላችሁን? በእርግጥ አትችሉም።

እኛ ሰዎች በአንድ ጊዜ መገኘት የምንችለው በአንድ የተወሰነ ስፍራ ብቻ ነው። እኔ ከእናተ ጋር እያለሁ፥ በዚያኑ ጊዜ በቤቴ መሆን አልችልም። በአንድ ጊዜ በዚያም በዚህም መሆን አልችልም፤ እግዚአብሔር ግን በአንድ ጊዜ ሁሉም ቦታ ይገኛል።

እግዚአብሔር በመጽሐፉ በየስፍራው የሚሄድ ወይም በየትም ስፍራ ሊሆን የሚችል ትልቅ አካል እንዳለው አይናገርም። በጭራሽ! እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ እናም በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ ይገኛል። ወደ የትም ስፍራ ብንሄድ ሁልጊዜ በእያንዳንዳችን አጠገብ ነው። ሁላችንንም ሁልጊዜ ሊያየን ይችላል።

መምህር ሆይ፡- ተማሪዎችህ ከጠላቶቻቸው ይደበቁ ዘንድ የሚጠቀሙበት፥ የምታውቀው ስፍራ ካለ ወይም መናፍስት ሊያገኙን ወይም ሊያዩን አይችሉም ብለው የሚያስቡት ስፍራ ካለ ጥቀሰውና እግዚአብሔር ሁልጊዜ በእነዚያ ስፍራዎች እንዳለ አረጋግጥላቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ በላይና ሉዓላዊ ነው።

እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንምና ምንም የለም። በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝ እርሱ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ከማንኛውም ነገር ደግሞም ከማንኛውም ሰው የላቀ ነው።

የእግዚአብሔርን መጽሐፍ በበለጠ እየተመለከትን በሄድን ቁጥር፥ እግዚአብሔር መንፈስ እንደሆነና በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ እንደሚኖር በላቀ ሁኔታ እየተገለጸልን እንሄዳለን።

መምህር ሆይ፡-

ሀ) እዚህ ነጥብ ላይ «እኛ ልንሄድ የምንችልበትና ዳሩ ግን እግዚአብሔር የማይገኝበት ቦታ ሊኖር ይችላልን?» ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይሆናል። «ከእግዚአብሔር መደበቅ እንችላለንን?» አድማጮችህ ከእግዚአብሔር መደበቅ እንደሚችሉ አድርገው የሚያስቡ ከሆነ፥ ምናልባት መልእክትህ ግልጽ አልነበረም ወይም ስለ እግዚአብሔር የነገርካቸውን ነገሮች እስካሁን አላመኑም ማለት ነው። መልእክትህ ግልጽ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልግሃል፤ በዚህ ትምህርት ስለ እግዚአብሔር ያስተማርካቸውን ነገሮች ካላመኑ ግን ብዙ አያሳስብህ። በሚቀጥሉት ትምህርቶች እነዚህኑ ነጥቦች ማስተማርህን በመቀጠል ለውጡን ሊያመጣ በሚችለው በመንፈስ ቅዱስ ተደገፍ።

ለ) ኃጢአተኞች ስለመሆናቸው ወይም ኃጢአትን በሚያደርጉበት ጊዜ እግዚአብሔር ሊያያቸው እንደሚችል አትጥቀስ። በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ኃጢአተኞች መሆናቸውን ወይም ኃጢአት ምን እንደሆነ ገና አልተረዱም። ኃጢአትን በሚያደርጉበት ጊዜ እግዚአብሔር እንደሚያያቸው በመንገር ልታስጠነቅቃቸው የምትችለው ስለ ሰው ልጅ ውድቀት ካስተማርካቸው በኋላ ነው።

ሐ. እግዚአብሔር ሥላሴ ነው።

የእግዚአብሔርን መልእክት ስታዳምጥ እግዚአብሔር አንድ ብቻ ቢሆንም፥ በመለኮትነት እኩል የሆኑ ሦስት አካላዊ ሕልውናዎች እንዳሉት ደግሞ ትማራለህ።

እነዚህ ሦስት አካላዊ ሕልውናዎች በማንኛውም ነገር እኩል ናቸው። አብ እግዚአብሔር ነው፤ ወልድ እግዚአብሔር ነው፤ ደግሞም መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው።

መምህር ሆይ፡- ሥላሴን ለማብራራትና ለመግለጽ አትሞክር። ይህ የማይቻል ነው። ማናቸውም (እንደ ውኃ፥ እንቁላልና ሦስት ማዕዘን ቅርጽ ያላቸው) መግለጫዎች ሁሉ እውነቱን ለመግለጽ የሚበቁ አይደሉም። ያልሠለጠኑ ሰዎች እነዚህን መግለጫዎች በቀጥታ ለመረዳት ስለሚሞክሩ በከፍተኛ ግራ መጋባት ላይ ሊወድቁ ይችላሉ። ስለዚህ የሥላሴን ምሥጢር ለመረዳት እንደማንችል ማመኑ የተሻለ ነው።

ሥላሴን እዚህ ነጥብ ላይ ማንሣት አስፈላጊ የሆኑበት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ) ሥላሴ ዘላለማዊ ነውና ከቅደም ተከተል አንጻር ከመጀመሪያ በፊት የሚመጣ ነው።

ለ) በዘፍጥረት 1፡1 የምናገኘው የእግዚአብሔር ስም በዕብራይስጥ «ኤሎሂም» የሚል ነው። በቋንቋው የቃሉ የመጨረሻ ፊደል የነጠላ ትርጉም ያለው የብዙ ቁጥር ስም ነው። ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን አሐደ-ብዙሕነቱን ነው።

ሐ) እግዚአብሔር ወልድ በመጀመሪያ ነበር። «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ» በሚለው ዐረፍተ ነገር ውስጥ እርሱ ከእግዚአብሔር አብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተካትቶ ተነግሯል።

መ) ከመጀመሪያው ጀምረን በብሉይ ኪዳን ሁሉ ውስጥ ሥላሴን ካላስተማርን ስለ ኢየሱስ መወለድ ታሪክ በምንናገርበት ጊዜ የኢየሱስን መለኮትነት መግለጥ እጅግ አስቸጋሪ ይሆንብናል።

ከመጀመሪያው ጀምረን ኢየሱስ ለዘላለም ከአብ ጋር እኩል እንደነበር፥ ፍጥረታትን በማስገኘትም ሆነ በብሉይ ኪዳን አጠቃላይ ታሪክ ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ እንደነበረው መግለጽ ለእኛ ለአስተማሪዎቹም ሆነ ለሚማረው ሕዝብ የበለጠ ቀላል ይሆናል። «... አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ ...» (ዮሐ. 8፡58) የመሰሉትን ዐረፍተ ነገሮች ሕዝቡ ሊረዱት ቀላል የሚሆንላቸው እግዚአብሔር ወልድ ከመጀመሪያ በፊት እንደነበር ካስተማርናቸው ነው።

ማስታወሻ፡- ብሉይ ኪዳንን በምናስተምርበት ጊዜ ኢየሱስ የሚለውን መጠሪያ ወይም ክርስቶስ የሚለውን የማዕረግ ስም አንጠቀምም። ሁለቱ ስሞች ከምድራዊ አገልግሎት ጋር የተያያዙ ናቸው። በብሉይ ኪዳን ትምህርት ጊዜ እግዚአብሔር ወልድ የሚለውን ስም ብቻ ተጠቀም።

ሠ) መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለተጠቀሰ የሥላሴን ርእሰ ጉዳይ ወደ ጐን ልንተወው አንችልም (ዘፍጥረት 1፡2ን ከ6፡3 ጋር አወዳድር)።

ረ) ዘፍጥረት 1፡26 የብዙ ቁጥርን ይጠቀማል (እንፍጠር . . .)

ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር የሚሄድበት መሬት፥ የሚተነፍሰው አየር፥ የሚበላው ምግብና የሚጠጣው ውኃ ያስፈልገዋልን? በጭራሽ! እግዚአብሔር ምንም አያስፈልገውም።

2. እግዚአብሔር ልክ እንደ እኛ ሥጋና አጥንት ያለው አካል አለውን? የለውም። እግዚአብሔር መንፈስ ነው።

3. እግዚአብሔር የት ይገኛል? እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ቦታ ይገኛል።

4. ስንት እግዚአብሔሮች አሉ? አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ።

5. አንድ አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ሦስቱ የመለኮት ሕልውናዎቹ እነማን ናቸው? እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ናቸው።

ትምህርት 4

አጠቃላይ ርእስ፡- ሰይጣን (ሳጥናኤል) እና መላእክቱ

የትምህርቱ አስተዋጽኦና መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. እግዚአብሔር መናፍስትን ሁሉ ፈጥሯል።

. እግዚአብሔር የሁሉ በላይና ሉዓላዊ ነው።

ለ. መናፍስት የተፈጠሩት እግዚአብሔርን ለማገልገል ነበር።

. እግዚአብሔር የሁሉ በላይና ሉዓላዊ ነው።

ሐ. መናፍስት በእግዚአብሔር በተፈጠሩ ጊዜ ፍጹማን ነበሩ።

. እግዚአብሔር ቅዱስ ነው።

መ. መናፍስት ታላቅ ጥበብና ብርታት ያላቸው ሆነው ተፈጥረዋል።

ሠ. መናፍስት ለመቆጠር በማይቻል ሁኔታ እጅግ ብዙ ናቸው።

. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

ረ. መናፍስት በሰማይ ይኖሩ ነበር።

ሰ. የሳጥናኤል የመጀመሪያ ስፍራ በሰማይ በእግዚአብሔር ፊት ነበር።

ሸ. የሳጥናኤል ዓመፃ።

ቀ. በሳጥናኤል ዓመፃ ሌሎች መላእክት አብረው ተካፈሉ።

በ. እግዚአብሔር ሳጥናኤልና ሌሎች መናፍስት ያሰቡትንና ያቀዱትን ያውቅ ነበር።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ተ. እግዚአብሔር ሳጥናኤልና ተከታዮቹን እግዚአብሔርን ያገለግሉበት ከነበረው ሥልጣናቸው አስወገዳቸው።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደሞዝ ሞት ይሆን ዘንድ ወስኗል።

ቸ. እግዚአብሔር ሳጥናኤልና እርሱን ለተከተሉ መናፍስት የእሳት ባሕርን አዘጋጅቷል።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደሞዝ ሞት ይሆን ዘንድ ወስኗል።

ኀ. ሳጥናኤልና መላእክቱ እግዚአብሔርን ይጠላሉ።

. ሳጥናኤል (ሰይጣን) ከእግዚአብሔርና ከፈቃዱ ጋር ይዋጋል።

ነ. የሰይጣንና የመላእክቱ መኖሪያ በሰማይ መሆኑ አብቅቷል።

የትምህርት 3 ጥያቄዎችን ከልስ።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማዳበር

መምህር ሆይ፡- እግዚአብሔር በዓይን የሚታዩ ማንኛቸውንም ቁሳዊ ነገሮችን እንዴት እንደፈጠረ ከማስተማራችን በፊት በአጠቃላይ አነጋገር በዓይን የማይታዩ የመናፍስት ዓለምን እንዴት እንደፈጠረ እንመለከታለን። ስለ መናፍስትና ስለ ሰይጣን በዚህ ደረጃ ላይ ማስተማር የተሻለ የሚሆነው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡-

ሀ) መላእክት ምድር ስትፈጠር ምስክሮች ነበሩ (ኢዮብ 38፡4-7)።

ለ) ሰይጣን በመጀመሪያ በግልጽ የሚታየው በዔድን ገነት ሔዋንን ባታለለበት ታሪክ ውስጥ ቢሆንም፥ የእግዚአብሔርን የፍጥረት ሥራም ሆነ ሰውን በፍጥረታት ላይ የሾመበት ተግባርን በቅርብ ይከታተል የነበረ ይመስላል። ሰይጣን በሰው ፍጥረት ላይ የነበረው አሳብ ሔዋንን በአባቢቱ በኩል ከመቅረቡ በፊት በሚገባ የታቀደ እንደነበር አያጠራጥርም።

ሐ) ለአስተማሪውም ሆነ ለተማሪዎች ቀላል የሚሆነው እያንዳንዱን ባለታሪክ ወዲያውኑ እንደተፈጠረ ወይም እንደተወለደ ማስተዋወቅ ነው። አለበለዚያ መምህሩ ቀደም ብለው ወደተፈጸሙት ታሪኮች እየተመለሰ በታሪኩ ውስጥ የሚፈጠሩ ክፍተቶችን ለመሙላት ጥረት ማድረግን ይጠይቀዋል።

መ) የዘፍጥረት 3 ታሪክ የፍጥረትን ታሪክና የሰይጣንና የሠራዊቱን ውድቀት ታሪክ ሳንጨምርበት እንኳ በራሱ የተወሳሰበ ነው።

ሀ. እግዚአብሔር መናፍስትን ሁሉ ፈጠረ።

በቅደም ተከተል ማሳያው ሠንጠረዥ ላይ «የእግዚአብሔር መላእክትንና ሳጥናኤል» የሚሉትን ቃሎች አሳይ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር መናፍስትን ሁሉ ፈጠረ። እናንተ የምትናገሩላቸው መናፍስት ሁሉ የተፈጠሩት በዚህን ጊዜ ነበር። በፊት አልነበሩም። ሕይወትን የሰጣቸው እግዚአብሔር ነበር። እግዚአብሔር ባይሰጣቸው ኖሮ ሕይወት አይኖራቸውም ነበር።

እግዚአብሔር ከመናፍስት ሁሉ በላይ ነው። ከእነርሱ በፊት ይኖር ነበር። የፈጠራቸው እርሱ ነው። ሕይወትን የሰጣቸው እርሱ ነው።

እግዚአብሔር መናፍስትን ሲፈጥር ቁሳዊ አካላትን አልፈጠረላቸውም። መናፍስት ስለሆኑና ሥጋና ደም ስለሌላቸው ወደ ፈለጉበት ስፍራ መንቀሳቀስ ይችላሉ። መናፍስት ወደ አንድ የተዘጋ ቤት ለመግባት በሩ ሊከፈትላቸው አያስፈልግም። ብንዘጋባቸው እንኳ አልፈው መግባት ይችላሉ።

መናፍስት እኛ ያለንን ዓይነት ቁሳዊ አካላት ባይኖራቸውም እንኳ አንዳንድ ጊዜ እራሳቸውን ሰው አስመስለው ወይም በሌላ ቅርፅ ማሳየት ይችላሉ።

መምህር ሆይ፡- መላእክት በሰው ቅርፅ መገለጽ እንደሚችሉ ልትገልጥላቸው አስፈላጊ ነው፤ አለበለዚያ በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን መላእክት ተገልጠው እንደታዩ ስትናገር እርስ በርሱ የሚጋጭ አሳብ እንደምትናገር ሊመስላቸው ይችላል። በተጨማሪ ርኩሳን መናፍስት ለሕዝቡ እራሳቸውን በተለያየ መንገድ ገልጠው ይሆናል። መናፍስት በተለያዩ መንገዶች እራሳቸውን እንደገለጡላቸው ከነገሩህ፥ መናፍስት ይህን ሊያደርጉ እንደሚችሉ እውነት እንደሆነ በመግለጽ በሰጡህ አሳብ ተስማማ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል መስማታቸውን በቀጠሉ መጠን መናፍስት በእርግጥ እነማን እንደሆኑ የበለጠ እንደሚረዱ ንገራቸው።

መናፍስት ልክ እንደ እግዚአብሔር ቁሳዊ አካላት ባይኖራቸውም እንኳ እንደ እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ ሊገኙ አይችሉም። መናፍስት በአንድ ጊዜ ሊገኙ የሚችሉት በአንድ ቦታ ብቻ ነው።

ለ. መናፍስት የተፈጠሩት እግዚአብሔርን ለማገልገል ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የበላይና ሉዓላዊ ነው።

መናፍስት ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲወዱና እንዲያገለግሉ የተፈጠሩ ነበሩ። በመጀመሪያ መናፍስት የእግዚአብሔር መልእክተኞች ነበሩ። እግዚአብሔር ስለፈጠራቸው የእርሱ ነበሩ። እግዚአብሔር የሚፈልገውን ለማድረግ የተፈጠሩ ነበሩ።

አንድ ቤት ብትሠሩ የሠራችሁት ቤት የማን ነው? ለሠራችሁት ቤት ሕጋዊ መብት ያለው ባለንብረት እናንተ አይደላችሁምን?

ለሠራችሁት ነገር ባለቤት እናንተ እንደሆናችሁ ሁሉ፥ እግዚአብሔርም ለፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ ባለንብረት ነው። የመናፍስት ሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር ነው። ሕይወትን የሰጣቸው እርሱ ነው፤ የፈጠራቸው እንዲያገለግሉትና እንዲታዘዙት ነው። ስለዚህ መናፍስት ሁሉ የእርሱ ንብረት ናቸው።

ሐ. መናፍስት በእግዚአብሔር በተፈጠሩ ጊዜ ፍጹማን ነበሩ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስ ነው።

እግዚአብሔር መናፍስትን ሁሉ ፍጹማን አድርጐ ፈጥሮአቸው ነበር። ከመካከላቸው ክፉና ጨካኝ አልነበረም።

እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ ክፉ ነገርን ሊፈጥር አይችልም። እግዚአብሔር የሚያስበው፥ የሚናገረውና የሚያደርገው ሁሉ ፍጹም ነው።

መ. መናፍስት ታላቅ ጥበብና ብርታት ያላቸው ሆነው ተፈጥረዋል።

እግዚአብሔር መናፍስትን የፈጠራቸው ከታላቅ ጥበብና ብርታት ጋር ነበር። በርካታ ነገሮችን ያውቃሉ ይረዳሉም። ታላላቅ ነገሮችን ማድረግ ይችላሉ። ግን እንደ እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ የሚችሉ አይደሉም። እግዚአብሔር ከመናፍስት ሁሉ የላቀ ብርቱና ጥበበኛ ነው።

ሠ. መናፍስት ለመቆጠር በማይችል ሁኔታ እጅግ ብዙ ናቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

እግዚአብሔር የፈጠራቸው መናፍስት መልእክተኞች ስንት ይመስሉሃል? እግዚአብሔር የፈጠራቸው መናፍስት ልንቆጥራቸው የማንችለውን ያህል እጅግ ብዙዎች ናቸው።

እግዚአብሔር እጅግ ብዙ፥ መልካም፥ ጠንካራና ብልህ የሆኑ መናፍስትን ሊፈጥር የቻለው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ይህን ሊያደርግ የቻለው ሁሉን ቻይ ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር ሊያደርግ የሚፈልገውን ሁሉ ማድረግ ይችላል።

ረ. መናፍስት በሰማይ ይኖሩ ነበር።

በመጀመሪያ መናፍስት ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር በሰማይ ይኖሩ ነበር። ሰማይ እግዚአብሔር የሚኖርበት ልዩ፥ አስደናቂ ስፍራ ነው። ይህ ስፍራ የት እንደሆነ አናውቅም። በምድር ግን አይደለም። ከጨረቃ፥ ከፀሐይና ከከዋክብት በላይ ነው። መናፍስት ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖሩበት ስፍራ ነበር።

መምህር ሆይ፡-

ሀ) ሕዝቡ ስለ መንግሥተ ሰማያትና ስለ ሌሎች መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች ያለው መረዳት በየታሪኩ እያደገ የሚሄድ ስለሆነ በዚህ ትምህርት ደግመህ ደጋግመህ ስለ መንግሥተ ሰማያት በመናገር ጊዜህን አታጥፋ።

ለ) ቀደም ብለህ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ይገኛል ብለህ ስላስተማርክ አሁን ደግሞ መንግሥተ ሰማያት የእግዚአብሔር ልዩ፥ አስደናቂ መኖሪያ ነው ስትል በሕዝቡ

መረዳት ላይ ችግር ትፈጥር ይሆናል። ይህ ችግር ከሆነ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ የሚገኝ ቢሆንም እንኳ እርሱ የሚኖርበት ልዩ ስፍራ ደግሞ መንግሥተ ሰማያት እንደሆነ አረጋግጥላቸው።

ሰ. ሳጥናኤል በመጀመሪያ ደረጃ በሰማይ በእግዚአብሔር ፊት ነበር።

እግዚአብሔር መላእክትን ሁሉ አንድ ዓይነት አድርጉ አልፈጠራቸውም። አንዳንዶቹ ከሌሎቹ ይልቅ በበለጠ አዋቂዎችና ብልሆች ነበሩ። ከሁሉም የላቀው መልአክ ሳጥናኤል በመባል ይጠራ ነበር። እግዚአብሔር በላይ በሰማይ ልዩ ደረጃ ሰጥቶት ነበር። በሌሎች መላእክት ላይ ታላቅ ሥልጣንና ኃይል ይኖረው ዘንድ ተሰጥቶት ነበር።

መምህር ሆይ፡- ተጨማሪ ነገር ከማስተማርህ በፊት በዚህ ትምህርት ያስተላለፍካቸውን ቁም ነገሮች አዳማጮችህ ተረድተው እንደሆነ ለመገንዘብ አጠር ያለ ክለሳ ስጥ።

ሸ. የሳጥናኤል ዐመፅ

ሳጥናኤል በእግዚአብሔር ስለተፈጠረና በሌሎች መላእክት ሁሉ ላይ አለቃ ይሆን ዘንድ የሾመው እግዚአብሔር ስለነበር እግዚአብሔርን ሊወድ፥ ሊታዘዝና ሊያገለግል ይገባው ነበር፤ ነገር ግን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በውበቱ በእውቀቱና በሥልጣኑ ታበየ። በፍጥረታት ሁሉ ላይ ገዥነትን ከእግዚአብሔር ለመቀማት ወሰነ። ክፉ ነገር ለማድረግ የመጀመሪያው ሳጥናኤል ነው። ክፉ ወይም መጥፎ ነገር እግዚአብሔር የማይስማማበት ወይም የማይፈልገው ነገር ነው።

ቀ. በሳጥናኤል ዓመፅ ሌሎች መላእክት አብረው ተከተሉት።

በርካታ የእግዚአብሔር መላእክት ሳጥናኤልን መሪያቸው አድርገው ተከተሉት። እነርሱም በእግዚአብሔር ላይ ዓመፁ።

በ. እግዚአብሔር ሳጥናኤልና ሌሎች መናፍስት ያሰቡትንና ያቀዱትን ያውቅ ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

እግዚአብሔር መናፍስትን ሁሉ ስለፈጠረ ምን እንዳሰቡና እንዳቀዱ ያውቅ ነበር። ሳጥናኤል እንደታበየና የፈጣሪውን የእግዚአብሔርን ሥልጣን እንደፈለገ እግዚአብሔር አውቆ ነበር። እግዚአብሔር የሳጥናኤልን አሳብና አብረውት የዓመፁትን የእያንዳንዳቸውን መናፍስት አሳብ አውቆ ነበር።

ከእግዚአብሔር ሊሰወር የሚችል አንዳችም ነገር የለም። እግዚአብሔርን ሊያስደንቀው የሚችል ነገር የለም። ማንኛውንም ነገር ከመፈጸሙ በፊት አስቀድሞ ያውቃል። የምናስባቸው ነገሮች ወደ አእምሮአችን ከመምጣታቸው በፊት እንኳ ያውቃቸዋል። እርሱ በሁሉም ስፍራ ይገኛል፤ ሁሉን ነገር ይመለከታል፤ ሁሉን ነገር ያውቃል።

ተ. እግዚአብሔር ሳጥናኤልንና ተከታዮቹን እግዚአብሔርን ያገለግሉ ከነበረበት ሥልጣን አስወገዳቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደሞዝ ሞት ይሆን ዘንድ ወስኗል።

እግዚአብሔር ሳጥናኤል ሥልጣኑን እስኪወስድበት ድረስ በዝምታ የሚያየው ይመስልሃልን? ለሳጥናኤል የስግብግብነት ምኞት የእግዚአብሔር ምላሽ ምን የነበረ ይመስልሃል?

አንድ ሰው በአንድ ሕዝብ ወይም መንደር ላይ አለቃ ቢሆን ሥልጣኑን ሊቀማ ከሚሞክር ሰው ጋር አይዋጋምን? ብልህና ብርቱ የሆነ ሰው አንድ ተራና ደካማ የሆነው ሰው ሥልጣኑን እንዲወስድበት መፍቀድ አለበትን? ብልህ ሰው «ለትዕቢተኛ ልጁ» ቤተሰቡን እንዲያስተዳድር መፍቀድ አለበትን?

ከእግዚአብሔር የበለጠ ብልህና ብርቱ የሆነ ማን ነው? እርሱ ሁልጊዜ ይኖር ነበር። የሚኖረው በራሱ ኃይል ነው። ለመኖር አንዳችም ነገር አያስፈልገውም። እርሱ ከጅማሬ በፊት ይኖር ነበር። ለመናፍስት ሁሉ ሕይወት የሰጠው እርሱ ነው። ሳጥናኤል ሥልጣኑን እንዲወስድበት አልፈቀደም። እውነተኛ አምላክ እርሱ ብቻ ስለሆነ ማንም የእግዚአብሔርን ቦታ ሊወስድ አይችልም።

እግዚአብሔር፥ በታላቅ ቁጣ ተነሥቶ ሳጥናኤልን ከመላእክት አለቅነት ሥልጣን አስወገደው። እግዚአብሔር፥ ሳጥናኤልን የተከተሉትን መላእክት ሁሉ በመንግሥተ ሰማያት ይሠሩበት ከነበረው አገልግሎት አስወገዳቸው።

እግዚአብሔር በሚያስበውና በሚያደርገው ሁሉ ፍጹምና ትክክለኛ ነው። ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር የማያስብና የማያደርግ ወደ እግዚአብሔር ሊቀርብና የእርሱ ወዳጅ ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔር ሳጥናኤልና የተከተሉት መናፍስት በመንግሥተ ሰማያት እንዲቆዩ አልፈቀደም።

ቸ. እግዚአብሔር ለሳጥናኤልና እርሱን ለተከተሉ መናፍስት የእሳት ባሕር አዘጋጅቷል።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደሞዝ ሞት ይሆን ዘንድ ወስኗል።

እግዚአብሔር ሳጥናኤልንና የተከተሉትን መናፍስት ለዘላለም የሚቀጣበት የእሳት ባሕር በመባል የሚጠራ እጅግ አስጨናቂ ስፍራ አዘጋጅቷል።

እግዚአብሔር የማይታዘዙትን አይታገሥም። እግዚአብሔር የሚጠሉትን ሁልጊዜ ይቀጣል።

መምህር ሆይ፡- እዚህ ነጥብ ላይ ስለ እሳት ባሕር የምታስተምረው ከሰይጣን ጋር በተያያዘ ሁኔታ ብቻ ነው። ሰዎች ወደ እሳት ባሕር ይሄዳሉ በማለት አታስተምር። ስለ ሰው አፈጣጠርና ስለሠራው ኃጢአት ገና እንዳላስተማርክ አስታውስ።

ኀ. ሳጥናኤልና መላእክቱ እግዚአብሔርን ይጠላሉ።

ዋና አሳብ፡- ሳጥናኤል ከእግዚአብሔርና ከፈቃዱ ጋር ይዋጋል።

ሳጥናኤልና ተከታዮቹ እግዚአብሔርንና እርሱ የሚወዳቸውን ማናቸውንም መልካም ነገሮች ይጠላሉ። ሳጥናኤልና እነዚህ ሌሎች መናፍስት እግዚአብሔር ከአገልግሎቱ ካስወገዳቸው ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ከእግዚአብሔርና ከሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ጋር እየተዋጉ ናቸው።

የሳጥናኤል የአሁን መጠሪያው ሰይጣን ሲሆን ትርጉሙ «ጠላት» ማለት ነው። የተከተሉት መናፍስት ደግሞ አጋንንት በመባል ይጠራሉ። ሰይጣን የእግዚአብሔር ትልቁ ጠላት ነው። ሰይጣን እግዚአብሔር የሚያደርጋቸውን ነገሮች ለማስቆም ቀንና ማታ ከእግዚአብሔር ጋር ይዋጋል። የሰይጣን አጋንንት ደግሞ እግዚአብሔርን በመቃወም ሰይጣንን ያግዙታል።

በቅደም ተከተል ማሳያው ሠንጠረዥ ላይ፡- «ሰይጣንና አጋንንቱ» የሚጠሩበትን ስሞች አሳይ።

ነ. የሰይጣንና የመናፍስት አገልጋዮቹ መኖሪያ በሰማይ መሆኑ አብቅቷል።

ሰይጣንና አጋንንቱ አሁን የሚኖሩት በምድር ዙሪያ ሁሉ ነው።

መምህር ሆይ፡- ይህ ነገር ሕዝቡ ስለሚያምኑባቸው መናፍስት ጥያቄዎችን መጠየቅ እንዲጀምሩ ሊያደርግ ይችላል።

በትምህርታችን የመጀመሪያ ደረጃዎች፥ እምነታቸውን የምንቃወም እንዳይመስልብን በሚገባ መጠንቀቅ ያለብን ቢሆንም ከጠየቁ ግን የሚያምኑባቸው መናፍስት በሙሉ በመጀመሪያ የእግዚአብሔር መላእክት እንደነበሩ፥ አሁን ግን በሰይጣን አመራር ሥር እንዳሉ እንዲያውቁ አድርግ።

አንዳንድ የወንጌል አገልጋዮች ሕዝቡ ፈውስ እንደሚሰጡአቸው የሚታመኑባቸውና መልካም የሚመስሉ መናፍስትን የእግዚአብሔር መላእክት ሊሆኑ ይችላሉ ብለው ሲናገሩ ሰምቻለሁ። ለዚህ አሳብ ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለንም። ያልዳኑ ሰዎች የሰይጣን ልጆች ስለሆኑ በአጋንንቱ አመራር ሥር የሚኖሩ ናቸው። የእግዚአብሔር መላእክት የእግዚአብሔርን ልጆች ብቻ ይንከባከባሉ (ዕብራውያን 1፡14)።

አንዳንድ አጋንንት መልካምና ደግ አድርገው እራሳቸውን ቢያቀርቡም አታላዮች ናቸው። እራሳቸውን እንደ ቅዱስና፥ የብርሃን መልአክ አድርገው ሊለውጡ ይችላሉ፤ ነገር ግን የሰይጣን አገልጋዮች ስለሆኑ ሕዝብ ያታልላሉ (2ኛ ቆሮንቶስ 11፡14)።

ሕዝቡ በሙሉ እነዚህ መናፍስት በመጀመሪያ መልካም መላእክት ሆነው በእግዚአብሔር ተፈጥረው እንደነበር፥ አሁን ግን የሰይጣን መላእክት እንደሆኑ መረዳታቸው አስፈላጊ ነው። ይህን እውነት ለመረዳትና ለመቀበል ግን ጊዜ ሊወስድባቸው ይችላል።

ጥያቄዎች

1. ከመጀመሪያ በፊት ይኖር የነበረ ማን ነው? እግዚአብሔር።

2. መናፍስት ሁሉ የመጡት ከየት ነበር? ሁሉም የተፈጠሩት በእግዚአብሔር ነው።

3. እግዚአብሔር መናፍስትን የፈጠራቸው ሥጋና አጥንት አድርጉ ነውን? አይደለም።

4. እግዚአብሔር መናፍስትን ሲፈጥር የተወሰኑትን መልካም ሌሎቹን ክፉ አድርጉ ነውን ወይስ ሁሉንም መልካም አድርጉ ነበር? ሁሉንም መልካም አድርጉ ነበር።

5. እግዚአብሔር መናፍስትን የፈጠራቸው ለምን ነበር? አገልጋዮቹ እንዲሆኑ ነበር።

6. መናፍስት ምን ያህል ብዙ ናቸው? ሊቆጠሩ የማይችሉ ያህል ብዙ ናቸው።

7. እግዚአብሔር በፈጠራቸው ወቅት በየት ይኖሩ ነበር? ከእግዚአብሔር ጋር በሰማይ ይኖሩ ነበር።

8. እግዚአብሔር ከፈጠራቸው መላእክት ሁሉ የላቀና ውብ መልአክ ማን ነበር? ሳጥናኤል

9. እግዚአብሔር ለሳጥናኤል የሰጠው ሥልጣን ምን ነበር? በሌሎች መላእክት ሁሉ ላይ አለቃ ይሆን ዘንድ ነበር።

10. ሳጥናኤል ምን አደረገ? እንደ እግዚአብሔር ለመሆንና የእግዚአብሔርን ሥልጣን ለመውሰድ ዐቀደ።

11. ሳጥናኤል በእግዚአብሔር ላይ ባመፀ ጊዜ እነማን ተከተሉት? በርካታ የእግዚአብሔር መላእክት።

12. ሳጥናኤልና ተከታዮቹ ያቀዱትን ነገር እግዚአብሔር አውቆ ነበርን? አዎን።

13. እግዚአብሔር ምን አደረገ? ሳጥናኤልንና በዓመፃው የተባበሩትን መላእክት እግዚአብሔርን ያገለግሉ ከነበረበት ሥልጣናቸው አስወገዳቸው።

14. እግዚአብሔር የማያየው፥ የማይሰማውና የማያውቀው ነገር አለን? የለም። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያያል፤ ይሰማል፥ ያውቃልም።

15. እግዚአብሔር ለሳጥናኤልና ለመናፍስቱ ያዘጋጀው የቅጣት ስፍራ ምንድን ነው? የእሳት ባሕር ነው።

16. የሳጥናኤል የአሁን ስሙ ማን ይባላል? ትርጉሙስ ምንድን ነው? ሰይጣን፥ ትርጉሙም ተቃዋሚ፥ ባላጋራ፥ ጠላት ማለት ነው።

17. ሰይጣን የሚቃወመው ማንን ነው? እግዚአብሔርን ነው።

ትምህርት 5

የትምህርቱ ክፍል፡- ኦሪት ዘፍጥረት 1፡1

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር ከምንም ነገር ሁሉንም ነገር ፈጠረ።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊው የእምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ» (ዘፍጥረት 1፡1)።

. እግዚአብሔር የሁሉ በላይና ሉዓላዊ ነው።

ለ. እግዚአብሔር ከምንም ነገር ሁሉንም ነገር ፈጠረ።

ሐ. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

መ. እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው።

የትምህርት 4 ጥያቄዎችን ከልስ።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማዳበር

ሀ. «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ።»

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ በላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘፍጥረት 1፡1 አንብብ። መጀመሪያው እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ መፍጠር የጀመረበት ጊዜ ነው። እግዚአብሔር መናፍስትን ሁሉ እንዴት እንደፈጠረና እንዴት ሳጥናኤልና ሌሎች በርካታ መላእክት በእግዚአብሔር ላይ እንዳመፁ ተምረናል። አሁን ደግሞ የተቀሩትን ነገሮች ሁሉ የፈጠረው እግዚአብሔር እንደሆነ እንማራለን። የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ተፈጠሩ።

ለ. እግዚአብሔር ከምንም ነገር ሁሉንም ነገር ፈጠረ።

ለሁሉም ነገር ጅማሬ እንዳለውና ከጅማሬ በፊት ምድር፥ ፀሐይ፥ ጨረቃ፥ ከዋክብትና ሌሎች ነገሮች ሁሉ እንዳልነበሩ ተመልክተናል። ከጅማሬ በፊት ይኖር የነበረ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ታዲያ እግዚአብሔር ምድር፥ ፀሐይ፥ ጨረቃ፥ ከዋክብትና ሌሎች ነገሮችን ሁሉ ለመፍጠር በምን ተጠቀመ?

እናንተ ወንዶች፥ ቤት ለመሥራት የምትጠቀሙት በምንድን ነው? ይህን ለመሥራት የሚያስፈልጋችሁ እንጨት ወይም አፈር ባይኖራችሁ ልትሠሩ ትችላላችሁን? በምንም ነገር ሳትጠቀሙ ቤት ልትሠሩ ትችላላችሁን? ቤቶቻችሁን ተመልከቱ! የቤቶቻችሁን ዕቃ ለመሥራት ከሸክላ አፈር የሚገኙ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ትጠቀማላችሁ። የሸክላ አፈር ባይኖር የሸክላ ዕቃ ለመሥራት ትችሉ ነበርን? ምንም ነገር ሳይኖር ቤት ልትሠሩ ትችላላችሁን?

እናንተ ሴቶች፥ ቅርጫቶችንና ዘንቢሎችን ለመሥራት በተክሎች ትጠቀሙ የለምን? እነዚህ ተክሎች ባይኖሩ ቅርጫቶችንና ዘንቢሎችን መሥራት ትችሉ ነበርን? አንዳችም ነገር ሳትጠቀሙ ልትሠሩአቸው ትችላላችሁን?

እናንተ ልጆች፥ ከእንጨት የመጫወቻ ዕቃዎችን ትሠራላችሁ። እንጨት ባይኖር እነዚህን ዕቃዎች ልትሠሩ ትችሉ ነበርን?

ጨርሶ! ማናችንም ብንሆን ከባዶ ተነሥተን አንድን ነገር ልንሠራ አንችልም ፤ ሥራውን ለመጀመር የተወሰኑ ቁሳቁሶች ያስፈልጉናል። አይደለም እንዴ?

መምህር ሆይ፡- ተማሪዎቹን ለምትጠይቃቸው ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ጊዜ ስጣቸው። አዕዋፍም ሆኑ እንስሳት ጕጆዎቻቸውን ለመሥራት የሚያስፈልጉአቸው ቁሳቁሶች ስላሉ እነርሱንም በምሳሌነት ተጠቀምባቸው።

ታዲያ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሊጠቀምበት ያስፈለገውና የተጠቀመው በምንድን ነው? እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ለመሥራት የተጠቀመበት ከመጀመሪያ በፊት የነበረ አንዳች ነገር ነበርን? አልነበረም። እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር የሠራው ከምንም ተነሥቶ ነው። አንድ ነገርን ከምንም ነገር ተነሥቶ ሊያደርግ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ከምንም ነገር ተነሥቶ ሁሉንም ነገር ፈጠረ።

መምህር ሆይ፡- ስለምትነግራቸው ነገሮች ቢከራከሩ አትጨነቅ፤ መልስህ «በመጀመሪያ ብቻውን የነበረ እግዚአብሔር ብቻ ነው»። እኛ የወንጌል አገልጋዮች በዚያ አልነበርንም፤ እናንተም በዚያ አልነበራችሁም። የእናንተም ሆኑ የእኛ ቅድመ አያቶች በዚያ አልነበሩም። በመጀመሪያ የነበረ እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ሁኔታው ምን ይመስል እንደ ነበር ሊነግረን የሚችል እርሱ ብቻ ነው።» የሚል ይሁን።

ሐ. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

እግዚአብሔር ማንኛቸውንም ነገሮች ከምንም ነገር ተነሥቶ ሊያበጅ እንዴት ተቻለው? እግዚአብሔር ይህን ሊያደርግ የቻለው ለእርሱ የሚሳነው ነገር ስለሌለ ነው። የሚፈልገውን ማንኛውንም ነገር ሊያደርግ ይችላል። ከምንም ተነሥቶ የሠራቸውን ነገሮች ሁሉ ተመልከቱ። ከእግዚአብሔር የበለጠ ብርቱ አለን? እናንተ ናችሁን? ሰይጣን ነውን? መናፍስት ናቸውን? ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን? የለም። እግዚአብሔር የሚፈልገውን ሁሉ ማድረግ ይችላል።

መ. እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው።

እግዚአብሔር ማናቸውንም ነገሮች መሥራት እንዴት አወቀ?

እኔና እናንተ ልንሠራቸው የማንችላቸው በርካታ ነገሮች አሉ። ልንሠራቸው የማንችላቸውን ነገሮች ለመሥራት መማር አለብን።

ሕፃናት እስኪማሩ ድረስ መራመድ ወይም መናገር አይችሉም። ትናንሽ ልጆች አደን ማደን፥ ጽሑፎችን ማንበብ፥ ቤቶችን መገንባት፥ የአትክልት ስፍራዎችን ማዘጋጀት ወይም ምግብ ማብሰል እስካልተማሩ ድረስ አያውቁም።

እግዚአብሔር የፈጠራቸው መናፍስትም ቢሆኑ ሁሉን ነገር አያውቁም።

ለእግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያስተማረው ማን ነው? እግዚአብሔርን ያስተምረው ዘንድ በመጀመሪያ የነበረ አለን? እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን እንዴት እንደሚፈጥር የሚያስተምረው ያስፈልገው ነበርን?

በጭራሽ! እግዚአብሔር እንደ እኛ አይደለም፤ እግዚአብሔር የማያውቀውና ሙሉ በሙሉ የማይረዳው አንዳችም ነገር የለም።

መምህር ሆይ፡- የሚከተሉትን ጠቃሚ ነጥቦች አትዘንጋ፡-

ሀ) ጊዜህን ለማስተማር ተጠቀምበት። ተማሪዎችህ ከአንተ ጋር በሚገባ ጉዳዩን እየተከታተሉ መሆኑን አረጋግጥ። ለአእምሮአቸውና ለተፈጥሮአዊ አስተሳሰባቸው በሚስማማ ሁኔታ ግለጠው።

ለ) እየተነጋገራችሁባቸው ስላሉት ርእሰ ጉዳዮች እንዲወያዩ ለማድረግ ሞክር። የሚሰጡትን ማንኛውንም አሳብ በማዳመጥ አክብሮትህን አሳያቸው።

ሐ) ስሕተት ሲሠሩ ሁልጊዜ ወዲያውኑ አታርማቸው።

መ) ከእግዚአብሔር ቃል እስካሁን ካስተማርካቸው ጉዳዮች ጋር የሚቃረን አሳብ ከሰነዘሩ፥ ስለ ርእሰ ጉዳዩ እግዚአብሔር ምን እንደሚል ጠይቃቸው። የተለየ አመለካከት የታየው በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል እንጂ በእነርሱና በአንተ መካከል ዓይነት ሆኖ መታየት የለበትም።

ሠ) እስካሁን ወደ አላስተማርከው ርእሰ ጉዳይ ወይም ዝርዝር እንዳይከቱህ ተጠንቀቅ። በታሪካዊ ቅደም ተከተል አንጻር ገና ለማስተማር ያልደረስክበትን ጉዳይ ከጠየቁህ «በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው! መልሱን ወደፊት ከሚገኝበት ከእግዚአብሔር መጽሐፍ እንመለከተዋለን» በማለት መልስላቸው።

ረ) በዚህ ትምህርት እግዚአብሔር ስለፈጠራቸው ሰማያትና ምድር ዝርዝሮች አታስተምር። እነዚህ ከሚቀጥለው ትምህርት ጀምሮ ፍጥረታት የተፈጠሩበት ስድስት ቀናት በሚሉት ትምህርቶች ይካተታሉ።

ጥያቄዎች

1. በመጀመሪያ ሰማይና ምድርን የፈጠረው ማን ነበር? እግዚአብሔር ነበር።

2. እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ለመፍጠር የተጠቀመው በምን ነበር? በምንም አልተጠቀመም። ከምንም በመነሣት ሰማይና ምድርን ፈጠረ።

3. እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ለመሥራት እንዴት ቻለ? እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው። ለእርሱ የሚሳነው ነገር የለም።

4. እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን መሥራት እንዴት አወቀ? እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው።

5. ለእግዚአብሔር ሁሉን ነገር መሥራት ማን አስተማረው? ማንም አላስተማረውም።

6. እንደ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የሚያውቅ ሰው ወይም መንፈስ አለን? የለም። ሁሉን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ትምህርት 6

የትምህርቱ ክፍል፡- አሪት ዘፍጥረት 1:2-23

አጠቃላይ ርእስ፡- የእግዚአብሔር ተፈጥሮና ባሕርይ በመፍጠር ሥራው ውስጥ ተገልጧል።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. ጨለማና ባዶነት በምድር ነበር (1:1-2)።

ለ. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ማንኛውንም ነገር ለመፍጠር ተዘጋጅቶ በመጠበቅ ላይ ነበር (1:2)።

ሐ. አንደኛ ቀን፡- ብርሃን ተፈጠረ (1:3-5)።

. እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው።

. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

. እግዚአብሔር ቅዱስ ነው።

መ. ሁለተኛ ቀን፡- ጠፈር ተፈጠረ (1:6-8)።

ሠ. ሦስተኛ ቀን፡- ደረቅ መሬት፥ ውቅያኖሶችና ዘርን የሚሰጥ ሣርና ቡቃያ ፍሬን የሚሰጥ ዛፍ ተፈጠረ (1:9-13)።

. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

. እግዚአብሔር ፍቅር ነው።

. እግዚአብሔር ቅዱስ ነው።

ረ. አራተኛ ቀን፡-ፀሐይ፥ ጨረቃና ከዋክብት ተፈጠሩ (1:14-19)

. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ ይገኛል።

. እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው።

. እግዚአብሔር ቅዱስ ነው።

ሰ. አምስተኛ ቀን፡- በባሕር የሚኖሩና በሰማይ የሚበሩ እንስሳትና አእዋፍ ተፈጠሩ (1፡20-23)።

. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

. እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው።

የትምህርት 5 ጥያቄዎችን ከልስ።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማዳበር

ሀ. ጨለማና ባዶነት በምድር ላይ ነበር።

ዘፍጥረት 1፡1፥ 2 አንብብ። ቀን የፀሐይ ብርሃን፥ ማታ ደግሞ የጨረቃ ብርሃን ባይኖር ኖሮ ደስ ይልሃልን? በምድር ላይ የእሳት ወይም የሰው ሠራሽ ብርሃን ወይም ሌላ ማንኛውም ዓይነት ብርሃን ባይኖር ኖሮ አስጨናቂ አይሆንም ነበርን? የት እንደምትሄዱ ለማየት አትችሉም ነበር። እርስ በርስ ለመተያየት አትችሉም ነበር። ዓሣ ለማጥመድ፥ አደን ለማዳን ወይም እህል ለመዝራት ማየት አትችሉም ነበር።

በመጀመሪያ ብርሃን አልነበረም፤ ጨለማ ምድርን በሙሉ ሸፍኖ ነበር። ደረቅ መሬትም አልነበረም። ምድር በሙሉ በውኃ ተሸፍና ነበር።

መምህር ሆይ፡- ምድር ጨለማና ባዶ የነበረችበትን ሁኔታ የሚያሳይ ሥዕል ሠርተህ አሳያቸው። ይህ የእግዚአብሔርን የመፍጠር ኃይል ለማሳየት ታላቅ ሚና ይጫወታል።

ለ. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ማንኛውንም ነገር ለመፍጠር ተዘጋጅቶ በመጠበቅ ላይ ነበር።

ዘፍጥረት 1፡2 አንብብ። በምድር ሁሉ ላይ ሕይወት ባልነበረ ጊዜ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በዚያ ነበር። ማናቸውንም ነገሮች የመፍጠር ታላቅ ሥራውን ለመጀመር በመጠባበቅ ላይ ነበር።

ቤት ለመሥራት በመትዘጋጁበት ጊዜ እንዳለው ዓይነት ሁኔታ ነው። በግለዳ ትነቁና ሥራ ለመጀመር ትዘጋጃላችሁ። እግዚአብሔር ስለማያንቀላፋ ሥራውን ለመሥራት በጊዜ መንቃት አያስፈልገውም።

በዚያን ጊዜም ሌሊት ገና አልነበረም። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግን ሁሉን ነገር ለመፍጠር በዝጅግት ላይ ነበር።

አንድ እግዚአብሔር ብቻ እንዳለ፥ ነገር ግን አንዱ እግዚአብሔር ሦስት አካላዊ ሕልውናዎች እንዳሉት እንደነገርኋችሁ ታስታውሳላችሁ? እነርሱም እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድና፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ናቸው፤ እነዚህ ሦስቱ በአንድነት ፍጥረታትን ሁሉ ፈጠሩ።

ሐ. አንደኛ ቀን! ብርሃን ተፈጠረ።

መምህር ሆይ፡- የእግዚአብሔር ባሕርይና ችሎታ በመፍጠር ተግባሩ ውስጥ በግልጽ ይታያል፤ ስለዚህ የስድስት ቀናት የመፍጠር ሥራውን ስታስተምር የእግዚአብሔርን ባሕርያት አመልክት።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው።

ዘፍጥረት 1፡3 አንብብ። ቃሉን በመናገር ብቻ ብርሃን የሚፈጥር ሰው ታውቃላችሁን? ብርሃን በሌለበት በጨለማ ጊዜ በጫካ ሆነህ ታውቃለህ? ታዲያ ምን አደረግህ? ቃል በመናገር ብቻ ጨለማውን ወደ ብርሃን ልትለውጠው ችለህ ነበር?

በእኩለ ሌሊት ከአንድ ጫካ ውስጥ ገብተህ ብርሃን እንዲሰጥህ የያዝከው መሣሪያ ባትሪው ቢያልቅ ብርሃን ሰጪውን መሣሪያ «ብርሃን ይሁን» ብለህ ልታዝዘው ትችላለህን? አትችልም። በምትኩ በቅርብ ወዳለ አንድ ቤት በመሄድ ቅጠል ፈልገህ በማሰር በእሳት ታቀጣጥልና ያንን እንደ ብርሃን በመጠቀም ወደ ቤትህ ትሄዳለህ።

እግዚአብሔር ግን በጨለማ እንዲያበራ ብርሃንን አዘዘ። እግዚአብሔር ብርሃንን መሥራት ሊያውቅ የቻለው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ብርሃንን እንዴት መሥራት እንዳለበት ያወቀው እርሱ ሁሉን አዋቂ ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር የማያውቀው አንዳችም ነገር የለም።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

ለእግዚአብሔር ብርሃን ለመፍጠር ከባድ ነገር ነበርን? አልነበረም። ለእግዚአብሔር ይህ ከባድ ነገር ያልነበረው ለምንድን ነው?

እግዚአብሔር ባለሙሉ ኃይል ስለሆነ ነው። ሊያደርግ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ማድረግ ይችላል።

እግዚአብሔር ብርሃንን እስኪፈጥር ድረስ በዓለም ብርሃን አልነበረም። ብርሃንን የፈጠረው ቃሉን በመናገር ብቻ ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስ ነው።

ዘፍጥረት 1፡4ን አንብብ። እግዚአብሔር የፈጠረው ብርሃን መልካም ነበር። እግዚአብሔር የፈጠረው ማንኛውም ነገር መልካም ነው፤ ምክንያቱም እርሱ ፍጹም ነውና ነው። እግዚአብሔር አንድ ነገርን በፈጠረ ቁጥር «መልካም» እንደሆነ ይናገር ነበር። በእርግጥ መልካም ነበር፤ ፍጹምም ነበር።

እኛም ብዙ ጊዜ አንዳንድ ነገሮችን እንሠራለን፤ የምንሠራቸው ነገሮች ግን ፍጹም አይደሉም። አነስተኛ የእንጨት አሻንጉሊት (የሰው ምስል) ትሠሩ ይሆናል፤ የምትሠሩት ይህ የሰው ምስል ዋጋ ቢስ ባይሆንም እውነተኛ ሰው እንዳይደለ ታውቃላችሁ። አንድን ነገር የተለየና የተሻለ አድርጉ ለመሥራት ምኞታችሁ ነው።

እግዚአብሔር ያደረገው ማንኛውም ነገር ግን ፍጹም ትክክለኛ ነው። ለምን? ምክንያቱም እርሱ መልካም ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። በእግዚአብሔር ዘንድ አንዳችም ስሕተት የለም። በእግዚአብሔር ዘንድ ማንኛውም ነገር መልካም ሆኖ የተፈጠር ነው።

ዘፍጥረት 1፡5 አንብብ። እግዚአብሔር ብርሃንን በፈጠረ ጊዜ ጨለማን ሁሉ አላስወገደም። ጨለማ በምሽት ጊዜ እንዲሰለጥን ተወው። እግዚአብሔር ብርሃኑን ቀን፤ ጨለማውን ደግሞ ሌሊት ብሎ ጠራው። በዓለም መጀመሪያ፥ የመጀመሪያው ቀን ይህ ነበር።

መምህር ሆይ፡- እግዚአብሔር በዚህ ጊዜ የፈጠረው ብርሃንን እንጂ ፀሐይን አይደለም።

መ. ሁለተኛ ቀን፡- ጠፈር ተፈጠረ።

ዘፍጥረት 1፡6-8 አንብብ። በሁለተኛ ቀን እግዚአብሔር አየርና ጠፈርን ፈጠረ። እግዚአብሔር በዓለም ካለው ውኃ የተወሰነውን ከፍል ከጠፈር በላይ አደረገው።

መምህር ሆይ፡- ሀ) ጠፈር ማለት በቀላሉ «ቀጭን፥ የተዘረጋ ሕዋ» ማለት ነው። ቀደም ሲል ለሕዝቡ ባስተማርንበት ክፍል ይህን አየርና ጠፈር ብዬ ገልጬዋለሁ። ይህም በቀን ወደላይ አንጋጠን ስንመለከት የምናየው ሰማይ ነው። በአድማጮችህ ቋንቋ ገላጭ የሚሆንበትን የተሻለ ቃል መርጠህ ተጠቀም።

እግዚአብሔር ውኃውን ከጠፈር በላይ ሲያደርግ ምን እንዳደረገ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ አይናገርም። ብዙ ተአማኒ የሆኑ ሳይንቲስቶች እንደሚያምኑት፥ ይህ ውኃ ደመና አይደለም። እግዚአብሔር ወደ እንፋሎትነት ለውጦት ምድርን እንደ ጃንጥላ ከቦ እንዲቆይ ያስቀመጠው ከአካባቢው አየር በላይ ያለው ነው። (ይህ አሳብ የተገኘው ሄንሪ ኤም ሞሪስ ጀኔሲስ ሪኮርድ በሚል ርእስ ከጻፈው በቤከር ቡክ ሃውስ ግራንድ ራፒድስ ሚሺጋን ገጽ 58፥ 59 ላይ ነው።)

እግዚአብሔር ምን እንዳደረገ በአእምሮአቸው በሚገባ ግልጽ እንዲሆን ማድረግ ጠቃሚ ነው፤ ምክንያቱም የጥፋትን ውኃ ታሪክ ስታስተምር፥ እግዚአብሔር ይህን ሂደት በመገልበጥ በጠፈር ያኖረውን ውኃ ወደ ምድር እንዴት እንደለቀቀው ለማስረዳት ቀላል ስለሚሆን ነው።

ለ) በዚህ ትምህርት ውስጥ ሌሎች ነጥቦችን ከማስተማርህ በፊት በትምህርቱ ውስጥ ያሳየሃቸውን አራት ነጥቦች በአጭሩ ከልስ።

ሠ. ሦስተኛ ቀን፡- ደረቅ መሬት፥ ውቅያኖሶችና ዘርን የሚሰጥ ሣርና ቡቃያ፥ ፍሬን የሚሰጡ ዛፎች ተፈጠሩ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

መምህር ሆይ፡- እግዚአብሔር የውቅያኖስን ወሰኖች በመሠረተበት ጊዜ ያሳየውን ኃይል፥ በመዝሙር [104]፡5-9 ላይ በምትመለከትበት ጊዜ አንተንም ደስ አሰኝቶ የማስተማር ፍላጎትህን ያነቃቃልሃል።

ዘፍጥረት 1:9-10 አንብብ። በመጀመሪያ ምድር ሙሉ በሙሉ በውኃ ተሸፍና ነበር። እግዚአብሔር ውኃውን እርሱ ወደሚፈልገው አቅጣጫ እንዲሰበሰብ እስኪናገር ድረስ ደረቅ መሬት አልነበረም።

ለመሆኑ ከእናንተ መካከል ወደ ባሕር ወይም ወደ ወንዝ በመሄድ፡- «ባሕር ወይም ወንዝ ሆይ፥ ወደ ማዶ መሻገር ስለምፈልግ ወደ ኋላህ ተመለስ» ለማለት የሚችል ሰው አለን? ቢልስ ይመለሳልን?

ውኃንና ምድርን ከፈጠረ ከእግዚአብሔር በስተቀር ማንም ተፈጥሮን ሊቆጣጠርና ሊያዝዝ አይችልም።

መምህር ሆይ፡- በአድማጮቻችን አእምሮ ውቅያኖስንም ሆነ ማንኛውም የውኃ አካል የሚቆጣጠር እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ በሚገባ አስረግጠን ከገለጥን ኢየሱስ አምላክ እንደሆነና በውኃ ላይ እንደተራመደ፥ ማዕበሉንም ጸጥ እንዳሰኘ፥ በኋላ ለማስተማር የሚገጥመን ብዙ ችግር አይኖርም። ኢየሱስ ሰው ብቻ ቢሆን ኖሮ እነዚህን ነገሮች ለሚድረግ አይችልም ነበር።

ዘፍጥረት 1:11-13 አንብብ። እግዚአብሔር አትክልትና ዕፀዋትን በሙሉ ፈጥሯል። እነዚህን እጅግ ብዙና የተለያዩ አትክልትና ዕፀዋት፥ ዛፎችና ፍሬ የሚሰጡ ተክሎችን ሁሉ የፈጠረ እንዴት ዓይነት አስደናቂ አምላክ ነው! ለእነዚህ ፍሬዎች የተለያዩ ቀለሞች፤ ጣዕሞችና ቅርፆች የሰጣቸው እርሱ ነው። በእያንዳንዳቸው ውስጥ የራሳቸውን ዓይነት ዘር የሚያራቡ ፍሬዎችን አደረገ። በመሆኑም ዛሬ የምናያቸው አትክልትና ዕፀዋት በሙሉ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ከፈጠረው የተገኙ ናቸው።

መምህር ሆይ፡-

ሀ) ሕዝቡ አስደናቂ ስለሆኑት ስለተለያዩ የአትክልትና የዕፀዋት ዝርያዎች ከፍተኛ እውቀት አላቸው። አንተም አትክልትንና ዕፀዋትን በሙሉ የፈጠረው እግዚአብሔር እንደሆነ ስታስተምራቸው፥ ምን ያህል የተለያዩ አትክልትና ዕፀዋት፥ ዛፎችና የሚበላ ፍሬ የሚሰጡ ተክሎች በጫካ እንደሚገኙ ጠይቃቸው። ስለእነዚህ ነገሮች እንዲናገሩ ዕድል ለመስጠትህ እርግጠኛ ሁን። ስለተለያዩ የአትክልትና

የዕፀዋት ደግሞም የዛፍ ዝርያዎች ከአንተ የበለጠ እንደሚያውቁ አምነህ መቀበል በጣም ጥሩ ነው።

ለ) የሚቀጥለው ክፍል እግዚአብሔር የሕግና የሥርዓት አምላክ በመሆኑ ላይ ያተኩራል። ሆኖም እንደ ዋና አሳብ ያልተዘረዘረው ለጊዜው ትኩረት ያደረገው በዚህ በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ላይ ብቻ ስለሆነ ነው።

እግዚአብሔር የፈጠራቸው ነገሮች በሙሉ ከሁሉ በተሻለ መንገድ የተፈጠሩ ናቸው። ለምን? ምክንያቱም እግዚአብሔር የሕግና የሥርዓት አምላክ ስለሆነ ነው።

ወደዚህ አበባ ተመልከቱ። የአበባው ቅጠሎች እንዴት እንደተቀናበሩ ልብ በሉ። እግዚአብሔር የሚሠራውን ነገር አዛብቶ አያውቅም፤ ስለ ሚሠራው በሚገባ ያውቃል።

ወደ ፓፓዩ ዛፍ ተመልከቱ፥ ከሥሩ በምትቆሙበት ጊዜ እያንዳንዱ ቅርንጫፍ ቆንጆ ጃንጥላ እንዲመስል ተስተካክሎ የተሠራ ነው። ሁሉንም የቅርንጫፍ አቃፊዎች በአንድ ጐን አላደረገም። እግዚአብሔር የሕግና የሥርዓት አምላክ ስለሆነ ዛፎችንና የቀሩትን ማናቸውንም ነገሮች በሥርዓትና በትክክለኛ መንገድ አበጅቶአቸዋል።

ዋና አሳብ፡ - እግዚአብሔር ፍቅር ነው።

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ዛፎችን የፈጠረው ለምን ነበር? እግዚአብሔር የፈጠራቸው እርሱ ይፈልጋቸው ስለነበረ ነውን? አይደለም። የፈጠራቸው ለእኛ ብሎ ነው። ያለ ዛፎች መኖር ሕይወትን አስቸጋሪ አያደርገውም ነበርን? ዛፎች ባይኖሩ ኖሮ ምግባችንን የምናበስልበትም ሆነ ቤቶቻችንን የምንሠራበት አንዳችም ዕንጨት አናገኝም ነበር። ዛፎች ባይኖሩ ኖሮ እጅግ ሞቃት ይሆን ነበር። በእርሻ ማሳዎቻችሁ ላይ ስትሠሩ በአጠገባችሁ ወዳሉ ዛፎች ጥላ ሄዳችሁ ማረፍ ትወዳላችሁ። እግዚአብሔር ዛፎችን የፈጠረው ሊፈጥረው ላቀደው ለሰው ልጅ ነበር። እግዚአብሔር ዛፎችን የፈጠረልን እርሱ አፍቃሪና ደግ አምላክ ስለሆነ ነው።

እግዚአብሔር ፍሬ የሚሰጡ ተክሎችን የፈጠረው ለምን ነበር? እግዚአብሔር ስለተራበና ለራሱ የሚበላ ነገር ስላስፈለገው ይህን

ለግድረግ የወሰነ ይመስልሃልን? እግዚአብሔር «ብዙ ነገሮችን ስለፈጠርኩ አሁን በእርግጥ ተርቤያለሁ፤ ስለዚህ የሙዝ ዛፍ ፈጥሬ ሙዝ እበላለሁ» ያለ ይመስልሃልን? እንደዚያ አላለም! እግዚአብሔር እንደ እኛ የሚራብ አካል የለውም። እግዚአብሔር ምግብ አያስፈልገውም። እግዚአብሔር ፍሬን የሚሰጡ ዛፎችና ተክሎችን የፈጠረው እርሱ አፍቃሪና ደግ ስለሆነ ነው። ዓለምን ሰው የሚኖርባት እንድትሆን እያዘጋጃት ነበር። ለመኖርና ለማደግ ምግብ የሚያስፈልገው አካል ሊሰጠን አቅዶ ነበር።

አንድ ወጣት ለጋብቻ ዝግጅት ሲያደርግ ቤት ይሠራል። ለሙሽራዪቱ የሚያስፈልጋትን ነገር ሁሉ ያዘጋጅላታል። ወጣቱ ግናቸውም ነገር የተሟላ እንዲሆን ይፈልጋል። እግዚአብሔር ደግሞ በዚህ ዓለም እኛን ደስ የሚያሰኘንና መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ አዘጋጀ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስ ነው።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ ሲፈጥር ሁሉም መልካም ነበር። ምንም መጥፎ ነገር አልነበረም። እሾህና አረም እንደ አሁን አይበቅሉም ነበር። መርዛማ የሆነ ፍሬ አልነበረም። አትክልትና ፍራፍሬዎች በበሽታ አይጠቁም ነበር። እግዚአብሔር ፍጹም ስለሆነ በመጀመሪያ እርሱ የፈጠራቸው ነገሮች ሁሉ ፍጹም ነበሩ፤ ጨርሶ ስሕተት ሊሠራ ስለማይችል የሚያደርገው ነገር ሁሉ ፍጹም ነው።

መምህር ሆይ፡- ተማሪዎቹ፥ በአሁን ጊዜ ያለው ነገር በፍጥረት መጀመሪያ ከነበረው ነገር በጣም የሚለየው ለምን እንደሆነ ከጠየቁህ፥ ነገሮች እንዲለወጡ ያደረገው ምን እንደሆነ ከእግዚአብሔር መጽሐፍ ወደፊት እንደሚማሩ ንገራቸው። ይህም ጠያቂዎቹን ትምህርቱን በበለጠ በንቃት እንዲከታተሉ ያደርጋቸዋል።

ረ. አራተኛ ቀን፡- ፀሐይ ጨረቃና ከዋክብት ተፈጠሩ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

መምህር ሆይ፡- ይህን ክፍል ስታስተምር የበለጠ እንድትነቃቃ መዝሙር (104)፡10-35 አንብብ።

ዘፍጥረት 1፡14-19 አንብብ። እግዚአብሔር ፀሐይን፥ ጨረቃና ከዋክብትን ፈጠረ። ይህን ያደረገው በመናገር ብቻ ነበር። ማንኛውም ሰው ይህን ለማድረግ ይችላልን? አልጋ ለመሥራት ብትፈልግ በመናገር ብቻ ልትሠራው ትችላለህን? ሰዎች፥ አውሮፕላንና ሌሎች መጓሪያዎችን ወይም የሚፈልጉትን ሌላ ነገር በመናገር ብቻ ሊሠሩ ይችላሉን? አይችሉም! በጭራሽ አይችሉም። ይህን ማድረግ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔር ፀሐይ፥ ጨረቃና ከዋክብትን በመናገር ብቻ መፍጠር አያቅተውም፤ ምክንያቱም የሚፈልገውን ማንኛውንም ነገር መሥራት ይችላልና ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉ ስፍራ ይገኛል።

እግዚአብሔር ፀሐይን፥ ጨረቃንና ከዋክብትን ከፈጠረ በኋላ በሰማይ ከፍ አድርጎ አስቀመጣቸው። ለእናንተ በጣም የራቁ ባይመስላችሁም የሚገኙት ከምድር እጅግ በጣም ርቀው ነው። እግዚአብሔር በሰማይ እጅግ አርቆ ሊያስቀመጣቸው የቻለው እንዴት እንደሆነ ለመገመት ትችላላችሁን?

ብርቱካን መብላት ብትፈልጉ ብርቱካኑን ከዛፉ ላይ እንዴት ታወርዱታላችሁ? ቤት ስትሠሩ ጣራውን ለማበጀት የምትወጡት እንዴት ነው?

ታዲያ እግዚአብሔር ከዋክብትን፥ፀሐይንና ጨረቃን ሰማይ ላይ ሊያስቀምጣቸው ሲፈልግ ያደረገው ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ? እግዚአብሔር «ፀሐይዋን ከፍ አድርጌ ላይ ልሰቅላት ስለምፈልግ፥ ረዥም መሰላል መሥራት አለብኝ፤ መሬት ላይ ልትከለውና በእርሱ ላይ ወጥቼ ወደ ፈለግሁት ቦታ ልስቀላት» ያለ ይመስልሃልን? ታዲያ ወደዚያ ከፍታ እንዴት ደረሰ? በመሰላል ወይስ በመብረር?

አይደለም። እግዚአብሔር እንደ እኛ አይደለም። ከፍተኛ ስፍራዎች ለመድረስ ወደ ላይ መውጣት አያስፈልገውም። እሩቅ ስፍራ ለመድረስ እግዚአብሔር መራመድ ወይም መብረር አያሻውም። ለምን? ምክንያቱም እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ የሚገኝ ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር ፀሐይ፥ ጨረቃና ከዋክብት ባሉበት እንዲሁም በዚህ ምድር ላይ ይገኛል። እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ይገኛል።

እግዚአብሔር አንድ ነገር ማድረግ ሲፈልግ ከአንድ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ መንቀሳቀስ አያስፈልገውም፤ እርሱ በዚያ ስፍራ አለ። እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ ይገኛል።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው።

እግዚአብሔር ፀሐይን፥ ጨረቃና ከዋክብትን በላይ በሰማይ እንዴት ሊያቆማቸው ቻለ? ለምን አይወድቁም?

አንድ ፍሬ ወደ ላይ ብንወረውር ወዲያውኑ ተመልሶ ይወድቃል? አይደለምን? ታዲያ ፀሐይ፥ ጨረቃና ከዋክብት ለምን አይወድቁም? እግዚአብሔር ሁሉን ነገር እንዴት መደረግ እንዳለበት ስለሚያውቅ በሰማይ እንዲቀመጡ አደረገ። በታላቅ ኃይሉ ቃል በመናገር ብቻ ፈጠራቸው። በፈለገው ስፍራ አኖራቸው፤ በዚያም ጠበቃቸው። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር እንዴት ማደረግ እንዳለበት ብቻ ሳይሆን የሚያውቀው እርሱ ኃያል ስለሆነ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ማድረግ ይችላል።

መምህር ሆይ፡-

ሀ) ተማሪዎቹ፥ እነዚህ ፍጥረታት (ፀሐይ፥ ጨረቃና ከዋክብት) ባሉበት ስፍራ የተቀመጡት እንዴት እንደሆነ የሚገልጡበት የራሳቸው ፅንሰ አሳብ ሊኖራቸው ይችላል፤ ስለዚህ በዚህ ነጥብ ላይ ብዙ ጊዜ አታጥፉ። ከተፈጥሮ ጋር በተያያዙ ሳይንሳዊ እውነቶች አለመስማማታቸውን ቢቀጥሉ እንኳ በመጀመሪያ ከሁሉ በላቀ ሁኔታ እንዲማሩ የምንፈልገው ስለ እግዚአብሔር ባሕርይና ችሎታ ነው።

ለ) በሚቀጥለው ክፍል ያለው አትኩሮት አሁንም እንደገና ያረፈው እግዚአብሔር የሕግና የሥርዓት አምላክ በመሆኑ ላይ ነው።

እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ጀምሮ ፀሐይ በየቀኑ እንድትወጣና እንድትጠልቅ፥ ጨረቃና ከዋክብት ደግሞ በምሽት እንዲሠለጥኑ፥ ይህም ከዓመት እስከ ዓመት ያለማቋረጥ እንዲከናወን አደረገ፤ ምክንያቱም እርሱ የሕግና የሥርዓት አምላክ ስለሆነ ነው። ስለ

የትኛውም ነገር ግድ የሌለው አልነበረም። የሚያደርጋቸውን ነገሮች በሙሉ በሕግጋቱ መሠረት ያደርጋቸዋል።

ሁሉን ነገር በትክክል ለመፈጸም የሚፈልጉ ሰዎችን እናውቃለን። ጥሩና ጠንካራ ቤት ለመገንባት ጊዜ ብመውሰድ ጥረታቸውን ያሳያሉ። የእርሻ መሬቶቻቸው ድንበሮች በትክክል የተሠሩ፥ አዝርዕቱ በመሥመር በቅለው በንጽሕና የተጠበቁ ናቸው። ከብቶቻቸውን ከአውሬ ለመጠበቅ አጥራቸውን በደንብ ያጠሩ ናቸው። ሆኖም እንደ እግዚአብሔር ግናቸውንም ነገሮች በፍጹምነት የሚያከናውን ግን ግንም የለም። እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ ከመጀመሪያው ጀምሮ ፍጹም አሳምሮ አበጃቸው። ይህን ያደረገው እርሱ የሕግና የሥርዓት አምላክ ስለሆነ ነው።

እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ በሥርዓቱ ያደረገው ሕይወታችን እርሱ በሚፈልገው መንገድ እንዲመራና እንዲደራጅ ነበር። ፀሐይ በጠዋት እንደምትወጣ ባናውቅ እንዴት አስቸጋሪ ይሆን ነበር? ፀሐይ መቼ እንደምትወጣ ባታውቁ ጠዋት ተነሥታችሁ ቁርስ ለመብላትም ሆነ በእርሻ መስኩቻቸሁ ላይ ለመሥራት እንዴት ማቀድ ትችሉ ነበር? ነገር ግን ፀሐይ በየዕለቱ ትወጣለች፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በዚያ መልክ አብጅቶአታልና ነው።

መምህር ሆይ፡- መዝሙር (104)፡ 19-24 ተመልከት።

ፀሐይ ስትወጣ በምትመለከትበት ጊዜ ሁሉ፥ እግዚአብሔር እንደፈጠራት፥ እንድትወጣና እንድትጠልቅ እንዳደረገ አስታውስ። ይህን ያደረገው ለመሥራት፥ ለመብላት፥ ለመተኛት እንድንችልና ሰብሎቻችን እንዲያድጉ ለማድረግ ነው።

ጨረቃና ከዋክብት በየዓመቱ የሚዞሩበት ሥርዓት ባይኖራቸውስ? ፀሐይን በመመልከት ለእርሻ መሬቶቻችሁ ቁጥቋጦዎችን መቼ መመንጠር እንዳለባችሁ ታውቃላችሁ። የእርሻ መሬቶቻችሁን መቼ ማዘጋጀት፥ ሰብሎቻችሁን መቼ ማጨድ እንዳለባችሁ ፀሐይን በመመልከት ታውቃላችሁ።

መምህር ሆይ፡- አብዛኛዎቹ ሰዎች ወደ ፀሐይ በመመልከት የእርሻ መሬቶቻቸውን የሚያዘጋጁትና ሰብሎቻቸውን የሚያጭዱት

መቼ እንደሆነ ያውቃሉ። ይህን ልታስታውሳቸው ይገባል። እግዚአብሔር እነዚህን ሰማያዊ አካላት የፈጠረበት ሌላው ምክንያት ይህ ነው።

እግዚአብሔር ይህን ሁሉ አቀናበረ። ጨረቃና ከዋክብትን በምትመለከቱበት ጊዜ ሁሉ ባሉበት ሁኔታ በሥርዓት እንዲጓዙ የሚቆጣጠራቸውም ሆነ አስቀድሞ የሠራቸው እግዚአብሔር እንደሆነ አስታውሱ።

እግዚአብሔር፤ ፀሐይ፥ ጨረቃና ከዋክብትን በዚህ መልክ የሠራው እርሱ የሕግና የሥርዓት አምላክ ስለሆነ ነው። እርሱ ግድየለሽ አምላክ አይደለም። እግዚአብሔር እርካታን የሚያገኘው ማንኛውም ነገር በትክክለኛ መንገድ ሲሠራ ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስ ነው።

እግዚአብሔር የፈጠራቸው ፀሐይ፥ ጨረቃና ከዋክብት ሁሉም እጅግ መልካም ነበሩ። እግዚአብሔርም በፈጠራቸው በእነዚህ ፍጥረታቱ ደስ ተሰኝቶ ነበር። እርሱ ፍጹም ስለሆነ የሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ፍጹማን ናቸው።

ሰ. አምስተኛ ቀን፡- የባሕር እንስሳትና አዕዋፍ ሁሉ ተፈጠሩ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው። እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው።

ዘፍጥረት 1፡20-23 አንብብ። በአምስተኛ ቀን እግዚአብሔር ውቅያኖሶችና ወንዞች በዓሦችና በሌሎች የባሕር እንስሳት እንዲሞሉ በቃሉ አዘዘ። እግዚአብሔር እንዳዘዘ ወዲያውኑ ትእዛዙ ተፈጸመና ውቅያኖሶችና ወንዞች በሙሉ በውኃ ውስጥ በሚኖሩ እንስሳት ተሞሉ።

እግዚአብሔር አዕዋፍንና የሚበርሩ እንስሳትንም ደግሞ ፈጠረ።

እጅግ የተለያየ ቀለም ቅርፅና መጠን ያላቸው ዓሦችንና አዕዋፍን ፈጠረ። ዓሦችን በውኃ ውስጥ እንዲኖሩ፥ አዕዋፍን ደግሞ በሰማይ ላይ እንዲበርሩ አድርጎ ፈጠራቸው።

አዕዋፍንና ዓሦችን ሊፈጥር የሚችል አለን? ቤቶችን መሥራት ትችላላችሁ። በውጭ አገር የሚኖሩ አንዳንድ ሰዎች አውሮፕላኖችንና ሰዓቶችን መሥራት ይችላሉ፤ ነገር ግን አዕዋፍን ሊፈጥሩና በሕይወት እንዲኖሩ ሊያደርጉ የሚችሉ ይመስላችኋልን? በአንዳንድ አገሮች የሚኖሩ ሰዎች ዓሦች፥ አዕዋፍና ሌሎች እንስሳትን ከፕላስቲክና ከሌሎች ቁሳቁሶች መሥራት ቢችሉም፥ በሠሩአቸው ነገሮች ውስጥ ሕይወትን መዝራት አልቻሉም። የሠሯቸው ነገሮች አይተነፍሱም። እንቁላል ሊጥሉና ሊፈለፍሉ አይችሉም። ሕይወት ያላቸውና ሊራቡ የሚችሉ ነገሮችን መፍጠር የቻለ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ወደ ጫካ ወይም ወደ ባሕር ስትሄዱ ዓሦችንና አዕዋፍን ሁሉ የፈጠረው እግዚአብሔር መሆኑን አስታውሱ። እንደ እግዚአብሔር ጥበብና ኃይል ባይሆን ናሮ ከእነዚህ ነገሮች የትኞቹም በዓለም ላይ ባልኖሩም ነበር።

ቅርጫቶችንና ሌሎች በርካታ ነገሮችን ትሠራላችሁ። እኔ ቅርጫት መሥራት አልችልም። ልታስተምሩኝ ይገባል። የማላውቃቸው በርካታ ነገሮች አሉ። እኔ አሁን ቅርጫት ብሠራ የምሠራው ቅርጫት ዕቃ ለመያዝ የማይችል እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ። ይህንን መሥራት ብፈልግ ልታሳዩኝ ይገባል። እስክንግራቸው ድረስ የማናውቃቸው በርካታ ነገሮች አሉ። ማናችንም ብንሆን ሁሉን ነገር መሥራት አንችልም።

ታዲያ እግዚአብሔር ብርሃንን፥ ደረቅ መሬትን፥ ባሕሮችንና ወንዞችን፥ ዛፎችንና ተክሎችን፥ ከዋክብትን፥ ፀሐይንና ጨረቃን፥ አዕዋፍንና ዓሦችን መፍጠር እንዴት ቻለ? እግዚአብሔር እነዚህን ሁሉን ነገሮች ለመፍጠር የቻለው እርሱ ሁሉን አዋቂ ስለሆነ ነው። የሚፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ ማድረግ ይችላል።

መምህር ሆይ፡- ስለ እግዚአብሔር ችሎታና ባሕርይ የሚናገረውን ይህንን መሠረታዊ ትምህርት በጥንቃቄ አስረዳቸው። ለምሳሌ፡- እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ እንደሆነ ስታስተምራቸው ነበር። በዚህ መሠረት ወደፊት እግዚአብሔር፥ ስለእያንዳንዱ ሰው ሁሉን ነገር እንደሚያውቅ ታስተምራቸዋለህ። እግዚአብሔር ስለ ኃጢአታችን ያውቃል።

እግዚአብሔር አስተሳሰባችንን እንኳ ያውቃል። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያውቃል። «... እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይናች ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ» (ዕብ. 4፡13)። በሕዝቡ አእምሮ ይህን የእውነት መሠረት በቅድሚያ በጥልቀት ካልመሠረትክ ኋላ ልትጠቀምበት አትችልም። እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ የኃጢአት ወቀሳን ለማምጣት ሊጠቀምበት አይችልም።

ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ለሰው ልጆች መኖሪያ እንድትሆን ምድርን ከማዘጋጀቱ በፊት ምን ትመስል ነበር? ባዶ ነበረች፤ ሙሉ በሙሉ ሥርዓት በሌለውና ጥልቅ ጨለማ በሰፈነበት ሁኔታ ነበረች።

2. እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የፈጠረው እንዴት ነበር? እንዲሆኑ በመናገርና በማዘዝ ነበር።

3. የምድር ውኆች እንዲሰበሰቡና ደረቅ ምድር እንዲታይ ያደረገ ማን ነው? እግዚአብሔር ነው።

4. እግዚአብሔር፥ ውቅያኖሶች እንዲሰበሰቡና እርሱ በፈለገበት እንዲቆዩ ለማዘዝ የቻለው እንደምን ነበር? እርሱ ሁሉን ቻይ ስለሆነና ውቅያኖስን ስለፈጠረ ነው።

5. ለእግዚአብሔር፥ ሁሉን ነገር መሥራት ያስተማረው ማን ነው? ማንም አላስተማረውም፥ እርሱ ሁሉን ያውቃል።

6. እግዚአብሔር፥ ሁሉን ነገር ውብ ያደረገው ለምንድን ነው? ውኃንና የተለያዩ ፍሬ የሚሰጡ የሚበሉ ዛፎችንና አትክልቶችን የፈጠረው ለምንድን ነው? ምክንያቱም እርሱ አፍቃሪና ደግ ስለሆነ ነው። እርሱ በምድር ላይ የሚያስፈልገንን ሁሉ ፈጠረ።

7. እግዚአብሔር ስለፈጠራቸው ነገሮች ሁሉ ምን ሲል ተናገረ? ሁሉም መልካም እንደሆኑ ተናገረ።

8. እግዚአብሔር፥ ነገሮችን ሁሉ ፍጹም አድርጐ ሊፈጥር የቻለው ለምን ነበር? እራሱ ፍጹም ስለሆነ ነበር።

9. እግዚአብሔርÍ ፀሐይ፥ ጨረቃና ከዋክብትን በሰማይ ላይ ለማድረግ መሰላል መውጣት አስፈልጐት ነበርን? አላስፈለገውም። እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ ስለሚገኝ እነዚህን ፍጥረታት በሰማይ ለማድረግ ሊደርስባቸው ወይም ሊዘል አያስፈልገውም ነበር።

10. እግዚአብሔር ፀሐይ በቀን እንድትወጣና በግታ እንድትጠልቅ፥ ጨረቃና ከዋክብትም ተመሳሳይ መንገድ እንዲከተሉ ያደረገው ለምን ነበር? እግዚአብሔር ይህን ያደረገው እርሱ የሕግና የሥርዓት አምላክ ስለሆነ ነው። ፀሐይ፥ ጨረቃና ከዋክብትን በሰማይ ላይ ያደረገው ቀናትን፥ ወራትን፥ ወቅቶችንና ዓመታትን እንዲያሳውቁን ነው።

ትምህርት 7

የትምህርት ክፍል፡- ዘፍጥረት 1፡24-31፤ 2፡7

አጠቃላይ ርእስ፡- የሰው ልጅ ልዩ አፈጣጠርና በምድር ላይ የተሰጠው ልዩ ሥልጣን

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. ስድስተኛ ቀን፡- የእንስሳት ዓለም አፈጣጠር (1፡24፥ 25)

. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው ።

. እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው።

ለ. በመጨረሻ ምድር ለሰው ተዘጋጀች።

. እግዚአብሔር ፍቅር ነው።

ሐ. እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ለመፍጠር ስለ ማቀዱ (1፡26)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው

1. የሰው አእምሮ

2. የሰው ስሜቶች

3. የሰው ፈቃድ

መ. የአዳም አፈጣጠር (1፡27፥ 2፡7)።

. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ሠ. እግዚአብሔር ከምድር አፈር ያበጀው የመጀመሪያውና ብቸኛው ሰው አዳም ነበር (2፡7)።

ረ. ሰው ምድርን ያስተዳድርና ይገዛ ዘንድ ተሾመ (1፡28-30)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ሰ. እግዚአብሔር የፈጠራቸው ነገሮች ሁሉ መልካም ነበሩ (1፡31)።

. እግዚአብሔር ቅዱስ ነው።

ሸ. የእግዚአብሔር መልካም መላእክት፥ ሰይጣንና የተከተሉት የወደቁት መላእክት ሁሉ ለሰው አፈጣጠር ምሥክሮች ነበሩ።

. ሰይጣን ከእግዚአብሔርና ከፈቃዱ ጋር ይዋጋል።

የትምህርት 6 ጥያቄዎችን ከልስ።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማዳበር (መተንተን)

ሀ. ስድስተኛ ቀን፡- የእንስሳት ዓለም አፈጣጠር

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

ዘፍጥረት 1፡24፥ 25 አንብብ። እግዚአብሔር ስንት የተለያዩ እንስሳትን ፈጠረ? እዚህ በአናንተ አካባቢ ያሉትን እንስሳት ስሞች ንገሩኝ።

በሌሎች ዓለማት የሚገኙትን የእነዚህን እንስሳት ሥዕሎች ተመልከቱ። አይታችኋቸው የማታውቋቸው እጅግ ብዙ ዓይነት እንስሳት አሉ። እግዚአብሔር በራሱ ታላቅ ኃይል ሁሉንም ፈጠራቸው። እንስሳትን መፍጠር የቻለ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው።

እንስሳትን ሁሉ የፈጠረ እግዚአብሔር ነበር። እራሳቸውን ሊፈጥሩ ወይም ሌላ ማንም ሊፈጥራቸው አይችልም ነበር። እግዚአብሔር አንዳንዶቹን በዛፎች ላይ እንዲኖሩ አድርጐ ፈጠራቸው፥ ሌሎቹን ደግሞ ዛፍ ላይ ዘልለው ለመውጣት የማይችሉ ትላልቅ አድርጐ ፈጠራቸው። እንዴት ዓይነት ታላቅ አምላክ ነው! እግዚአብሔር፥ ሁሉን አዋቂ ስለሆነ እንስሳትን ሁሉ እንደሚፈልገው አድርጐ ፈጠራቸው። አንዳንዶችን በዛፎች ላይ የሚኖሩ አደረጋቸው! ሌሎችን ደግሞ በምድር የሚንቀሳቀሱ አደረጋቸው። ስንት ያህል የተለያዩ እንስሳትን ታውቃላችሁ? የሚኖሩት በየት ነው? የሚመገቡት ስንት ዓይነት የተለያዩ ምግቦችን ነው? እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ስለሆነ ብዙ የተለያዩ ዓይነት እንስሳትን ለመፍጠር ቻለ።

ለ. በመጨረሻ ምድር ለሰው ተዘጋጀች

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ፍቅር ነው።

እግዚአብሔር እንስሳትን ሁሉ ፈጥሮ እንደጨረሰ ምድር ለሰው ልጅ ተዘጋጀች። ለእርሻ ወይም ለአትክልት ስፍራ የመረጣችሁት ቦታ አስቀድሞ ሰው ያልኖረበት ጫካ ከሆነ፥ በዚያ ለመኖር ከመጀመራችሁ በፊት በርካታ ዝግጅት ማድረግ አለባችሁ፥ አይደለምን? ዛፎች መቆረጥ አለባቸው፥ መሬቱ መጽዳት፥ ቤት መሠራት አለበት። ወደ አዲሱ መሬታችሁ ከመንቀሳቀሳችሁ በፊት ብዙ ነገሮች መዘጋጀት አለባቸው።

በምድርም የሆነው እንደዚሁ ነበር። እግዚአብሔር የምድር ክፍሎችን በሙሉ አዘጋጀ፥ ለራሱ ግን አልነበረም። እግዚአብሔር ምድርን ለሰው ልጅ አዘጋጀ። እግዚአብሔር፥ የመጀመሪያውን ሰው ከመፍጠሩ በፊት እርሱ አፍቃሪና ደግ ስለሆነ ሰው የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ አዘጋጀ።

ሐ. እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ለመፍጠር ስለ ማቀዱ።

ዘፍጥረት 1፡26 አንብብ፡- እግዚአብሔር «ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር» ብሎ ሲናገር ለማን እየተናገረ ይመስላችኋል? እየተነጋገሩ ያሉት እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነበሩ። ሰውን በአምላክ አምሳል ለመፍጠር ባወጡት ዕቅድ ላይ እየተወያዩ ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

በጣም አስፈላጊ የሆነ አንድ ነገር ለመሥራት በምታቅዱበት ጊዜ (ለምሳሌ፥ ቤት፥ የእርሻ ቦታ) በመጀመሪያ ስለ ሥራውና ስለ አፈጻጸሙ ታስባላችሁ፥ ታቅዳላችሁም።

እግዚአብሔርም ያደረገው እንዲሁ ነበር። የመጀመሪያውን ሰው እንዴት እንደሚፈጥር ዐቀደ። እግዚአብሔር በምድር ላይ ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ እጅግ በጣም አስፈላጊው ፍጥረት ሰው ስለ ነበር፥ እግዚአብሔር «በአምሳሉ» ሊፈጥረው ወሰነ። እግዚአብሔር አስቀድሞ መናፍስት፥ ፀሐይ፥ ጨረቃ፥ ከዋክብት፥ መሬትና የቀሩት ነገሮች ሁሉ እንዴት መሆን እንዳለባቸው እንደወሰነ ሁሉ፥ ሰውም እንዴት መፈጠር እንዳለበት ወሰነ። የወሰነው እርሱ

ብቻ ነው። የማንንም ምክር አልጠየቀም፤ ምን ማድረግ እንዳለበት የትኛውንም መናፍስት አላማከረም፤ የማንንም ምክርና እርዳታ አልጠየቀም። እግዚአብሔር የሁሉ የበላይ ነው። ከሁሉም ይበልጣል፤ የነገሮች ሁሉ፥ የሰዎችና የመናፍስት ሁሉ የበላይ ነው።

ሰው በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠር ነበረበት። እግዚአብሔር በራሱ መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ሰው በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠር ነበረበት ሲል ምን ማለቱ ነው?

ስለ አካል እንደማይናገር እናውቃለን፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር እንደ እኛ ሥጋና አጥንት ያለው አካል የለውም። እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ በአምሳሉ የፈጠረው አካላችንን አይደለም። በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው የሰውነታችን የማይታየው ክፍል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን የማይታየውን የአካላችንን ክፍል ነፍስና መንፈስ ይለዋል። የሰው አካል በእግዚአብሔር አምሳል ለተፈጠረው የሰውነታችን ክፍል ማደሪያ እንዲሆን የተፈጠረ ነበር። እግዚአብሔር ይህ የማይታየው የሰው አካል አእምሮ፥ ስሜትና ፈቃድ እንዲኖረው ዐቀደ።

1. የሰው አእምሮ

እግዚአብሔር አእምሮ ስላለው በምድር የሚኖሩ ሕዝቦች እግዚአብሔርን የሚያውቁበት፥ እንደ እግዚአብሔር የሚያስቡበትና የሚያመዛዝኑበት አእምሮ እንዲኖራቸው ዐቀደ። እግዚአብሔር ከሰው ጋር ለመነጋገር ፈለገ፤ ባንጻሩ ደግሞ ሰው ከእርሱ ጋር እንዲነጋገር ፈለገ። እግዚአብሔር፥ ሰው በምድር ላይ ሥራውን የሚሠራለት እንዲሆን ዐቀደ።

ከእንስሳት ጋር ብቻ በመነጋገር በጫካ ውስጥ መኖር ትፈልጋለህን? ማንም ሰው ቢሆን ሁልጊዜ ከእንስሳት ጋር ብቻ መነጋገር ደስ አያሰኘውም። ከእንስሳት ይልቅ ከሰዎች ጋር ጎብረት ማድረግ የበለጠ ደስ ያሰኛል፤ ምክንያቱም እንስሳት የሰው ዓይነት አእምሮ ስለሌላቸውና ከሰዎች ጋር ግን ተነጋግረው መግባባት ስለማይችሉ ነው።

በጣም ደስ ሲላችሁ ደስታችሁን ለበጎቻችሁ ትገልጣላችሁን? ቤት መሠራት ብትፈልጉ ልትሠሩ ያሰባችሁበትን መንገድ ለውሻችሁ ወይም ለበጎቻችሁ ታማክራላችሁን? እንስሳቱ እንዲረዷችሁ ከእነርሱ ጋር ተቀምጣችሁ ትወያያላችሁን? አታደርጉትም! እነዚህን ነገሮች ለእንስሳት መግለጥ አትችሉም፤ ምክንያቱም እንስሳት ለማሰብና ለማመዛዘን ስለማይችሉ ነው። ይህን ማድረግ የሚችሉ ሰዎች ብቻ ናቸው። እግዚአብሔር፥ እንስሳትን እንደራሱ አድርጐ አልፈጠራቸውም። እንስሳት ሰዎች ያላቸው አእምሮ የላቸውም።

እግዚአብሔር ግን ሰውን በራሱ አምሳል ሊፈጥር ወሰነ፤ ስለዚህ እርሱ የሚያስብና የሚያመዛዝን እንደሆነ ለሰውም ይህ ችሎታ እንዲኖረው አእምሮ ሊሰጠው ወሰነ። ይህ ማለት ማንኛውም ሰው እግዚአብሔር እንደሚያስበው ያስባል እንደ እርሱም ያመዛዝናል ማለት እንዳይደለ እርግጥ ነው።

ደረጃው ልክ እንደ ወላጅና ልጅ ሁኔታ ነው። የእናንተ ትናንሽ ልጆች እናንተ የምትሠሩትን ነገር ሁሉ ያውቃሉን? በጭራሽ አያውቁም። እንደ እናንተ የሆነ አእምሮ ስላላቸው ግን ልታስተምሯቸው ትችላላችሁ።

በዓለም ላይ የሚገኝ ታላቁ ብልህ ሰው እንኳ ከእግዚአብሔር ጋር ሲወዳደር እንደ ትንሽ ልጅ ነው፤ እግዚአብሔር ግን ሰው እእምሮ እንዲኖረው አድርጐ ስለፈጠረው የእግዚአብሔርን ንግግር ሊሰማ ሊረዳና እርሱ ያለውን ሊያደርግ ይችላል። እግዚአብሔር ለሰው ያቀደው ይህ ነበር። እግዚአብሔር ለሰው አእምሮ ሊሰጠው ዐቀደ። በአእምሮው ምክንያት ከእርሱ ጋር እንዲነጋገር፥ በጎብረቱ ደስ እንዲሰኝ ነበር። ደግሞም የእግዚአብሔርን ሥራ እንዲሠራ ሊያስተምረው ፈልጐ ነበር።

2. የሰው ስሜቶች

እግዚአብሔር አእምሮ አለው፤ ደግሞም ስሜቶች አሉት። ይወዳል፥ ይጠላል፥ ያዝናል ደግሞም ደስታና ሐሤት ይሰማዋል።

እግዚአብሔር ስሜቶች ስላሉት ሰውንም ከስሜቶች ጋር ሊፈጥረው ወሰነ።

እናንተ ሁላችሁ ልጆቻችሁን ትወዳላችሁ አይደል? በዚያው መልክ ልጆቻችሁ እንዲወዷችሁ ትፈልጋላችሁን? በእርግጥ ትፈልጋላችሁ! እያንዳንዱ ወላጅ ልጆቹ እንዲወዱት ይፈልጋል።

እግዚአብሔርም ልክ እንደዚያ ነው። እግዚአብሔር ሰውን ሊወድ እንዳቀደ ሁሉ፥ እርሱም ሰው እንዲወደው ይፈልጋል። እግዚአብሔር ሰውን ከስሜቶች ጋር ለመፍጠር ያቀደው በዚህ ምክንያት ነበር።

3. የሰው ፈቃድ

እግዚአብሔር፥ ከአእምሮና ከስሜት ሌላ ፈቃድም አለው። አንድን ነገር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ የመወሰን ችሎታ አለው። ስለዚህ እግዚአብሔር፥ ሰውን ለራሱ ውሳኔ ማድረግ የሚችል ፍጡር አድርጐ ሊሠራው ወሰነ።

አንድን ቀስት በመወንጨፊያው ላይ አድርገህ ልትወረውረው ስትፈልግ የቀስቱን ጫፍ ወደምትፈልግበት አቅጣጫ ታነጣጥራለህ፤ ግን ይህ ቀስት ወዴት እንደሚበር የመወሰን ምርጫ አለውን? ተወርውሮ በመሄድ መውጋት ያለበት ርግብ ይሁን ወይም ጦጣ መምረጥ ይችላልን?

ወደ አንድ ቦታ ለመሄድ ወደ መኪና ውስጥ ብትገቡ መኪናውን ወዴት መሄድ እንደሚፈልግ ትጠይቁታላችሁን? አትጠይቁትም። ወደመረጣችሁት ስፍራ እንዲሄድ ታደርጉታላችሁ።

እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው ሲፈጥር ልክ እንደቀስቱና መኪናው ምንም ምርጫ የሌለው አድርጐ ሊፈጥረው ይችል ነበር። በዚህ መንገድ ሰው፥ እግዚአብሔር እንዲያደርግ የሚፈልገውን ነገር ብቻ የሚያደርግ ፍጡር ሊሆን ይችል ነበር።

እግዚአብሔር፥ ፀሐይን፥ ጨረቃንና ከዋክብትን የፈጠረው በዚህ ዓይነት ሁኔታ ነው። በየዕለቱ፥ በየወሩና በየዓመቱ ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርጉ ሆነው በእግዚአብሔር ተፈጠሩ። እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ግን በዚያ ዓይነት መንገድ አልነበረም። እግዚአብሔር ፈቃድ አለው። እግዚአብሔር ምን እንደሚሠራ እራሱ ይወስናል።

እግዚአብሔር በምርጫ የሚፈልገውን እንደሚያደርግ፥ ሰውንም ሲፈጥር እንደ እርሱ በምርጫ የሚወስን አድርጐ ፈጠረው።

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ዕቅዱ እግዚአብሔርን ለመውደድና ለመታዘዝ ፈቃደኛ ይሆናል የሚል ነበር። ለዚህም ምክንያቱ ሰው በአእምሮው አማካይነት እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ደግና ሁሉን አዋቂ ፈጣሪ መሆኑን ስለሚያውቅ ነው። ልጆች፥ ወላጆቻቸው ብልህና ደግ መሆናቸውን ካወቁና ካመኑ ለወላጆቻቸው ለመታዘዝ ይቀላቸዋል።

የእግዚአብሔር ዕቅድ፥ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እንዲነጋገርና እርሱ ብልህና አፍቃሪ አምላክ መሆኑን እንዲያውቅ ነበር። ይህ እስከሆነም ሰው የፈጠረው እግዚአብሔር የቱን ያህል አስደናቂ መሆኑን በመረዳት እርሱን ለመታዘዝ መምረጥ የሚችል ሊሆን ይገባል።

እግዚአብሔር፥ ሰውን በአምሳሉ ሲፈጥር ያቀደው በምድር ላይ የእርሱን ሥራ የሚሠራ ወኪል እንዲሆን ነበር። ሰው የተፈጠረው በምድር ላይ እግዚአብሔርን ወክሎ ይኖር ዘንድ ነበር። ሰው በምድር ላይ ያሉትን የእግዚአብሔርን ነገሮች እንዲጠብቅና በእንስሳት፥ በአዕዋፋትና በዓሣዎች ሁሉ ላይ መሪና ገዥ እንዲሆን ነበር።

መምህር ሆይ፡- የሰው ልጅ አፈጣጠር ልዩ ነው። ለእግዚአብሔር ተገቢውን የሥልጣን ስፍራ መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ፥ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በፍጥረታት ሁሉ ላይ የሰጠውን የመጀመሪያውን ልዩ የሥልጣን ስፍራ በአትኩሮት ማጤን አለብን።

እግዚአብሔር ስለ እኛ ካለው ግምት አንጻር የራሳችንን ዋጋና ጠቀሜታ ለመረዳት እንችላለን። ስለዚህ እያንዳንዱ የአካባቢው ሰው እግዚአብሔር ለእርሱ የሚሰጠውን ዋጋ በሚያይበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት የማድረግን አስፈላጊነት ይገነዘባል። ስለሆነም ስለ ሰው ልዩ ተፈጥሮና በምድር ላይ ስለተሰጠው ልዩ ሥልጣን አትኩሮት መስጠት አስፈላጊ ነው።

ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ስለተፈጠረ ምክንያታዊ፥ ሥነ-ምግባራዊና መንፈሳዊ ተደርጐ ተፈጥሮአል። በሌላ አነጋገር ሰው ለእግዚአብሔር ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት የሚችል ፍጡር ተደርጐ ተፈጥሮ ነበር ማለት ነው። እግዚአብሔርን ማወቅ እንዲችል አውቀትን የሚያካብት አእምሮ ተሰጥቶታል። እግዚአብሔርን መውደድ እንዲችል ስሜቶች ተሰጥተውት ነበር። እግዚአብሔርን መታዘዝ እንዲችል ከፈቃድ ጋር ተፈጠረ። ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ስለመፈጠሩ ስንናገር በአካላዊ አምሳያነት አለመሆኑን ግልጽ አድርገው።

መ. የአዳም አፈጣጠር

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው

እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

በቅደም ተከተል ማሳያው ሰንጠረዥ ላይ፡-

«አዳምና ሔዋን» የሚሉትን ሰሞች አሳይ። ዘፍጥረት 1:27፥ 2:7 አንብብ። እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ወንድና የመጀመሪያይቱን ሴት ፈጠረ። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ወንዱን ፈጠረና በመቀጠል ደግሞ ሚስት ፈጠረለት። ቆይተን ግን እግዚአብሔር ሴቲቱን እንዴት እንደፈጠረ እንማራለን። ዛሬ ከእግዚአብሔር መጽሐፍ የምናነበው እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው እንዴት እንደፈጠረ ነው። ስሙ አዳም ይባል ነበር። ትርጉሙም «ሰው» ማለት ነው።

እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ሲፈጥር ቃል ብቻ በመናገር ሕልውና እንዲኖራቸው ያደርግ ነበር። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ግን የሰውን አካል ከምድር አፈር አበጀው።

መምህር ሆይ፡- ለመጽሐፍ ቅዱስ ድርጊቶች ምናባዊ መግለጫዎች ለመስጠት በምትሞክርበት ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ሥዕላዊ አምሳል የሚሰጡ የቃል በቃል ትርጉሞችና መግለጫዎችን አትጠቀም። አንድ የወንጌል አገልጋይ ሲያስተምር እግዚአብሔር በእጁ የምድርን አፈር ወስዶ፥ ሰውን እንደፈጠረ ሲናገር በመስማቴ በጣሙን ተደንቄአለሁ። ይህ የወንጌል አገልጋይ እግዚአብሔር ይህን በሚያደርግበት ጊዜ

በእጁ ጥፍሮች መሃል ቆሻሻ እንኳ ገብቶ እንደሆነ አድግሎቹን ሲጠይቅ ሰምቼዋለሁ። እግዚአብሔርን እንደ ኃያል ሰው አድርጉ በሚያቀርብ በእንዲህ ዓይነት ቀጥተኛ አተረጓጐም ልንጠቀም አይገባም። ቃሉ የሚለውን ብቻ አስተምር እንጂ ከተጻፈው በላይ ትርጉም ሊሰጥ በሚችል ቀጥተኛም ሆነ መንፈሳዊ ትርጉም አትጠቀም። እግዚአብሔር ሰውን ለመፍጠር የምድር አፈርን በእጁ አልወሰደም። እግዚአብሔር እንደ እኛ ሥጋና አጥንት ያለው አካላዊ እጅ የለውም። እግዚአብሔር መንፈስ ነው።

እግዚአብሔር እያንዳንዱን የሰው አካል ከፈጠረ በኋላ እንኳ ሰው ሕይወት አልነበረውም። እያንዳንዱ የሰውነቱ አካል በዚያ ነበር፤ ነገር ግን እንደ በድን ነበር። አካሉ እስትንፋስ አልነበረውም፤ ምክንያቱም በእግዚአብሔር አምሳል የነበረው ክፍል በሰውነቱ ውስጥ ገና አልነበረም። ሰው እግዚአብሔርን ለማወቅ፥ ለመውደድና ለመታዘዝ የሚችል ሕያው ፍጥረት የሆነው እግዚአብሔር በአካሉ ውስጥ እፍ ካለበት በኋላ ብቻ ነው።

ለሰው አካል ሕይወት ለመስጠት ኃይል ያለው ማን ነበር? የእግዚአብሔር ቅዱሳን መላእክት ለሰው ሕይወትን ሊሰጡ ይችሉ ነበርን? ሰይጣን ወይም እርሱን የተከተሉት መናፍስትስ ለሰው ሕይወትን ሊሰጡ የሚችሉ ነበር? ፀሐይ፥ ጨረቃ ወይም መሬት ለሰው ሕይወትን ሊሰጡ የሚችሉ ናቸው? አእዋፍ ወይም እንስሳት ለሰው ሕይወትን ሊሰጡ ይችሉ ነበርን? ሰው ስለ ራሱ ሕይወትን መስጠት የሚችል ነው?

ፀሐይ፥ ጨረቃ፥ መሬት፥ አዕዋፍ፥ እንስሳት፥ ዓሣ፥ የእግዚአብሔር መላእክት፥ ማንኛውም ሰው፥ ሰይጣን ወይም የተከተሉት መናፍስት ሕይወት መስጠት አይችሉም። ነገሮች ሁሉ ሕይወትን የተቀበሉት ከእግዚአብሔር ነውና ለማንም ሆነ ለምንም ሕይወትን ለመስጠት አይችሉም።

የወንዝ ውኃ ከተራሮች በላይ ካሉ የውኃ ምንጮች የሚመጣ ነው። የውኃው ምንጮች ቢደርቁ ወንዞቻችሁም ይደርቃሉ። ፀሐይ በምድር ላይ በማብራት ብርሃንን ትሰጣለች። ፀሐይ በምድር ላይ ማብራቷን

ብታቆም ምንም ዓይነት የቀን ብርሃን አይኖርም። በአጠቃላይ በሕይወትም ውስጥ እንዲሁ ነው። እግዚአብሔር እንደምንሞ ነው። እግዚአብሔር እንደ ፀሐይ ነው። ሕይወት ያላቸው ነገሮች በሙሉ ሕይወትን ያገኙት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።

እግዚአብሔር በመጀመሪያው በሰው አፍንጫ ላይ በተነፈሰ ጊዜ ሰው ወዲያውኑ ሕይወት ያለው ነፍስ ሆነ። ሰውም መተንፈስ በመጀመር ጠንካራና ጤነኛ ሆነ። በምድር ላይ በሽታ ወይም ሞት አልነበረም።

እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረበት በዚሁ ቀን የመጀመሪያዋን ሴት ደግሞ ፈጠረ፤ ነገር ግን ቀደም ብዬ እንደነገርኳችሁ የእግዚአብሔር መጽሐፍ ስለዚህ ጉዳይ ቆይቶ ይነግረናል፤ ስለዚህ እስክንደርስበት ድረስ እናቆየዋለን።

ሠ. እግዚአብሔር ከምድር አፈር ያበጀው የመጀመሪያውና ብቸኛው ሰው አዳም ነበር።

ዘፍጥረት 2፡7 አንብብ። እግዚአብሔር ከምድር አፈር ያበጀው የመጀመሪያውና በቸኛው ሰው አዳም ነበር። እግዚአብሔር ፈረንጅ ሰውና ጥቁር ሰው ደግሞም የሌሎች ዝርያ ሰዎችን አልፈጠረም። እግዚአብሔር አንድ ወንድና አንዲት ሴት በመፍጠር እንዲባዙና ልጆች እንዲያፈሩ በመጨረሻም ምድርን እንዲሞሉ አዘዘ።

አዳም የሰው ዘር ሁሉ የመጀመሪያ ነው። አዳም አባታችሁ ነው። አዳም አባታችን ነው። እርሱ የሰዎች ሁሉ አባት ነው። ሁላችንም የተገኘነው ከዚህ ከመጀመሪያው ሰው ነው። እርሱ የመጀመሪያና የመላው የሰው ዘር አባት ነው።

መምህር ሆይ፡- ሕዝቡ ስለዝርያቸው አጀማመር የራሳቸው እምነት ይኖራቸዋል፤ ስለዚህ ቀደም ብለን በተራ ቁጥር ሠ. ያነሣነው አሳብ በጣም ጠቃሚ ነው። ሰዎች ሁሉ የተገኙት ከአንድ ምንጭ መሆኑን ሰይጣን እንዲያውቁ አይፈልግም። አዳማጮችህ ሁላቸውም የተገኙት ከመጀመሪያው ሰው «ከአዳም» መሆኑን መረዳታቸው እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። «በአዳም» በኩል መሞታቸውን ካልተቀበሉ

«በክርስቶስ» የሆነውን ደኅንነት ሊቀበሉ ጨርሶ አይችሉም (ሮሜ 5፡12-21፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡22)።

ስለዚህ በቅዱሳት መጻሕፍት አማካይነት እውነተኛ ጅማሬያቸውን ግሳየት አለብን። በአንድ ብቸኛና እውነተኛ አምላክ በተፈጠረ በአንድ አባት ምክንያት፥ ከቀረው ሰብአዊ ፍጡር ጋር አንድ እንደሆኑ መረዳት አለባቸው። በዘፍጥረት የመጀመሪያዎቹ 10 ምዕራፎች ውስጥ የተመዘገቡት ታሪኮች የእነርሱም ሆነ የእኛ አባቶች ታሪክ መሆኑን ግወቅ አለባቸው። እነዚህን የመጀመሪያ የዘፍጥረት መጽሐፍ 10 ምዕራፎች በምናስተምርበት ጊዜ ደግመን ደጋግመን ይህን እውነት እናቀርብላቸዋለን።

እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ፈጠረና ባዘጋጀላቸው በዚህች ውብ ምድር አስቀመጣቸው። በዙሪያቸው እግዚአብሔር በምድር ላይ ያዘጋጀላቸው ነገሮች ነበሩ፤ ወደላይ ሲመለከቱ ደግሞ ፀሐይ፥ ጨረቃና ከዋክብት ነበሩ። እግዚአብሔር ውቅያኖስ፥ ምድርና ወንዞችን ፈጥሮ ነበር። የተለያዩ ዓይነት ዛፎች፥ ፍሬ የሚሰጡ ተክሎችና አዝርዕቶች ይበቅሉ ነበር። የተለያዩ የዓሣ ዝርያዎች በውኃ ውስጥ ሲገኙ፥ እንስሳት ደግሞ በምድር ላይ ይኖሩ ነበር። እግዚአብሔር የሠራቸው ነገሮች በሙሉ መልካም መሆናቸውን አይቶ ነበር። በተለይ ደግሞ በፈጠራቸው ወንድና ሴት እጅግ ደስ ተሰኝቶ ነበር።

መምህር ሆይ፡- ምሳሌ 8፡30፥ 31 ተመልከት።

ረ. ሰው ምድርን ያስተዳድርና ይገዛ ዘንድ ተሾመ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ዘፍጥረት 1፡28-30 አንብብ።

እናንተ አባቶች ብርቱና ጤነኛ የሆነ ወንድ ልጃችሁን ስትመለከቱ ምን ይሰማችኋል? እርሱስ ትልቅ የዱር እንስሳ አድኖ ሲገድል ስትመለከቱ ምን ይሰማችኋል? በጣም ደስ ትሰኙበታላችሁን?። ፈገግ ትላላችሁ፥ የእርሱ አባት በመሆናችሁም ትኮራላችሁ። ከእርሱ ጋር መሆን በጣም ያስደስታችኋል። ለመማር ወይም ለማድረግ በሚፈልገው በማንኛውም ነገር ልትረዱት ትፈልጋላችሁ። አሁን ያደገና ብልህ የሆነ

ስለሚሆን በቤተሰብ ውስጥ ለብዙ ነገሮች ኃላፊነት እንዲወስድ ታደርጋላችሁ። ከእርሱ ጋር በመነጋገር ምን እንዲሠራ እንደምትፈልጉ ትነግሩታላችሁ።

እግዚአብሔርም ደግሞ በፈጠረው በመጀመሪያው ሰው በጣም ደስተኛ ነበር። እግዚአብሔር፥ ለመጀመሪያው ሰው ለአዳም በምድር ላይ እርሱን ወክሎ ምን ማድረግ እንዳለበት ነግሮት ነበር። እግዚአብሔር በምድርና በውስጧ ባሉት ነገሮች ሁሉ ላይ ገዥ አድርጐ አስቀመጠው።

እግዚአብሔር፥ ምድርን የሰጠው ለቅዱሳን መላእክቱ ወይም ለሳጥናኤልና ለተከተሉት ክፉ መላእክት አልነበረም። እግዚአብሔር ምድርን ለየትኞቹም መናፍስት አልሰጠም ነበር።

እግዚአብሔር በምድርና በውስጧ ያሉትን ነገሮች ሁሉ እንዲገዛ ለሰው ሥልጣን ሊሰጥ የቻለ ብቸኛው አካል የሆነው ለምንድን ነው? አዎን፥ ነገሮችን ሁሉ የፈጠረው እግዚአብሔር ብቻ በመሆኑ ነው፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚፈልገው ሊሰጠው ይችል ነበር።

ምድር ወይም ሌላ ማንኛውም ነገር የመናፍስት አይደለም። ምድርን አልፈጠሩም፥ እግዚአብሔርም ለእነርሱ አልሰጣቸውም፤ ስለዚህ በምድር ላይ ያሉ ማናቸውንም ነገሮች የመቆጣጠር መብት የላቸውም።

እናንተ በራሳችሁ ምጣድ ይጠቀም ዘንድ ለምትፈልጉት ሰው የመስጠት መብት አላችሁ። ያለእናንተ ፈቃድ ግን ማንም የመውሰድ መብት የለውም። ማንኛውም ሰው የራሱ ያልሆነውን ንብረት ወስዶ ሌሎች ሰዎች እንዲጠቀሙበት የመስጠት መብት የለውም።

ጠላቶቻችሁ ቢመጡና በዕቃዎቻችሁ መጠቀም ቢጀምሩ፥ የጫካ መመንጠሪያ ቆንጨራችሁን ቢወስዱባችሁ፥ ወይም ወደ እርሻ ቦታችሁ በመምጣት አትክልቶቻችሁን ቆፍረው ቢወስዱባችሁ ያስደስታችኋልን? ለሌሎች ሰዎች በእናንተ ዕቃ መጠቀም ቢፈልጉና ጠላታችሁ ደግሞ የእርሱን ፈቃድ መጠየቅ እንዳለባቸው ቢናገር ተገቢ ነውን?

እግዚአብሔር የነገሮች ሁሉ ፈጣሪ ነው፤ ስለዚህ ይህች ዓለምና በውስጧ ያሉት ነገሮች በሙሉ የእግዚአብሔር ናቸው። ምድርን ለማን መስጠት እንዳለበት ወሰኖ ነበርና ለሰው ልጅ ሰጠው። እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

መምህር ሆይ፡- እግዚአብሔር የሰውን ልጅ የእርሱ ምክትል ገዢ እንዲሆን እንደ ሾመው ለማስረዳት በምሳሌነት የሚጠቅምና ሕዝቡ የሚያውቀው አንድ ሰው ሊኖር ይችል ይሆናል። ይህም ሰው በፕሬዘዳንቱ ሥር የሚያገለግል አገረ ገዥ ወይም በሌላ ከፍተኛ ባለሥልጣን ሥር ያለ ከንቲባ ሊሆን ይችላል። ወይም በነገድ አለቃው ሥር ሆኖ የነገድ አለቃው በሚሰጠው ኃላፊነት የሚሠራ ተመሳሳይ ሥልጣን ያለው ሰው ሊሆን ይችላል።

ሰ. እግዚአብሔር የፈጠራቸው ነገሮች ሁሉ መልካም ነበሩ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስ ነው።

ዘፍጥረት 1፡31 አንብብ። እግዚአብሔር ፍጹምና መልካም ስለሆነ የሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ሙሉ በሙሉ ትክክልና ደግሞም ውብ ናቸው።

በመጀመሪያ ጊዜ ከእንስሳት መካከል የትኛውም ሰውን የሚጐዳ አልነበረም። እሾህ፥ አሜከላና አረም ዛሬ በምድር ላይ እንደሚበቅሉ ያኔ አልነበሩም።

መምህር ሆይ፡- ወደፊት ባሉት ታሪኮች ውስጥ እግዚአብሔር ምድርን እንደ ረገመ ስታስተምር ትርጉም የሚሰጥ እንዲሆንላቸው (ዘፍጥረት 3፡17-19) ይህን ነጥብ በሚገባ መረዳታቸውን አረጋግጥ። አሁን ያለው ሁኔታ ለምን ፈጽሞ የተለየ እንደሆነ ከጠየቁህ (ለምሳሌ፡- እባቦች ለምን እንደሚናደፉ? እሾሆች ለምን እንደሚበቅሉ) መልሱ ወደፊት በሚቀጥሉት ታሪኮች እንደሚሰጥ ንገራቸው።

ሸ. የእግዚአብሔር ቅዱሳን መላእክት፥ ሰይጣንና የተከተሉት የወደቁት መላእክት ሁሉ የሰው አፈጣጠር ምሥክሮች ነበሩ።

ዋና አሳብ፡- ሰይጣን ከእግዚአብሔርና ከፈቃዱ ጋር ይዋጋል።

በሰማይ ያሉ የእግዚአብሔር መላእክት እግዚአብሔር ምድርን ሲያዘጋጅና ሰውን ሲፈጥር ይመለከቱ ነበር። እነዚህ የእግዚአብሔር መላእክት በእግዚአብሔር ሥራ ደስ በመሰኘት እነዚህን ሁሉ ነገሮች የፈጠረ እግዚአብሔር እንዴት ታላቅና አስደናቂ ነው አሉ። እግዚአብሔርን አመስግነውና አምልከው ነበር።

እንደዚሁም ሰይጣንና በምድር የነበሩ መናፍስት ሁሉም እየተመለከቱ ነበር። ታዲያ ደስ የተሰኙ ይምስላችኋልን? እግዚአብሔርን አመስግነውና አምልከው ነበርን? ምን እያሰቡ የነበር ይመስላችኋል?

መምህር ሆይ፡- ከላይ በሸ. የጠቀስናቸው እውነቶች ከኢዮብ 38፡4-11ና ከቅዱሳት መጻሕፍት የተወሰዱና ስለ ሰይጣን ባሕርይ በምናውቀው ነገር ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ይህ ነጥብ በሚቀጥለው የዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ትምህርት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት ለማበላሸት ሰይጣን የተጠቀመበትን ማታለያና ውሸት ለማስተማር የሚያዘጋጅ ነው።

ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ምድርን ያዘጋጀው ለማን ነበር? ለሰው ልጅ ነው።
2. በሰው አፈጣጠርና በእንስሳት አፈጣጠር መካከል ያለው ትልቅ ልዩነት ምን ነበር? እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ስለፈጠረ ነበር።
3. እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ፈጠረው ማለት ምን ማለት ነው? እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው የሰው አካል አልነበረም። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን እርሱን የሚያውቁ፥ የሚወዱ ሊሆኑ እንዲችሉ አድርጐ ፈጠራቸው።
4. እግዚአብሔር በመጀመሪያ የፈጠራቸው ስንት ወድና ስንት ሴት ነበሩ? እግዚአብሔር የፈጠራቸው አንድ ወንድና አንዲት ሴት ብቻ ናቸው።
5. የመጀመሪያው የእናንተና የእኛ አባት ማን ነው? አዳም ነው።

6. የመጀመሪያው ሰው አዳም ከተፈጠረ በኋላ እግዚአብሔር በምን ላይ ሾመው? በምድርና በውስጧ ባሉት ነገሮች ሁሉ ላይ ሾመው።

7. መናፍስት፥ በምድርና በውስጧ ባሉት ነገሮች ሁሉ ላይ መብት የሌላቸው ለምንድን ነው? ምክንያቱም እግዚአብሔር፥ በምድር ላይ ባሉ በማንኛውም ነገሮች ስለአልሾማቸው ነው። እግዚአብሔር የሾመው ሰውን ብቻ ነበር።

8. በምድር ላይ የሚገኙ ነገሮች በሙሉ በመጀመሪያ ምን ይመስሉ ነበር? መልካም ነበሩ፥ ነገሮች ሁሉ ፍጹም ነበሩ።

9. እግዚአብሔር የሠራውን ነገሮች ሁሉ ይመለከቱ የነበሩ እነማን ናቸው? የእግዚአብሔር መላእክት፥ ሰይጣንና የተከተሉት ክፉ መናፍስት በሙሉ።

10. እግዚአብሔር ሰውን በአምላሉ በመፍጠሩና በምድር ሁሉ ላይ በመሾሙ ሰይጣን የተደሰተ ይመስልሃልን? አይመስለኝም።

ትምህርት 8

የትምህርቱ ክፍል ዘፍጥረት 2፡1-9፥ 16፥ 17

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር አዳምን በኤደን አኖረው

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. እግዚአብሔር ሊሠራ ያቀደውን በሙሉ ሠርቶ ጨረሰ (2፡1)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ለ. እግዚአብሔር ከመፍጠር ሥራው በሰባተኛው ቀን ዐረፈ (2፡2፥ 3)።

. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

ሐ. ዝናብ ሳይሆን ጉም ምድርን ያርሳት ነበር (2፡4-6)።

መ. እግዚአብሔር የዔደን ገነትን አዘጋጀ (2፡7፥ 8)።

. እግዚአብሔር ፍቅር ነው።

ሠ. እግዚአብሔር አዳምን በገነት አኖረው (2፡8)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ረ. የሕይወት ዛፍ (2፡9)።

. ለሰው እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሰ. መልካምንና ክፉን የሚያሳውቅ የእውቀት ዛፍ (2፡16፥ 17)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ሸ. እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ ቅጣቱ ሞት ነው (2፡17)።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። ለኃጢአት ሞት እንደሚገባው ደንግጓል።

1. ከእግዚአብሔር መለየት።

2. ከአካል (ከሥጋ) መለየት።

3. ለዘላለም በእሳት ባሕር ለመሆን መለየት።

ቀ. እግዚአብሔር በአዳም ላይ ያለው ሥልጣን።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. እግዚአብሔር ፍቅር ነው።

. እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው።

የትምህርት 7 ጥያቄዎችን ከልስ።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

ሀ. እግዚአብሔር ሊሠራ ያቀደውን በሙሉ ሠርቶ ጨረሰ

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ዘፍጥረት 2፡1 አንብብ። እግዚአብሔር ሊሠራ ያቀደውን በሙሉ ሠርቶ ጨረሰ። ብዙ ጊዜ ሰዎች አንዳንድ ነገሮችን ለመሥራት ይወስናሉ፥ ግን ቆይተው አሳባቸውን ይለውጣሉ። ፍላጐት ሊያጡ ወይም ሥራው ከባድ ሊሆንባቸው ይችላል። አንዳንዶቻችሁ ቤት መሥራት ጀምራችሁ ግማሽ ያህል እንደሠራችሁ ትታችሁት ይሆናል። ለምን?

እግዚአብሔር እንደ እኛ አይደለም። ሊሠራ ያቀደውን ጉዳይ ታክቶት አይተወውም። አንድ ሥራ ሲጀምር ሁልጊዜ ወደፍጻሜ ያመጣዋል፤ አሳቡን ቀይሮ የተለየ ነገር አያደርግም።

አንዳንድ ጊዜ፥ ጠዋት ተነሥታችሁ ወደ ገበያ ለመሄድ ታቅዳላችሁ። ነገር ግን ጠዋት ሳትሄዱ ትቀራላችሁ። ለምን እንዳልሄዳችሁ ስጠይቃችሁ ኃይለኛ ዝናብ ነበር ወይም ልጇ ታሟል ትሉኛላችሁ። ዕቅዶቻችንን ተግባራዊ እንዳናደርግ ብዙ ነገሮች ሊከላከሉን ይችላሉ።

በእግዚአብሔር ዘንድ ግን እንዲህ ዓይነት ነገር የለም። እግዚአብሔር ሊያደርግ ካቀደው ነገር ወደኋላ ተመልሶ አያውቅም። እግዚአብሔር ሊያደርግ ያቀደውን የሚከለክል ማንም ወይም ምንም ነገር የለም። እግዚአብሔርን ሊያቆም የሚችል መንፈስ የለም። እግዚአብሔርን ሊገታ የሚችል ሰው የለም። ሰይጣን እግዚአብሔርን ሊገታ አይችልም። እግዚአብሔር ከሁሉ የላቀ ነው። ያቀደውን ነገር ሁልጊዜ ያደርጋል፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አንድ ነገር ሊፈጽምልን ቃል ሲገባልን እንደሚያደርገው እርግጠኞች መሆን አለብን።

ለ. እግዚአብሔር ከመፍጠር ሥራው በሰባተኛው ቀን ዐረፈ

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

ዘፍጥረት 2፡2፥ 3 አንብብ። እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሁሉ ለመፍጠር ስንት ቀናት ፈጀበት? ስድስት ቀናት ብቻ ፈጀበት።

አንድ ቤት ለመሥራት ምን ያህል ጊዜ ይወስድባችኋል? ረጅም ጊዜ ይወስዳል አይደለም? የመሥሪያ ቁሳቁሶችን ከጫካ ለማዘጋጀት እንኳ ረጅም ጊዜ ይወስዳል።

እግዚአብሔር በስድስት ቀናት የፈጠራቸውን ነገሮች ሁሉ ተመልከት። እንደ እግዚአብሔር ያለ ታላቅ አምላክ የለም። እርሱ ሁሉን ቻይ ነው። የሚፈልገውን ማናቸውንም ነገሮች መሥራት ይችላል።

እግዚአብሔር ለመሥራት ያቀዳቸውን ነገሮች በሙሉ በስድስት ቀናት አጠናቀቀና ከመፍጠር ሥራው በሰባተኛው ቀን ዐረፈ። እግዚአብሔር ከመፍጠር ሥራው ያረፈው የሠራቸው ሥራዎች ስላደከሙት ነበርን?

ማገዶ ለማምጣት ሄዳችሁ ወደ ቤታችሁ ስትመለሱ ማድረግ የምትፈልጉት ምንድን ነው? ቀኑን ሙሉ ስትደክሙ ውላችሁ ስትመለሱ እንጨት መፍለጥና ገብስ መውቀጥን የመሰለ ከባድ ሥራ ለመጀመር ትፈልጋላችሁን? በፍጹም! ለምን? ከባድ ሥራ ስንሠራ ወይም ረጅም መንገድ ስንጓዝ በጣም ስለሚደክመን ማረፍ እንፈልጋለን።

እግዚአብሔር ማረፍ የፈለገው ስለደከመው ይመስላችኋልን? ፀሐይን፥ ጨረቃናን በሚሊየን የሚቆጠሩ ከዋክብትን ፈጥሯል። በምድር ላይ የሚገኙ የእግዚአብሔርን ፍጥረታት ተመልከቱ፤ እግዚአብሔር ጋደም በማለት «እጅግ ደክሞኛል ዛሬ ጥሩ ዕረፍት ያስፈልገኛል» ያለ ይመስላችኋልን?

በፍጹም አላለም። እግዚአብሔር ልክ እንደ እኛ ሊታክትና እንቅልፍ እንቅልፍ ሊለው አይችልም። ዕረፍት ወይም እንቅልፍ የሚፈልግ ሥጋዊ አካል የለውም። እግዚአብሔር መንፈስ ነው። እርሱ ሁልጊዜ ያው ነው። ምድርን በፈጠረበት ጊዜ በነበረው ብርታት ዛሬም አለ። እግዚአብሔር አይለወጥም አይደክምም።

ቤት መሥራት ቢኖርባችሁ የምታደርጉት የመጀመሪያ ነገር ምንድን ነው? ተስማሚ ቦታ መፈለግ ነው? ጥሩ! ትክክለኛውን ቦታ ካገኛችሁ በኋላስ ቀጥሎ ምን ታደርጋላችሁ?

መምህር ሆይ፡- እንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎችን የመጠየቅ ዓላማ ለምናስተምረው ርእስ የሚጨምሩት አንዳችም ነገር ባይኖርም እንኳ፥ የሕዝቡን ፍላጐት ለማነቃቃትና በመግለጫው ላይ የሚያክሉት አሳብ እንዲኖር ዕድል ለመስጠት ነው።

ቤታችሁን መሥራታችሁን በማጠናቀቅ ሌላ የምትጨምሩበት ነገር ባይኖርና እኔ ግን «ዛሬም ቤታችሁን ትሠራላችሁን?» ብዬ ብጠይቃችሁ፥ ምናልባት ብዙዎቻችሁ የምትሰጡት መልስ፥የቤት ሥራዬን ስለጨረስሁ የምሠራው የለኝም፥ ስለዚህ በሠራሁት ቤት ልዝናና ነው የሚል ይሆናል።

በእግዚአብሔርና በፈጠራቸው ፍጥረታት ዘንድ የሆነው ነገር እንደዚሁ ነበር። እግዚአብሔር በሠራቸው ሥራዎቹ ሁሉ እጅግ ተደሰተ።

ዘር በምትዘሩባቸው ወራቶች ለጤፍ እርሻ መሬቶቻችሁን ታዘጋጃላችሁ። መሬቱ በተዘጋጀ ጊዜ የጤፍ ዘር ትዘሩበታላችሁ። ጐረቤቶቻችሁ እንዲረዷችሁ ትጠይቁዋቸዋላችሁ። የእርሻ መሬቶቻችሁ ከተዘሩና ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ እንዴት ግሩም የሆነ ስሜት ይሰማችኋል። ዘር ከመዝራት ሥራ ታርፋላችሁ። ቁጥቋጦዎችን

መንጥራችኋል፥ ዛፎቻችሁን ቆርጣችኋል፥ አቃጥላችሁዋቸዋል፤ ደግሞም ዘር ዘርታችሁዋል። ይህ ማለት ሌላ ምንም የቀረ ሥራ የላችሁም ማለት ነውን? በእርግጥ አይደለም፤ ነገር ግን ዘር ከመዝራት ሥራ ዐርፋችኋል ማለት ነው። በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ተነሥታችሁ «የእርሻ መሬቴን ማዘጋጀት አለብኝ» አትሉም ማለት ነው።

እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሁሉ በስድስት ቀናት ውስጥ ከፈጠረ በኋላ በሰባተኛው ቀን ዐረፈ። እግዚአብሔር ከመፍጠር ሥራው ያረፈው ሊያደርግ ያቀዳቸው ሥራዎቹን በሙሉ ስለ ፈጸመ ነበር።

ሐ. ዝናብ ሳይሆን ጉም ምድርን ያርሳት ነበር።

ዘፍጥረት 2፡4-6 አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች ምን እንደሚያስተምሩ ከመመልከታችን በፊት እግዚአብሔር ለራሱ በሌላ ስም መጠቀም እንደጀመረ ልብ በሉ። በመጀመሪያው ምዕራፍ እግዚአብሔር ለራሱ የተጠቀመበት «እግዚአብሔር» የሚለው ስም ትርጉም፥ እርሱ ሰማያትንና ምድርን በውስጣቸው ያሉትን ሁሉ የፈጠረ ታላቅና ሁሉን ቻይ አምላክ መሆኑን ያመለክታል። በእነዚህ ቁጥሮች አሁን የሚጠቀምበት «ጌታ» የሚለው ስም ግን እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ እራሱን የቻለ፥ በምንም ነገር ላይ ያልተደገፈና የማይለወጥ ዘላለማዊ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱስ ስሙን አንዳንድ ጊዜ «እግዚአብሔር» በሌላ ጊዜ ደግሞ «ጌታ እግዚአብሔር» አንዳንድ ጊዜ ደግሞ «ጌታ» እያለ በመቀያየር ይጠቀምበታል።

እነዚህ ቁጥሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፍ አንድ ላይ ስላልተጠቀሱ ስለ መጀመሪያ ነገሮች ምን ያስተምሩናል? እግዚአብሔር በመጀመሪያ ምድርን ሲፈጥር ምድርን በውኃ ያረሰረሳት ዝናብ በማዝነብ አልነበረም። ምድር ከውስጧ በወጣ ጉም ረስርሳ ነበር።

መምህር ሆይ፡-

ሀ. ይህ መግለጫ የጥፋት ውኃን ታሪክ ለመናገርም ሆነ ሰው ስላየው የመጀመሪያ ዝናብ ለማስረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው። «ኖኅ ገና ስለማይታየው ነገር ተረድቶ ...» (ዕብራውያን 11፡7)

ለ. በተጨማሪ እግዚአብሔር ዝናብን የሚሰጥ አምላክ የመሆኑን እውነት ለሕዝቡ ያሳውቃል። የምታስተምራቸው ሰዎች ዝናብን የሚሰጠን አንድ መንፈስ አለ በማለት ምናልባት ያምኑ ይሆናል።

መ. እግዚአብሔር የዔድን ገነትን አዘጋጀ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ፍቅር ነው።

ዘፍጥረት 2፡7፥ 8 አንብብ። እግዚአብሔር አዳምን እጅግ ስለወደደው ለእርሱ የሚሆን የተለየ የአትክልት ስፍራን አዘጋጀለት።

እግዚአብሔር በዚህ የአትክልት ስፍራ አዳምን ደስተኛ፥ ብርቱና ጤነኛ የሚያደሩግትን የአትክልትና የፍራፍሬ ዓይነቶች በሙሉ አዘጋጀለት።

እንደዚህ ዓይነት የአትክልት ስፍራዎች የምታዘጋጁት ለማን ነው? የአትክልት ስፍራዎች አዘጋጅቶ ለሌላ ሰው የሚሰጥ ማን ነው? ምናልባት አንተ ይህን ካደረግህ ያን የምትሰጠውን ሰው በጣም ትወደዋልህ ማለት ነው።

እግዚአብሔር አዳምን ስለሚወደው እጅግ ውብ የሆነ የአትክልት ስፍራ አዘጋጀለት።

ሠ. እግዚአብሔር አዳምን በገነት አኖረው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘፍጥረት 2፡8 አንብብ። እግዚአብሔር ይህን የአትክልት ስፍራ ካዘጋጀ በኋላ አዳምን ወስዶ በዚያ አኖረው። እግዚአብሔር፥ አዳምን በዚያ መኖር ይፈልግ እንደሆነ አልጠየቀውም። አዳምን በቀጥታ ወስዶ ዔድን ገነት በተባለው ስፍራ አኖረው።

እግዚአብሔር ለመጀመሪያው ሰውን እንዲህ አላለውም፥ «አዳም፥ በጣም ውብ የሆነ የአትክልት ስፍራ አዘጋጅቼልሃልሁ። በዚያ መኖር ትፈልጋለህን?» እግዚአብሔር ይህንን ስፍራ ለአዳም ይኖርበት ዘንድ እንደሚፈልግ አልጠይቀውም ። እግዚአብሔር የፈጠረውን ሰው ወስዶ በዔድን ገነት አኖረው። እግዚአብሔር እንዲህ ያደረገው ለምድን ነው?

ምክንያቱም ሰውን የፈጠረው እግዚአብሔር ስለሆነ በፈለገው ስፍራ ሊያኖረውና ምን ማድረግ እንዳለበት ሊነግረው መብት ስላለው ነው።

እኔ ግን ለምሳሌ ወደ ቤታችሁ በመግባት ሬዲዮናችሁን አንሥቼ ከተመለከትኩ በኋላ ይህ በጣም ጥሩ ሬዲዮ ነው ብዬ ወደ ቤት ይዤ የመሄድ መብት የለኝም። ሬዲዮኑ የእናንተ እንደመሆኑ ወደምትፈልጉት ቦታ ወስዳችሁ ልታስቀምጡት፥ ልትወስዱት ትችላላችሁ፤ እኔ ግን አልችልም። የእኔ አይደለምና።

ወደ ቤታችሁ መጥቼ በቤታችሁ ያሉትን ዕቃዎች ከቦታ ቦታ የማዘዋወር መብት የለኝም። ዕቃዎቻችሁ የእናንተ ንብረቶች ናቸውና።

አንድ ከእናንተ መንደር አካባቢ የሚኖር ሰው ወደ መንደራችሁ በመምጣት በመንደሮቻችሁ የተሰማሩትን በጎች ከነበሩበት ስፍራ ወደሌላ ስፍራ ቢያንቀሳቅሳቸው ወይም አንዲት ሴት ወደ ቤታችሁ በመግባት ድስቶቻችሁን በመውሰድ በቤቷ ብታኖረው ትክክል ነውን? ለምን ትክክል አይሆንም? ሰዎች ሊወስዱትና እንደፈለጉ ከስፍራ ስፍራ ሊያዘዋውሩት የሚችሉት የራሳቸው ንብረት የሆነውን ነገር ብቻ ነው። አይደለምን?

ለአንድ ለሌላ ሰው «ቤት ሠርቼ ቆንጆ የአትክልት ስፍራም አዘጋጅቼአለሁ፥ ስለዚህ በዚያ ቤት እየኖርክ ስፍራውን መንከባከብ አለብህ» ልትል ትችላለህን? ይህንን ለሚስትህና ለልጆችህ ልትል ትችላለህ፤ ምክንያቱም እነርሱ የአንተ ቤተሰቦች ናቸው። ለሌሎች ልትለው ግን መብት የለህም።

እሺ፤ አዳምን በተመለከተስ እግዚአብሔር አዳምን ወስዶ በዔድን ገነት ሊያኖረው መብቱ ነውን?

አዳም የማን ንብረት ነው? የእግዚአብሔር ንብረት ነው፤ ምክንያቱም የፈጠረው እግዚአብሔር ነው።

እግዚአብሔር የነገሮች ሁሉ ባለቤት ነው። በእኛም ሆነ በፈጠራቸው በማናቸውም ነገሮች የሚፈልገውን የማድረግ መብት አለው። ምን ማድረግ እንዳለብን ሊነግረን መብት አለው። እግዚአብሔር አዳምን ስለፈጠረ አዳም የእግዚአብሔር ነው።

እግዚአብሔር ከሁሉ የላቀ ባለሥልጣን ነው። ከእግዚአብሔር የሚበልጥ ማንም የለም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር መልካም ስለሆነና ስለሚወደን በፈጠራቸው በየትኞቹም ነገሮች ላይ የማይገባ ነገር ጨርሶ አያደርግም።

እግዚአብሔር ለአዳም የኤድን ገነትን የአትክልት ስፍራ እንዲጠብቅ ነገረው። ለአዳም የተሰጠው ሥራ ከባድ አልነበረም፥ ምክንያቱም አረም የሚባል ነገር አልነበረም ሁሉም ነገር ፍጹም ነበር። ቀንድ አውጣዎች፥ ትላትሎችና የተለያዩ ነፍሳት ፍሬዎችንና አትክልቶችን አይበሉበትም ነበር።

መምህር ሆይ፡- ወደሚቀጥለው ነጥብ ከማለፍህ በፊት እስካሁን ድረስ ስለተነጋገራችሁባቸው ነጥቦች አጭር ክለሳ በማድረግ መልእክትህ ግልጽ መሆኑን አረጋግጥ።

እግዚአብሔር ያቀደውን የፍጥረት ሥራ በሙሉ አጠናቋልን? አዎን እግዚአብሔር ፀሐይ፥ ጨረቃ፥ ከዋክብት ምድርንና በውስጧ ያሉትን ነገሮች ሁሉ ፈጥሯል። እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች በሙሉ የፈጠረው ከምንም ሲሆን ሁሉም ደግሞ የእርሱ ናቸው።

እግዚአብሔር የጀመረውን ነገር ሁሉ ወደ ፍጻሜ ያመጣል። አሳባቸውን እንደሚቀይሩ ወይም በጀመሩትና ባቀዱት ነገር ፍላጐት እንደሚያጡ ሰዎች አይደለም። እግዚአብሔር፥ ሊያደርግ ከሚፈልገው ነገር ማንምና ምንም ሊያግደው አይችልም።

እግዚአብሔር፥ በምድር ላይ ሊያደርጋቸው ያሰባቸውን ነገሮች ሁሉ ከፈጠረ በኋላ በምድር እንዲኖርና ምድርንና በውስጧ ያሉትን ነገሮች እንዲገዛ የሾመው ማንን ነው?

እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ስለሆነ ቃል ብቻ በመናገር ፍጥረታትን ሁሉ በስድስት ቀናት ፈጥሮ ጨረሰ።

እግዚአብሔር፥ በሰባተኛው ቀን ፍጥረታትን ከመፍጠር ሥራው ዐረፈ። እግዚአብሔር፥ ከዚህ ተግባሩ ያረፈው ስለ ደከመው ነውን?

እግዚአብሔር ለአዳም ምን ስፍራን አዘጋጅቶ ነበር?

እግዚአብሔር አዳምን ወስዶ ወዳዘጋጀለት የአትክልት ስፍራ ሊያኖረው መብት ነበረውን?

ረ. የሕይወት ዛፍ

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 2፡9 አንብብ። እግዚአብሔር አንድ በጣም ልዩ የሆነ ዛፍ በዔድን ገነት የአትክልት ስፍራ መሃል ላይ አኖረ። ይህ ዛፍ የሕይወት ዛፍ በመባል ይታወቅ ነበር።

በዚያን ጊዜ ሕመም፥ ደዌና ሞት አልነበረም። አዳም ለዘላለም ለመኖር ከፈለገ ከዚያ የሕይወት ዛፍ ፍሬ መብላት ነበረበት።

እግዚአብሔር አዳምን ይህን ፍሬ እንዲበላ አላደረገውም። ይህ የአዳም ምርጫ ነበር። የእግዚአብሔር ፍላጐት አዳም እግዚአብሔር ከሰጠው የሕይወት ዛፍ ፍሬ ለመብላት ወይም ላለመብላት እንዲመርጥ ነበር።

የእግዚአብሔር ፍላጐት አዳም ለማንኛውም ነገር ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ላይ መደገፍ እንደሚያስፈልገው እንዲረዳ ነበር። እግዚአብሔር የፈለገው አዳም «እግዚአብሔር ሆይ አንተ ለእኔ በማንኛውም ነገር ታስፈልገኛለህ። አንተ ሕይወቴ ነህ። አንተ ፈጣሪዬ ነህ። ለሚያስፈልጉኝ ነገሮች ሁሉ በአንተ እደገፋለሁ። በዔድን ገነት የአትክልት ስፍራ መካከል ላይ ለእኔ ካኖርከው ከዚህ የሕይወት ዛፍ ፍሬ ተለይቼ ለመኖር አልችልም። አንተ የእኔ ፈጣሪ ስለሆንክ ምን ማድረግ እንዳለብኝና ምን ማድረግ እንደሌለብኝ ታሳውቀኛለህ። እኔም እታዘዝሃለሁ፤ ምክንያቱም አምላኬ ሆይ፥ ከአንተ ተለይቼ መኖር አልችልምና ነው» እንዲል ነበር።

ሰ. መልካምንና ክፉን የሚያሳውቅ የእውቀት ዛፍ

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ሲያደርግ።

እግዚአብሔር፥ አዳምን በዔድን ገነት ሲያኖር አዳም መሥራት ያለበትን ትክክለኛ ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ነገር እንዲወስን ፈቃድ አልሰጠውም ነበር። እግዚአብሔር አዳምን፥ ምን መሥራት እንዳለበት ይናገረው ነበር።

እግዚአብሔር ዛሬም አልተለወጠም። ትክክለኛ የሆነውና የተሳሳተው ነገር የቱ እንደሆነ እንድንወስን አልተወንም። እግዚአብሔር እርሱን ደስ የሚያሰኘውንና የማያሰኘውን ለመለየት እንድንችል መጽሐፍ ቅዱስን ሰጥቶናል።

ዘፍጥረት 2፡16፥ 17 አንብብ። እግዚአብሔር፥ አዳምን በዔድን ገነት ከሚገኙ የዛፍ ፍሬዎች ከአንዱ በቀር ሁሉንም መብላት እንደሚችል ነገረው። እንዳይበላ የተከለከለው የዛፍ ፍሬ ክፉንና ደጉን ለመለየት የሚያስችል የእውቀት ዛፍ ነበር።

እግዚአብሔር አዳምን ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ለአዳም መልካም የሆነውን ነገር የሚወስን እግዚአብሔር ነበር። እግዚአብሔር ለአዳም መልካም የሆነውን ነገር በመወሰን በዔድን ገነት የአትክልት ስፍራ አኖረው። አዳም ክፉ ወይም መጥፎ የሆነ አንዳችም ነገር አያውቅም ነበር፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ ሰጥቶት ነበርና።

አዳም፥ እግዚአብሔርን ሳይታዘዝ ቀርቶ መልካምንና ክፉን ከሚያሳውቅ የእውቀት ዛፍ ቢበላ ከእግዚአብሔር ተለይቶ እራሱን ችሎ ለመኖር እንደወሰነ የሚያሳይ ነበር። የዛፉን ፍሬ ከበላበት ጊዜ ጀምሮ መልካሙን ብቻ ሳይሆን ክፉውንም ጭምር አወቀ ማለት ነው። ከእንግዲህ መልካምና ክፉ የሆነውን ነገር የሚነግረው እግዚአብሔር መሆኑ ቀረና ራሱ በራሱ መወሰን ጀመረ።

እግዚአብሔርን ካልታዘዘና በእግዚአብሔር መደገፍ ትቶ ለራሱ መኖር ከፈለገ ውጤቱ ሞት፥ ከእግዚአብሔር መለየት ነበር።

ሸ. እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ ቅጣቱ ሞት ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። ለኃጢአት ሞት እንደሚገባው ደንግጓል።

ዘፍጥረት 2፡17 አንብብ። እግዚአብሔር አዳምን እንዲህ አለው። «... ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና ...»

እስከዚህ ጊዜ ድረስ አዳም የተለማመደው መልካም ነገርን ብቻ ነበር፤ ምክንያቱም ለአዳም የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ የሚሰጠው

እግዚአብሔር ነበር። አሁን ግን ከተከለከለው የዛፍ ፍሬ በመብላት ከእግዚአብሔር ተለይቶ ለመኖር ቢፈልግና እግዚአብሔርን ባይታዘዝ፥ ክፉ የሆነውንም ነገር እንደሚያውቅ በመንገር እግዚአብሔር አስጠነቀቀው። አዳምን ሞትን ትሞታለህ አለው። እግዚአብሔር አዳምን ሞትን ትሞታለህ ሲለው ምን ማለቱ ነበር?

1. ከእግዚአብሔር መለየት።

ሰይጣንና የተከተሉት መላእክት ኃጢአትን ባደረጉ ጊዜ ምን እንደሆኑ ታስታውሳለህን? ከእግዚአብሔር ፍቅርና ወዳጅነት ተለዩ። ሰይጣንና የተከተሉት መላእክት በእግዚአብሔር ላይ በማመፃቸው የእግዚአብሔር ወዳጅ መሆናቸው ቀረ። ከእግዚአብሔር ተለዩ። በሰማይ ከነበራቸው ሥልጣን ተወገዱ። እግዚአብሔር በመጨረሻ ለዘላለም እንዲኖሩበት አሰቃቂ የቅጣት ቦታ አዘጋጀላቸው።

ሁለት ጓደኛሞች ሊረሱት የማይፈቅዱት ከፍተኛ ጸብና ክርክር ውስጥ ቢገቡ በአንድነት ዓሣ ሊያጠምዱ ወይም አደን ሊወጡና ጊዜያቸውን አብረው ሊያሳልፉ ይችላሉን?

ባልና ሚስት ያለማቋረጥ ቢጣሉና ቢለያዩ አብረው መሆን ይወዳሉን? አይወዱም! ያለመግባባት መለያየትን ያመጣል። ሰዎች ከማይግቧቸው ሰዎች ጋር መኖርን አይወዱም።

እግዚአብሔር አዳምን ሲያስጠነቅቅ ትእዛዙን ካልተቀበለ የእግዚአብሔር ወዳጅ መሆኑ እንደሚቋረጥ አስታወቀው። ሰይጣን የእግዚአብሔር ጠላት እንደሆነ ሁሉ አዳምም እግዚአብሔርን ካልታዘዘ ጠላት ይሆናል። አዳም ከእግዚአብሔር ፍቅርና ወዳጅነት ይለያል፤ ይሞታል። አዳም የሕይወትና የመልካም ነገሮች ሁሉ ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር ይለያል። አዳም ከተከለከለው ፍሬ ከበላ፥ በእግዚአብሔር አምሳል በመፈጠሩ እንዲያውቅ፥ እንዲወድና እንዲታዘዝ የሚያስችለው የተፈጥሮ ክፍሉ ከእግዚአብሔር ይለያል።

2. ከአካል (ከሥጋ) መለየት።

አዳም ከተከለከለው ዛፍ ፍሬ በበላበት በዚያኑ ቀን በአካል ይሞታል ማለት አልነበረም፤ ነገር ግን በዚያ ቀን የሕይወት ሁሉ ምንጭ ከሆነው

ከእግዚአብሔር ይለያል ማለት ነበር። በዚህም ምክንያት ውሎ ቢያድርም በአካልም ይሞታል ማለት ነው።

ዛፎቹ ሲቆረጡ ወዲያውኑ አይሞቱም አይደለም? ቅጠሎቻቸው ለጥቂት ቀናት አረንጓዴ ሆነው ይቆያሉ። ዛፎቹም ከመቆረጣቸው በፊት በነበሩበት ሁኔታ ያሉ ይመስላሉ። ከሥሮቻቸው በመለየታቸው በሕይወት እንዲቆዩ የሚያስፈልጋቸውን እያገኙ መኖር አይችሉም፤ ከምድር ውኃና ምግብ ሊቀበሉ አይችሉም። ከትንሽ ቀናት በኋላ ዛፎቹ ይጠወልጉና ይደርቃሉ።

በአዳም ላይ እንደሚደርስ እግዚአብሔር የተናገረው ይህን ነበር። አዳም ይህን ፍሬ ከበላ የሕይወቱ ምንጭ፥ የሕይወቱ ሰጭና የሕይወቱ ጠባቂ ከሆነው ከእግዚአብሔር ወዲያውኑ ይቆረጣል። የሚቀጥለው ውጤቱ ደግሞ በአካል መሞት ጭምር ይሆናል።

አንድ ሰው ሲሞት ከአካሉ (ከሥጋው) ይለያል። በዓይን የማይታይ የሰው ሰብእና ክፍል የሆኑት መንፈሱና ነፍሱ ከአካሉ (ከሥጋው) ይለያሉ።

እግዚአብሔር፥ የአዳምን አካል በመጀመሪያ ሲፈጥረው አዳም ምንም ሕይወት አልነበረበትም። አካሉ እንደ ሞተ ሰው አካል ነበር። ቀጥሎ እግዚአብሔር የሕይወትን እስትንፋስ በአፍንጫው እፍ አለበት። እግዚአብሔር ለአዳም ነፍሱንና መንፈሱን የሰጠው የሕይወት እስትንፋስ እፍ ባለበት ጊዜ ነበር። አካላችን የነፍሳችንና የመንፈሳችን መኖሪያ ነው። እያንዳንዱ ሰው የራሱ ነፍስና መንፈስ በአካሉ ውስጥ አለው።

ልትጐበኙኝ ወደ ቤቴ ትመጣላችሁ፥ ትጠሩኛላችሁ፤ እኔም ከቤቴ ሆኜ እመልስላችኋለሁ። ወደ አገሬ ከሄድኩ ግን ቤቴን እተዋለሁ። በውስጡ መኖሬም ያበቃል። ከቤቴ እለያለሁ። ከዚያም አንድ ሰው የት እንደምኖር መጥቶ ቢጠይቃችሁ «ወደ አገሩ ሄዷል ከዚህ በኋላ እዚህ ስለማይኖር በቤቱ አታገኘውም» ብላችሁ ትመልሱለታላችሁ።

ሰው ሲሞት የሚሆነው ይህ ነው። የመንፈሱና የነፍሱ ቤት የሆነውን አካሉን ይተዋል።

እግዚአብሔር አዳምን ለእርሱ ባለመታዘዝ መልካሙንና ክፉውን ከሚያሳውቀው የዛፍ ፍሬ ከበላ ሕይወት ከሰጠው ከእግዚአብሔር እንደሚለይ ነገረው። ይህ ማለት በቅድሚያ አዳም የእግዚአብሔር ፍቅርና ወዳጅነት ከሚያስገኘው ደስታ ይለያል ማለት ነው ።

በመቀጠልም የአዳም አካል ይሞታል። በዚህም ነፍሱና መንፈሱ ከአካሉ ይለያሉ።

3. ለዘላለም በእሳት ባሕር ለመሆን መለየት

በመጨረሻ አዳም እግዚአብሔርን ባይታዘዝ የአካሉ መሞት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ አዘጋጀው አሰቃቂ የቅጣት ስፍራ እንዲሄድ ይደረጋል። የአዳም ቅጣትም ከዘላለም እስከዘላለም ይሆናል፤ የማምለጫም መንገድ የለውም። ከእግዚአብሔር ሊያመልጥ የሚችል የለም።

መምህር ሆይ፡- ሞት ማለት ምን ማለት እንደ ሆነና አዳም ከተከለከለው ዛፍ በመብላት የሕይወቱ ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር እንዴት እንደ ተለየ፥ በአንድ የዛፍ ቅርንጫፍ ምሳሌነት ልታስረዳ ትችላለህ። አንድ የዛፍ ቅርንጫፍ ወደ ትምህርት ክፍል ይዘህ ሂድ። ከአንድ ዛፍ ላይ እንደቆረጥከው ለተማሪዎች ተናገር። ከሕይወት ምንጩ ተለይቶ አሁን ይህ ቅርንጫፍ በሕይወት መኖር ይችላል ወይ? ብለህ ጠይቃቸው። ይህን እውነት አዳም እግዚአብሔርን ካልታዘዘ የሕይወቱ ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር እንደሚለይ ለመግለጥ ተጠቀምበት። ይህ ማለት አዳም ከዚህ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር በአንድነት ወይም በወዳጅነት ሊቆይ አይችልም ማለት ነው። አዳም ነፍሱና መንፈሱ ከአካሉ ሲለዩ በሥጋው ይሞታል፤ ከሞተ በኋላ ደግሞ ከእግዚአብሔር ለዘላለም ይለያል።

ታሪኮችን በጊዜ ቅደም ተከተል እያስተማርክ በሄድክ መጠን ይህ የዛፍ ቅርንጫፍ አሁንም በምሳሌነት ስለሚያገለግልህ አስቀምጠው። አዳም የተከለከለውን ፍሬ በበላ ጊዜ ከእግዚአብሔር ስለ መለየቱ ለማስተማር ልትጠቀምበት ትችላለህ። በቅርንጫፉ ላይ ከሚገኙት ቀንበጦች አንዱ፥ ከአዳም የተወሰደችውን ሔዋንን ለመግለጥ

ያገለግላል። ሌሎቹ ትናንሽ ቀንበጦች ቃየልና አቤልን፥ ጫፍ ላይ ችፍግ ያሉት ደግሞ የአዳም ዝርያዎችን ሊወክሉ ይችላሉ።

ሌላ ሞትን የሚያስረዳ መግለጫ ከአካልና ከአካል ክፍሎች መውሰድ ይችላል። አንድ ከንድ ከአካሉ ቢቆረጥና ቢለይ ከንዱ፥ እጁና ጣቶች ሁሉ ይሞታሉ።

ቀ. እግዚአብሔር በአዳም ላይ ያለው ሥልጣን።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር አዳምን ስለ ፈጠረ ምን ማድረግ እንዳለበት ሊነግረው መብት አለው። እግዚአብሔር አዳምን ፈጥሮ ሕይወትን ስጠው። አዳም የእግዚአብሔር ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ፍቅር ነው።

እግዚአብሔር የፈጠረውን ሰው ስለሚወድ በአዳም ፍቅርና ወዳጅነት ደስ ለመሰኘት ይፈልግ ነበር።

እግዚአብሔር፥ ለአዳም ምን ማድረግ እንዳለበት ሊነግረው መብት የነበረው አዳም የእግዚአብሔር ፍጡር በመሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር አዳምን ስለሚወደውና ከሁሉ የላቀና የተሻለ እንዲሆንለት ይፈልግ ስለ ነበር ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው።

እግዚአብሔር ለአዳም ምን ማድረግ እንዳለበት ሊነግረው መብት የነበረው፥ እግዚአብሔር ከአዳም የላቀ እውቀት ስላለው ነው። እግዚአብሔር ጠቢብ ነው። እርሱ ሁሉን ያውቃል። እግዚአብሔር፥ ለአዳም የሚስማማው ከሁሉ የተሻለና የላቀ ነገር ምን እንደሆነ ያውቅ ነበር።

እናንተ አዛውንቶች ለወጣቶች ትክክለኛውን ነገር እንዲያደርጉ የመንገር መብት አላችሁን? አዎን አላችሁ። እናንተ ትላልቆች ናችሁ። ብዙ ልምምዶች አላችሁ። የሕይወትን መንገዶች ታውቃላችሁ። ከወጣቶች የላቃችሁ ብልሆች ናችሁ፤ ስለዚህ መደረግ ያለባቸውን ትክክለኛ ነገሮች ልትነግሯቸው ይገባል።

እንደ እግዚአብሔር ያለ ጠቢብ ግን የለም። እርሱ ሁሉን ነገር ያውቃል። ለአዳም ከሁሉ የተሻለው ምን እንደሆነ ያውቅ ነበር። እግዚአብሔር፥ አዳም መልካምንና ክፉውን ከምታሳውቀው ዛፍ ከበላ፥ ከእግዚአብሔር ከፈጣሪው እንደሚለይ ያውቅ ነበር።

እግዚአብሔር አሁንም ቢሆን ከሁሉ የላቀውን ያውቃል። እውነትን ያውቃል። እኛ ደግሞ እውነትን ማወቅ እንድንችል መጽሐፍ ቅዱስን ሰጥቶናል። እርሱ ጠቢብ ፈጣሪያችን ስለሆነ የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ ልንሰማ ይገባል።

ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ጀምሮ ያልጨረሰው ነገር ሊኖር ይችላልን? አይኖርም።

2. እግዚአብሔር የማይጨርሰውን ነገር ለምን መጀመሪያውኑ አይጀምረውም? ምክንያቱም እግዚአብሔር ከቶ ስለማይለወጥ ነው። ሊያደርግ ያቀደውን ከመፈጸም የሚያግደው አንዳችም ነገር የለም።

3. እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ያረፈው ለምን ነበር? ምክንያቱም ፍጥረታትን የማስገኘት ተግባሩ ተጠናቆ ነበር።

4. እግዚአብሔር በመጀመሪያ ምድርን ሲፈጥር አትክልቶችን በውኃ ለማረስረስ ዝናብን አዘነበን? አላዘነበም። እግዚአብሔር ምድርን ያረሰረሰው ከራሷ በወጣ ጉም ነበር።

5. እግዚአብሔር የዔድን ገነትን የአትክልት ስፍራ ያዘጋጀው ለማን ነበር? ለአዳም።

6. እግዚአብሔር የአዳምን ፈቃድ ሳይጠይቅ አዳምን በዔድን ገነት ማኖሩ ትክክል የሆነው ለምንድን ነው? እግዚአብሔር አዳምን ስለፈጠረና አዳም የእርሱ ንብረት ስለሆነ ነው።

7. ነገሮች ሁሉ፥ መናፍስትና ሕዝቡ የማን ናቸው? የፈጣሪያቸው የእግዚአብሔር ናቸው።

8. በዔድን ገነት ከነበሩ ዛፎች መካከል አዳም እንዲበላ የተፈቀደለት የስንቱን ዛፍ ፍሬ ነበር? ከአንዱ በስተቀር የሁሉንም ዛፍ ፍሬ ነበር።

9. በዔድን ገነት መካከል የነበረ አዳም ቢበላው ለዘላለም ይኖር ዘንድ የሚያስችለው ዛፍ ስም ምን ነበር? የሕይወት ዛፍ ነው።

10. ለአዳም የሕይወትን ዛፍ በገነት ያኖረለት ማን ነው? እግዚአብሔር ነው።

11. እግዚአብሔር፥ አዳም ፍሬውን እንዳይበላው የከለከለው ዛፍ ማን ነበር? መልካምንና ክፉን ለመለየት የሚያስችለውን ዛፍ ነበር።

12. እግዚአብሔር፥ መልካምንና ክፉውን ከሚለየው ዛፍ አዳም በበላ ጊዜ ምን ይሆናል አለ? ይሞታል አለ።

13. እግዚአብሔር ሰውን «ይሞታል» ሲል ምን ማለቱ ነበር?

ሀ. ሰው የሕይወቱ ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር ወዲያውኑ ይለያል።

ለ. መንፈሱና ነፍሱ ከአካሉ ሲለዩ በሥጋው ይሞታል።

ሐ. የሰው ሥጋ ነፍሱና መንፈሱ ለዘላለም ከእግዚአብሔር ተለይተው እግዚአብሔር ለሰይጣንና ለተከተሉት መናፍስት ወደ አዘጋጀው ስፍራ ይሄዳሉ።

ትምህርት 9

የትምህርቱ ክፍል፡- ዘፍጥረት 2፡18-25

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር ሔዋንን ፈጠረ።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ የእምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. እግዚአብሔር፥ አዳም ብቻውን እንዳይሆን ረዳት የምትሆን ሚስት እንደሚያስፈልገው ወሰነ (2፡18)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. እግዚአብሔር ፍቅር ነው።

ለ. እግዚአብሔር፥ እንስሳትን ሁሉ ወደ አዳም አምጥቶ ስም እንዲያወጣላቸው አደረገ (2፡19፥ 20)።

ሐ. ከእንስሳት መካከል ለአዳም የሚሆን ተስማሚ ጓደኛ አልተገኘም (2፡20)።

. ሰው እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

መ. እግዚአብሔር፥ ከአዳም የጐን አጥንት ሔዋንን ፈጠረ (2፡21፥ 22)።

. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

ሠ. ጋብቻን የመሠረተ እግዚአብሔር ነው (2፡23፥ 24)።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው።

ረ. አዳምና ሔዋን ራቁታቸውን መሆናቸውን አያውቁም ነበርና ሙሉ ለሙሉ አይተፋፈሩም ነበር (2፡25)።

የትምህርት 8 ጥያቄዎችን ከልስ።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ በዝርዝር ማቅረብ።

ሀ. እግዚአብሔር፥ አዳም ብቻውን እንዳይሆን ረዳት የምትሆን ሚስት እንደሚያስፈልገው ወሰነ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘፍጥረት 2፡18 አንብብ። አዳም ብቻውን መኖር እንደሌለበት እግዚአብሔር ወሰነ። እግዚአብሔር ፈጣሪው ስለሆነ ለእርሱ ከሁሉ የሚሻለውን ያውቅ ነበር። እግዚአብሔር፥ አዳምን ምን እንደሚፈልግ ወይም ምን እንደሚያስብ አልጠየቀውም። እግዚአብሔር ለአዳም ሚስት እንደሚያስፈልገው ወሰነ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ፍቅር ነው።

እግዚአብሔር አዳምን ይወደው ስለ ነበር ደስተኛ እንዲሆን ይፈልግ ነበር። አዳም ብቻውን ከሆነ ደስተኛ ሊሆን እንደማይችል እግዚአብሔር ያውቅ ነበር። እግዚአብሔር አዳምን ይወደው ስለ ነበር ከሁሉ የተሻለውን ነገር ለእርሱ በማሰብ ሚስት ሊፈጥርለት ወሰነ።

ለ. እግዚአብሔር፥ እንስሳትን ሁሉ ወደ አዳም አምጥቶ ስም እንዲያወጣላቸው አደረገ።

ዘፍጥረት 2፡19፥ 20 አንብብ። እግዚአብሔር አዳምን በእንስሳት ሁሉ ላይ ገዥ አደረገው። በተጨማሪ ለእንስሳቱ ሁሉ ስም እንዲያወጣላቸው እግዚአብሔር ኃላፊነትን ሰጠው።

ሐ. ከእንስሳት መካከል ለአዳም የሚሆን ተስማሚ ጓደኛ አልተገኘም።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 2፡20 አንብብ። እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ከእንስሳት ሁሉ የተለየ አድርጐ ነው። ሰው እግዚአብሔርን እንዲያውቅ፥ እንዲወድ፥ እንዲታዘዝ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠረ። እንስሳት፥ ግን እንደ ሰው አይደሉም፤ ስለዚህ እግዚአብሔርን ሊያውቁ፥ ሊወዱና ሊታዘዙ አይችሉም።

የእንስሳት ፍላጐትና የሰዎች ፍላጐት ተመሳሳይ አይደለም። ሰዎች የሚያደርጓቸውን አብዛኛዎቹን ነገሮች ለማድረግ አይችሉም።

አዳም ሊያነጋግረው የሚችልና፥ ከእርሱ ጋር ተመሳሳይ ድርጊት የሚፈጽም ጓደኛ ያስፈልገው ነበር። የትኛውም እንስሳ ለሰው እንዲህ ዓይነት ጓደኛ ሊሆን አይችልም።

ሰው ጓደኛና ሚስት እንዲኖረው በራሱ ሊያደርገው የሚችል አንዳችም ነገር አልነበረም።

መናፍስት፥ ለአዳም ሚስት ሊፈጥሩለት አይችሉም ነበር።

እግዚአብሔር ግን ሰውን ስለሚወድ ብቻውን እንዲሆን አልፈለገም። ታዲያ እግዚአብሔር ምን ያደረገ ይመስላችኋል?

መ. እግዚአብሔር ከአዳም የጐን አጥንት ሔዋንን ፈጠረ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

ዘፍጥረት 2፡21፥ 22 አንብብ። ይህን ሊያደርግ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። እርሱ ሁሉን ያውቃል። የሚፈልገውንም ሁሉ ማድረግ ይችላል።

እግዚአብሔር የመጀመሪያዋን ሴት ለመጀመሪያው ሰው ስጦታ አድርጐ ሰጠ።

አንድ የሚወዳችሁ ሰው በጣም ግሩም የሆነ ውድ ስጦታ ቢሰጣችሁ ለስጦታው እንክብካቤ ታደርጉለታላችሁን? እግዚአብሔር ለአዳም ሚስት ሲሰጠው እንዲንከባከባትና እንዲወዳት ፍላጐቱ ነበር።

መምህር ሆይ፡-

ሀ. በአድማጮችህ ግምት በጣም ውድ የሆነ ባህላዊ ስጦታን በመግለጫነት መርጠህ ተጠቀም። (ለምሳሌ ወርቅና የአገር ባህል ልብስ)።

ለ. በዚህ ነጥብ ላይ ረጅም ጊዜ አታባክን።

ሐ. በባልና ሚስት መካከል ስላሉ ግንኙነቶች መናገር አትጀምር።

መ. ሕዝቡ ደኅንነትን ሳይረዱና ሳይቀበሉ ስለተሐድሶ ወይም ቅድስና አትስበክ። አሁን ወደ ፊት የምንገነባበትን መሠረት እየጣልን ነው።

ሠ. ሴቶች ከወንዶች በታች ተደርገው በሚታዩበትና ተገቢውን ክብር በማያገኙበት ኅብረተሰብ በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት መሠረት ተገቢውን ስፍራቸውን ለመስጠት በዚህ

ዕድል መጠቀም አለብን። እግዚአብሔር ይህንን በመጠቀም የወንዶችን ሕሊና በመውቀስ እርሱ ለሴቶች ያለውን ተገቢ ስፍራ እንዲያስቡ ያደርጋቸው ይሆናል። ሴቶችን ደግሞ ወንዶች ተገቢውን ስፍራ ባይሰጡአቸውም እንኳ እግዚአብሔር ስለ እነርሱ እንደሚያውቅና እንደሚወዳቸው በማወቅ እንዲጽናኑ ያደርጋቸው ይሆናል። ይህ ሴቶቹን የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰሙ ሊያበረታታቸው ይገባል።

ሠ. ጋብቻን የመሠረተ እግዚአብሔር ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው።

ዘፍጥረት 2፡23፥ 24 አንብብ። እግዚአብሔር ለወንድ ሴትን በመፍጠር እንዲጋቡ አብረው እንዲኖሩና ልጆች እንዲወልዱ ዐቀደ። «... ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ...» በማለት እግዚአብሔር አዳምን አዘዘው።

እግዚአብሔር የሚያደርገውና የሚናገረው ሁሉ ፍጹም ስለሆነ መልካም ነው። መጥፎ የሆነ ነገር ሊያስብ ሊናገር እና ሊያደርግ አይችልም። ጋብቻ መልካም ነው፤ ምክንያቱም ጋብቻን ለሰው የሰጠ እግዚአብሔር ነው።

አዳም፥ በእግዚአብሔር ስጦታ እጅግ ደስ ተሰኝቶ ነበር።

መምህር ሆይ፡- በዚህ ነጥብ ላይ ስለአመንዝራነት፥ ብዙ ሚስቶች ስለማግባት ወይም ሥነ-ምግባር ስለጐደለው ፍትወተ ሥጋ ማስተማር አትጀምር። የኃጢአት ፍሬን ማስተማር ከመጀመራችን በፊት ትምህርታችን ከኃጢአት ሥራ መጀመር አለበት። በዘፍጥረት 3 ስለ ኃጢአት ሥር እናስተምራለን። ሰው ባለመታዘዙ ከእግዚአብሔር ተለየና በተፈጥሮው ኃጢአተኛ ሆነ። በዘፍጥረት 4 የሰውን ኃጢአታዊ ተፈጥሮ በግልጽ የሚያስረዳ ነገር በቃየል ሕይወት አማካይነት እንመለከታለን። ሰዎች የሚያደርጉት ነገር የማንነታቸው ነጸብራቅ መሆኑን ከመገንዘባቸው በፊት፥ የኃጢአት ፍሬ በሆኑት (ለምሳሌ፡- ዝሙት፥ ስርቆት፥ ውሸት ወዘተ) ላይ ካተኰርን፥ በእግዚአብሔር ፊት እራሳቸውን በራሳቸው ለማንጻት ወደሚያመራ አጉል አስተሳሰብ ሊያመሩ ይችላሉ። በታሪካዊም ሆነ በሥነ-መለኮት ትምህርት ቅደም ተከተላዊ

ገለጻህ ውስጥ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊና ከታሪካዊ የጊዜ ቅደም ተከተሎች አትቅደም።

ረ. አዳምና ሔዋን ራቁታቸውን መሆናቸውን አያውቁም ነበርና ሙሉ ለሙሉ አይተፋፈሩም ነበር።

ዘፍጥረት 2:25 አንብብ።

መምህር ሆይ:- ይህ ነጥብ ለዘፍጥረት 3:7 ማዘጋጂያ ነው።

ጥያቄዎች

1. አዳም ረዳት የምትሆን ሚስት እንደሚያስፈልገው የወሰነው ማን ነበር? እግዚአብሔር ነበር።

2. እግዚአብሔር፥ ለአዳም ሚስት ይፈጥርለት ዘንድ የወሰነው ለምን ነበር? እግዚአብሔር፥ አዳምን ስለሚወደውና ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም እንዳይደለ ስላሰበ ነው።

3. እግዚአብሔር፥ አዳምን ሳይጠይቅ ይህን መወሰኑ ትክክል ነበርን? አዎን፥ እግዚአብሔር አዳምን ስለፈጠረ እርሱ ከሁሉ ነገር፥ ከመናፍስት ሁሉና ከማንኛውም ሰው ትክክለኛ ነው።

4. እግዚአብሔር የመጀመሪያዋን ሴት የፈጠረው እንዴት ነበር? እግዚአብሔር አዳምን ከባድ እንቅልፍ ጥሎበት ከጐድኑ አንድ አጥንት በመውሰድ የመጀመሪያዋን ሴት ከአዳም ጐድን አጥንት ፈጠራት።

5. እግዚአብሔር፥ ሔዋንን ከአዳም ጐድን አጥንት ሊፈጥራት እንዴት ቻለ? ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለም። ሊያደርግ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ማድረግ ይቻለዋል።

6. አዳምና ሔዋን እንዲጋቡና ልጆችን እንዲወልዱ የነገራቸው ማን ነበር? ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር ነበር።

ትምህርት 10

የትምህርት ክፍል፡- ዘፍጥረት 1፤ 2

አጠቃላይ ርእስ፡- እስካሁን ድረስ ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ሰይጣንና ስለ ሰው የተሰጡትን ትምህርቶች ከልስ

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች

ሀ. እግዚአብሔር

ለ. ሰይጣን

ሐ. ሰው

የትምህርት 9 የክለሳ ጥያቄዎችን አሁን እንዲከልሱ አትንገራቸው፤ ምክንያቱም በዚህ ትምህርት በሐ. ሥር ተጠቃለው ስለቀረቡ ነው።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ።

መምህር ሆይ፡- ዘፍጥረት 1 ና 2ን ስናስተምር በመጠኑም ቢሆን ስለ እግዚአብሔር፥ ሰይጣንና ሰው አስተዋውቀናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለተመዘገቡት ታሪካዊ ገቢሮች ሦስቱ ዋና ተዋንያን እነርሱ ናቸው። አሁን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙ ክፍሎች ሁሉ በላቀ ሁኔታ ተፈላጊ የሆነውን ዘፍጥረት 3ን ለማስተማር እየተዘጋጀን ነው። የሰው ኃጢአት ጅማሬ፥ ሞትና በዓለም ላይ የሚገኙ አስቸጋሪ ነገሮች ሁሉ አመጣጥ፥ ከመጀመሪያው የአዳኝ ተስፋ ጋር የተገለጠው በዘፍጥረት 3 ነው። ሆኖም የዘፍጥረት 3 ታሪካዊና መሠረታዊ እምነት ትምህርት የእግዚአብሔርን፥ የሰይጣንና የሰውን መሠረታዊ ባሕርይ ሳንገነዘብ በሚገባ ልንረዳው አንችልም፤ ስለዚህ አዳማጮቻችን በእርግጥ ይህን ይረዱ ዘንድ በትምህርት 10 ስለእነዚህ ሦስት ሕልውናዎች የተመለከትናቸውን ዋና ዋና ነጥቦች እንከልሳለን። ክለሳው ጥያቄዎችን በመጠየቅ ይሆናል።

ሀ. ጥያቄዎችን ስትጠይቅ ሊመልሱት ካልቻሉ በሌላ መንገድ ጥያቄውን አቅርብላቸው፤ ወይም ለመልሱ አንዳንድ ፍንጮችን ስጥ። ጥቂት ፍንጭ ከሰጠኻቸው በኋላ መመለስ

ካልቻሉ መልሱን ንገራቸው። መልሱን ባያውቁትም እንኳ አትገስፃቸው። ወይም ማንንም ሰው በማንጓጠጥ እንዳታሳፍር ተጠንቀቅ።

ለ. አንዳንድ ጥያቄዎችን በግል አንዳንዶችን ደግሞ በጋራ እንዲመልሱ አድርግ።

ሐ. አብዛኛዎቹን ጥያቄዎች የሚመልሱት አንድ ወይም ሁለት ሰዎች ብቻ ከሆኑ «እከሌና እከሌ የዚህን ጥያቄ መልስ ያውቁት ይሆናል፤ ስለዚህ ይህን ጥያቄ ሌሎች ሰዎች እንዲመልሱት እፈልጋለሁ» በማለት ሌሎች እንዲመልሱት መጋበዝ ትችላላችሁ።

ሀ. እግዚአብሔር

ከእግዚአብሔር መጽሐፍ ስለ አዳምና ሔዋን ተጨማሪ ነገር ከመማራችን በፊት ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ሰይጣንና ስለ መጀመሪያዎቹ እግዚአብሔር ስለፈጠራቸው ወንድና ሴት ከዚህ ቀደም የተማርነውን እንከልሳለን። የምንጀምረው ስለ እግዚአብሔር አንዳንድ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ነው።

1. ዙሪያችሁን ተመልከቱ፥ ለመሆኑ መጀመሪያ የሌለው ምን ነገር ልታዩ ትችላላችሁ? ምንም ነገር የለም። ሁሉም ነገር መጀመሪያ አለው።

2. ከሁሉ ነገሮች በፊት የነበረና ከመሬት፥ ከፀሐይ፥ ከጨረቃ፥ ከከዋክብት፥ ከሰዎችና ከመናፍስት ሁሉ የሚበልጥ ማን ነው? እግዚአብሔር ነው።

3. የእግዚአብሔር መጀመሪያ መቼ ነበር? እግዚአብሔር ፈጽሞ መጀመሪያ የለውም።

4. እግዚአብሔርን የፈጠረው አለን? የለም።

5. እግዚአብሔር እንደ እኛ ተወልዷልን? አልተወለደም።

6. እግዚአብሔር እራሱን ፈጥሯልን? አልፈጠረም ።

7. እግዚአብሔር ያልነበረበት ጊዜ ነበርን? አልነበረም።

8. እግዚአብሔር፥ ሊለወጥ ወይም ሊሞት ይችላልን? ፈጽሞ። እርሱ ሁልጊዜ ያው ነው። ፈጽሞ አይለወጥም።

9. እግዚአብሔር ልክ እንደ እኛ ሥጋና አጥንት ያለው አካል አለውን? የለውም፤ እግዚአብሔር መንፈስ ነው።

10. እኛ ምግብ፥ ውኃ፥ አየር፥ የምንራመድበት መሬትና የሚያሞቀን ፀሐይ ያስፈልገናል። ለእግዚአብሔርስ ምን ያስፈልገዋል? ምንም አያስፈልገውም።

11. ታዲያ እግዚአብሔር የሚኖረው እንዴት ነው? በራሱ ኃይል ነው።

12. እግዚአብሔር ያለው የት ነው? እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ ይገኛል።

13. ስንት አምላኮች (እግዚአብሔሮች) አሉ? አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ።

14. በአንዱ እግዚአብሔር ውስጥ ያሉት ሦስት አካላዊ ሕልውናዎች እነማን ናቸው? እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ናቸው።

15. ሰማይና ምድርን፥ በውስጣቸውም ያሉትን ነገሮች ሁሉ የፈጠረ ማን ነው? እግዚአብሔር ነው።

16. እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ለመፍጠር በምን ተጠቀመ? በአንዳችም አልተጠቀመም። ነገሮችን ሁሉ ከምንም ፈጠራቸው።

17. እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ የፈጠረው እንዴት ነበር? ይሁን የሚል ቃል በመናገርና በማዘዝ ብቻ ነው።

18. እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን እንዴት ሊፈጥር ቻለ? እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው። ሊያደርገው የማይችለው አንዳችም ነገር የለም።

19. እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን መፍጠር እንዴት አወቀ? እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው።

20. እግዚአብሔር ስለፈጠራቸው ነገሮች ሁሉ ምን አለ? መልካም ናቸው አለ።

21. እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ፍጹም ሊያደርግ እንዴት ቻለ? እርሱ ፍጹም ስለሆነ ነው።

22. እግዚአብሔር በምድር ላይ ለሰው ልጅ ሁሉን ነገር ውብና መልካም ያደረገው ለምን ነበር? እግዚአብሔር አፍቃሪና ደግ ስለሆነ ነው።

23. እግዚአብሔር ፀሐይ፥ ጨረቃና ከዋክብት ሁልጊዜ በተመሳሳይ መንገድ እንዲሠሩ አድርጐ ፈጠራቸው። ይህ ስለ እግዚአብሔር ምን ያስተምረናል? እግዚአብሔር የሕግና የሥርዓት አምላክ መሆኑን ያስተምረናል።

24. እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ትክክለኛ ባለመብት የሆነው ለምንድን ነው? ነገሮችን ሁሉ ስለፈጠረና ለነገሮች ሁሉ ሕይወትን ስለሰጠ ነው።

25. እግዚአብሔር እንታዘዘው ዘንድ መብቱ የሆነው ለምንድን ነው? እርሱ ፈጣሪያችን ስለሆነ ነው።

ለ. ሰይጣን

1. መናፍስት ሁሉ የመጡት ከየት ነበር? በእግዚአብሔር ተፈጥረው ነበር።

2. እግዚአብሔር መናፍስትን የፈጠረው ሥጋና አጥንት ያላቸው አድርጐ ነውን? አይደለም።

3. እግዚአብሔር፥ መናፍስትን ሁሉ መልካም አድርጐ ፈጠረን? ወይስ አንዳንዶቹን መልካም ሌሎቹን ደግሞ ክፉ አድርጐ ነበር? እግዚአብሔር ሁሉን መልካም አድርጐ ፈጠራቸው።

4. እግዚአብሔር መናፍስትን የፈጠረው ለምን ነበር? አገልጋዮቹ እንዲሆኑ ነበር።

5. እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሲፈጥራቸው የሚኖሩት በየት ነበር? ከእግዚአብሔር ጋር በሰማይ ይኖሩ ነበር።

6. መናፍስት ሁሉ እንደ እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉ ስፍራ ይገኛሉን? አይገኙም፤ መናፍስት በመላው ዓለም ቢገኙም፤ ዳሩ ግን እንደ እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ አይገኙም።

7. በእግዚአብሔር ከተፈጠሩ መላእክት ሁሉ እጅግ ውብና ጠቢብ የነበረው መልአክ ማን ነው? ሳጥናኤል ነው።

8. እግዚአብሔር ለሳጥናኤል የሰጠው ሥልጣን ምን ነበር? በሌሎች መላእክት ሁሉ ላይ መሪ እንዲሆን ነበር።

9. ሳጥናኤል፥ ለማን እንዲያገለግልና እንዲታዘዝ ይገባው ነበር? ለፈጠረው ለእግዚአብሔር።

10. ሳጥናኤል ሊያደርግ ያቀደው ምን ነበር? እንደ እግዚአብሔር ለመሆንና የእግዚአብሔርን ሥልጣን ለመውሰድ ነበር።

11. ሳጥናኤል በእግዚአብሔር ላይ ባደረገው ዓመፃ ማን ተከተለው? በርካታ የእግዚአብሔር መላእክት ተከተሉት።

12. እግዚአብሔር በዚህ ጉዳይ ላይ ምን እርምጃ ወሰደ? እግዚአብሔር ሳጥናኤልንና እርሱን ተከትለው በእግዚአብሔር ላይ ያመፁትን መላእክት እግዚአብሔርን ያገለግሉ ከነበሩበት ሥልጣናቸው አስወገዳቸው።

13. ሳጥናኤል የአሁኑ ስሙ ማን ነው? ትርጉሙስ? ሰይጣን ነው። ትርጉሙም ባላጋራ፥ ተቃዋሚ፥ ጠላት ማለት ነው።

14. እግዚአብሔር፥ ለሰይጣንና ለአጋንንቱ ያዘጋጀው የቅጣት ስፍራ ምንድን ነው? እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸው የቅጣት ቦታ የእሳት ባሕር ነው።

15. ሰይጣን የሚቃወመው ማንን ነው? እግዚአብሔርንና እግዚአብሔር የሚወዳቸውን ሁሉ ይቃወማል።

16. እግዚአብሔር፥ ሰማይን፥ ምድርንና በውስጧ ያሉትን ነገሮች ሁሉ ሲፈጥር የእግዚአብሔር መላእክት፥ ሰይጣንና አጋንንት አይተውታልን? አዎን።

ሐ. ሰው

1. እግዚአብሔር ምድርን ካዘጋጀ በኋላ ማንን ፈጠረ? ሰውን።

2. በሰው አፈጣጠርና በእንስሳት አፈጣጠር መካከል ያለው ትልቁ ልዩነት ምንድን ነው? ዋናው ልዩነት እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው እርሱን ሊያውቅ፥ ሊወድና ሊታዘዝ ይችል ዘንድ በአምሳሉ ከመሆኑ ላይ ነው።

3. እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ፈጠረ ማለት ምን ማለት ነው? ሰው እግዚአብሔርን እንዲያውቅ፥ እንዲወድና እንዲታዘዝ ይችል ዘንድ እንደ እራሱ አድርጎ ፈጠረው ማለት ነው።

4. ሰው፥ እግዚአብሔር ሲፈጥረው መልካም ነበር ወይስ ክፉ? መልካም ነበር።

5. እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው አዳምን ከፈጠረ በኋላ በምን ላይ ሥልጣንን ሰጠው? በምድርና በውስጧ ባሉት ነገሮች ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጠው።

6. እግዚአብሔር፥ አዳምን ከፈጠረ በኋላ በየት አኖረው? እግዚአብሔር ለአዳም ባዘጋጀው ዔድን ገነት በተባለ የአትክልት ስፍራ አኖረው።

7. እግዚአብሔር በዔድን ገነት ያኖራቸው ተጨማሪ ሁለት እጅግ ጠቃሚ ዛፎች የትኞቹ ናቸው? የሕይወት ዛፍና መልካምንና ክፉን የሚያሳውቅ የእውቀት ዛፍ ናቸው።

8. እግዚአብሔር፥ አዳምን ፍሬውን እንዳይበላ የከለከለው ዛፍ የትኛው ነው? መልካምንና ክፉን የሚያሳውቀውን የእውቀት ዛፍ ነው።

9. ሰው እግዚአብሔርን አልታዘዝም ብሎ መልካምንና ክፉውን ከሚያሳውቀው ዛፍ ቢበላ ምን እንደሚሆን እግዚአብሔር ተናገረ? ሰው ሞትን እንደሚሞት ተናገረ።

10. እግዚአብሔር፥ ሰውን ሞትን ትሞታለህ ሲለው ምን ማለቱ ነው?

    ሀ. ወዲያውኑ የሕይወቱ ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር ይለያል። ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ወዳጅነት ይቋረጣል።

    ለ. ነፍሱና መንፈሱ ከአካሉ ሲለዩ የሥጋን ሞት ይሞታል።

    ሐ. የሰው አካሉ፥ ነፍሱና መንፈሱ እግዚአብሔር ለሰይጣንና ለአጋንንቱ ወደ አዘጋጀው ስፍራ በመሄድ ለዘላለም ከእግዚአብሔር ይለያሉ።

11. እግዚአብሔር፥ አዳምን በዔድን ገነት ካኖረው በኋላ ማንን ፈጠረለት? ሚስት ትሆነው ዘንድ ሔዋንን ፈጠረለት።

12. እግዚአብሔር ሔዋንን የፈጠረው ለምን ነበር? ለአዳም ምቹ ረዳት ጓደኛ ሊሆን የሚችል ከእንስሳት መካከል ስላልነበረና እግዚአብሔር ይወደው ስለ ነበር ብቻውን እንዳይሆን ሔዋንን ፈጠረለት። እግዚአብሔር፥ ሰው ልጆች እንዲኖሩት ይፈልግ ነበር።

ትምህርት 11

የትምህርት ክፍል፡ - ዘፍጥረት 3፡1-8

አጠቃላይ ርእስ፡ - አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ሳይታዘዙ ቀሩ።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች።

ሀ. ሰይጣን እራሱን ለውጦ በማቅረብ ሔዋንን ለማታለል በእባብ ተጠቀመ (3፡1)።

. ሰይጣን እግዚአብሔርንና ፈቃዱን ይዋጋል። ሰይጣን ዋሾና አታላይ ነው። ሰውን ይጠላል።

ለ. ሰይጣን ሔዋንን ተፈታተናት አታለላትም (3፡1-5)።

. ሰይጣን እግዚአብሔርንና ፈቃዱን ይዋጋል። ሰይጣን ዋሾና አታላይ ነው። ሰውን ይጠላል።

ሐ. ሔዋን ፍሬውን በላች፤ ለባሏም ሰጠችው (3፡6)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። እግዚአብሔር ያስፈልገዋል። እራሱን ለማዳን ፈጽሞ አይችልም።

መ. የአዳምና ሔዋን ኃጢአት ቅጽበታዊ ውጤቶች (3፡7፥ 8)።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደሞዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትን የተሞላና የጸጋ አምላክ ነው።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝ ደግሞም ሁሉን አዋቂ ነው።

ሠ. ሰይጣን አዳምና ሔዋንን እግዚአብሔርን ወደ አለመታዘዝ የመራበት ምክንያቶች።

. ሰይጣን እግዚአብሔርንና ፈቃዱን ይዋጋል። ሰይጣን ዋሾና አታላይ ነው። ሰውን ይጠላል።

ረ. ማጠቃለያ

ከትምህርት 10 የመጨረሻዎቹን ሰባት ጥያቄዎች ከልስ

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ።

ሀ. ሰይጣን እራሱን አስመስሎ ለማቅረብና ሔዋንን ለማታለል በእባብ ተጠቀመ

ዋና አሳብ፡- ሰይጣን እግዚአብሔርንና ፈቃዱን ይወጋል። ሰይጣን ዋሾና አታላይ ነው። ሰውን ይጠላል።

አዳምና ሔዋን የሚኖሩት በዔድን ገነት ነበር። የሚያስፈልጓቸው ነገሮች ሁሉ ነበሯቸው። እግዚአብሔር ወዳጃቸው ነበር። እግዚአብሔር ስለሚወዳቸው በጣም ደስተኞች ነበሩ።

ትልቁን የእግዚአብሔርን ጠላት ሰይጣንን ታስታውሱታላችሁን? ሰይጣን፥ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ተመልክቶ ነበር። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን እንደሚወድ ያውቅ ነበር። እግዚአብሔር፥ አዳምን በምድር እና በውስጧ ባለው ሁሉ ላይ ገዥ አድርጐ ሲሾመው ሰይጣን ተመልክቶ ነበር። መልካምንና ክፉውን ስለሚያሳውቀው የእውቀት ዛፍ እግዚአብሔር ለአዳም የሰጠውን ማስጠንቀቂያ ሰይጣን ያውቅ ነበር። ሰይጣን፥ እግዚአብሔርን ስለሚጠላ እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ወንድና ሴት ለማጥፋት ፈለገ፤ ስለዚህ ሰይጣን፥ አዳምና ሔዋንን ለማጥፋት ሊያታልላቸውና ሊፈትናቸው ዐቀደ።

ዘፍጥረት 3፡1 አንብብ። ይህ ከሔዋን ጋር ንግግር የሚያደርግ እባብ ብቻውን አልነበረም። ሰይጣን እራሱን ለውጦ ለማቅረብና ሔዋንን ለማታለል በእባቢቱ ውስጥ ገባ። ሰይጣን እባቢቱን የመረጠው ሔዋን ከሌሎች እንስሳት ይልቅ ልትሰማ የምትችለው እባብን ስለሆነ ይሆናል። እባብ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ የላቀ ቅልጥፍና ነበራት።

በእባቢቱ ውስጥ ሆኖ የሚናገረው እርሱ መሆኑን ሔዋን እንድታውቅ ሰይጣን አልፈቀደም ነበር። ዛሬም ቢሆን የሚያደርገው እንደዚሁ ነው። የእግዚአብሔርን መጽሐፍ የበለጠ ባወቅህ ቁጥር

ሰይጣን ምን ያህል አታላይና ክፉ እንደሆነ እየተገነዘብህ ትሄዳለህ። ሰይጣን፥ እራሱን ለውጦና ደብቆ ሰዎችን ሊያጠምዳቸውና ሊያጠፋቸው እንደመጣ እንዳይረዱ ያደርጋቸዋል።

ርግቦችን ወይም ጥንችሎችን ለመያዝ በምትፈልጉበት ጊዜ ርግቧና ጥንቸሎቹ ወጥመዱን እንዲያዩና በርግገው እንዲሸሹ ታደርጋላችሁን? አታደርጉም። ወጥመዱን ሳይሆን ምግቡን ብቻ እንዲያዩ ታደርጋላችሁ። አይደለም?

ሰይጣን እንስሳትን አያጠምድም። ደግሞም እኛ በምናደርገው ዓይነት ወጥመድ አይጠቀምም። ከሔዋን ጋር እንዳደረገው ንግግር ዛሬ በእባብ በኩል ወይም በሌሎች እንስሳት በኩል አይናገርም፤ ነገር ግን ሔዋን እባቢቱ ስትናገር ማን ይናገራት እንደ ነበር እንዳላወቀች ሁሉ፥ አሁንም እራሱን ለውጦ በማቅረብ እንዲሁ ያደርጋል። እርሱ እንደሚናገር እንዳያውቁ እራሱን ከአባቶቻችሁ እንደሰወረ፥ አሁንም እራሱን በመደበቅና ለውጦ በማቅረብ በዓለም ላይ ያሉ ሕዝቦችን በሙሉ በወጥመዱ በመክተት ሊያጠፋቸው ይሞክራል።

ሰይጣን፥ ብዙ ጊዜ ለሰዎች አእምሮ ውሸት በመናገር ሕዝቡን ያጠምዳቸዋል። ሰይጣን፥ ለሕዝቡ ለመናገር ወደሰዎች በሚመጣበት ጊዜ የሚናገረው እርሱ እንደሆነ ሰዎች እንዲያውቁ አያደርግም። በአእምሮአቸው ያለው አሳብ የራሳቸው እንደሆነ ያስባሉ፤ ነገር ግን ያንን አሳብ ወደ አእምሮአቸው የሚያመጣው ሰይጣን ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በምታዳምጡበት ጊዜ እንኳ ሰይጣን ይነግራችኋል። በአእምሮአችሁ ውስጥ «መጽሐፍ ቅዱስን ማመን ያለብኝ ለምንድን ነው?» የሚለውንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በመጫር ከጥርጣሬ ላይ ይጥላችኋል።

በተጨማሪ ሰይጣን በሌሎች ሰዎች በመጠቀም እግዚአብሔር በመጽሐፉ ከነገረን እውነት ዞር እንድንል ሊያደርገን ይሞክራል። ምናልባት አንድ ሰው የሚከተለውንና ሌሎችንም የመሳሰሉ ጥያቄዎች ሊጠይቀን ይችላል። «ወንጌላዊያን የሚነግሩህ እውነት መሆኑን እንዴት ታውቃለህ? መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ለመሆኑ እርግጠኛ ነህን?» ሌሎቹ ደግሞ «የምንሰማው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት

የወንጌላዊያን እምነት ነው፤ ስለዚህ አንፈልገውም፥ እኛ የራሳችን አኗኗርና እምነት አለን።» ሊሉህ ይችላሉ። ተጠንቀቁ! ሰይጣን ባይነቃበትም እንኳ በሰዎች ይጠቀማል። በአእምሮአቸው የጥርጣሬ አሳብን በመጫር፥ በአፋቸው የክህደት ቃልን በማናገር በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ የሚገኘውን እውነት እንዳትሰሙ ሊያደርግ ይጥራል።

ሰይጣን፥ በእግዚአብሔር ላይ ባደረገው ዓመፃ ተባባሪ በነበሩትና አሁን በዓለም ዙሪያ ባሉት በወደቁት መላእክት (መናፍስት) አማካይነት ይናገራል። አባቶቻችሁ ይመስላቸው እንደ ነበረ አሁን ለእናንተ የሚናገሯችሁ የዛፎች መናፍስት እንደሆኑ ታስባላችሁ፤ ነገር ግን የዛፍ መንፈስ ማን ነው? የሰይጣን መልአክ ነው። ሰይጣን በእነዚህ መናፍስት በመጠቀም ውሸቱን እየተናገረ የእግዚአብሔርን ቃል ከማመን እንድትታቀቡ ለማድረግ ይጥራል።

ሰይጣን፥ በተለያዩ ስፍራ የሚኖሩ ሰዎችን እንዲያምኑ በሚያስተምራቸው ትምህርቶቹ ያጠምዳቸዋል። ሰይጣን፥ ማንም ሰው በእግዚአብሔርና በእውነት እንዲያምን አይፈልግም። የእግዚአብሔርን ቃል እንድታምኑ አይፈልግም። ተጠንቀቁ! ሐዋንን እንዳጠመደ ሊያጠምዳችሁ ይሞክራል። ሰይጣን ብልህና አታላይ ነው። እራሱን በመደበቅና ለውጦ በማቅረብ ያታልላል።

መምህር ሆይ፡- በማያስፈልጉ በርካታና ዝርዝር ጥያቄዎች በመዋከብ ወደ ኋላ አትመለስ። ለምሳሌ «እንስሳት በመጀመሪያ ይነጋገሩ ነበርን?» የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። ሆኖም መልሱን ስለማናውቀው እንዳለ ልንተወው ያስፈልጋል።

አዳማጮችህ ሰይጣን፥ አታላይ መሆኑን ሊረዱ ይገባል። ይህን ከተረዱ ባለፉት ብዙ መቶ ዓመታት ውስጥ ሰይጣን አባቶቻቸውን ውሸት እየተናገረ እንዳታለላቸው ይገነዘባሉ።

እውነት የሚገኘው በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ እንደ ሆነና የእነርሱ ሃይማኖታዊ እምነቶች የሰይጣን ማጭበርበሪያዎች መሆናቸውን እንዲረዱ ያለማቋረጥ ጸልይ። ሆኖም ይህንን ታረጋግጥላቸው ዘንድ ከሚገባ በላይ ስሜታዊ ሆነህ አትጨነቅ። በቀላሉ የእውነትን ዘሮች ዝራ፥ በሚገባ ውኃ አጠጣቸው፥ በጸሎትና በተጨማሪ የዕድገት ትምህርት ተንከባከባቸው። የሚያሳድግና የሚያበዛ እግዚአብሔር

ስለሆነ በእርሱ ታመን። የአጥፊውን የሰይጣንን ዕቅድ ሙሉ በሙሉ የምትገልጥበት ጊዜ ይመጣል። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ እንዲሠራ ጊዜ በመስጠት በእግዚአብሔር ጊዜ ልንናገር ይገባል።

ማንም ሰው በምንም ነገር ላይ ሳይደገፍ እራሱን ችሎ መኖር እንደማይችል እንዲገነዘቡ ያሻል። ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ወይም በሰይጣን ጭቆና ሥር ናቸው። ሰው ቁሳዊ፥ ሰብአዊና እንዲሁም መንፈሳዊ አካል ሆኖ ተፈጥሯል፤ ስለዚህ የመንፈሳዊና የቁሳዊ ግዛት አካል ነው። ሰው አንድም ‹በዚህ ቁሳዊ ዓለም አምላክ› ቁጥጥር ሥር ይሆናል ወይም የነገሮች ሁሉ ፈጣሪና ባለቤት በሆነው በእውነተኛ አምላክ ይመራል፥ ይተዳደራልም።

ሰይጣን በሕይወታቸው ላይ ሊሠወት የሚችለውን የማታለል ተግባርና በዚህም ሊቀዳጀው ስለሚችለው የበላይነት በማስመልከት የሚከተለውን ታሪክ ንገራቸው።

አንድ ታሪክ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። ይህ ስለእውነተኛ ሰዎች የሚናገር ታሪክ አይደለም፤ ነገር ግን ለእያንዳንዳችሁ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ትርጉም አለው።

ማናቸውም የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ የነበረው አንድ ሃብታም ሰው ነበር። ጥሩ የእርሻ መሬት፥ ጠንካራ ቤት፥ በርካታ የቡና ተክሎችና ከብቶች ነበሩት። በአጭሩ ሰው የሚመኘው ነገር ሁሉ ነበረው፤ ነገር ግን የሚጠላውና ሊያጠፋው ያቀደ ጠላት ነበረው።

አንድ ምሽት ይህ ጠላት በመንገዱ ዳር በቁጥቋጦ ውስጥ ተደበቀ። ሰውዬው ከዚያ በደረሰ ጊዜ ጠላቱ ጥቃት ሰንዝሮ ዓይናቹን በማጥፋት ዕውር አደረገው። በዚህ ምክንያት ሰውዬው ባለው ንብረት መጠቀም ወይም ደስ መሰኘት አልቻለም። ወደ እርሻ መሬቱ ሊወጣና አዝመራውን ለመመልከት አልቻለም። በመሆኑም በጣም አስከፊ ከሆነ የችግር ማጥ ውስጥ ወደቀ።

በዚህ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ከቆየ በኋላ አንድ ቀን ፈራርሶ ሊወድቅ በደረሰ ቤቱ ውስጥ ተቀምጦ እንዳለ፥ ‹ወዳጄ› ብሎ የሚጣራ አንድ ድምፅ ሰማና ፈራ። ማን ይሆን በማለት በመደነቅ ያስብ ጀመር፤

ስለዚህ ወዲያውኑ መልስ አልሰጠም፤ ነገር ግን ድምፁ ባለማቋረጥ መጣራቱን ስለቀጠለ ሰውዬው መልስ ሰጠና ወደ ቤቱ እንዲገባ ጠየቀው።

ይህ እንግዳ ሰው ዕውሩን ሰውዬ ለመርዳት ፍላጎት ነበረው። ከመጠን በላይ ደግ በመሆን የተለያዩ ስጦታዎች አበረከተለት። ደግሞም ገላውን መታጠብ እንዲችል እጁን ይዞ ወደ ወንዝ አመጣው። ቀስ በቀስ ዕውሩ ሰው ሙሉ በሙሉ እንዲታመንበትና እንዲደገፍበት አደረገ። ዕውሩ ሰው ወዳጄና ረዳቴ ነው ብሎ ባመነው በዚህ ሰው የበለጠ እየተደገፈ ሄደ።

ከዕለታት አንድ ቀን ግን ይህ ሰው ለዕውሩ ሰውዬ እንዲህ አለው። «ዛሬ ረጅም መንገድ እንሄዳለን።» አነጋገሩ ለስለስ ያለና የወዳጅነት ሁኔታ የተገለጠበት ስለ ነበር፥ ዕውሩ ሰው እጁን ሰጥቶት በሚመራው መንገድ ይከተለው ጀመር።

ይህ «ወዳጅ» ዕውሩን ሰው በጫካ ውስጥ ይመራው ጀመር፤ ነገር ግን አንድ ስፍራ ላይ ደርሰው የሚቀጥለውን እርምጃ ለመራመድ ዕውሩ ሰው እግሩን ሲሰነዝር «ወዳጅ» የተባለው ሰው እጁን በፍጥነት መንጭቆ አላቀቀ። ከዕውሩ ሰው እግሮች በታች ምንም አልነበረም። ከገደል አፋፍ እየወደቀ መሆኑ እንደተሰማው ወዲያዉኑ፥ ከአናቱ የሳቅና የፌዝ ድምፅ ተሰማው። ልክ ወድቆ ተከስክሶ ከመሞቱ በፊት ይህ የፌዝና የሳቅ ድምፅ ዓይኑን ያሳወረው የጠላቱ ድምፅ መሆኑን ተገነዘበ።

ሰይጣን፥ በአባቶቻችሁ ላይ ያደረገው ይህን ዓይነት ማታለል ነው። ሰይጣን ሰብአዊ ዓይናቸውን ሳይሆን አእምሮአቸውን በማሳወር እግዚአብሔርን ለማወቅና ለመረዳት እንዳይችሉ አደረጋቸው። ሰይጣን አታልሎ እንዲታመኑበት አሳባቸውን ሰረቃቸው። አገልጋዮቹ በሆኑት መናፍስት የአባቶቻችሁን መላ ሕይወት መቆጣጠር ጀመረ። በርካታ ነገሮች እንደሚያደርግላቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር። ለእናንተም ዛሬ በርካታ ቃል ኪዳኖች ይገባል። አንዳንድ ጊዜ ችግር ሲገጥማችሁና ስትታመሙ ጥሪ በምታደርጉለት ጊዜ ጥሪያችሁን ለመመለስ ይመጣል፤ ነገር ግን እናንተን የሚረዳበት ብቸኛ ምክንያት በዚህ

ምድር በሥልጣኑ ሥር ሊያቆያችሁ ስለሚፈልግ ነው። በመጨረሻ ለእርሱ ወደተዘጋጀው ዘላለማዊ የቅጣት ቦታ እንደምትሄዱ ያውቃል።

ሰይጣን፥ ሰዎች ሁሉ በእርሱ ቁጥጥር ሥር ሆነው እንዲጠፉ ስለሚፈልግ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት በማይፈልጉበት ጊዜ በጣም ደስ ይለዋል።

መምህር ሆይ፡- ሰይጣን በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚሠራቸውን ኃይለኛ ነገሮች ለመካድ አንችልም። ይህንን የሚጠቀምበት ለራሱ ዓላማና በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን ሰውን ለማጥፋት ነው። መናፍስት ይሠሩልናል ብለው የሚያስቧቸው መልካም ሥራዎች ሁሉ፥ ሰይጣን ሊያታልላቸውና የመጨረሻ ጥፋታቸውን ለማምጣት ብቻ የሚሠራቸው እንደሆኑ ግልጽ አድርግላቸው።

ለ. ሰይጣን ሔዋንን ተፈታትኖ አታለላት።

ዋና አሳብ፡- ሰይጣን እግዚአብሔርንና ፈቃዱን ይዋጋል። እርሱ ውሸታምና አታላይ ነው። ሰውን ይጠላል።

ዘፍጥረት 3፡1 አንብብ። ሰይጣን ትክክለኛውን መልስ እያወቀ ሔዋንን ይህን ጥያቄ ጠየቃት። ሊያጭበረብራት ይችል ዘንድ ተፈታተናት። እግዚአብሔር ስለተናገረው ነገር ግድ አልነበረውም።

ዘፍጥረት 3፡2፥ 3። እግዚአብሔር ፍሬውን እንዳትበሉ እንጂ እንዳትነኩ አላላቸውም። እግዚአብሔር ይህን ትእዛዝ ለአዳም እንጂ ለሔዋን አልሰጠም። እግዚአብሔር የተናገረውን ለሔዋን የነገረው አዳም ነበር። እግዚአብሔር ይህን ትእዛዝ በቀጥታ ለሔዋን ባይሰጥም እንኳ ትእዛዙ እርሷንም ይጨምር ነበር። እግዚአብሔር ለአዳም ያለው ሁሉ ሔዋንንም ይመለከት ነበር።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ቃሎች የተነገሩት ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ስለነበሩ ሰዎች ነው፤ ነገር ግን ዛሬም ለእያንዳንዳችን ከእግዚአብሔር የተሰጡን ቃሎች ናቸው። እግዚአብሔር ለተለያዩ ሰዎች የተለያዩ መልእክቶች የሉትም። መልእክቱ ለሁላችንም አንድ ዓይነት ነው። ለጥቁሮች፥ ለነጮች፥ ለወንዶች ለሴቶች እና ለልጆች ለሁሉም ያው ነው።

ለእኔ በቃሉ ያለው ሁሉ ለእናንተም ነው።

ዘፍጥረት 3፡4፥ 5 አንብብ። ሰይጣን፥ እግዚአብሔር ለአዳም የተናገረውን በተቃራኒ ተናገረ። ሰይጣን፥ እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እውነት አይደለም አለ። ይህ እግዚአብሔርን ውሸታም ብሎ እንደመጥራት ያህል ነው። እግዚአብሔር ለአዳም ያለው መልካምንና ክፉውን ከምታሳውቀው ከዚህች ዛፍ ፍሬ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ ነበር። ይህ ማለት አዳምና ሔዋን ሕይወትን ከሰጣቸው ከእግዚአብሔር ይቆራረጣሉ (ይለያሉ) ማለት ነበር። እግዚአብሔር ሞትን ትሞታላችሁ አለ። ሰይጣን ደግሞ «አትሞቱም» አለ። እውነት የተናገረው ማን ይመሳልችኋል? እግዚአብሔር ወይስ ሰይጣን?

መምህር ሆይ፡- የሰውን ያለመታዘዝና የእግዚአብሔርን ቅጽበታዊ የሞት ፍርድ እስካሁን ያልተናገርከ ቢሆንም፥ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ፍቀድላቸው። የዋሸው ሰይጣን ነው የሚል መልስ ከሰጡ የእግዚአብሔር ቃል ሥር እየሰደደ ስለሆነ እግዚአብሔርን ልታመሰግን ትችላለህ።

ሰይጣን ኃጢአትን ያደረገው የእግዚአብሔርን ሥልጣን ለመውሰድ በመፈለጉ ነበር። ሰይጣን እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ከዚህ በኋላ ፈቃደኛ አልነበረም። ከእግዚአብሔር ተለይቶና እራሱን ችሎ የራሱን ሕይወት ለመምራት ፈለገ። ሰይጣን፥ ሔዋን እንድታደርግ አሳብ የሚያቀርብላት ይህንን ነበር። ሰይጣን፥ ለሔዋን ያቀረበው አሳብ ፍሬውን እንድትበላና ከእግዚአብሔር ጋር እኩል እንድትሆን፥ በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር ትክክል የሆነውንና ያልሆነውን እንዲነግራት በማያስፈልግ ሁኔታ እንድትኖር ነበር።

እግዚአብሔር ግን ሰዎች በራሳቸው አሳብና እውቀት እንዲኖሩ አይፈልግም ነበር። እግዚአብሔር በቃሉ እንድንመራ አድርጐ ፈጥሮናል። እኔ፥ እናንተና ሌሎች የምናስበው ወይም ሰይጣንና መናፍስት የሚናገሩት ምንም ፍሬ ነገር ወይም ለውጥ አያስገኝም። ወሳኙ ነገር እግዚአብሔር የሚለው ብቻ ነው።

ሐ. ሔዋን ፍሬውን በላች፥ ለአዳምም ሰጠችው።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። እግዚአብሔር የሚያስፈልገውና እራሱን ለማዳን ጨርሶ የማይችል ነው።

ዘፍጥረት 3፡6 አንብብ። ሰይጣን፥ ሔዋንን አታለላት፤ እርሷም አመነችው። ሰይጣን የተናገረው እውነት እንደሆነ በማመን እንደ እግዚአብሔር እንደምትሆን አሰበች። አዳም እግዚአብሔር ይህን ፍሬ እንዳይበሉ እንዳዘዛቸው እያወቀ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጣሰ። አዳም በእግዚአብሔር ከመታመን ወደ ኋላ አለ። ከእግዚአብሔር ተለይቶ በራሱ ብቻ ለመኖር ሞከረ። ክፉውንና ደጉን ለእራሱ ለመወሰን መረጠ። በአዳም ልብ የመጀመሪያው ተቀዳሚው እግዚአብሔር መሆኑ ቀረና እራሱ አዳም ሆነ። የራሱ አለቃ በመሆን የሚፈልገውን ለማድረግ መረጠ። ከዚህ በኋላ የሕይወቱ ገዥ እግዚአብሔር እንዳይሆን ወሰነ።

እግዚአብሔር በአዳም ላይ ገዥ የመሆን መብት ነበረውን? አዎን የፈጠረው እግዚአብሔር ነው። የነበረው ሁሉ ከእግዚአብሔር የተገኘ ነበር። እግዚአብሔር፥ ማድረግ ያለብንን ሊነግረን መብት አለውን? አዎን። ያለን ሁሉ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ነው። ሕይወት የሰጠን እርሱ ነው።

መ. የአዳምና ሔዋን ኃጢአት ቅጽበታዊ ውጤት።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ዘፍጥረት 3፡7፥ 8 አንብብ። እግዚአብሔር፥ መልካምንና ክፉውን የምታሳውቀውን ዛፍ ከበሉ ምን ይሆናሉ ብሎ ተናገረ?

እግዚአብሔር «ሞትን ትሞታላችሁ» ሲል ምን ማለቱ ነበር? ፍሬውን እንደበሉ ወዲያውኑ አልሞቱም። ገና በሕይወት እየተመላለሱ ነበር። ኃፍረተ ሥጋቸውን ቅጠል በማገልደም ሸፈኑ። ይህ ማለት የእግዚአብሔር ቃል አልተፈጸመም ማለት ነበርን? ሰይጣን ያደረገው ትክክል ነበር ማለት ነውን?

አልነበረም! ፍሬውን እንደበሉ ወዲያውኑ ከእግዚአብሔር ተለይተዋል። እግዚአብሔር ሁልጊዜ የተናገረውን ይፈጽማል። ፈጽሞ አይለወጥም። ትእዛዙን የሚጥሱ ሁሉ እንደሚቀጡ የተናገረውን አይረሳም።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ጻድቅና ቅዱስ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ስለሆነ ትእዛዙን ከሚጥሱ ጋር ወዳጅነቱን አይቀጥልም። ክፉ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ይጠላል። ትእዛዙን የሚጥሱትን ሁሉ በሞት ይቀጣል። አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ስላልታዘዙ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው የወዳጅነት ግንኙነት ተቋረጠ። ከእግዚአብሔር ጋር በአንድነት መቀጠላቸው ተቋረጠ። ከእግዚአብሔር ታላቅ ጠላት ከሰይጣን ጋር በመተባበራቸው የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆኑ።

የእናንተ ጓደኛ የነበረ አንድ ሰው እናንተን ክዶ የሚጠላችሁንና ሊገድላችሁ የሚፈልገውን ጠላት ቢከተል፥ ይህ ወዳጃችሁ የነበረው ሰው ጠላታችሁ አይሆንምን?

ሰይጣን የእግዚአብሔር ትልቁ ጠላት ነው። አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ከደው ሰይጣንን በመከተል የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆኑ።

ከዛፍ ላይ የቆረጥኩትን ይህን ቅርንጫፍ ታስታውሳላችሁን? ሕይወትን ያገኘበት ከነበረው ዛፍ ተቆርጧል። ቅጠሎቹ ግን ልክ ቅርንጫፉ እንደተቆረጠ አልሞቱም። ለመሞት ብዙ ቀናት ወሰደባቸው። አሁን ግን ሞተዋል።

በአዳምና ሔዋን የሆነው ይህ ነበር። የእግዚአብሔርን ሕግ በጣሱበት ዕለት በሥጋ አልሞቱም። እየተነፈሱ በአካባቢው እየተዘዋወሩ ነበር። ለእግዚአብሔር ግን ሞተው ነበር። እግዚአብሔርን ማወቅ፥ መውደድና መታዘዝ እንዲችሉ የሚያደርጋቸው፥ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩበት የሕልውናቸው ክፍል የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሲጥሱ ወዲያውኑ ከእግዚአብሔር ተለየ። ከእግዚአብሔር በመለየታቸው የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆኑ። በመጨረሻም ሥጋቸው ይሞትና እግዚአብሔር ለሰይጣንና ለክፉ መናፍስት ወደ አዘጋጀው ስፍራ ለዘላለም ቅጣት ይሄዳሉ።

ከእግዚአብሔር የመለየታቸው ምልክቶች የሚከተሉት ነበሩ፡-

በመጀመሪያ ደረጃ፥ ስለ ሥጋዊ አካላቸው የነበራቸው ግንዛቤ ወዲያውኑ ተቀየረ። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከመጣሳቸው በፊት ራቁታቸውን ነበሩ፤ አይተፋፈሩም ነበር። አሁን ግን ከእግዚአብሔር በመለየታቸው አእምሮአቸው በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር አልነበረም። አእምሮአቸው ክፉ ሆነ። ለሥጋዊ አካላቸው ያላቸው ዝንባሌ ተለወጠ። ዕርቃናቸውን በመሆናቸው ተፋፈሩ።

በሁለተኛ ደረጃ፥ የራሳቸውን ፍላጐት በራሳቸው ለማሟላት ጣሩ። ከእግዚአብሔር ከመለየታቸው በፊት የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ እንዲያዘጋጅላቸው ወደ እግዚአብሔር ይመለከቱ ነበር፤ አሁን ግን ለራሳቸው የሚሆን ነገር ለመሥራት ጣሩ። ኃፍረተ ሥጋቸውን ለመሸፈን ቅጠል አገለደሙ። የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ ለማግኘት በእግዚአብሔር መታመናቸውን አቆሙ። ከእግዚአብሔር ተለይተው እራሳቸውን በመርዳት ለመኖር መጣር ጀመሩ።

በሦስተኛ ደረጃ፥ እግዚአብሔር፥ አዳምና ሔዋንን ለመጐብኘት ሲመጣ ከእርሱ ለመደበቅ ሞከሩ።

ዋና አሳብ፡ - እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ መሐሪና ጸጋ የተሞላ ነው።

እነርሱን መጠየቅ እጅግ ደስ የሚያሰኛችሁ ወዳጆች አሏችሁን? እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ይወድ ስለ ነበረ በቀኑ መጨረሻ ከእነርሱ ጋር ለመነጋገር መጣ።

ከእግዚአብሔር ከመለየታቸው በፊት ይወዱት ስለ ነበር ከእርሱ ጋር ለመነጋገር ይፈልጉ ነበር። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከጣሱ በኋላ ግን እግዚአብሔር ወደ እነርሱ ሲመጣ አዳምና ሔዋን ተደበቁ። ለእግዚአብሔር የነበራቸው ዝንባሌ ተለውጦ ነበር። እግዚአብሔር በመጀመሪያ አዳምና ሔዋንን ሲፈጥር ከእግዚአብሔር ጋር አንድ አእምሮ ነበራቸው። አሁን ግን አእምሮአቸው የተለየ ነበር። የአሁኑ አእምሮአቸው ከሰይጣን ጋር አንድ ዓይነት ነበር። እግዚአብሔርን ማወቅና መረዳት የማይችሉበት ደረጃ ነበር። ለእግዚአብሔር የነበራቸው ፍቅር ተቋርጦ ነበር። በሰይጣን ቁጥጥር ሥር ሆነው ነበር። አሁን የሰይጣን ደጋፊ ሆነዋል።

እግዚአብሔርን ስላልታዘዙ አፍረው እግዚአብሔርን ተደበቁ፤ ደግሞም ፈሩ።

ልጆቻችሁ አውቀው (ሆን ብለው) ትእዛዛችሁን ሲጥሱ አጠገባችሁ መሆን ይፈልጋሉን? ዓይናችሁን ማየት ይደፍራሉን? በእናንተ ፊት ለመሆን ይደሰታሉን? ሁለት ጓደኛሞች ቢጣሉ በአንድነት ሆነው ቡና ሊጠጡ ይችላሉን? ከመጣላታቸው በፊት እንደነበሩት በአንድነት ሊስቁና ሊነጋገሩ ይችላሉን? አይችሉም። የተለያዩ አመለካከቶችና ዝንባሌዎች ያላቸው ሰዎችና እርስ በርስ የሚያከራክር ጉዳይ ያላቸው ሰዎች በአንድነት መቀጠል አይፈልጉም።

ኃጢአትና እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ ፍርሃትን ያመጣል። ሰዎችም ከእግዚአብሔር መንገድ እንዲመለሱ ያደርጋል።

እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ሲፈጥር ምንም ነገር አይፈሩም ነበር። በዓለም ላይ የሚፈሩት አንዳችም ነገር አልነበረም። እግዚአብሔር ወዳጃቸው ነበር። የትኞቹም እንስሳት አይጐዷቸውም ነበር። ዓለም ሁሉ መልካምና ውብ ነበር። በሽታና ሞት አልነበሩም።

በዓለም ላይ ፍርሃት የመኖሩ ምክንያት እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ ነው። አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከጣሱበት ወቅት ጀምሮ በወንዶችና በሴቶች ልብ አሰቃቂ ፍርሃት ተፈጠረ። ብዙ የምትፈሯቸው ነገሮች አሉ አይደለም? እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን በፈጠረ ጊዜ ያልፈሯቸው የነበሩ፥ ዛሬ ግን እናንተ የምትፈሩአቸውን ነገሮች ንገሩኝ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ሊፈሩት ይገባል ብላችሁ ታስባላችሁን? እግዚአብሔር ላለመታዘዛቸው በእርግጥ እየቀጣቸው ነበርን? ወይስ እግዚአብሔር እንደ ብዙ ሰዎች ዛቻ እያደረገ ነበር? አንዳንድ ሰዎች እጅግ በሚቆጡበት ጊዜ ሰውን ለመግደል ይዝቱ ይሆናል። ኋላ ቁጣቸው ሲበርድላቸው ግን ምንም ነገር አያደርጉም። የተናገሩት ነገር መና ሆኖ ይቀራል። እግዚአብሔርስ እንደነዚያ ዓይነት ሰዎች እንደሆነ ታስባለህን? ሳጥናኤልና መላእክቱ በእግዚአብሔር ላይ ባመፁበት ጊዜ እግዚአብሔር ባዶ ዛቻ ዛተባቸውን?

አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን የሚፈሩበት በቂ ምክንያት ነበራቸው። እርሱ ፈጣሪያቸው ሆኖ ሳለ እነርሱ ግን ትእዛዙን ጥሰው ነበር። ለማንኛውም ነገር የሚታመኑት በእግዚአብሔር ነበር። በአካሎቻቸው ውስጥ ያለውን እስትንፋስ የሰጣቸው እግዚአብሔር ነበር። የነበራቸው ሁሉ በእግዚአብሔር የተሰጣቸው ሆኖ ሳለ፥ አዳም ሆን ብሎ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጣሰ። እግዚአብሔር ከትእዛዛቱ የትኛውንም የሚጥሱትን ሁሉ ሁልጊዜ ይቀጣል።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ከእግዚአብሔር ሊደበቅ የሚችል አለን? የለም! አዳምና ሔዋን በዛፎች መካከል ለመደበቅ በሚሞክሩበት ጊዜ እንኳ እግዚአብሔር ያያቸው ነበር። እግዚአብሔር የሌለበት ለመደበቅ ልንሄድበት የምንችልበት ስፍራ አለን? እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ይገኛል። ከእርሱ ለመደበቅ የሚችል ማንም የለም። ለእርሱ ጨለማና ብርሃን ያው ናቸው።

ሰዎች ትክክል እንዳልሆነ የሚያውቁትን ነገር ሲሠሩ ብዙ ጊዜ ተደብቀው ያደርጉታል። ሰዎች ክፉ ነገር የሚያደርጉት በጨለማ ወይም በጫካ ውስጥ ነው። እግዚአብሔር ግን ሁልጊዜ ማንኛውንም ነገር ያያል፥ ደግሞም ይሰማል። ከእግዚአብሔር ሊሰወር የሚችል አንዳችም ነገር የለም።

እግዚአብሔር ከተወለዳችሁበት ጊዜ ጀምሮ የሠራችሁትንና የተናገራችሁትን ሁሉ አይቷል ሰምቷልም።

ሠ. ሰይጣን አዳምና ሔዋንን በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምፁ ያደረገበት ምክንያቶች።

ዋና አሳብ፡- ሰይጣን እግዚአብሔርንና ፈቃዱን ይዋጋል። ሰይጣን ዋሾና አታላይ ነው። ሰውን ይጠላል።

ሰይጣን የተፈጠረው በእግዚአብሔር ነበር፤ ነገር ግን ታበየና የእግዚአብሔርን የሥልጣን ስፍራ ተመኘ። እግዚአብሔር፥ ሰይጣንን ከመንግሥተ ሰማያት አባረረው። ሰይጣን እስካሁን ድረስ እግዚአብሔርን ይጠላል። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለውን ዕቅድ

ለማሰናከል የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል። ሰይጣን ቀንና ሌሊት እግዚአብሔርን ይዋጋል።

ሰይጣን የሚጠላው እግዚአብሔርን ብቻ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ለክብሩ የፈጠረውን የሰውን ልጅ ጭምር ነው። እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው እርሱን እንዲያውቅ፥ እንዲወድና እንዲታዘዝ ስለሆነ ሰይጣንና የተከተሉት መናፍስት ሰዎችን ሁሉ ይጠላሉ።

ሰይጣን የሰው ልጆችን በሙሉ ስለሚጠላ እግዚአብሔር ለእርሱና ለመናፍስቱ ወደ አዘጋጀው የዘላለም ቅጣት ቦታ አብረውት እንዲሄዱ ይፈልጋል። ሰይጣን ማንም ሰው የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰማ አይፈልግም። የእግዚአብሔርን መጽሐፍ እንድትሰሙ፥ እንድትገነዘቡና እንድታምኑ አይፈልግም።

ረ. ማጠቃለያ

ሰይጣን አዳምና ሔዋንን በመፈተን እግዚአብሔርን እንዳይታዘዙ ካደረገበት ታሪክ ውስጥ በርካታ ነገሮች መማር አለብን።

ልንማረው የሚገባው ተቀዳሚው ነገር እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሚናገረው እውነት መሆኑን ነው። አስቀድሞ እንደተናገረ አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ተለዩ። በኃጢአታቸው ምክንያት ከእርሱ ወዲያውኑ ተለዩ።

ሁልጊዜ እውነትን ከሚናገረው ከእግዚአብሔር በተጻራሪ ሰይጣን ውሸታም ነው። አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ባይታዘዙ አይሞቱም አለ፤ እንደሚሞቱ ግን ያውቅ ነበር።

ሰይጣን ውሸታም ብቻ ሳይሆን ነፍሰ ገዳይ ጭምር ነው። አዳምና ሔዋንን በማታለልና በመዋሸት የፈተናቸው እንዲሞቱ ስለሚፈልግ ነበር።

መምህር ሆይ፡ - ዮሐንስ 8፡44 ተመልከት

ሰይጣን ዛሬም ቢሆን ያው ነውና ተጠንቀቁ! ከእግዚአብሔር ለዘላለም እንድትለዩ ስለሚፈልግ የእግዚአብሔርን ቃል እንድትሰሙ አይፈልግም።

ጥያቄዎች

1. ሰይጣን፥ ሔዋንን ሊያታልል በመጣ ጊዜ ማንነቱ እንዳይታወቅ ያነጋገራት ፊት ለፊት ቀርቦ ነበርን? አልነበረም።

2. ሰይጣን፥ ሔዋንን ባነጋገረ ጊዜ እራሱን ለውጦ ለማቅረብ የተጠቀመው በምን ነበር? በእባቢቱ።

3. እግዚአብሔር፥ አዳምና ሔዋንን መልካምንና ክፉውን ከምታሳውቀው ዛፍ ፍሬ በበሉ ጊዜ እንደሚሞቱ ነገራቸው፤ ሰይጣን ግን ለሔዋን አትሞቱም አላት። ይህን ሲል ስለ እግዚአብሔር ምን ማለቱ ነበር? እግዚአብሔርን ውሸታም ነው ማለቱ ነበር።

4. ሰይጣን፥ ለሔዋን ከዚህ ፍሬ በበላችሁ ጊዜ ምን ትሆናላችሁ አላት? አትሞቱም፤ ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ፥ መልካሙንና ክፉውን ለራሳችሁ ለይታችሁ ታውቃላችሁ አላት።

5. ሰይጣን ዛሬም ቢሆን ሊያታልለንና ተንኰል ሊሠራብን ይችላልን? አዎን።

6. ሰይጣን፥ ዛሬ የሚናገረን እንዴት ነው?

   ሀ. ለአእምሮአችን ይናገራል።

   ለ. በሌሎች ሰዎች ይናገራል።

   ሐ. በመናፍስት ይናገራል።

7. ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል እንድትሰሙ እና እንድታምኑ ይፈልጋልን? አይፈልግም።

8. ሰይጣን፥ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዳይሰሙ እና እንዳያምኑ የሚፈልገው ለምንድን ነው?

   ሀ. እግዚአብሔርን ስለሚጠላ ነው።

   ለ. ሰዎችን ሁሉ ስለሚጠላና ወደ ዘላለማዊ እሳት እንዲሄዱ ስለሚፈልግ ነው።

9. እግዚአብሔር፥ መልካሙንና ክፉውን ከሚያሳውቀው ፍሬ አዳምና ሔዋን ከበሉ ሞትን እንደሚሞቱ ተናገረ። ሰይጣን ግን አትሞቱም አለ። እውነትን የተናገረው ማን ነበር? እግዚአብሔር ነበር።

10. አዳምና ሔዋን ራቁታቸውን መሆናቸውን ሲያውቁ ምን አደረጉ? ቅጠል ለራሳቸው አገለደሙ።

11. አዳምና ሔዋን እግዚአብሔር ሊያያቸው እንደመጣ በሰሙ ጊዜ ምን አደረጉ? ተደበቁ።

12. ከእግዚአብሔር መደበቅ ይችላልን? አይቻልም። እርሱ በሁሉም ስፍራ ይገኛል።

ትምህርት 12

የትምህርት ክፍል፡- ዘፍጥረት 3፡9-20

አጠቃላይ ርእስ፡- የእግዚአብሔር የተስፋ ቃልና እርግማን።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. እግዚአብሔር አዳምን ጠራው (3፡9)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ሲያደርግ።

ለ. አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ለመደበቅ ሞከሩ (3፡10)።

ሐ. እግዚአብሔር አዳምን ጠየቀው (3፡11)።

መ. አዳምና ሔዋን ጥፋቱን ወደ ሌላው አካል ለማስተላለፍ ሞከሩ (3፡12፥13)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። እራሱን ለማዳን ምንም ኃይል ስለሌለው እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሠ. እግዚአብሔር እባቢቱን ረገማት (3፡14)።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ረ. ከሴቲቱ ዘር የሚመጣው ተስፋ (3፡15)።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ መሐሪና ጸጋን የተሞላ ነው።

ሰ. የእግዚአብሔር እርግማን በሴቲቱ ላይ (3፡16)።

ሸ. የእግዚአብሔር እርግማን በወንዱና በምድር ላይ (3፡17-19)።

ቀ. አዳምና ሔዋን የሰዎች ሁሉ ወላጆች ናቸው (3፡20)።

የትምህርት 11 ጥያቄዎችን ከልስ።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

ሀ. እግዚአብሔር አዳምን ጠራው

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ሲያደርግ

ዘፍጥረት 3:9 አንብብ። አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር ስላልመጡ እግዚአብሔር አዳምን «አዳም፥ ወዴት ነህ?» በማለት ተጣራ፥ እግዚአብሔር የተጣራው ለምን ነበር? የት እንደተደበቁ አያውቅም ነበርን? በሁሉም ስፍራ አለ አይደለምን? ከተደበቁበት ዛፎች አጠገብ አልነበረምን? ሁልጊዜ ያያቸው አልነበረምን? አዎን እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን በተደበቁበት ስፍራ ሊያያቸው ይችል ነበር። ታዲያ እግዚአብሔር አዳምን የጠራው ለምን ነበር?

እግዚአብሔር ለኃጢአታቸው ቅጣትን ሊፈጽምባቸው ያሰበ ቢሆንም፥ አዳምን የጠራው ይወዳቸው ስለነበረ ነው። በእርሱ ምትክ ሰይጣንን በማመናቸው መሳሳታቸውን አምነው እንዲቀበሉና እግዚአብሔር የነገራቸው እውነት እንደሆነ እንዲስማሙ ይፈልግ ነበር።

እግዚአብሔር አልተለወጠም፤ እንደ አዳም ድምፁን ለመስማት ባንችልም እንኳ ዛሬም ይጠራናል። እግዚአብሔር ዛሬ የሚጠራን እንዴት ነው?

እግዚአብሔር ዛሬ የሚጠራን በዙሪያችን ልናያቸው በምንችላቸው ነገሮች ሁሉ ነው። በየዕለቱ የእግዚአብሔር ድምፅ እንዲህ ይለናል «አድምጡኝ። እኔ የሁሉ ነገር ፈጣሪ ነኝ። እኔ እውነተኛ አምላክ ነኝ። ሁሉን ነገር አውቃለሁ። ሁሉን ቻይ ነኝ። ለእናንተ ያዘጋጀሁላችሁን ምግቦች ሁሉ ተመልከቱ። እወድአችኋለሁ። እኔን አድምጡኝ ፈልጉኝም።» በዚህ ዓለም ያሉትን ነገሮች ሁሉና በሰማይ ያሉትን ነገሮች ስትመለከቱ እግዚአብሔር እየጠራችሁ መሆኑንና እንድትሰሙት እንደሚፈልግ አስታውሱ።

እግዚአብሔር የሚናገረው ግን በፈጠራቸው ነገሮች አማካይነት ብቻ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ደግሞ ይጠራናል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠን መልእክት ነው። የእግዚአብሔርን መልእክት እንድናውቀው፥ እንድንረዳውና እንድንታመንበት በጣም አስፈላጊ ነው።

ለ. አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ለመደበቅ ሞከሩ።

ዘፍጥረት 3፡10 አንብብ። አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን የፈሩት ትእዛዙን ስለጣሱ ነው።

አንድ ሰው፥ ከአንድ የአትክልት ስፍራ የአትክልት ፍሬዎችን እየሰረቀ እያለ፥ የአትክልት ስፍራው ባለቤት ቢደርስበትና ሊያየው የሚችልበት ሁኔታ ቢፈጠር ምን ያደርጋል? አዳምና ሔዋን እንዳደረጉት ይደበቃል።

ሐ. እግዚአብሔር አዳምን ጠየቀው።

ዘፍጥረት 3፡11 አንብብ። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ንስሐ እንዲገቡ ዕድል ሊሰጣቸው፥ ማለትም አሳባቸውን ለውጠው ያደረጉት ነገር ትክክል እንዳልነበረ አምነው እንዲቀበሉና ከእግዚአብሔር ጋር እንዲስማሙ ለማድረግ ጥያቄ ጠየቃቸው።

እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ስለፈጠራቸው ጥያቄ ሊጠይቃቸው ሥልጣንና ኃይል ነበረው።

በሠራችሁት ነገር ላይ የምትፈልጉትን ለማድረግ መብት አላችሁን? የሠራችሁትን ቤት ለሌላ ሰው ልትሸጡት ትችላላችሁን? የሠራችሁትን መሶብ ለሌላ ሰው አሳልፋችሁ ለመስጠት ትችላላችሁን? ከብቶቻችሁን ወደምትፈልጉበት እንዲሄዱ የማድረግ መብት አላችሁን?

እግዚአብሔር አዳምን ከፈጠረ በኋላ ሔዋንን ደግሞ ከአዳም ጐን ከወሰደው አጥንት ፈጠራት፤ ስለዚህ ሁለቱም የእግዚአብሔር ናቸው። የፈጠራቸው እንዲወዱትና እንዲታዘዙት ነበር።

እግዚአብሔር ለእኛና ለሰዎች ሁሉ ደግሞ ሕይወትን ይሰጣል፤ ስለዚህ ባለመብቱ እርሱ ነው። አዳምና ሔዋን ላደረጉት ነገር ለእግዚአብሔር መልስ ሊሰጡ ያስፈልግ እንደ ነበር ሁሉ፥ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ላሰብናቸውና ላደረግናቸው ነገሮች ሁሉ መልስ መስጠት አለብን።

መ. አዳምና ሔዋን ጥፋቱን ወደሌላ አካል ለማስተላለፍ ሞከሩ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። እግዚአብሔር ያስፈልገዋል። አራሱን ለማዳን ኃይል የለውም።

ዘፍ. 3፡12-13 አንብብ። አዳም ለተሠራው ስሕተት ሔዋንን ተጠያቂ ሲያደርግ፥ እርሷ ደግሞ በእባቢቱ አሳበበች። እግዚአብሔር ግን የተፈጸመውን በዝርዝር ያውቅ ነበር። ከእርሱ የተሰወረ አንዳችም ነገር ሊኖር አይችልም።

አንድ ሰው የሠራው ስሕተት ሲታወቅበት ብዙ ጊዜ ለስሕተቱ ተጠያቂ የሚያደርገው ሌላውን አካል ነው። አንዳንድ ጊዜ ጥፋተኛው ሰው ተጠያቂነቱን ምንም ጥፋት ባላጠፋው ላይ በማላከኩ ብቻ፥ ንጹሕ ሰው ያለአግባብ ሲቀጣ እናያለን።

ፍርድ የሚሰጡንን ሰዎች በማታለል እውነተኛ ያልሆነውን ነገር እንዲያምኑን ልናደርጋቸው እንችላለን፤ ነገር ግን ጥፋተኛው ሰው በእርሱ ኃጢአት ሌሎች እንዲቀጡለት እግዚአብሔርን ሊያታልለው ይችላልን? በፍጹም አይችልም! እግዚአብሔር ስለእያንዳንዳችን እውነት የሆነውን ነገር ይመለከታል፤ ያውቃል። ውሸትን እንዲያምን በግድረግ ማንም ሰው እግዚአብሔርን ሊያታልል አይችልም። ሌላውን ሰው በመክሰስ ወይም በሌላው ላይ በማላከክ የእግዚአብሔርን ፍርድ ለማምለጥ አንችልም።

ሠ. የእግዚአብሔር እርግማን በእባቢቱ ላይ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ዘፍ. 3፡14 አንብብ። እግዚአብሔር፥ እባቢቱን የረገማት ሰይጣን ስለተጠቀመባት ነው። እባቢቱ ከዚህ ቀደም ምናልባት እግሮች ወይም ክንፎች ነበሯት። እግዚአብሔር በመጽሐፉ ይህንን አልነገረንም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በመጀመሪያ እባብን ሲፈጥራት በልቧ የምትሳብ ፍጥረት አልነበረችም። አሁን ግን በልቧ የምትሳብ እንድትሆን እግዚአብሔር አዘዘ።

ሔዋንን በእባቢቱ ውስጥ በማደር የፈተናት ሰይጣን እንደሆነ እግዚአብሔር ያውቅ ነበር፤ ሰይጣንና መናፍስቱ የሚያስቡትንና ሊያደርጉ የሚያቅዱትን ሁሉ እግዚአብሔር ያውቃል። ከእግዚአብሔር አንዳችም ነገር ሊሰውሩ አይችሉም። እግዚአብሔር ሁሉንም ይቀጣቸዋል።

ሠ. ከሴቲቱ ዘር የሚመጣው ተስፋ።

አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጥሰው የሰይጣንን ምክር ከተከተሉ ጀምሮ፥ ከእግዚአብሔር ተለይተው በሰይጣን ቁጥጥር ሥር ከሆኑበት ከዚያን ጊዜ አንሥቶ የእግዚአብሔር ልጅ ሊባሉ አልቻሉም። የሰይጣን ልጆች ሆነዋልና ሰይጣን የዚህ ዓለም አምላክ ሆነ።

ሰይጣን፥ እግዚአብሔርን እንዳሸነፈና ዓለምንና ሰዎችን ሁሉ ሙሉ በሙሉ እንደተቆጣጠረ ምናልባት አስቦ ይሆናል፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን ሊያሸንፍ የሚችል ማንም የለም። እርሱ ሉዓላዊ ፈጣሪ ነው። እግዚአብሔር፥ ሰይጣንን የሚያሸንፍና ከእርሱ ኃይል የሰው ልጆችን ሁሉ ነፃ የሚያወጣ ታዳጊ እንደሚልክ ተስፋ ሰጠ። ዘፍጥረት 3፡15 አንብብ።

ይህ ታዳጊ፥ ከድንግል እንደሚወለድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ዐቅዶ ነበር። ይህ ነፃ አውጪ ከሰይጣን ጋር በመዋጋት ድል ይነሣዋል። ሰይጣን ደግሞ ከነፃ አውጪው የእግዚአብሔር ተስፋ ጋር በመዋጋት ያቆስለዋል፤ ነገር ግን ከሥልጣኑ ሊያስወግደው አይችልም ነበር። ይህ የተስፋው አዳኝ ሰይጣንን በመደምሰስ የሰውን ልጅ ነፃ ሊያወጣና ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ጎብረት እንደገና ያድስ ዘንድ የተዘጋጀ ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ቀደም ብለን ስለ እግዚአብሔር በርካታ ነገሮችን ተምረናል። ዘላለማዊ መሆኑን እናውቃለን። መጀመሪያ አልነበረውም። እርሱ ሁሉን ቻይ፥ ሁሉን አዋቂ፥ በአንድ ጊዜ በሁሉ ስፍራ የሚገኝ አፍቃሪና ደግ ነው። እርሱ ቅዱስና ጻድቅ እንደሆነም ደግሞ

ተምረናል። ከእርሱ ጋር የሚዋጉትንና ትእዛዙን የሚጥሱትን ሁሉ ይቀጣል።

አሁን ደግሞ በተጨማሪ ለመጀመሪያ ጊዜ ጸጋና ምሕረትን የተሞላ እንደሆነ እንመለከታለን። አዳምና ሔዋን እንዲሞቱና ወደ ዘላለም ቅጣት እንዲሄዱ ሊተዋቸው ይችል ነበር። የሚገባቸው የነበረው ፍርድም ያ ነበር። እግዚአብሔር ግን እነርሱንና የሰው ልጆችን ሁሉ ከሰይጣን ቁጥጥር ነፃ በማውጣት ወደ እራሱ የሚመልሳቸውን የአዳኙን ተስፋ ሰጠ። እግዚአብሔር ጸጋና ምሕረትን የተሞላ ነው።

እስቲ ከዚህ በፊት ጨርሶ የማላውቀው አንድ ሰው ወደ እኔ ቤት እንደመጣ አድርገን እንገምት። ይህ ሰው ትልቅ የቆላ ቁስል በእግሩ ላይ ያለበትና የእኔን የሕክምና እርዳታ አጥብቆ የሚፈልግ ነው እንበል፤ ስለዚህ መድኃኒት አድርጌ ቁስሎቹን ሸፈንኩለት። ደግሞም የሚበላው ምግብ ሰጠሁት፥ ከፍተኛ ቸርነት አሳየሁት። ነገር ግን ይህ ሰው ይህን ሁሉ አጠናቆ ከቤቴ ሲለቅ፥ በልብስ ማስጫው ላይ የተንጠለጠለ ቁምጣ ሱሪ አይቶ ናሮ ለመስረቅ ከብብቱ ውስጥ ሲወሽቀው አየሁት።

በሚቀጥለውም ቀን ወደ እኔ ተመልሶ በመምጣት የተለመደ እርዳታዬን ጠየቀኝ። በእግሩ ላይ ያለውን ቆሻሻ ጨርቅ ቀየርኩለት፤ ቁስሉንም አጸዳሁለት። የምሳ ሰዓት በደረሰ ጊዜ ምሳውን እንዲበላ ምግብ ሰጠሁት። ቅጣት የሚገባው ሆኖ ሳለ፥ ቸርነቴን በማሳየት እጅግ ደግ ሆንኩለት። በመጀመሪያ ወደ እኔ ሲመጣ ፍቅርንና ቸርነትን ላሳየው ዘንድ ምንም ያደረገልኝ ነገር አልነበረም። አሁን ግን ቅጣት የሚገባው በደል ፈጽሞብኛል። ያም ሆኖ ግን የሚያስፈልገውን እርዳታ አደረግኩለት፤ ምግብንም ሰጠሁት።

በአዳምና ሔዋን ላይ የሆነውም እንደዚሁ ዓይነት ነገር ነበር። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ሲፈጥር የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ ሰጣቸው። እግዚአብሔር በርካታ መልካም ነገሮችን ይሰጣቸው ዘንድ አንዳችም ግዴታ አልነበረበትም፤ ነገር ግን እርሱ አፍቃሪና ደግ አምላክ ስለሆነ ይህንን አደረገላቸው። አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ላይ ባመፁ ጊዜ የእግዚአብሔር ቁጣ በላያቸው እንዲወርድ የተገባቸው

ነበሩ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ምን አደረገ? ወደዘላለማዊ ቅጣት ወዲያውኑ ላካቸውን? አልላካቸውም! እርሱ ምሕረትና ጸጋን የተሞላ አምላክ ስለሆነ ከሚገባቸው ቅጣት የሚያድናቸው ነፃ አውጭ ሊልክላቸው ተስፋን ሰጣቸው።

መምህር ሆይ

ሀ. የእግዚአብሔር ጸጋ ምን ማለት እንደሆነ ለሕዝቡ ግልጽ ማድረግ አለብን። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር ፈጣሪ ስለሆነ ለሰው ልጅ የሚያስፈልገውን ሁሉ በመስጠት አፍቃሪ ቸርነቱን ገለጠ። ይህ ጸጋ አይደለም። የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ እያወቀ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በጣሰ ጊዜ፥ የእግዚአብሔር ቁጣ ወዲያውኑ ሊወርድበት በተገባም ነበር፤ ሆኖም ግን እግዚአብሔር ደኅንነት የማይገባውን ሰው ለማዳን ወሰነ። የእግዚአብሔር ጸጋ ማለት ይህ ነው።

ለ. ነፃ አውጪው የሰይጣንን ራስ ይቀጠቅጣል፥ ሰይጣን ደግሞ ሰኰናውን ይቀጠቅጣል የሚለው ቃል በቀጥታ ስለሥጋዊ መቀጥቀጥ የሚናገር ያለመሆኑን ግልጽ አድርግ። ራስ ሁልጊዜ የሚያመለክተው ሥልጣንን ነው። እግርን በተሸናፊው በአንገት ላይ መጫን ድልን ያመለክታል (ኢያሱ 10:24)። እንደሚመጣ ተስፋ የተነገረለት ነፃ አውጪ ሰይጣንን ድል በመንሣት፥ ለጊዜው በዚህ ዓለምና በሰው ልጅ ላይ አግኝቶት የነበረውን ሥልጣን ይቀማዋል።

ሐ. የመዋጀት ታሪክ የሚጀምረው በዚህ ስፍራ ነው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ስለሚመጣው ነፃ አውጪ ያለማቋረጥ እናመለክታለን። ይህን ትንቢትና ተስፋ የሚያሟላው ማን እንደሆነ በዚህ ደረጃ አንገልጽም፤ ምክንያቱም ብሉይ ኪዳን የአዳኙን የተለዩ ባሕርያት አይገልጽምና ነው፤ ማንነቱን የምንገልጸው በአዲስ ኪዳን ስለልደቱ ስናስተምር ይሆናል።

ሰ. የእግዚአብሔር እርግማን በሴቲቱ ላይ።

ዘፍጥረት 3:16 አንብብ። እግዚአብሔር ለሔዋን ጌታን ስላልታዘዘች እርሷና ወደ ፊት እናት የሚሆኑ ሴቶች በሙሉ ልጅ በሚወልዱበት ጊዜ ምጣቸው እንደሚጠነክር ለባላቸውም እንደሚገዙ ነገራት።

ሸ. የእግዚአብሔር እርግማን በወንዱና በምድር ላይ።

ዘፍጥረት 3:17-19 አንብብ። አዳም እግዚአብሔር የተናገረውን ከማስታወስ ይልቅ ለሔዋን በምኝነት ተታለለላት።

አንዳንድ ጊዜ የራሳችን ቤተሰቦች የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት እንድንቆጠብ ሊያደርጉን ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ ባሎች ሚስቶችን ሊከለክሉ ይችላሉ። ሚስቶች ደግሞ ባሎችን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ከመቀበል እንዲታቀቡና በቀድሞ እምነታቸው እንዲቆዩ ሊያበረታቱ ይችላሉ። ወላጆች፥ ልጆቻቸውን የእግዚአብሔርን ቃል እንዳይሰሙ ሊነግሩአቸው ይችላሉ። ልጆችም እንኳ ወላጆቻቸው የእግዚአብሔርን ቃል እንዳይሰሙ ሊከለክሉ ይችላሉ። ሰይጣን የሚሠራበት መንገድ ይህ ነው። ሰይጣን ሔዋንን አታለለና አዳምን እንድትፈታተን አደረገ። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል እንዳትሰሙ ሊያደርጋችሁና ሌሎችን ከብርሃን ወደ ጨለማ እንድትመሩ ሊጠቀምባችሁ ስለሚሞክር መጠንቀቅ አለባችሁ።

አንድ ዕውር ሰው ሌላውን ዕውር ወጥመድ ወዳለበት ቢመራው የሚከሰተው ምንድን ነው?

ከእግዚአብሔር ንግግር ይልቅ ሰይጣንን ብትሰሙትና ብታምኑት እንደ ዕውር ሰው ትሆናላችሁ። ትክክለኛውን መንገድ ለማየት አትችሉም፤ የሰይጣንን ወጥመድ ልታውቁም አትችሉም። ከእግዚአብሔር ቃል ዘወር እንዲሉ ሌሎች ሰዎች ላይ ተጽዕኖ ብታደርጉ ዕውር እንደሚመራ ዕውር ሰው ትሆናላችሁ። አዳምና ሔዋን እንዳደረጉት በሰይጣን ወጥመድ ትወድቃላችሁ። ወደ ዘላለማዊ ቅጣትም ትሄዳላችሁ።

አዳምና ሔዋን ሰይጣንን ስለሰሙ በወጥመዱ በመውደቅ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጣሱ፤ ስለዚህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ምድር የተረገመች እንደምትሆን እግዚአብሔር ተናገረ። አዳም ኃጢአትን

ከማድረጉ በፊት የዔድን ገነትን ይንከባከብ ነበር። አዳም ምንም ዓይነት ከባድ ሥራ ሳይሠራ ሁሉም አዝርዕት በቀላሉ ያድግ ነበር። አዳም ኃጢአትን ካደረገ በኋላ ግን እግዚአብሔር ምድሪቱን ስለረገመ ብዙ አረሞች መብቀል ጀመሩ። ይህም የአዳምን ሥራ ከባድ አደረገው።

በዓለም ላይ የሚገኙ መጥፎ ነገሮች በሙሉ ሰው እግዚአብሔርን ስላልታዘዘ ሕልውና ያገኙ ናቸው።

እግዚአብሔር፥ አዳምን ከምድር አፈር አበጅቶት ነበር። አዳም ኃጢአትን ባደረገ ጊዜ አካሉ እንደሚሞትና ወደ ምድር አፈር እንደሚመለስ ነገረው። እግዚአብሔር፥ አዳምና ሔዋንን በፈጠረ ጊዜ እንዲሞቱ አላቀደም ነበር፤ አሁን ግን እግዚአብሔርን ስላልታዘዙ ይሞቱ ዘንድ ግድ ሆነ። በእናንተ መካከል ያሉ ሰዎችም ሆኑ በዓለም ዙርያ ያሉ ሰዎች የሚሞቱት በዚህ ምክንያት ነው። የኃጢአት ቅጣት ሥጋዊ ሞት ብቻ ሳይሆን ከአሁን ጀምሮ ለዘላለም ከእግዚአብሔር መለየት ጭምር ነው።

መምህር ሆይ፡- ሕዝቡ የእርግማንን እውነታነት በእርግጥ ከልምድ ያውቁታል። ከድርቅ፥ ከዓውሎ ነፋስ፥ ከጦርፍ፥ ከተናዳፊ እባቦችና ሸለምጥማጦች፥ ከተለያዩ ጥቃቅን ነፍሳት ጉዳት፥ ከአረም፥ ከበሽታ፥ ከምጥ፥ ከጽኑ ድካምና ከሞት ጋር ያለማቋረጥ የሚታገሉት ለምን እንደሆነ እንዲገነዘቡ እርዳቸው። ለእነዚህ ጉዳዮች የራሳቸው የሆነ ባህላዊ እምነቶች ሊኖራቸው ይችላል፤ አንተ ግን ለእነዚህ ሁሉ ነገሮች እውነተኛ የሆነውን ምክንያት ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አንጻር ግለጥላቸው።

ቀ. አዳምና ሔዋን የሰው ልጆች ሁሉ ወላጆች ናቸው።

ዘፍጥረት 3፡20 አንብብ። ሔዋን፥ የመጀመሪያዪቱ ሴትና የሰው ልጆች ሁሉ እናት ናት። አዳም የሁላችን አባት ነው። እኛ ሰዎች የተለያየ የቆዳ ቀለም ቢኖረንም፥ አስቀድመን የተገኘነው ግን ከአንድ ወላጆች ማለትም ከአዳምና ከሔዋን ነው።

አዳም፥ እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ዞር ስላለ ከእግዚአብሔር ተለየ። ይህ ማለት የእርሱ ልጆች የሆኑት ሁሉ ይሞታሉ ማለት ነው። በሁሉም

አገሮች የሚገኙ ሰዎች ሁሉ ይሞታሉ፤ ምክንያቱም እኛ ሁላችን የአዳም ዝርያዎች በመሆናችን ነው።

መምህር ሆይ፡- ይህ እውነት የትምህርታችን እጅግ ጠቃሚው ክፍል ነው፤ ስለዚህ ለአድማጮችህ በግልጽ መርዳት ስትል በጥሩ ሁኔታ አብራራው እንጂ ገረፍ አድርገህ አትለፈው።

ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር አዳምን የጠራው አዳምና ሔዋን የት እንደነበሩ ስለማያውቅ ነውን? አይደለም። እግዚአብሔር የት እንደነበሩ ያውቅ ነበር። እግዚአብሔር የፈለገው በፈቃደኝነት ወደ እርሱ እንዲመጡና ኃጢአታቸውን እንዲያምኑ ነበር።

2. ማንም ሰው ከእግዚአብሔር ሊደበቅ ይችላልን? አይችልም። ወደየትም ስፍራ በማንኛው ጊዜ ብንሄድ እንኳ እግዚአብሔር ያየናል።

3. እግዚአብሔር አዳምን ሊጠራና ሊጠይቀው መብት የነበረው ልምንድን ነው?

   ሀ. የአዳም ፈጣሪ እግዚአብሔር ስለሆነ፥

   ለ. አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔር ስለሆኑ፥

   ሐ. እግዚአብሔር አዳምን የፈጠረው እንዲወደውና እንዲታዘዘው ስለነበረ ነው።

4. እግዚአብሔር፥ እንታዘዘው ዘንድ ሊጠይቀን መብት ያለው ለምንድን ነው? ምክንያቱም ለሁላችንም ሕይወትን የሰጠን እርሱ ስለሆነ ነው።

5. እግዚአብሔር አባቢቱን የረገማት ምን ብሎ ነበር? ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሆዷ እንድትሳብ ነበር።

6. ሰይጣንና መናፍስት ከእግዚአብሔር ምን ሊደብቁ ይችላሉ? ከእግዚአብሔር አንዳችም ነገር ሊደብቁ አይችሉም። አሳባቸውን በሙሉ ያውቃል።

7. እግዚአብሔር ማንን እንደሚልክ ተስፋ ሰጠ? ከድንግል የሚወለደውን ወንድ ልጅ እንደሚልክ ተስፋ ሰጠ።

8. እግዚአብሔር ከድንግል የሚወለደው ልጅ ምን እንደሚያደርግ ተናገረ? ሰይጣንን ድል በመንሳት የሰው ልጅን ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ነፃ እንደሚያወጣ ተናገረ።

9. እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ነፃ አውጪ እንደሚልክ ቃል የገባው ለምን ነበር? እግዚአብሔር ሰዎችን ስለሚወድ ነው።

10. አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔር ፍቅርና ነፃ አውጪነት ተስፋ ሊሰጣቸው ይገባቸው ነበርን? አይገባቸውም ነበር። ወደዘላለማዊ ቅጣት ሊሄዱ ብቻ ይገባቸው ነበር።

11. እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን እንደረገማቸው የሚያመለክቱ ዛሬ በምድር ላይ የምንመለከታቸው ምን መረጃዎች አሉ? ሕመም፥ ሐዘን፥ ምጥ፥ ሞት፥ ከባድ ሥራ፥ እሾህና አረም፥ ድርቅ፥ ከፍተኛ ጥፋት የሚያስከትል ማዕበል፥ መርዛማ አትክልቶች፥ እባቦች፥ መርዘኛ ሸረሪቶችና ጨካኝ አራዊቶች፥ እነዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር እርግማን ምልክቶች ናቸው።

12. የሰዎች ሁሉ የመጀመሪያ ወላጆች እነማን ናቸው? አዳምና ሔዋን።

13. ሰዎች ሁሉ የሚሞቱት ለምንድን ነው? አዳም ስላልታዘዘ የአዳም ዘሮች በሙሉ ይሞታሉ።

ትምህርት 13

የትምህርት ክፍል፡- ዘፍጥረት 3፡21-24

አጠቃላይ ርእስ፡- የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታና የእግዚአብሔር ፍርድ።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ የእምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. እግዚአብሔር፥ አዳምና ሔዋን ለራሳቸው ያደረጉትን የቅጠል መሸፈኛ ሳይቀበለው ቀረ (3፡21)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው፤ ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. ሰው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ወደ እግዚአብሔር መምጣት ይችላል።

ለ. እግዚአብሔር እንስሳትን ገደለ።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ዋጋ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

ሐ. እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን መሸፈኛ ቁርበትን አዘጋጀ።

. እግዚአብሔር፥ አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

መ. እግዚአብሔር፥ አዳምንና ሔዋንን ቁርበት አለበሳቸው።

ሠ. እግዚአብሔር፥ አዳምና ሔዋንን ከገነት በማስወጣት ከሕይወት ዛፍ አራቃቸው (3፡22፥ 23)።

. እግዚአብሔር፥ ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

. እግዚአብሔር፥ የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ረ. እግዚአብሔር ወደ ሕይወት ዛፉ የሚወስደውን መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ ሰይፉን አስቀመጠ (3፡24)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር፥ በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

የትምህርት 12 ጥያቄዎችን ከልስ።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

ሀ. እግዚአብሔር፥ አዳምና ሔዋን ለራሳቸው ያደረጉትን የቅጠል መሸፈኛ ሳይቀበለው ቀረ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሰው፥ ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ዘፍጥረት 3፡21 አንብብ። አዳምና ሔዋን የተከለከለውን ፍሬ ከበሉና ዕራቁታቸውን መሆናቸውን ካወቁ በኋላ ምን እንዳደረጉ ታስታውሳላችሁን? የራሳቸውን ሃፍረተ ሥጋ በቅጠል ለመሸፈን ሞከሩ። እግዚአብሔርን ስላልታዘዙ እግዚአብሔር ራቁታቸውን ሆነው እንዳያያቸው አፈሩና ለራሳቸው የቅጠል መሸፈኛ አዘጋጁ።

እግዚአብሔር ግን አዳምና ሔዋን ለራሳቸው ያዘጋጁትን መሸፈኛ ሳይቀበለው ቀረ። እግዚአብሔር ይህንን ያደረገበት ምክንያት ከቅጠል ወይም ከሣር የተሠራ መሸፈኛ (ልብስ) ስለማይወድ አልነበረም። እነርሱ የሠሩትን መሸፈኛ (ልብስ) ያልተቀበለበት ምክንያት በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያገኙ ዘንድ በራሳቸው ሊሠሩት የሚችሉት አንዳችም ነገር እንደሌለ ሊያስተምራቸው ስለፈለገ ነበር።

የተዋቡና ያጌጡ ልብሶችን በመልበስ ራሳችንን መልካም አድርጉ ለማቅረብ መሞከር በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንድናገኝ ሊያደርገን አይችልም። እግዚአብሔር፥ በሰው አሳብ የተሠሩ ማናቸውንም ነገሮች አይቀበልም። እግዚአብሔር የሚቀበለው በእርሱ መንገድ የተሠሩትን ነገሮች ብቻ ነው። ማንኛውም ሰው በሚያደርገው

ነገር ራሱን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሊያደርግ አይችልም።

ለ. እግዚአብሔር እንስሳትን ገደለ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

በዓለም ላይ የመጀመሪያውን ሞት እንዲመጣ ያደረገው እግዚአብሔር ነበር። እግዚአብሔር እንስሳትን ገደለ። የእንስሳቱ ደም ፈሰሰ። ቀጥሎም እግዚአብሔር የእንስሳቱን ቆዳ ገፈፈ። አዳምና ሔዋን ይህን አላደረጉም። እግዚአብሔር እንስሳቱን በመግደል ቆዳቸውን ገፈፈ። እግዚአብሔር፥ ለአዳምና ለሔዋን ለእርሱ ባለመታዘዛቸው ወደ ዓለም ሞትን እንዳመጡ እያስታወሳቸው ነበር።

ሐ. እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን መሸፈኛ ቁርበትን አዘጋጀ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋና የተሞላ አምላክ ነው።

እግዚአብሔር እንስሳትን የገደለው ለምን ነበር? ለጥፋተኞቹ ለአዳምና ሔዋን ልብስ ለማዘጋጀት ነበር።

እግዚአብሔር ከገደላቸው እንስሳት ቆዳ ልብስን አዘጋጀላቸው። እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን ባይገባቸውም እንኳ ይህን አደረገ። በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ልብስ ሊያዘጋጅላቸው የሚችል እርሱ ብቻ ነበር።

መ. እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ቁርበት አለበሳቸው።

እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ቁርበት አለበሳቸው። ይህን የቁርበት ልብስ በመስጠት ልበሱት አላላቸውም። ያዘጋጀውን የቁርበት ልብስ አምጥቶ አዳምንና ሔዋንን ራሱ አለበሳቸው።

መምህር ሆይ፡- እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ያዘጋጀው በኢሳይያስ 61:10 ላይ ለተጠቀሰው የመዋጀት ዕቅድ እውነትነት፥ ተምሳሌታዊ መግለጫ ነው። «... የማዳንን ልብስ አልብሶኛልና፥ የጽድቅንም መጐናጸፊያ ደርቦልኛልና ...»።

ቆየት ብለን ይህን መግለጫ በክርስቶስ በማመን በሚገኝ እምነት የሚከፈልልንን ካሣና የምንደርበውን የጽድቅ መጐናጸፊያ በማነጻጸሪያነት እናነሣዋለን። ይህንን እውነት ስለ ወንጌል በመናገር አሁኑኑ አታዛምድላቸው። በአሁኑ ደረጃ አዳምና ሔዋን ያደረጉትን እግዚአብሔር እንዳልተቀበለና እርሱ ራሱ ልብስን እንዳዘጋጀላቸውና እንደዚሁም በውጫዊ መንገድ የምንገልጠው ማናቸውም ነገር እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ልንጠቀምበት እንደማንችል ግልጽ አድርግላቸው። በዚህ ወቅት ልትናገረው የሚያስፈልገው ነገር ይህ ብቻ ነው። መሠረቶችን እየጣልክና መንፈሳዊ መመሪያዎችን እያነጽህ ነው። ኋላ ወንጌልን በምታስተምርበት ጊዜ ወደዚህ መግለጫ በመመለስ ትጠቀምበታለህ።

ሠ. እግዚአብሔር፥ አዳምና ሔዋንን ከገነት በማስወጣት ከሕይወት ዛፍ አራቃቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ዋጋ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

ዘፍጥረት 3፡22-23 አንብብ። እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስለ አዳምና ሔዋን እየተነጋገሩ ነበር። እግዚአብሔር በመጀመሪያ አዳምና ሔዋንን ሲፈጥራቸው ክፉ ወይም መጥፎ የሆነ አንዳችም ነገር አያውቁም ነበር። የሚያውቁት በጐ የሆነውን ነገር ብቻ ነበር። እግዚአብሔር የፈጠረውና የሰጣቸው ነገሮች ሁሉ መልካም ነበሩ። እግዚአብሔር እንዲያደርጉ የነገራቸው ነገሮች ሁሉ መልካም ነበሩ። እግዚአብሔር ፈጣሪያቸውን ባለመታዘዝ በተራመዱ ጊዜ ግን፥ ነገሮች ሁሉ መልካም እንዳይደሉ ሆነው አገኟቸው። አንዳንድ ነገሮች ክፉ እንደሆኑ ተገነዘቡ።

ሰይጣን ሔዋንን አታለላትና መልካምንና ክፉውን የሚያሳውቀው የእውቀት ዛፍ ፍሬ ለምግብ መልካም እንደሆነ አሰበች። አዳምና ሔዋን ይህንን ፍሬ እንደበሉ ወዲያውኑ በፍርሃት ተሞሉ። አሁን ሁሉ ነገር መልካም እንዳልሆነ ከማወቃቸውም በላይ አንዳንዶቹ ነገሮች ክፉ እንደሆኑ ተረዱ። እግዚአብሔር ግን የትኛው መልካም የትኛው ክፉ እንደሆነ ያውቅ ስለነበር፤ ስለዚህ ነገር ለራሳቸው ለማወቅ

ከመፈለጋቸው ይልቅ እግዚአብሔር እንዲነግራቸው ሊታመኑበት በተገባ ነበር።

እግዚአብሔር በዔድን ገነት ያኖራቸው ሁለት እጅግ ጠቃሚ ዛፎች የትኞቹ ነበሩ? እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን እንዲበሉ የፈቀደላቸው ዛፍ የትኛው ነበር?

እግዚአብሔር የሕይወትን ዛፍ በዔድን ገነት መካከል ያኖረው፥ ከሌሎች ይልቅ አዳምና ሔዋን እጅግ የሚያስፈልጋቸው ይህ ዛፍ ስለነበረ ነው። እግዚአብሔር የሕይወትን ዛፍ እንዲበሉ የፈለገው ሞት ጨርሶ የማይነካቸው እንዲሆኑ ነበር። ሆኖም እግዚአብሔርን ስላልታዘዙ የሕይወትን ዛፍ እንዳይበሉ ከለከላቸው። ከእግዚአብሔር ስለተለዩ ሥጋዊ ሞት ሊሞቱ ግድ ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር፥ የሁላችንም አባትና እናት የሆኑትን አዳምና ሔዋንን ከዔድን ገነት በማባረር ከሕይወት ዛፍ አራቃቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር በቅድሚያ በዔድን ገነት በማኖር የሕይወትን ዛፍ እንዲበሉ ነገራቸው። በእርሱ ፊት ኃጢአተኛ በሆኑበት ጊዜ ግን እግዚአብሔር ከዔድን ገነት በማባረር ከሕይወት ዛፍ እንዲርቁና እንዲሞቱ አደረገ።

እግዚአብሔር፥ ሰይጣን ኃጢአትን ባደረገ ጊዜ በሰማይ ከነበረው አስደናቂ የሥልጣን ስፍራ አስወገደው። አሁንም እግዚአብሔር ኃጢአትን ስለሚጠላ አዳምና ሔዋንን ከዔድን ገነት አባረራቸው። እግዚአብሔር ምን ማድረግ እንዳለበት ማንንም አይጠይቅም። በዓለም ሁሉ እርሱ የበላይ ነው።

ረ. እግዚአብሔር ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውን መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ ሰይፍን አስቀመጠ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። እራሱን ለማዳን አይችልምና እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 3፡24ን አንብብ። እግዚአብሔር፥ አዳምና ሔዋን ወደ ዔድን ገነት ተመልሰው በመምጣት የሕይወትን ዛፍ እንዳይበሉ ከጥሩ

መላእክቱ መካከል ኪሩቤል የሚባሉትንና የሚገለባበጥ ሰይፍን በዔድን ገነት በምሥራቅ አቅጣጫ አኖረ።

ወደ ሕይወት ዛፍ ሊመለሱ የሚችሉበት አንዳችም መንገድ አልነበረም። እግዚአብሔር ከዔድን ገነት ሲያባርራቸው ጉዳዩ ተደመደመ። ወደ ሕይወት ዛፍ ለመመለስ ሙከራ ቢያደርጉ የእግዚአብሔር መላእክት ሊያዩአቸውና በሚገለባበጥ ሰይፍ ሊገድሏቸው ይችሉ ነበር። ሊያደርጉት የሚችሉት አንዳችም ነገር አልነበረም። ማርጀታቸውና መሞታቸው የግድ ሆነ።

ከእግዚአብሔር ጋር ተዋግቶ ሊያሸንፍ የሚችል የለም። እግዚአብሔርን ልናሞኘው ወይም ልናታልለው አንችልም። እግዚአብሔር ለትእዛዙ ያለመገዛትን ይጠላል፤ ስለዚህ ማንኛውም የማይታዘዝ ሰው ከእርሱ ጋር እንዲኖር አይፈቅድም።

መምህር ሆይ፡-

ሀ. ሰው ከዔድን ገነት ስለመባረሩ በምታስተምርበት ጊዜ፥ የመመለስ ዕድል እንዳልነበረው ማስረገጥ ያስፈልግሃል። ይህን የእግዚአብሔር ቃል ለሕዝቡ በምናስተምርበት ጊዜ፥ ለሰው ልጅ እግዚአብሔር ራሱ የመመለሻ መንገድ እስካላዘጋጀለት ድረስ ለዘላለም ቅጣት የተተወ መሆኑን መሠረት እየጣልን ነው።

ለ. የሚገለባበጥ ሰይፍን ለመግለጥ የመብረቅ ብርሃንን በመግለጫነት መጠቀም ይቻላል።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

እስቲ አዳም ለሔዋን የሚከተለውን አማከራት ብለን እናስብ፡- «በዚህ ስፍራ ቁሚና መላእክትን አዘናጊያቸው፤ እነርሱን በንግግር ስታጠምጂያቸው እኔ ይህን ቅርጫት ይዤ ቀስ ብዬ ወደ ዔድን ገነት አምልጬ በመግባት የሕይወትን ዛፍ ፍሬ ሞልቼ እመጣለሁ።» ግን የእግዚአብሔርን ኪሩቤል ለማለፍ የሚችሉ ይመስላችኋል? እግዚአብሔርንስ አታለው ከጀርባ በመሄድ ለማምለጥ ይችሉ ነበርን?

አይችሉም። ይህን ለማድረግ ቢሞክሩ እግዚአብሔር ያያቸው ነበር፤ ስለዚህ የእግዚአብሔርን መላእክት ለማለፍ አይችሉም ነበር።

እግዚአብሔር አልተለወጠም። የምታደርጉትን ነገር ሁሉ ይመለከታል፥ ያውቃል። ከእርሱ ልትደበቁ የምትችሉበት ስፍራ የለም። እግዚአብሔርን ማታለል ወይም ማቄል አይቻልም። ጥቅጥቅ ባለ ደን ውስጥ ስትጓዙ ያያችኋል። ለእግዚአብሔር ብርሃንና ጨለማ ያው ነው። ከእርሱ ዓይን ልትሰውሩ የምትችሉበት ጊዜ የለም። እርሱ አስተሳሰባችሁን ሁሉ እንኳ ያውቃል።

ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር፥ አዳምና ሔዋን ለራሳቸው የሠሩትን ልብስ ያልተቀበለው ለምን ነበር? ምክንያቱም፥ እግዚአብሔር፥ አዳምና ሔዋንን በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ ሊያደርጋቸው የሚችል አንዳችም ነገር እንደሌለ ሊያስተምራቸው ስለፈለገ ነው።

2. ያማረ ልብስ በመልበስ ወይም ማንኛውንም ነገር በማድረግ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንድናገኝ ማድረግ እንችላለን? አንችልም።

3. አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ ሊያደርግ የሚችል ብቸኛው ማን ነው? እግዚአብሔር ነው።

4. እግዚአብሔር፥ ለአዳምና ሔዋን ልብስ ለማዘጋጀት እንስሳትን የገደለው ለምን ነበር? እግዚአብሔር፥ አዳምና ሔዋንን የኃጢአት ቅጣት ሞት መሆኑን ሊያስታውሳቸው ስለፈለገ ነበር።

5. እግዚአብሔር ልብስ የሠራላቸው ለምን ነበር? ኃጢአትን ቢያደርጉም እንኳ ይወዳቸው ነበር። በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ ሊያደርጋቸው የሚችል እርሱ ብቻ መሆኑን ሊያሳያቸው ፈልጐ ነበር።

6. አዳምና ሔዋን መልካምንና ክፉውን ከሚያሳውቀው የእውቀት ዛፍ ፍሬ በበሉበት ጊዜ እንደ እግዚአብሔር የሆኑት በምን መንገድ ነበር? ክፉና መልካም መኖሩን በማወቃቸው ነበር።

7. እግዚአብሔር፥ አዳምና ሔዋንን ከዔድን ገነት ያባረራቸው ለምን ነበር? ከሕይወት ዛፍ ፍሬ እንዳይበሉና ለዘላለም እንዳይኖሩ ነበር።

8. እግዚአብሔር፥ አዳምና ሔዋን ወደ ዔድን ገነት እንደማይመለሱ እርግጠኛ የሆነው እንዴት ነበር? ኪሩቤል የሚባሉ መላእክትን በማቆምና በሁሉም አቅጣጫ የሚገለባበጥ ሰይፍ በማድረግ ነበር።

9. እግዚአብሔርን ለማምኘት ወይም ለማታለል የሚችል አለን? የለም።

ትምህርት 14

የትምህርት ክፍል፡- ዘፍጥረት 4፡1-16

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር ቃየንንና መሥዋዕቱን ሳይቀበል ቀረ፤ አቤልንና መሥዋዕቱን ግን ተቀበለ።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. እግዚአብሔር ሕይወትን ሰጪ ነው (4፡1)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ለ. ቃየንና አቤል የተወለዱት ከሔድን ገነት ውጭ ነበር (4፡2)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሐ. ቃየንና አቤል ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን አቀረቡ (4፡3፥ 4)።

. ሰው፥ ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

መ. እግዚአብሔር እርሱን ለማምለክ ሲመጡ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ነግሮአቸው ነበር።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር፥ የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. እግዚአብሔር፥ አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

. እግዚአብሔር፥ ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ዋጋ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ሠ. የአቤል መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አገኘ (4:4)።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ እንዲያሰኝና እንዲድን እምነት ሊኖረው ያስፈልጋል።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው

ረ. የቃየንን መሥዋዕት እግዚአብሔር ሳይቀበለው ቀረ (4:5)።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ እንዲያሰኝና እንዲድን እምነት ሊኖረው ያስፈልጋል።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ሰ. እግዚአብሔር የተቆጣውን ቃየንን ለማሳመን በቂ ምክንያት አቀረበ (4:6፥ 7)።

. እግዚአብሔር፥ ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. እግዚአብሔር፥ አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ሸ. ቃየን እግዚአብሔርን መስማት እምቢ ብሎ አቤልን ገደለው (4:8)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. ሰይጣን ከእግዚአብሔርና ከፈቃዱ ጋር ይታገላል። ሰይጣን አታላይና ውሸታም ነው። ሰውን ይጠላል።

ቀ. የእግዚአብሔር ፍርድ በቃየን ላይ (4:9-16)።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል። እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

የትምህርት 13 ጥያቄዎችን ከልስ።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

ሀ. እግዚአብሔር ሕይወትን ሰጪ ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘፍጥረት 4፡1 አንብብ። ሔዋን ይህንን ያለችው እግዚአብሔር ሕይወትን ሁሉ የሚሰጥ እንደሆነ ታውቅ ስለ ነበር ነው። እግዚአብሔር፥ አዳምን ከምድር አፈር አበጅቶ ሕይወትን ይሰጠው ዘንድ የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት። እያንዳንዱ ሰው ሕይወት የተሰጠው በእግዚአብሔር ነው። የእያንዳንዳችን ሕይወት የተሰጠን ከእግዚአብሔር ነው።

በታሪካዊ ቅደም ተከተል ሠንጠረዥ ላይ፡- ቃየን፥ አቤል፥ ሴት፥ ሄኖክ የሚሉትን ስሞች በቅደም ተከተል አስቀምጥ።

ለ. ቃየንና አቤል የተወለዱት ከዔድን ገነት ውጭ ነበር።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 4፡2 አንብብ። አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ስለሠሩ፥ ከዔድን ገነት ውጭ ከሕይወት ዛፍ ርቀው እንዲቀመጡ ተደረገ።

ቃየንና አቤል፥ አባታቸው አዳም ኃጢአተኛ ስለ ነበር ኃጢአተኛ ሆነው ተወለዱ። ቃየንና አቤል ከዔድን ገነት ውጭ ከሕይወት ዛፍ ራቅ ባለ ስፍራ ተወለዱ፤ ምክንያቱም አዳም አባታቸው ከዔድን ገነት ውጭ ነበር። የእነርሱም ፍጥረታቸው በእግዚአብሔር አምሳያ ቢሆንም፥ ዳሩ ግን ያ እግዚአብሔርን ሊያውቁ፥ ሊወዱና ሊታዘዙ እንዲችሉ የሚያደርጋቸው ክፍል በሰይጣን ቁጥጥር ሥር ነበር።

የዚህ የምትኖሩበት አካባቢ የሚገኘው ሕዝብ አካል ልትሆኑና በዚህ ሰፍራ ልትወለዱ የቻላችሁት እንዴት ነው? እንዳላችሁበት እንደዚህ አካባቢ ሕዝብ እንድትመለከቱ፥ እንድታስቡ፥ እንድትናገሩና እንድትሠሩ የሆናችሁት ለምንድን ነው? በወላጆቻችሁ ምክንያት አይደለምን? ወላጆቻችሁ በአሜሪካ የሚኖሩ አሜሪካውያን ቢሆኑ እናንተም እንደ አሜሪካውያን በተመለከታችሁ፥ ባሰባችሁ፥ በተናገራችሁና ባደረጋችሁ ነበር።

እግዚአብሔር፥ አዳምና ሔዋንን በፈጠረ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም ነበሩ። እርሱም ይወዳቸውና ይቀበላቸው ነበር። ታዘውት ቢሆን ኖሮ በዔድን ገነት መኖራቸውን በመቀጠል የሕይወትን ዛፍ ፍሬ በበሉ ነበር። ልጆቻቸውም ፍጹም ሆነው በመወለድ በዔድን ገነት በኖሩ ነበር። እነርሱም እግዚአብሔርን በወደዱና በእርሱ ዘንድ ሙሉ ተቀባይነት ባገኙ ነበር። አዳም፥ የተከለከለውን ፍሬ በመብላት በፈጸመው ኃጢአት ግን፥ ቃየንና አቤል ኃጢአተኛ ሆነው ተወለዱ። ከእግዚአብሔር ተለይተው ከዔድን ገነት ውጭ የሕይወት ዛፍ ከሚገኝበት ርቀው ኖሩ።

አዳም፥ የቃየንና የአቤል ብቻ ሳይሆን የሰው ዘር ሁሉ አባት ነው። አዳም የእናንተም ሆነ የእኛ የመጀመሪያው አባት ነው፤ ስለዚህ አዳም እግዚአብሔርን ስላልታዘዘና ከእርሱ ስለተለየ በዚህ ዓለም የሚገኙም ሰዎች በሙሉ ኃጢአተኞች በመሆን ከእግዚአብሔር ተለይተውና የሰይጣን ተከታዮች ሆነው ይወለዳሉ።

ሕይወትን ለሰዎች ሁሉ የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው፤ ነገር ግን የተወለድነው ከእግዚአብሔር ጋር ባለ ወዳጅነት ወይም አንድነት አይደለም። ሰይጣን፥ የእግዚአብሔርን ስፍራ ከሰዎች ሕይወት በመውሰድ መንፈሳዊ አባታቸው ሆነ። ይህ ማለት የእግዚአብሔር አምሳል በመሆኑ እግዚአብሔርን እንድናውቀው፥ እንድንወደውና እንድንታዘዘው ሊያደርገን የሚችለው ክፍል ከመወለዳችን ጀምሮ በሰይጣን ቁጥጥር ሥር ሆኗል ማለት ነው።

ኃጢአተኛ ሆናችሁ መወለዳችሁን መገንዘብ ጠቃሚ ነው። ልክ እንደ እኛ ሁሉ እናንተም ከእግዚአብሔር ተለይታችሁና ሰይጣን አባት ሆኗችሁ ተወለዳችሁ።

መምህር ሆይ፡- ይህን ነጥብ እንዴት እንደምትገልጸው ተጠንቀቅ። ይህንን ስታስረዳቸው ሕዝቡ፥ ሰይጣን የሰብአዊ ሕይወታቸውና የሥጋዊ አካላቸው አባት እንደሆነ አድርገው እንዲያስቡ ማለትህ እንዳይደለ እርግጠኛ ሁን።

ሰይጣን፥ ስለሰው ዘር ጅማሬ የሚናገረው በርካታ ውሸቶች አሉት። ሰይጣን በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ ሰዎች ስለጅማሬያቸው፥ ከየት እንደተገኙ፥ የመጀመሪያ ወላጆቻቸው እነማን እንደሆኑ በርካታ የተለያዩ ታሪኮችን ይነግራቸዋል። እናንተም ስለዚህ ጉዳይ የራሳችሁ እምነት አላችሁ። እግዚአብሔር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እውነቱን ይነግረናል። የእናንተ ሕዝቦችም ሆኑ ሌሎችም ሰዎች ሁሉ ማለትም ሁላችንም በሰይጣን ቁጥጥር ሥር ሆነን የመወለዳችን እውነተኛ ታሪክ ይህ ነው።

ምናልባት በዚህ መልክ ልንረዳው እንችላለን። ለምሳሌ፡- በጉርብትና የሚኖር ሌላ ሕዝብ ጋር በጦርነት ላይ ናችሁ እንበል። ይጠሏችኋልና ስለዚህ ሊጐዳችሁ የሚችል ማንኛውንም ነገር ሊያደርጉባችሁ ይፈልጋሉ። አንድ ከእናንተ ነገድ የሆነ ወጣት ሰው ከጠላቶቻችሁ ወገን በሆነች አንዲት ሴት በፍቅር ተማረከ እንበል። ከዚያም ይህችን ሴት ያገባና የእርሷ ወገን የሆነውን ሕዝብ መስሎ መኖር ይጀምራል። እነዚህ ሁለት ወጣቶች ልጅ በሚወልዱበት ጊዜ ልጆቻቸው የየትኛው ወገን ይሆናሉ? አባታቸው የራሱን ሕዝብ ትቶ በመሄድ የሕዝቡ ጠላት ከሆነው ሌላ ሕዝብ ጋር በመተባበሩ ልጆቹስ የእናንተ ጠላቶች አይደሉምን? አዎን ናቸው፥ ይሆናሉም።

አዳም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሆን ብሎ ሲጥስ ያደረገው ይህንን ነበር። እራሱን በሰይጣን ቤተሰብ ውስጥ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ከእርሱ በኋላ የሚመጣውን የሰውን ዘር በሙሉ በአባትነቱ የሰይጣን ቤተሰብ አደረገ። ሁላችንም ኃጢአተኞች በመሆን በሰይጣን ቁጥጥር ሥር ተወልደናል፤ የእግዚአብሔር ጠላቶች ነን።

መምህር ሆይ፡ -

ሀ. ከዚህ ቀደም አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር እንደተለዩ ለመግለጽ የተጠቀምክበትን የዛፍ ቅርንጫፍ ጉዳይ እንዲያስታውሱ አድርግ። በቅርንጫፉ የላይኛው ክፍል የሚገኙት ሁለት ትናንሽ ቅርንጫፎች ቃየልና አቤልን ሊወክሉ ይችላሉ። እነዚህ ቅርንጫፎች ለሕልውናቸው ጥገኛ የሆኑት በዋናው ቅርንጫፍ ላይ ስለነበረ እነርሱም መሞታቸውን አሳይ። ቃየንና አቤል ከዔድን ገነት ውጭ ከእግዚአብሔር ተለይተው የተወለዱት በአባታቸው በአዳም ያለመታዘዝ ምክንያት ነው። እነርሱ የሕይወትን ዛፍ ፍሬ ለመብላት አይችሉም ነበር።

ለ. በቅርንጫፍ ጫፎች ላይ የሚገኙት የመጨረሻዎቹ ትናንሽ ቀንበጦች፥ በአዳም ምክንያት ለእግዚአብሔር ሙት ሆነው የተወለዱትን አዳማጮችህንና በዓለም ሁሉ ላይ ያሉትን ሰዎች እንደሚወክሉ አመልክት።

በዚህ ስፍራ ክፍሉን ባንጠቅሰውም እንኳ እያስተማርን ያለነው ሮሜ 5:12 ነው። «ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ።» ቃየንና አቤል በመጀመሪያ ኃጢአትን ያደረጉት እንዴት ነበር? በአባታቸው በአዳም በኩል ነበር።

ባለቤቴ አውስትራሊያዊት ናት። ለምን? የተወለደችው በአውስትራሊያ ስለሆነ ነው። አባቷ የተወለደው ግን በእንግሊዝ አገር ነው። ታዲያ የእኔ ሚስት እንግሊዛዊ ያልሆነችው ለምንድን ነው? አባቷ እንግሊዛዊ ሆነው ሳሉ እርሷ አውስትራሊያዊ የሆነችው እንዴት ነው? ምክንያቱ አባቷ አገራቸውን ትተው አውስትራሊያ ስለሄዱ ነው። ስለዚህ ባለቤቴ አውስትራሊያዊት ሆና ተወለደች።

አዳም ኃጢአትን ስላደረገ ከዔድን ገነት ተባረረ። ስለዚህ ቃየንና አቤል ከዔድን ገነት ውጭ ከሕይወት ዛፍ ርቀውና ከእግዚአብሔር ተቆራርጠው ባሉበት ተወለዱ።

ሐ. ቃየንና አቤል ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን አቀረቡ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ወደ እግዚአብሔር የሚመጣው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

መምህር ሆይ፡- ከዚህ በኋላ የምታነባቸው ጥቅሶች ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ በግና ስለ እረኛ ተግባር የሚናገሩ ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ የእረኛ ተግባር በጣም ታዋቂ ስለሆነ የእረኛን ሥራና የበጎችን ዓይነትና ባሕርይ ለመግለጽ በቂ ጊዜ መስጠት አለብህ። በፖላዋን እንዳለው ሁሉ በአንተም አካባቢ ታዋቂ የሆኑት ፍየሎች ከሆኑ በጎችን ለመግለጥ ተጠቀምባቸው። ከእረኞች ጋር ያሉ በጎችን በሚያሳይ ሥዕል መጠቀም ይረዳል።

ሮሜ 4፡3፥ 4 አንብብ፥ ቃየልና አቤል በእግዚአብሔር መኖር ያምኑ ነበርና ሁለቱም ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን አቀረቡ።

በእግዚአብሔር ማመንና መልካም ነው ብለን የምናስበውን ነገር ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጉ ማቅረብ ብቻውን በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት እንድናገኝ አያደርገንም። ሰይጣንም እንኳ በእግዚአብሔር እንደሚያምንና ስለ እግዚአብሔር በሚያስብበት ጊዜ በፍርሃት እንደሚንቀጠቀጥ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ነገር ግን ይህ ሰይጣንን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ አያደርገውም። በመቀጠል በቃየንና በአቤል ምን እንደደረሰ ስለምንግራችሁ፥ በጥንቃቄ አድምጡ።

መ. እግዚአብሔር እርሱን ለማምለክ ሲመጡ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ነግሮአቸው ነበር።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። እራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

አዳምና ሔዋን ወይም ቃየንና አቤል ወደ እግዚአብሔር ሊመጡ የሚችሉበት መንገድ አልነበረም። ሁሉም ኃጢአተኞች ነበሩ። እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትን ይጠላል። ከእግዚአብሔር ተለይተው ነበር። የኃጢአት ቅጣት ሞት ነው። ኃጢአቶቻቸውን ለመክፈል ለእግዚአብሔር ሊሰጡት የሚችሉት አንዳችም ነገር አልነበራቸውም።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር፥ አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ግን ወደ እርሱ የሚመጡበትን መንገድ ዐቀደ። ይህ የሰው መንገድ አልነበረም። ይህን መንገድ የወሰነው እግዚአብሔር ነበር። ለእነርሱ መንገድን ሊያበጅላቸው የሚችል ማንም አልነበረም። እግዚአብሔር ስለወደዳቸው መንገድን አበጀላቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

እግዚአብሔር፥ አዳምና ሔዋን ወደ እርሱ ለመምጣት ከፈለጉ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ነግሮአቸው ነበር።

እንደዚሁም አዳምና ሔዋን፤ ለቃየንና ለአቤል ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት ከፈለጉ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ምናልባት ነግረዋቸው ይሆናል።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

እግዚአብሔር፥ ወደ እርሱ በሚመጡበት ጊዜ በመሥዋዕትነት በግ ማቅረብ እንዳለባቸው ነግሮአቸው ነበር። በግ ካመጡ በኋላ በማረድ ደሙ እንዲፈስ ማድረግ ነበረባቸው።

የእንስሳት ደም የኃጢአታቸውን ዋጋ መክፈል አይችልም ነበር። እግዚአብሔር በግ እንዲያርዱ ያዘዘበት ምክንያት ምንድን ነው? እግዚአብሔር የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንደሆነ እንዲያስታውሱ ይፈልግ ስለነበር ነው። እርሱ ካላዳናቸው በስተቀር እንደሚሞቱና ወደዘላለም ቅጣት እንደሚሄዱ እንዲያስታውሱ ይፈልግ ነበር። ኃጢአተኛ በመሆናቸውና ከዘላለም ቅጣት ሊያድናቸው የሚችል እርሱ ብቻ በመሆኑ ከተስማሙ እግዚአብሔር እንደነገራቸው በግ አምጥተው በእግዚአብሔር ትዕዛዝ መሠረት ሊያርዱ ይገባ ነበር።

መምህር ሆይ፡- እግዚአብሔር የቃየንን መሥዋዕት ለምን ሳይቀበል እንደቀረና የአቤልን መሥዋዕት ለምን እንደተቀበለ በሚገባ መረዳቱ ለሁላችንም አስፈላጊ ነው።

ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት እንደማይቻል መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (ዕብራውያን 11:6)። አቤል የእምነት ሰው ነበር፥ ቃየን ግን አልነበረም (ዕብራውያን 11:4፤ 1ኛ ዮሐ. 3:12)። እውነተኛ እምነት በማንኛውም ጊዜ የሚመሠረተው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ነው (ሮሜ 10:17)። እግዚአብሔርን ከመለኮታዊ ምሪት አቅጣጫ በተዛነፈ መንገድ መቅረብ ግብዝነትና በእግዚአብሔር ዘንድ ሁልጊዜ ተቀባይነት እንዳይኖረን የሚያደርገን ነው። ከሰው የሚመነጭ ማንኛውም ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም። በዚህ መሠረት ስንመለከተው የአቤል እምነት ከእግዚአብሔር በተሰጠ ግልጽ ምሪት ላይ የተደገፈ እንደነበር እርግጠኞች መሆን እንችላለን። የተፈጸመው በዚህ መልክ ባይሆን ኖሮ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አያገኝም ነበር።

አቤል፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተከትሎ እንደነበር የሚያመለክተን ሌላው ነገር አቤል ያቀረበው የሰባውን በግ መሆኑ ነው። በቅዱስ መጽሐፍ የኋለኛ ክፍል እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ስቡን እንዲያቀርቡ እግዚአብሔር አዞአቸዋል (ዘሌዋውያን 3:16)። ስለዚህም ስቡን ማቅረብ በአቤል እንደተጀመረ አድርጉ መናገር ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ጠቅላላ አትኩሮት ጋር ይቃረናል። እግዚአብሔር ከሰው የመነጨ ማንኛውንም ነገር አይቀበልም።

በተጨማሪ በኖኅ ዘመን እንኳ እንስሳት ንጹሕ የሆኑና ንጹሕ ያልሆኑ በመባል ተከፋፍለው ስለነበር እንደ እግዚአብሔር ምሪት እንስሳት ንጹሕ የሆኑና ንጹሕ ያልሆኑ በመባል በአቤልም ጊዜ ቢሆን ተከፋፍለው ነበር ለማለት ይቻላል። አቤል ንጹሕ የሆነ፥ አንዳችም ነቀፋ የሌለበት፥ ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን ልጅ አምሳያ በግ መምረጡ አጋጣሚ ሊሆን ጨርሶ ያለመቻሉ ነገር የተረጋገጠ ነው (ኢሳይያስ 53:7፤ ዮሐ. 1:29፤ 1ኛ ጴጥ. 1:19፥ 20)። ጌታ ኢየሱስ ነቀፋ የሌለበት ፍጹም የእግዚአብሔር በግ ሆኖ መሥዋዕት የመሆኑ ጉዳይ ምድር ከመፈጠሯ በፊት በዘላለማዊው በእግዚአብሔር

አእምሮ የታቀደ እንጂ በአቤል አእምሮ የታቀደ አይደለም (ራእይ 13፡8)።

ሠ. የአቤል መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አገኘ።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት እምነት ሊኖረው ያስፈልጋል።

ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ነው።

ዘፍጥረት 4፡4 አንብብ። አቤል ከበጎቹ አንዱን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጐ አቀረበ። ለመሥዋዕት ያቀረበው በኩሩን በግ ነበር።

አቤል የበጉ ደም እንዲፈስ ካረደው በኋላ ከስቡ ጋር ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ አቀረበው። አቤል ይህን በማድረግ ኃጢአተኛ መሆኑንና ወደ ዘላለም ቅጣት ከመሄድ ሊያድነው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ በመሆኑ ከእግዚአብሔር ጋር መስማማቱን አሳየ።

አቤል፥ በጉን አርዶ ደሙን በማፍሰስ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጐ ያቀረበው እግዚአብሔርን ስላመነ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። አቤል፥ እግዚአብሔር ለወላጆቹ ያስተማረውን አመነ። እግዚአብሔር ሰይጣንን ለመደምሰስና ሰውን ከሰይጣን ኃይል ለማዳን ታላቅ ነፃ አውጪ እንደሚልክ ተስፋ ሰጥቶ ነበር።

እግዚአብሔር፥ በአቤል መሥዋዕት ደስ ተሰኝቷልን? እግዚአብሔር አቤልን ተቀበልን? አዎን ተቀብሏል። እግዚአብሔር ባቀረበው መሥዋዕት እጅግ ደስ ስለተሰኘ አቤልን ተቀበለው።

የእንስሳት ደም የኃጢአትን ደመወዝ ሊከፍል ጨርሶ እንደማይችል መረዳታችን በጣም አስፈላጊ ነው። የአቤል የኃጢአት ደመወዝ ሞት በመሆኑ እግዚአብሔር በአቤል ሞት ፈንታ የበጉን መሥዋዕት አልተቀበለም። የኃጢአት ደመወዝን ኃጢአተኛው ለዘላለም ከእግዚአብሔር በመለየት መክፈል አለበት። እግዚአብሔር ግን

የአቤልን ኃጢአት ይቅር በማለት ተቀበለው። ምክንያቱም አቤል በራሱ ሳይሆን ነፃ አውጪ ሊልክ የተስፋ ቃል ኪዳንን በሰጠው በእግዚአብሔር ላይ ስለታመነ ነው።

መምህር ሆይ፡-

ሀ. በእያንዳንዱ ታሪክ ውስጥ አዳማጮችህ ጸጋን መረዳታቸው በጣም አስፈላጊ ነው። ሰው ለደኅንነቱ ሊያደርግ የሚችለው አንዳችም ነገር እንደሌለ ወደ መገንዘብ መምጣት አለባቸው።

ለ. በአፍሪካና በፊሊፒንስ የሚገኙ ሕዝቦች የአቤልን የመሥዋዕት በግ ታሪክ ተዛምዶ በተሳሳተ መንገድ ተረድተውታል። በአፍሪካ የሚገኙ ሕዝቦች ለእግዚአብሔር በግ ለመስጠት በጣም ፈቃደኞች ናቸው፥ ምክንያቱም የመንጋቸው ዋና ክፍል በግ በመሆኑ ነው። ከዚህ በተጻራሪ በፊሊፒንስ የሚኖሩ ሕዝቦች ግን ወደ ወንጌላውያኑ በመምጣት አዘኔታቸውንና ቁጣቸውን ገለጹ። በግ አይተው ሳያውቁና ሊያገኙ በማይችሉበት ሁኔታ ሆነው እግዚአብሔር በግን መሥዋዕት አድርገው እንዲያመጡ መጠየቁ ፈጽሞ ተገቢ አይደለም አሉ።

ስለዚህ አዳማጮችህ የእንስሳት ደም የኃጢአትን ደመወዝ እንደማይከፍልና ሊከፍል እንደማይችል መረዳታቸውን እርግጠኛ ሁን። የኃጢአት ደመወዝ እንዲከፈል የሰው ሕይወት መሰጠት አለበት። የእንስሳ ደም ከሰው ደም ወይም ሕይወት ጋር እኩል አይደለም (ዕብ. 10:4፥ 5)። እግዚአብሔር ኃጢአትን ዝም እንደማይል ሙሉ በሙሉ ግልጽ ማድረግህን አረጋግጥ። ኃጢአት በሙላት መከፈል አለበት። ኃጢአትን የምትሠራ ነፍስ ትሞታለች፥ ግለትም ለዘላለም ከእግዚአብሔር ትለያለች።

ረ. የቃየንን መሥዋዕት እግዚአብሔር ሳይቀበለው ቀረ።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ሊኖረው ያስፈልጋል። ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ዘፍጥረት 4:5 አንብብ። ቃየን ከእርሻው ፍሬ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን አቀረበ። እግዚአብሔር ግን ቃየንንና መሥዋዕቱን አልተቀበለም። ለምን? የቃየን የእርሻ ፍሬ መልካም ስላልነበረ ነውን? ወይስ እግዚአብሔር መሬት የምታበቅለውን ስለማይፈልግ ነው? አይደለም፥ ምክንያቱ ይህ አልነበረም። እግዚአብሔር የቃየንን መሥዋዕት ያልተቀበለው ከአቤል የባሰ ኃጢአተኛ ስለነበረ ነውን? አይደለም፥ እግዚአብሔር ያልተቀበለው በዚህ ምክንያት አልነበረም። አቤልም ሆነ ቃየን የተወለዱት ኃጢአተኞች ሆነው ነበር።

ስለዚህ እግዚአብሔር ቃየንንና መሥዋዕቱን ያልተቀበለው፥ ቃየን ወደ እግዚአብሔር የመጣው ኃጢአተኛ መሆኑን በማመንና በመቀበል ሳይሆን በራሱ መንገድ፥ በራሱ አስተሳሰብና እግዚአብሔር ባላዘዘው መንገድ በመሆኑ ነበር። ቃየን እግዚአብሔርን አላመነም። በእግዚአብሔርና ወደ እርሱ እንዲመጡበት በመረጣቸው መንገድ አልታመነም። እግዚአብሔር ያልተቀበለው ለዚህ ነው።

መምህር ሆይ፡- እምነትን ከአቤል መሥዋዕት ጋር አለማመንን ደግሞ ከቃየን ተግባር ጋር አያይዞ በአትኩሮት መናገር ተገቢ ነው። ከእምነት ይልቅ መታዘዝ ላይ ካተኰርን የሕዝቡ አእምሮ ከእምነት ይልቅ ወደተግባር እንዲያዘነብል እናደርገዋለን። እንደ ዕብራውያን 11 አሳብ መሠረት እግዚአብሔር አቤልንና መሥዋዕቱን ተቀበለ፥ ምክንያቱም አቤል በእግዚአብሔር አምኖ ነበር። በቃየንና በአቤል መካከል ያለው ትልቁ ልዩነት እምነት ነው።

ወደ ወንጌል በምንመጣበት ጊዜ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የምናገኘው በእምነት ብቻ መሆኑን ሕዝቡ እንዲገነዘብ፥ ለዚህ እግዚአብሔርን የማመን መሠረታዊ እውነት ግልጽና ጠንካራ መሠረት ከአሁኑ መጣል አለበት። ሆኖም በእምነትና በመልካም ተግባራት መካከል ያለው ግንኙነት ሚዛን ሊጠበቅ ያሻል። አቤል እግዚአብሔርን ስላመነ በግ መሥዋዕት አድርጐ አቀረበ። ኖኅ እግዚአብሔርን ስላመነ መርከብ ሠራ። አብርሃም እግዚአብሔርን ስላመነ የእግዚአብሔር ምርጫ ወደሆነው ስፍራ ሄደ።

ብሉይ ኪዳንን በምታስተምርበት ጊዜ ዕብራውያን 11ን አትጠቀም፤ ነገር ግን የብሉይ ኪዳንን ባሕርያት ድርጊት ለመተርጐም እንዲጠቅምህ በአእምሮህ ያዘው።

አዳምና ሔዋን ለራሳቸው የሠሩትን ልብስ እግዚአብሔር እንዴት እንዳልተቀበለ ታስታውሳለህ? እግዚአብሔር፥ የሠሩትን ልብስ ያልተቀበለው ለምን ነበር? ምክንያቱም በሚያደርጉት በማንኛውም ነገር ራሳቸውን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዲያገኙ ሊያደርጉ እንደማይችሉ ለማሳየት ነበር። ለአንድ ሥራ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ማግኘት ሥራው መሠራት ያለበት በእግዚአብሔር መንገድ መሆን አለበት። አዳምና ሔዋን ራሳቸውን የሚሸፍኑበት ልብስ እንዲያገኙ እንስሳቱ እንዲሞቱና ደማቸው እንዲፈስ ግድ ነበር።

በቃየንና በአቤል የሆነውም እንዲሁ ነበር። እግዚአብሔር በእርሱ ካልታመኑና እርሱ ባላቸው መንገድ ወደ እርሱ ካልቀረቡ አይቀበላቸውም ነበር። እግዚአብሔር የሚቀበላቸው በግ አምጥተው በእርሱ ፊት በማረድ ደሙን ካፈሰሱ በኋላ ብቻ ነበር። አቤል እግዚአብሔርን በማመን እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ ቀረበ፥ ስለዚህ እግዚአብሔር ተቀበለው። ቃየን ግን በራሱ መንገድ በመታመን ቀረበ፥ እግዚአብሔርም ሳይቀበለው ቀረ።

እግዚአብሔር አልተለወጠም። አሁንም ያው ነው። ወደ እርሱ የሚቀርበው በግ በማምጣትና በማረድ እንደሆነ ባይናገርም እንኳ እንዴት ወደ እርሱ መቅረብ እንደምንችል የሚነግረን እርሱ ነው። ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር መምጣት ያለብን እርሱ በሚለው መንገድ ነው። አለበለዚያ ቃየንን እንዳልተቀበለ እኛንም አይቀበለንም። የእግዚአብሔርን መልእክት በሚገባ አድምጡ። ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት የምትችሉበትን መንገድና ከሰይጣንና ከዘላለማዊ ቅጣት ነፃ የምትወጡበትን መንገድ ልታውቁ የምትችሉት በዚህ ሁኔታ ብቻ ነው።

ይህ ከረጅም ጊዜ በፊት ከዛፍ ላይ የቆረጥኩት ቅርንጫፍ ነው። ይህ ቅርንጫፍ አሁን ሞቷል፤ ምክንያቱም ሕይወትን ይቀበል ከነበረበት ከዛፉ ግንድ በመለየቱ ነው። አሁን ግን ይህ ቅርንጫፍ ተመልሶ

ሕይወት እንዲያገኝ መልሼ ከግንዱ ላጣብቀው ነው። ይህን ቅርንጫፍ ከግንዱ ጋር መልሼ ባስረው ወደ ሕይወት ይመልስ ይሆን? ቅጠሎቹስ ተመልሰው አረንጓዴ ይሆናሉ? ቅርንጫፎቹስ ማደግ ይጀምራሉ? አንደኛውም ነገር አይሆንም! ለመሆኑ ቅርንጫፉ ሕይወት እንዲኖረው ከግንዱ ጋር መልሼ ላጣብቀው የምችል ይመስላችኋልን? አልችልም። ይህ ቅርንጫፍ ሕይወት እንዲኖረው በዛፉ ላይ መልሼ ላጣብቀው አልችልም። ከዛፉ ስለለየሁት መልሼ ከዛፉ ጋር ላገናኘው አልችልም።

መምህር ሆይ፡- ይህ መግለጫ በተለይ በጣም የሚጠቅመው በራሳቸው የግል ጥረቶች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ወደ ትክክለኛው ሥፍራ ለመመለስ እንደሚችሉ አድርገው በማሰብ የተታለሉ ሰዎችን ለመርዳት ነው። አንድ ሰው ከግንዱ በመለየቱ የሞተውን ቅርንጫፍ መልሶ በግንዱ ላይ በማድረግ ሕይወት ሊሰጠው እንደማይችል ካሳየህ በኋላ፥ ቃየን ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር መልሶ ለማዋሐድ ካደረገው ከንቱ ሙከራ ጋር አዛምድ። ከዚህ በኋላ ይህን ትምህርት በቀጥታ ከሕዝቡ ጋር በማዛመድ፥ በራሳቸው ጥረት ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛና ለደኅንነት የሚያበቃ ግንኙነት እንፈጥራለን በማለት የሚያደርጓቸው ሙከራዎች የቃየንን ስሕተት መድገም እንደሆነ አሳያቸው።

የአዳም፥ የሔዋን፥ የቃየንና የአቤል ሁኔታ እንደተመለከትነው ነበር። አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ስላልታዘዙ ከእግዚአብሔር ተለዩ። ስለዚህ ቃየንና አቤል ከዔድን ገነት ውጪ ከእግዚአብሔር ተለይተው ተወለዱ። ከእግዚአብሔር ዘንድ ወዳለ ኅብረት ራሳቸውን ለመመለስ አልቻሉም።

አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዲያገኙ ለራሳቸው ኃፍረተ ሥጋቸውን መሸፈኛ ሠሩ፥ እግዚአብሔር ግን የሠሩትን መሸፈኛ ሳይቀበለው ቀረ። ቃየንም በራሱ መንገድ ወደ እግዚአብሔር መጣ፥ እግዚአብሔር እርሱንና መሥዋዕቱን ሳይቀበል ቀረ። ወደ እግዚአብሔር እንድንመለስና ወዳጆቹ እንድንሆን መንገድን ሊያዘጋጅልን የሚችል እግዚአብሔር ራሱ ብቻ ነው።

እኛ ሁላችንም የአዳም ዝርያዎች ነን። ሁላችንም በአባታችን በአዳም ምክንያት ኃጢአተኞች ሆነን ከእግዚአብሔር ተለይተን ተወለድን። ራሳችንን የእግዚአብሔር ወዳጆች ለማድረግ አንችልም። ወደ እግዚአብሔር የምንመለስበትን መንገድ ሊያዘጋጅ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ሰ. እግዚአብሔር የተቆጣውን ቃየንን ለማሳመን በቂ ምክንያት አቀረበ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

እግዚአብሔር፥ አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ዘፍጥረት 4፡6፥ 7 አንብብ። ቃየን እያወቀ እግዚአብሔርን ለማመን እምቢ በማለት በራሱ መንገድ ቢሄድም እንኳ እግዚአብሔር ወቅሶ ሊመልሰው ሞከረ። እግዚአብሔር አፍቃሪና ምሕረትን የተሞላ ስለሆነ ከቃየን ጋር በመነጋገር በትክክለኛው መንገድ ወደ እርሱ እንዲመለስ ለማድረግ ሞከረ።

እግዚአብሔር፥ ቃየን እንዲያውቅ የፈለገው ነገር እርሱም እንደ ወንድሙ እንደ አቤል እግዚአብሔርን በማመን፥ ደምን መሥዋዕት አድርጐ ቢያቀርብና እንደዚሁም እግዚአብሔር ነፃ አውጭ እንደሚሰጥ በሰጠው ተስፋ ቢደገፍ፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንደሚያገኝ ነበር።

ሸ. ቃየን እግዚአብሔርን መስማት እምቢ ብሎ አቤልን ገደለው።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 4፡8 አንብብ። ቃየን እጅግ ተቆጥቶ ነበር። እግዚአብሔርን አልሰማም። አባትና እናቱ በዔድን ገነት እንዳደረጉት ሰይጣንን አዳመጠ።

እግዚአብሔርን ለመስማት ያለመፍቀድ በጣም ሞኝነት ነው። በአዳምና በሔዋን ላይ እንደደረሰባቸው ሁልጊዜ ወደ ችግርና ሞት ያመራል።

እግዚአብሔር ዛሬ በቃሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ይናገረናል። ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች «መንፈላውያንን አትስሙ» ይሏችሁ ይሆናል። እኛ የምንነግራችሁ ግን እግዚአብሔር የሚለውን ነው። እንደ ቃየን በመሆን እግዚአብሔርን መስማት እምቢ አትበሉ።

ዋና አሳብ፡- ሰይጣን እግዚአብሔርንና ፈቃዱን ይዋጋል። እርሱ ውሸታምና አታላይ ነው፥ ሰውንም ይጠላል።

ቃየንን የሚመራው ማን ነበር? ቃየን የሚያዳምጠው ማንን ነበር? ሰይጣንን ነበር። ቃየን ወንድሙን አቤልን እንዲገድል ያሳሰበው ማን ነበር? ሰይጣን ነበር። ሰይጣን ነፍሰ ገዳይ ነው።

ሰይጣን፥ በመጀመሪያ የቃየንን አባትና እናት ገደለ። «አትሞቱም»፥ ምንም ችግር አይገጥማችሁም፥ እግዚአብሔርን አትስሙት፥ እግዚአብሔር መልካም የሆኑ አንዳንድ ፍሬዎችን እንዳትበሉ ለማድረግ ፈልጐ ነው በማለት ደልሏቸው ነበር። ነገር ግን አዳምና ሔዋን ይህ መልካምንና ክፉውን የሚያሳውቀውን ዛፍ ፍሬ ቢበሉ ሞትን እንደሚሞቱ ሰይጣን ያውቅ ነበር። «አትሞቱም» ሲላቸው እየዋሸ ነበር። ሰይጣን፥ አዳምና ሔዋን እንዲሞቱ እንደፈለገ ቃየንም፥ አቤልን እንዲገድለው ፈለገ። ሰይጣን ነፍሰ ገዳይ ነው።

ሰይጣን፥ ሰዎችን ሁሉ ስለሚጠላ በመዋሸትና በማታለል እርሱ ወደሚሄድበት የዘላለም ቅጣት ስፍራ እንዲሄዱ ይጥራል።

መምህር ሆይ፡- ምንም እንኳ ሰይጣን በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በቀጥታ ባይጠቀስም ውስጥ ውስጡን እንደነበረ ግን እናውቃለን። 1ኛ ዮሐ. 3፡12 ስለ ቃየን እንዲህ ይላል «...ከክፉው እንደ ነበረ ወንድሙንም እንደ ገደለ»። ሰይጣን ከመጀመሪያው ጀምሮ ውሸታምና ነፍሰ ገዳይ ነው (ዮሐንስ 8፡44)።

ቀ. የእግዚአብሔር ፍርድ በቃየን ላይ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው። እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ዘፍጥረት 4፡9 አንብብ። እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ በሚጠይቅበት ጊዜ ቃየን አቤልን እንደገደለው ያውቅ ነበር፤ በሚገድለው ጊዜ

ተመልከቶት ነበር። እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ ይገኛል፥ ሁሉን ያውቃል።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው። እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ዘፍጥረት 4፡10-15 አንብብ። እግዚአብሔር በሌሎች ሰዎች ላይ የሚሠራውን ኃጢአት ሁሉ የሚበቀል ነው። ምክንያቱም ኃጢአት ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ የሚሠራ ዓመፅ ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር የሰዎች ሁሉ ፈጣሪ ስለሆነ በሌሎች ሰዎች ላይ ጐጂ የሆነውን ነገር የተናገረ ወይም ያደረገን ማንኛውንም ሰው ይቀጣል።

የሠራኸውንና የምትወደውን ቆንጆ የሰሌን ባርኔጣ ሌላ ሰው ቢያበላሽብህና ቢያጠፋብህ ምንም አይሰማህምን? አንድ ሰው ሚስትህን፥ ልጅህን ወይም የምትወደውን ሰው ሲጐዳ ብታይ ዝም ብለህ ቆመህ ታያለህን?

እግዚአብሔር የሰዎች ሁሉ ፈጣሪ ነው። ለአዳም ሕይወትን ሰጠው፤ ደግሞም ለእያንዳንዳችን ሕይወትን ሰጠን። ከእግዚአብሔር የተለየን ብንሆንም እንኳ የእርሱ ነን።

አንድ ሰው ከብቶቻችሁን ቢሰርቅ እነዚያ ከብቶች የእናንተ ንብረት መሆናቸው ቀርቶ የሌባው ንብረት ይሆናሉን? ሌባው ከብቶቻችሁን ቢግድልባችሁም እንኳ ከብቶቹ የእናንተ መሆናቸው አይቀርም? አይደለም?

ሰይጣን፥ አዳምንና ሁላችንን ከእግዚአብሔር ቢሰርቅም እንኳ ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ናቸው። ስለዚህ እግዚአብሔር ሌሎች ሰዎችን የሚጐዱ ሰዎችን ይቀጣል።

ይህ ማለት እግዚአብሔር ክፉ ሥራዎችን ሁሉ ወዲያውኑ ይቀጣል ማለት አይደለም። ነገር ግን የኃጢአት ሁሉ ደመወዝ መከፈል አለበት። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው። በሌሎች ሰዎች ላይ ለሠራነው ኃጢአት የገንዘብ ካሣ መክፈላችን እግዚአብሔርን አያረካውም። እግዚአብሔር የእያንዳንዱ ሰው ባለቤት ስለሆነ ኃጢአት ሁሉ በመጨረሻ በእግዚአብሔር ይቀጣል።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል

ዘፍጥረት 4፡16 አንብብ። ቃየን እግዚአብሔርን ለመስማት ባለመፍቀድ ቀጠለ። የሰይጣንን መንገዶች በመከተል ከእግዚአብሔር ራቀ። ንስሐ አልገባም። በእግዚአብሔርና በኃጢአቱ ላይ ያለውን ዝንባሌ ለመለወጥ ሳይፈቅድ ቀረ።

የቃየን ዝርያዎች በእግዚአብሔር ላይ ማመጽን ከቃየን ተቀብለው ቀጠሉበት። ቃየንና ዝርያዎቹ ሲሞቱ ሁሉም ወደ ዘላለም ቅጣት ይሄዳሉ።

መምህር ሆይ፡- ስለ ንስሐ ስናስተምር መጠንቀቅ አለብን። ብዙ ሰዎች ንስሐ ማለት ማንኛውንም ኃጢአት አለመሥራት ወይም ላለመሥራት ቃል መግባት እንደሆነ ያስተምራሉ። ነገር ግን ይህ ትክክል አይደለም።

ንስሐ፥ ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ራስ ኃጢአት ያለንን ዝንባሌ መለወጥ ማለት ነው። ንስሐ ማለት አንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር ፊት ሆኖ «እግዚአብሔር ሆይ አንተ ትክክል ነህ፥ እኔ ደግሞ በደለኛ ነኝ። አንተ ያልከው ነገር ሁሉ መልካም፥ ጻድቅና ቅዱስ ነው። እኔ ወድቄያለሁ። በራሴ ምንም ተስፋ የሌለኝ ነኝ» ብሎ ደካማነቱንና በደለኛነቱን በግልጽ መናዘዝ ነው። ይህ ነው እውነተኛ ንስሐ የሚባለው።

ትእዛዝን ከመጠበቅ ወይም ከማድረግ ይልቅ በእምነት ላይ ማተኩርህን አረጋግጥ። መታዘዝ ላይ ካተኮርን አማኞችን ሳይሆን ተከታዮችንና አድራጊዎችን እናፈራለን።

እግዚአብሔር አንድን ኃጢአተኛ ከማዳኑ በፊት ኃጢአተኛውን ዳግም ኃጢአት እንዳይሠራ ቃል ይገባ ዘንድ አይጠይቀውም። እግዚአብሔር ከኃጢአተኛ ጋር አይደራደርም። አንተ ይህን ታደርጋለህ እኔ ደግሞ ይህን አደርጋለሁ አይልም። እግዚአብሔር ከደኅንነት በፊት ተሐድሶን አይጠይቅም።

ጥያቄዎች

1. ለእያንዳንዱ ሰው ሕይወት የሰጠ ማን ነው? እግዚአብሔር ነው።

2. ቃየንና አቤል የተወለዱት የት ነበር? ከዔድን ገነት ውጭ ነበር።

3. ቃየንና አቤል ኃጢአተኛ ሆነው የተወለዱትና ከእግዚአብሔር የተለዩት ለምን ነበር? በአባታቸው በአዳም ምክንያት ነበር።

4. እኛ ሁላችን ኃጢአተኞች ሆነን የተወልድነውና ከእግዚአብሔር የተለየነው ለምን ነበር? የእኛም አባት አዳም ስለሆነ ነው።

5. እግዚአብሔር አቤልንና መሥዋዕቱን የተቀበለው ለምን ነበር?

   ሀ. አቤል ኃጢአተኛ ስለሆነ ከዘላለም ቅጣት የሚያድነው እግዚአብሔር ብቻ በመሆኑ ተስማማ።

   ለ. አቤል በእግዚአብሔር አመነ። እግዚአብሔር ነፃ አውጪ እንደሚልክ ለአዳምና ሔዋን በገባው ቃልም ላይ ታመነ።

   ሐ. አቤል ለእግዚአብሔር በግ በማቅረብ እግዚአብሔር እንዳዘዘው አርዶ ደሙ እንዲፈስስ አደረገ።

6. እግዚአብሔር ቃየንንና መሥዋዕቱን ያልተቀበለው ለምን ነበር?

   ሀ. ቃየን ኃጢአተኛ ስለሆነ ከዘላለም ቅጣት ሊያድነው የሚችል እግዚአብሔር ብቻ በመሆኑ አልተስማማም ነበር።

   ለ. ቃየን በእግዚአብሔር ስላላመነ፤ እግዚአብሔር ሰይጣንን በመደምሰስ ሰውን የሚያድን ነፃ አውጪ እንደሚልክ የገባውን ቃል ኪዳንም አልተቀበለም ነበር።

   ሐ. ቃየን እግዚአብሔር እንዲያመጣ የጠየቀውን መሥዋዕት አላቀረበም።

7. እግዚአብሔር ቃየንን የማሳመኛ አሳብ በማቅረብ ከእርሱ ጋር የተነጋገረው ለምን ነበር? እግዚአብሔር ቃየንን ይወድ ስለነበረና ቃየን ኃጢአተኛ መሆኑን በማመን ትክክለኛውን መሥዋዕት ማምጣት እንዲችል ለማድረግ ነበር።

8. ቃየን እግዚአብሔርን በማመን ከእርሱ ጋር ስምምነት አደረገን? አላደረገም።

9. ቃየን ምን አደረገ? ተቆጣ። አቤልን ገደለው።

10. እግዚአብሔር ቃየን ያደረገውን ያወቀው እንዴት ነበር? እግዚአብሔር ሁሉን ስለሚመለከትና ስለሚያውቅ ነው።

11. እግዚአብሔር በሌሎች ሰዎች ላይ ክፉ በመናገራችንና በማድረጋችን የሚቀጣን ለምንድን ነው? ምክንያቱም ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር በመሆናቸው ነው። ስለዚህ ሌሎች ሰዎችን ስንጎዳና ስንበድል እግዚአብሔርንም እንበድላለን።

12. አንድን ሰው ብንበድልና ከሰውየው ጋር ያለንን ግንኙነት ካጣ በመከፈል ብናስተካክል እግዚአብሔር በደላችንን ይረሳልናል? አይረሳም። እግዚአብሔር ለኃጢአት ሁሉ የደነገገው ቅጣት ከእግዚአብሔር ተለይቶ ለሰይጣንና እርሱን ለተከተሉ ክፉ መናፍስት ወደተዘጋጀው የዘላለም ቅጣት ስፍራ መሄድ ነው።

13. ቃየን በመጨረሻ አስተሳሰቡን ቀየረን? አልቀየረም። እንዲያውም ከእግዚአብሔር እስከጭራሹ ኮበለለ።

14. ውጤቱ ምን ነበር? የቃየን ዝርያዎች የእርሱን ምሳሌነት ተከተሉ። ሁሉም ከእግዚአብሔር ተለይተው በመኖር ከእግዚአብሔር ተለይተው ሞቱ።

ትምህርት 15

የትምህርቱ ክፍል፡- ዘፍጥረት 4፡16-26፤ 5፡3-5፥ 22-32

አጠቃላይ ርእስ፡- የቃየን ዝርያዎችና ሴት፥ ሄኖክና ኖኅ።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. የቃየን ዝርያዎች አእምሮአቸው በቁሳዊ አስተሳሰብ የተሞላ ነበር (4፡16-24)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ለ. እግዚአብሔር አቤልን ለመተካት ሴትን ሰጠ (4፡25)።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ እንዲያሰኝና እንዲድን እምነት ሊኖረው ያስፈልጋል።

ሐ. የሴት ልጅ የሆነው ሄኖስ በተወለደበት ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ የነበረው እምነትና አምልኮ ታደሰ (4፡26)።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትና ጸጋን የተሞላ ነው።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

መ. አዳም ሞተ (5፡3፥ 4)።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሠ. ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ። (5፡22፥ 23)

ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ሊኖረው ያስፈልጋል።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ረ. እግዚአብሔር ሄኖክን ወሰደው (5፡24)።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ሰ. ኖኅና ልጆቹ ሴም፥ ካምና ያፌት (5፡25-32)።

የትምህርት 14 ጥያቄዎችን ከልስ።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

ሀ. የቃየን ዝርያዎች አእምሮአቸው በቁሳዊ አስተሳሰብ የተሞላ ነበር።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። እራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

የቃየን ዝርያዎች የእርሱን ምሳሌነት በመከተል ያለ እግዚአብሔር ኖሩ። የቃየን ዝርያዎች ሕይወት በቁሳዊና በዓለማዊ ነገሮች የተሞላ ነበር። ከተሞችን ይገነቡ፥ የከብት መንጋዎችን ያረቡ፥ ልዩ ልዩ ዕቃዎችንና የሙዚቃ መሣሪያዎችን ይሠሩ ነበር። አእምሮአቸውና ጊዜያቸው የሚፈልጉትን ነገሮች በማድረግ የተያዘ ነበር። በሰይጣን ቁጥጥር ሥር ነበሩ። ለእግዚአብሔርና እርሱ እንዲያውቁት ለሚፈልጋቸው ነገሮች ፍላጐት ወይም ጊዜ አልነበራቸውም፥ ዘፍጥረት 4፡16-24 አንብብ።

ለእግዚአብሔር ያለመታዘዝ በዓለም ላይ ያመጣውን እጅግ ጠንቀኛ ተጽዕኖ ተመልከት። አዳምና ሔዋን ኃጢአትን ስላደረጉ ልጆቻቸው በሙሉ ከእግዚአብሔር ተለይተው ከእግዚአብሔር ጋር የአእምሮ አንድነት ሳይኖራቸው ተወለዱ። የመጀመሪያ ልጃቸው ቃየን ሁለተኛ ልጃቸውን አቤልን ገደለ። ቃየን ለእግዚአብሔር ጀርባውን በመስጠት ቃሉቹን ሳይሰማ ቀረ። ስለዚህ የቃየን ልጆችና የልጅ ልጆች በእግዚአብሔር መንገድ ሳይሆን በራሳቸው መንገድ ሄዱ።

እግዚአብሔርንና የእርሱን እውነት ስላላወቁ በራሳቸው የኃጢአት ኑሮ ተመላለሱ። በሰይጣንና በውሸቱ ተመሩ።

ይህ አንድ ነገር ለመሥራትና ገንዘብ ለማግኘት ካላችሁ ከፍተኛ ፍላጐት የተነሣ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ጊዜ ለሌላችሁና ፍላጐት ላልሆነባችሁ ሰዎች ማስጠንቀቂያ ሊሆናችሁ ይገባል። መሥራት በጣም መልካም ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን እንዴት ታውቁት እንደምትችሉና ከሰይጣን ቁጥጥርና ዘላለማዊ ቅጣት እንዴት ነፃ እንደምትወጡ እንዲያስተምራችሁ ጊዜ ልትሰጡት ይገባል።

እናንተ ወላጆች ከእግዚአብሔር እውነት ብታፈነግጡና እግዚአብሔርን መስማት እምቢ ብትሉ ልጆቻችሁም የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽሞ ላይሰሙ ይችላሉ። እናንተ ኃላፊነት ያለባችሁ ለራሳችሁ ብቻ ሳይሆን ለልጆቻችሁ ጭምር ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ልታደምጡ ልጆቻችሁም ቃሉን እንዲያደምጡ ልታደርጉ ይገባል። ስለ እግዚአብሔር መልእክት በቤታችሁ፥ ወይም በሥራ ቦታችሁ፥ እርሻ ስታርሱ ወይም ገበያ ስትወጡ ሁሉ መነጋገር አለባችሁ።

የእግዚአብሔር መልእክት ጠቃሚና አስፈላጊ የሚሆነው የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብና ለመማር በምንሰባሰብበት ጊዜ ብቻ አይደለም። ነገር ግን በእያንዳንዱ የሕይወት ክፍላችን እጅግ አስፈላጊና ከሁሉ የላቀ ሊሆን ይገባል።

ለ. እግዚአብሔር አቤልን ለመተካት ሴትን ሰጠ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ዘፍጥረት 4:25 አንብብ። እግዚአብሔር፥ ለአዳምና ሔዋን ቃየን በገደለው በአቤል ምትክ ሌላ ልጅ ሰጣቸው። ስሙንም ሴት ብለው ጠሩት።

እግዚአብሔር፥ ሰይጣንን ድል የሚነሳ ነፃ አውጪ እንደሚልክ በዔድን ገነት ቃል ገብቶ ነበር። ይህ የተስፋ ቃል ኪዳን የሚሟላው በእግዚአብሔር በታመነው በአቤል የዘር ግንድ ነበር። ነገር ግን ቃየን አቤልን እንዲገድል ሰይጣን መራው። ሰይጣን፥ እግዚአብሔር ነፃ

አውጪ እንደሚልክ የገባውን የተስፋ ቃል ዕቅድ ለማኰላሸት የሚችለውን ሁሉ ይሞክር ነበር።

ይህ ማለት እግዚአብሔር ነፃ አውጪ ለመላክ ለሰው ልጅ የገባውን ቃል ኪዳን ከሽፎ ቀረ ማለት ነውን? አይደለም! እግዚአብሔር ሁልጊዜ የገባውን ቃል ኪዳን ይፈጽማል። ሰይጣን በሚያደርገው ነገር ተስፋ አይቆርጥም ወይም አሳቡን አይለውጥም።

እግዚአብሔር በአቤል ምትክ ለአዳምና ለሔዋን ሴትን ሰጠ።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ሴት፥ ከእግዚአብሔር ተለይቶ የተወለደ ቢሆንም እንኳ አቤል እንዳደረገው በእግዚአብሔር ታመነ።

እግዚአብሔር ነፃ አውጪው በሴት የዘር ግንድ በኩል እንዲመጣ ዐቀዶ ነበር።

ሐ. የሴት ልጅ የሆነው ሄኖስ በተወለደበት ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ የነበረው እምነትና አምልኮ ታደሰ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ዘፍጥረት 5፡26 አንብብ። ሴት ዕድሜው ሲደርስ ሚስት አገባ። ሚስቱም ወንድ ልጅ ወለደች፥ ስሙንም ሄኖስ ብለው ጠሩት።

እግዚአብሔር በመጽሐፉ ውስጥ የሚነግረን ይህ ልጅ በተወለደበት ጊዜ የሴት የቤተሰብ ግንድ እግዚአብሔርን ማስታወስና ምን ያህል እንደሚያስፈልጋቸው ማሰላሰል ጀመሩ። ወደ እግዚአብሔር መቅረብና እንዲቀበላቸው መጣራት ጀመሩ።

አቤል ወደ እግዚአብሔር የመጣበትንንና ተቀባይነት እንዲያገኝ የጠየቀበትን ሁኔታ ታስታውሳለህን? አቤል፥ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጐ ያቀረበው ምን ነበር? እግዚአብሔር አቤልንና መሥዋዕቱን ተቀበለን? እግዚአብሔር አቤልንና መሥዋዕቱን

የተቀበለው ለምን ነበር? እግዚአብሔር አቤልን የተቀበለው ኃጢአተኛ ስለመሆኑ ከእግዚአብሔር ጋር በመስማማቱና እግዚአብሔር ነፃ አውጪ እንደሚልከ የገባውን ቃል ኪዳን በማመን እግዚአብሔር አምጡ ያለውን የደም መሥዋዕት በማቅረቡ ነው።

ሴትና ልጁ ሄኖስ፥ እንደዚሁም ቤተሰቡና ተከታታይ ትውልዶቹ ወደ እግዚአብሔር መምጣት የጀመሩት በዚህ መልክ ነበር። አቤል ወደ እግዚአብሔር በመጣበት መንገድ መጡ። ወደ እግዚአብሔር በእምነት በመምጣት በግ አርደው ደሙን አፈሰሱ።

እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው የሚመለከትበት መንገድ አንድ በመሆኑ ተቀበላቸው። እግዚአብሔር ግንንም በተለየ መንገድ አይመለከትም። ጥቁር ወይም ነጭ፥ ሃብታም ወይም ድሃ፥ ወጣት ወይም ሽማግሌ፥ ወንድ ወይም ሴት ልጆች ቢሆኑ እግዚአብሔር በፈለገው መንገድ ወደ እርሱ ቢመጡ ይቀበላቸዋል።

የሴት ዝርያ የሆኑ ሰዎች በእግዚአብሔር ቢያምኑም እንኳ አብዛኛው ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር አልመጡም ነበር። የሚኖሩት ለዚህ ዓለም ሕይወት ብቻ ነበር። ከእግዚአብሔር ስለመለየታቸውና በመሞት ለዘላለም ከእግዚአብሔር የሚለዩ ስለመሆናቸው ግድ አልነበራቸውም።

መ. አዳም ሞተ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 5፡3፥ 4 አንብብ። አዳም 930 ዓመታት ኖረ። አዳምና ሔዋን ሁለቱም ሞቱ። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሲፈጥራቸው እንዲሞቱ አላቀደም ነበር። በመጀመሪያ በዓለም ላይ ሞት አልነበረም። አዳምና ሔዋን የሞቱት ኃጢአት ከእግዚአብሔር ስለለያቸውና ከሕይወት ዛፍ ፍሬ እንዳይበሉ እግዚአብሔር ስለከለከላቸው ነበር።

ሁላችንም የአዳም ዝርያዎች ስለሆንን ሞት በዓለም ላይ ቀጥሏል።

ሠ. ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሰው እግዚአብሔርን ደስ እንዲያሰኝና እንዲድን እምነት ሊኖረው ያስፈልጋል። ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ዘፍጥረት 5፡22፥ 23 አንብብ። መጽሐፍ ቅዱስ አሁን የሚነግረን የሴት ዝርያ ስለሆነው ሄኖክ ስለተባለው ሰው ነው።

ሄኖክ የተወለደው ኃጢአተኛ ሆኖ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔርን አመነና እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ ወደ እርሱ ቀረበ። ሄኖክ፥ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረግ እግዚአብሔርን ደስ አሰኝቷል።

ሄኖክ በጊዜው ለነበሩ ሕዝቦች የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነበር። በዚያን ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ አልነበረም። ነገር ግን ለሕዝቡ የሚነግረውን ነገር እግዚአብሔር ለሄኖክ ይነግረው ነበር። ሄኖክ፥ ሕዝቡን ባለማመናቸውና በክፉ መንገዶቻቸው እግዚአብሔር እንደሚፈርድባቸውና እንደሚቀጣቸው በመናገር አስጠነቀቃቸው። ይህም ሆኖ ከሕዝቡ አብዛኛው አላመኑም ነበር።

መምህር ሆይ፡- ይሁዳ 14፡15 ተመልከት። እነዚህ ቀደምት አማኞች ታሪካቸው በአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ከተመዘገበበት በላቀ ሁኔታ ልባቸው የበራና የተረዱ እንደነበር እንገነዘባለን። እንዲያውም ሄኖክ ክርስቶስ በዓለም ላይ ሊፈርድ እንደሚመጣም አስቀድሞ ተናግሯል።

ረ. እግዚአብሔር ሄኖክን ወሰደው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ዘፍጥረት 5፡24 አንብብ። ሄኖክ ኃጢአተኛ የነበረና የእግዚአብሔር ምሕረት የማይገባው ቢሆንም እንኳ እግዚአብሔር ሄኖክን ስለወደደውና ስለተቀበለው ከዚህ ዓለም ወሰደው።

እግዚአብሔር፥ ሄኖክን ወዴት ወሰደው? ወደ መንግሥተ ሰማያት ወሰደው። ሰይጣንና መናፍስት በእግዚአብሔር ላይ ከማመፃቸው በፊት ይኖሩ የነበረው በዚያ ነበር። እግዚአብሔርና መላእክቱ አሁንም የሚኖሩት በዚያ ነው።

መንግሥተ ሰማያት ምንም ዓይነት ፍርሃት፥ ሐዘን፥ በሽታ ወይም ሞት የሌለበት ውብ ቦታ ነው። በዚያ ለሚኖሩ እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ ይሰጣቸዋል።

ከመካከላችሁ አሜሪካ የነበራችሁ ስንቶች ናችሁ? ብዙዎቻችሁ አሜሪካንን ባታዩም እንኳ ስለ አሜሪካ ሰምታችኋል። ቦታው እውነተኛ ቦታ ነው? ሰዎች እንደሚያወሩት በርካታ ቤቶች፥ ሕንፃዎች፥ ሰዎችና መኪናዎች በአሜሪካ አሉን? አዎን ሰዎች እንደሚሉት የተለያዩ ነገሮች ያሉበት ትክክለኛ ቦታ ነው። እናንተ በዚያ ያልነበራችሁና ጨርሶ ያላያችሁት ቢሆንም እንኳ እውነተኛ ቦታ ነው።

መንግሥተ ሰማያትም እንደዚሁ ነው። ሆኖም በዚህ ዓለም ላይ አይደለም፤ ከጨረቃ፥ ከፀሐይና ከከዋክብት እጅግ ርቆ የሚገኝ ሰፍራ ነው። ከመካከላችን በዚያ የነበረ ወይም ያየው ሰው ባይኖርም እንኳ እውነተኛ ቦታ ነው። እግዚአብሔር ሄኖክን የወሰደው ወደዚያ ሰፍራ ነው። ሄኖክ አልሞተም። ከነሕይወቱ እግዚአብሔር ወሰደው።

መምህር ሆይ፡- መንግሥተ ሰማያት እውነተኛ ሰፍራ መሆኑን ለመናገር ጊዜ ውሰድ፥ ስለሚያውቁት ነገር ግን ስላላዩት አንድ ከተማ ንገራቸው። አንተ ወይም ከመካከላቸው ያለ አንድ ሰው የነበረበትን ቦታ ምረጥ። ለምሳሌ፡- አሜሪካ ስዊድን ወይም ጀርመን፤ እነዚህ ሰፍራዎች እሩቅ ስለሆኑ አንዳንድ ጊዜ አፈታሪክ ይመስላሉ። አንተ ግን በዚያ ነበርክ፥ ቦታዎቹ እውነተኛ ቦታዎች ናቸው። ይህን ሁኔታ ከመንግሥተ ሰማይ ጋር በማመሳሰል አቅርብ። እስካሁን ያላየነው ወይም በዚያ ያልነበርንበት ቢሆንም እንኳ እውነተኛ ቦታ ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ናቸው። እግዚአብሔር በማንኛውም ሰው ላይ የሚፈልገውን ማድረግ ይችላል። እግዚአብሔር ሄኖክን የወሰደው ሄኖክ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመሄድ ስለፈለገ ብቻ

አልነበረም። እግዚአብሔር ሊወስደው ዐቅዶ ነበር። እግዚአብሔር አንድ ነገር ለማድረግ ሲፈልግ ማንንም ሊጠይቅ አያስፈልገውም። ከእግዚአብሔር የሚበልጥ የለም። እርሱ ከማንምና ከምንም በላይ ነው።

ሰ. ኖኅና ልጆቹ ሴም፥ ካምና ያፌት

በቅደም ተከተል ማሳያ ሠንጠረዥ ላይ፡- ኖኅ፥ ሴም፥ ካምና ያፌት የሚሉትን ስሞች አሳይ።

በዚህ ጊዜ ሳይሞት ወደ መንግሥተ ሰማያት የተወሰደው ሄኖክ ብቻ ነበር። በዚያ ዘመን የኖሩ ሌሎች ሰዎች ግን ረጅም ዕድሜ እየኖሩ ይሞቱ ነበር። ከሰዎች ሁሉ በላይ ረጅም ዕድሜ የኖረው የሄኖክ ልጅ ማቱሳላ ነበር። ዘፍጥረት 5፡25-27 አንብብ።

የማቱሳላ የልጅ ልጅ ስም ኖኅ ይባል ነበር። ዘፍጥረት 5፡28-32 አንብብ። የኖኅና የሦስቱ ልጆቹ፥ የሴም፥የካምና የያፌት ታሪክ በጣም አስፈላጊ ነው። በሚቀጥለው ትምህርታችን ስለ እነርሱ እናጠናለን።

ጥያቄዎች

1. ቃየንና ዝርያዎቹ የኖሩለት ዋና ዓላማ ምን ነበር? ገንዘብና ለሕይወት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ነበር።

2. እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ሊኖረው የሚገባ ስፍራ ምንድን ነው? በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት የመጀመሪያ ስፍራ ሊይዝ ይገባዋል።

3. እግዚአብሔር ሴትን የሰጠው ለምን ነበር?

   ሀ. አቤልን ለመተካት።

   ለ. ነፃ አውጪው በእርሱ የዘር ግንድ በኩል እንዲመጣ ለማድረግ።

4. ይህ ስለ እግዚአብሔር ምን ያስተምረናል? እግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳን የማይረሳና ያቀደውን ከማድረግ የሚያግደው አንዳችም ኃይል የሌለ አምላክ መሆኑን ነው።

5. አዳምና ሔዋን ለምን ሞቱ? እግዚአብሔርን ስላልታዘዙና በሥጋም እንዲሞቱ ከሕይወት ዛፍ ስላራቃቸው ነበር።

6. አሁንም ድረስ ሰዎች የሚሞቱት ለምንድን ነው? ሁላችንም የአዳም ዘሮች ስለሆንን ነው።

7. ሴት፥ ሄኖስ፥ ሄኖክና ሌሎች ወደ እግዚአብሔር የመጡት እንዴት ነበር? አቤል በመጣበት መንገድ ነበር። በእግዚአብሔርና በተስፋ ቃሉ በመታመን መጡ። በግ አርደው ደሙን አፍስሰው ቀረቡ።

8. በሄኖክ የሆነው ያልተለመደ ነገር ምንድን ነው? በእግዚአብሔር ወደ መንግሥተ ሰማያት መወሰዱ ነው።

9. መንግሥተ ሰማያት ያለው በየት ነው? ከፀሐይ፥ ከጨረቃና ከከዋክብት እጅግ ርቆ ነው።

10. ሄኖክን ለመውሰድ እግዚአብሔር ምን ሥልጣን ነበረው? ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ናቸው። እግዚአብሔር በሰዎች ሊያደርገው የሚፈልገውን ሁሉ ያደርጋል።

ትምህርት 16

የትምህርት ክፍል፡- ዘፍጥረት 6፡1-22

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር ዓለምን እቀጣለሁ አለ። ነገር ግን ኖኅንና ወደ መርከቡ የሚገቡትን ሁሉ ለማዳን ቃል ገባ።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. የሕዝብ ቁጥር እጅግ ጨመረ (6፡1፥ 2)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ለ. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ለመመለስ ይታገል ነበር (6፡3)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትና ጸጋን የተሞላ ነው።

ሐ. ክፋት እጅግ ጨመረ (6፡5፥ 11)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

መ. እግዚአብሔር የማያምነውን ዓለምና ኃጢአቱን ተመለከተ (6፡5፥ 12)።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ሠ. እግዚአብሔር ዓለምን ለማጥፋት ወሰነ (6፡6፥ 7)።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ረ. እግዚአብሔር ለኖኅ እጅግ ቸር ነበር (6፡8-10)።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ሰ. እግዚአብሔር ለኖኅ ትእዛዛትን ሰጠው (6፡13-21)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ሸ. ኖኅ እግዚአብሔርን ታዘዘ (6፡22)።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ቀ. ኖኅ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነበር።

. ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

የትምህርት 15 ጥያቄዎችን ከልስ።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ።

ሀ. የሕዝብ ቁጥር እጅግ ጨመረ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 6፡1-2 አንብብ። አዳም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ 1500 ዓመታት አልፈዋል፤ ቃየን፥ አቤልን ከገደለ ረጅም ጊዜ አልፎአል። በዚህ ጊዜ በምድር የሚኖረው ሕዝብ ቁጥር እጅግ ብዙ ነበር። አብዛኛዎቹ ሰዎች ለእነርሱ መልካም መስሎ በሚታያቸው ነገር ላይ ጊዜያቸውን በማሳለፍ ብቻ ደስ ይሰኙ ነበር። በፍትወተ ሥጋ ፍላጐትና በመጋባት ላይ ብቻ በማተኰር እግዚአብሔርን እንዴት ደስ እንደሚያሰኙ የሚያስቡበት ጊዜ አልነበራቸውም።

መምህር ሆይ፡- ማቴዎስ 24፡37-39 የእነዚህን ሰዎች ዝንባሌ ይገልጻል። (ይህንን ክፍል አትጥቀሰው፥ ነገር ግን በምታስተምርበት ጊዜ እንደመመሪያ ተጠቀምበት)።

ለ. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ለመመለስ ይታገል ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው። እግዚአብሔር የዚህን ሕዝብ ኃጢአት ተመለከተ፤ ጠላውም። ነገር ግን ሕዝቡን ስለሚወድ ንስሐ እንዲገቡ ፈለገ። አእምሮአቸውን እንዲለውጡና መሳሳታቸውን እንዲቀበሉ በእርሱም እንዲያምኑ ይፈልግ ነበር። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ንስሐ እንዲገቡ ያለማቋረጥ ቢነግራቸውም ፈቃደኛ ሆነው አልተገኙም።

ዘፍጥረት 6፡3 አንብብ። እግዚአብሔር፥ የእርሱ የሆነውን መልእክት ሁልጊዜ ያለማቋረጥ እንደማይነግራቸው በማሳወቅ አስጠነቀቃቸው። እርሱን አልሰማ በማለት ከቀጠሉ ሰይጣንን እንዲከተሉ በመተው እንደሚቀጣቸው ተናገረ። እግዚአብሔር 120 ዓመታት እንደሚሰጣቸው ነገራቸው። በ120 ዓመታት ውስጥ ንስሐ ካልገቡ እንደሚቀጣቸው ነገራቸው።

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በአእምሮአችን ይናገረናል፥ ደግሞም በሌሎች ሰዎች በኩል ይናገረናል። ሰይጣንም፥ በበኩሉ በአእምሮአችን ውስጥ ስለሚናገረን አንዳንድ ጊዜ በውስጣችን ጦርነት እየተካሄደ ያለ ይመስላል። የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ድምፅ እንዲህ ይላችኋል «የእግዚአብሔርን መንገድ አድምጡ በእርሱም ተደገፉ»። የሰይጣንና የመናፍስቱ ድምፅ እንዲህ ይላችኋል «የእግዚአብሔርን መልእክት አትስሙ የአባቶቻችሁን እምነቶችና ወጐች አትተዉ።»

የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማትና ማመን እምቢ ብትሉ ግን የሚናገራችሁ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ድምፅ ትታችሁ ሊሄድ ይችላል። ድምፁ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን እንድታምኑ ለማድረግ አይሞክርም ይሆናል። በእርሱ ለማመንና ከእርሱ ጋር ለመስማማት ፈቃደኛ ባለመሆን ብትቀጥሉ ድምፁ ቀስ በቀስ እየቀነሰ የራሳችሁን መንገድ እንድትሄዱ ይተዋችኋል። ስትሞቱ ከእግዚአብሔር ለዘላለም መለየት ወደሆነው ዘላለማዊ ቅጣት ትሄዳላችሁ።

ሐ. ክፋት እጅግ ጨመረ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 6፡5፥11 አንብብ። አብዛኛው ሕዝብ ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለበትን የቃየን መንገድ ተከተለ። የበለጠ ኃጢአተኛ እየሆኑ መጡ። የእግዚአብሔርን መልእክት ለማመንና በእርሱና በምሕረቱ ለመደገፍ ሳይፈቅዱ ቀሩ።

እነዚህ ሕዝቦች የአዳም ዝርያዎች ስለነበሩ ኃጢአተኞች ሆነው የተወለዱ ነበሩ። በተጨማሪ ኃጢአታቸውን በመውደድ ሆን ብለው ከእግዚአብሔር ጋር ሳይስማሙ ቀሩ። እስቲ እያደረጉት የነበሩትን ነገሮች አድምጡ። እናንተስ ከእነዚህ ነገሮች በስንቶቹ የጥፋተኝነት ስሜት ይሰማችኋል? ሕይወታቸው በሙሉ እንደ እግዚአብሔር አመለካከት ትክክለኛ ባልሆኑ ነገሮች ቁጥጥር ሥር ነበር። ለሚያዩትና ለሚገምቷቸው ነገሮች ሁሉ ስግብግብ ነበሩ። የሌሎችን ይመኙ ነበር። ቀናተኞችና ሰውን የሚጠሉ ነበሩ። ሁልጊዜ በጠብ ላይ ነበሩ። ጨካኞችና ብዙዎችን የሚገድሉ ነበሩ። አንዱ ሌላውን ያሞኝ፥ ይዋሽና ያታልል ነበር። ሌሎችን በክፉ ማማት የዘወትር ተግባራቸው ነበር።

መምህር ሆይ፡- የሕዝቡን የሥነ-ምግባር ሁኔታዎች በምትገልጥበት ጊዜ ሮሜ 1፡18-32 ላይ ያለውን ክፍል በመጠቀም በኖኅ ዘመን የነበሩ ሰዎችን ክፉት ለመግለጽ ተጠቀምበት። ከጥፋት ውኃ በፊት የነበሩትን ሰዎች ዝንባሌዎችና የሥነ-ምግባር ውድቀቶች በሚገባ ይገልጻል።

እነዚህ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ እኛ ሁላችን የአዳም ልጆች ነን። እኛ ሁላችን ከአዳም ወገን ስለሆንን ከዔድን ገነት ውጪ ከእግዚአብሔር ተለይተን የተወለድን ኃጢአተኞች ነን። ሰዎች ሁላችን ኃጢአትን የምናደርገው ከእግዚአብሔር ተለይተን ኃጢአተኞች ሆነን ስለተወለድን ነው። ሰዎች ኃጢአትን የሚያደርጉት ኃጢአታቸውን ስለሚወዱም ነው። ማንም ሌላውን ሊወነጅል አይችልም።

መ. እግዚአብሔር የማያምነውን ዓለምና ኃጢአቱን ተመለከተ

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ዘፍጥረት 6:5፥ 12 አንብብ። እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን በሙሉ ተመለከተ፤ ሰዎች አታላይነታቸውን፥ አምንዝራነታቸውን፥ ሌብነታቸውንና ነፍሰ ገዳይነታቸውን ከሌሎች ሰዎች ይደብቁ ይሆናል። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ሊደብቁት አይችሉም። እርሱ ሁሉን ያያል።

እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ ያያል። ማንም ሰው ከእግዚአብሔር ምንም ነገር ሊደብቅ አይችልም። እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ስለሚገኝ ሁሉን ነገር ሁልጊዜ ያያል። በጫካ በምትሆኑበት ወይም እጅግ በሚጨልምበትና ማንም ሊያያችሁ በማይችልበት ቦታ ይህንን አስታውሱ። አስታውሱ! እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያያል፥ ደግሞም እርሱ ፈራጅ ነው። እርሱ ኃጢአትን ሁሉ ይቀጣል።

ሠ. እግዚአብሔር ዓለምን ለማጥፋት ወሰኖ ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ዘፍጥረት 6:6፥ 7 አንብብ። ሰዎች በክፋታቸው እጅግ እየባሱ ስለሄዱ እግዚአብሔር፥ ሰውንና ለሰው የተፈጠሩ ነገሮችን በሙሉ ለማጥፋት ወሰነ።

እግዚአብሔር፥ በንስሐ ያልተመለሱና በእርሱ ያልተደገፉትን ሁሉ በእርግጥ የሚያጠፋ ይመስልሃልን? አዎን እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ ያደርጋል። እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን በዔድን ገነት በነበሩበት ጊዜ «ካልታዘዛችሁኝ ትሞታላችሁ። ከእኔ ትለያላችሁ» ብሏቸው ነበር። አልታዘዙምና ልክ እግዚአብሔር እንዳለው ሞቱ። እግዚአብሔር ለቃየንና ለአቤል ወደ እርሱ በመቅረብ ተቀባይነት ለማግኘት ከፈለጉ በግ አምጥተው ደሙን ሊያፈሱ እንደሚገባ ገለጸላቸው። እግዚአብሔር ያለውን አደረገ። ቃየን በራሱ መንገድ ስለ መጣ ሳይቀበለው ቀረ። በኖኅ ጊዜ እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንዲህ አለ። «ካልሰማችሁኝ ምድርን አጠፋለሁ ታላቅ ዝናም አመጣለሁ። ከዚህ በፊት ዘንቦ የማያውቅ ዝናብ ይዘንባል። እናንተና እንስሳት በሙሉ በጕርፍ ትጥለቀለቃላችሁ።» እግዚአብሔር በዚህ ጊዜ ያለውን በእርግጥ ያደርጋል ብለህ ታስባለህን? እግዚአብሔር፥ በእርግጥ ቃሉን

ይጠብቃልን? ይህ ነገር ማስፈራሪያ ዛቻ ብቻ ነበርን? በምትቆጡበት ጊዜ ሁሉ ሌሎች ሰዎችን ታስፈራራላችሁ። ነገር ግን ያላችሁትን ሁሉ ሁልጊዜ ታደርጉታላችሁን? ሁልጊዜ አታደርጉትም። እግዚአብሔር እንደ ሰዎች ነውን? ዝም ብሎ ማስፈራሪያ ዛቻ ያደርጋልን? አያደርግም! እርሱ የተናገረውን ሁሉ ሁልጊዜ ይፈጽማል።

ሠ. እግዚአብሔር ለኖኅ ቸር ነበር

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እግዚአብሔር አፍቃሪና መሐሪ ስለሆነ የማያጠፋው አንድ ሰው ነበር። ዘፍጥረት 6፡8-10።

የአዳም ዝርያዎች በሙሉ እንደሆኑት ሁሉ ኖኅም በሰይጣን ቁጥጥር ሥር የተወለደ ኃጢአተኛ ነበር። ኖኅ፥ እግዚአብሔር ያድነው ዘንድ የሚገባው አልነበረም። እርሱም ደግሞ ቅጣት የሚገባው ነበር።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ያሰኝ ዘንድ እምነት ያስፈልገዋል።

ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ነገር ግን ኖኅ፥ እንደ አቤል፥ ሴትና ሄኖክ ወደ እግዚአብሔር የእንስሳትን ደም በማቅረብ ቀረበ። ኖኅ እግዚአብሔር ያለውን ነገር አደመጠ። ንስሐ በመግባትና በማመን እግዚአብሔር በነገረው መንገድ ወደ እርሱ ቀረበ።

ኖኅ፥ እግዚአብሔር በሚመጣው ነፃ አውጪ በኩል እንደሚያድነው አመነ። እግዚአብሔር በጸጋው ኖኅን ይቅር ብሎ ተቀበለው።

ጸጋ ማለት ምን ማለት እንደሆነ መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። ቀጥሎ የምንገራችሁ ታሪክ እውነተኛ ታሪክ አይደለም። ነገር ግን ጸጋን ለመግለጥ እንጠቀምበታለን።

አንድ ሰው ሁልጊዜ ከአንድ ከሌላ ሰው ይሰርቃል። አንድ ቀን ይህ የተሰረቀው ሰው ከዓሣ ማጥመድ ሥራው ሲመለስ ሌባውን የሞላ ወንዝ ሊወስደው ሲያንገላታው አገኘው። ሊሰምጥ ጥቂት እስከሚቀረው በጣም ተደክክሞ ነበር። የተሰረቀው ሰው ግን ከውኃው ውስጥ ጐትቶ አወጣው። ሌባ መሆኑን ቢያውቅም እንኳ ወደ ቤቱ ወሰደውና ረዳው። ለጤንነቱ የሚገባውን እንክብካቤ አደረገለት አበረታው፥ እንጂ ያን ክፉ የስርቆት ሥራውን ጨርሶ አላነሳበትም።

እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የሚስማሙትንና በእርሱ የሚደገፉትን የሚንከባከበው እንደዚሁ ነው። እግዚአብሔር ሊቀጡ የሚገባቸውን ያድናል።

ኖኅ በእግዚአብሔር ጸጋ ዳነ። ኖኅ ሊድን አይገባውም ነበር። የእግዚአብሔር ችሮታ እንዲደረግለት ያደረገው አንዳችም ነገር የለም።

ሰ. እግዚአብሔር ለኖኅ ትእዛዛትን ሰጠ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ሕዝቡ እጅግ በክፉቱ እየጨመረ ስለሄደና አሳባቸውን ለውጠው ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት ስላልፈቀዱ በጥፋታቸው ሊቀጣቸው የወሰነውን ውሳኔ ሊገፋበትና ምድርን ሁሉ ሊያጠፋ እግዚአብሔር ወሰነ።

የኖኅና የቤተሰቦቹ ጉዳይስ? እንዴት መዳን ይችላሉ? እግዚአብሔር ለኖኅ የተናገረውን አድምጡ። ዘፍጥረት 6፡13-21 አንብብ። እግዚአብሔር፥ ለኖኅ ምድርን ሁሉ የሚሸፍን ጐርፍ እንደሚያመጣ ተናገረው፥ በተጨማሪም በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሁሉ ሊጠለሉበት የሚችሉትን ትልቅ መርከብ እንዲሠራ እግዚአብሔር ኖኅን አዘዘው።

ዋና አሳብ፡- ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ይህ መርከብ፥ እግዚአብሔር ለኖኅ በነገረው መሠረት መሠራት ነበረበት። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሊከተል የግድ ያስፈልግ ነበር። መርከቢቱ በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት መገንባት ነበረባት።

እግዚአብሔር ለኖኅ እንዲህ አላለውም። «ኖኅ፥ እነሆ በዓለም ላይ እፈርድ ዘንድ ወስኜአለሁ። ታላቅ የጐርፍ ጥፋት ላመጣ ነው። ስለዚህ አንድ ነገር ብታደርግ ይሻላል። ስለዚህ አሁን መርከብን ሥራ»። እግዚአብሔር እንዲህ አላደረገም። በምትኩ እግዚአብሔር ኖኅን አንድ ትልቅ መርከብ እንዴት መሥራት እንዳለበት መመሪያን ሰጠው። እንዴት መሥራት እንዳለበት በትክክል ነገረው። ይህን መርከብ ለመሥራት ኖኅ የራሱን ዕቅድ አላበጀም።

የአዳምና የሔዋን ልብስ የተሠራው በዚሁ መንገድ ነበር። እነርሱ ለራሳቸው የሠሩት ልብስ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም ነበር። ልብሳቸው እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ መሠራት ነበረበት። የቃየንና የአቤል መሥዋዕትም እግዚአብሔር በተናገረው መንገድ መሆን ነበረበት። መርከቢቱም በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት መሠራት ነበረባት።

እግዚአብሔር፥ ስለዚህች መርከብ አሠራር ለኖኅ ከተናገረው ውስጥ እንድታስታውሱት የምፈልገው አንድ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነ ነጥብ አለ። እግዚአብሔር ለዚህች ትልቅ መርከብ እንዲሠራ ያዘዘው አንድ የጐን በር ብቻ ነበር። ወደ ውስጥ ለመግባት የሚቻልበት አንድ መንገድ ብቻ ነበር። ከእግዚአብሔር ፍርድ ለመዳን እያንዳንዱ እንስሳና እያንዳንዱ ሰው በዚህ በር መግባት ነበረበት። ሰዎች ከእግዚአብሔር ቁጣ ሊድኑበት የሚችሉት አንድ መርከብ ብቻ ነበር። ወደ መርከቢቱ ለመግባት የሚቻለው በአንድ በር ብቻ ነበር።

መምህር ሆይ፡- የመዳኛው መርከብ አንድ ብቻ የመሆኑን ጉዳይና ወደዚያ የሚገባበት በር አንድ ብቻ መሆኑ ስለ ክርስቶስና ስለ ወንጌል መልእክት ለመናገር የሚጠቅም ስለሆነ በቂ አትኩሮት ስጥበት፥ አሁን ግን ቀጥተኛ ተዛምዶውን አትናገር። በማስተማር ሥራህ እየቀጠልክ ስትሄድ ይህ ነጥብ ጠቃሚ ይሆናል። ስለዚህ በዚህ ደረጃ ላይ በጥንቃቄ ማንሣት ያስፈልጋል። እንደነዚህ ዓይነት ነጥቦችን በቀላሉ ጨርፈህ አትለፋቸው። ቆይተህ ወንጌልን ስታስተምር በሚገባ የምትጠቀምባቸው አስፈላጊ መሠረቶች ናቸው።

ሸ. ኖኅ ለእግዚአብሔር ታዘዘ።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 6፡22 አንብብ። ኖኅ እግዚአብሔርን አመነ። እግዚአብሔር እንደሚልከው ከተናገረው የውኃ ጥፋት እርሱንና ቤተሰቡን እንደሚጠብቅ በማመን በእግዚአብሔር ተደገፈ።

ከዚህ በፊት በምድር ላይ ዝናብ እንዳልነበረ አስታውስ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ምድር የምትረሰርሰው ከመሬት በሚነሣ ጤዛ ነበር። ማንም ሰው ዝናብን አይቶ አያውቅም ነበር።

ይህም ቢሆን እንኳ ኖኅ፥ እግዚአብሔር ዝናብን እልካለሁ ካለ እንደግይዋሽ አመነ። ኖኅ በእግዚአብሔር አመነ። እግዚአብሔርን በመታዘዝ በታዘዘው መሠረት መርከብን ሠራ።

መምህር ሆይ፡- ዕብራውያን 11፡7 ተመልከት።

የእግዚአብሔር መንግሥት ሰማያትና እግዚአብሔር ያዘጋጀው የቅጣት ስፍራ በዓይን የማይታዩ ስለሆነ አንዳንድ ሰዎች በእነዚህ ነገሮች ሕልውና አያምኑም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው በሙሉ እውነት ነው። ኖኅ ዝናብ አይቶ የማያውቅ ቢሆንም እንኳ በእግዚአብሔር አመነ።

ቀ. ኖኅ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

አሁን እኔ እንደምነግራችሁ ኖኅ ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል ይነግራቸው ነበር። እግዚአብሔር ክፉ መንገዳቸውን እንደጠላና በዓለም ላይ ያለውን ነገር ሁሉ ሊያጠፋ የጥፋት ውኃን እንደሚሰድ ነገራቸው። አስተሳሰባቸውንና ዝንባሌያቸውን ከለወጡና በእግዚአብሔር ከታመኑ እግዚአብሔር ለኖኅ እንዲሠራ ወዳዘዘው መርከብ በመግባት ሊድኑ እንደሚችሉ ነገራቸው።

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኖኅ ለሕዝቡ የተናገረውን ነገር ሕዝቡ እንዲያስተውሉ ያሳሰባቸው ነበር። ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል ማስታወስ ባይፈልግም እንኳ መንፈስ ቅዱስ ግን ይረሱት ዘንድ አልተዋቸውም።

ስላስተማርኳችሁ ነገር ስታስቡ፥ መንፈስ ቅዱስ የተማራችሁትን ቃል በጥንቃቄ እንድታስቡበትና የእግዚአብሔርን መልእክት እንዳትረሱት ለማድረግ ይሞክራል።

እግዚአብሔር በኖኅ ጊዜ የነበሩ ሕዝቦች እንዲጠፉ አይፈልግም ነበር። እናንተም ከእግዚአብሔር ተለይታችሁ እንድትኖሩና በዚህ ሁኔታ እንድትሞቱ አይፈልግም።

በኖኅ ዘመን የነበሩ ሰዎች እግዚአብሔር በኖኅ በኩል ለተናገራቸው ነገሮች ምንም ግድ አልነበራቸውም። የራሳቸውን የኃጢአት አኗኗር ስለወደዱ ንስሐ ሳይገቡ ቀሩ። ከእናንተ ማንም በኖኅ ዘመን እንደነበሩ ሞኝ ሰዎች እንደማይሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

ጥያቄዎች

1. ኖኅ በኖረበት ዘመን የነበሩ የአብዛኛዎቹ ሰዎች ዝንባሌ ምን ነበር? የፍትወተ ሥጋ ፍላጐታቸውን በማሟላት፥ በመጋባትና ራሳቸውን በማስደሰት ብቻ የተጠመዱ ነበሩ። ስስታምና ዓመፀኞች ነበሩ። እግዚአብሔርን የማወቅም ሆነ የማስደሰት ፍላጐት ፈጽሞ አልነበራቸውም።

2. የዛሬው ዘመንና የኖኅ ዘመን የሚመሳሰሉባቸው በርካታ ነገሮች አሉን? አዎን። በርካታ ነገሮች አሉ።

3. ሕዝቡ፥ አስተሳሰባቸውንና ዝንባሌያቸውን እንዲለውጡና ወደ እግዚአብሔር በእምነት እንዲመጡ የሚናገራቸው ማን ነበር? እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነበር።

4. የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስታውሳችሁና እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጻፋቸውን ነገሮች በሚገባ እንድትመለከቱና እንድታምኑ የሚያሳስባችሁ ማን ነው? እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው።

5. ሕዝቡ ንስሐ ስላልገባ እግዚአብሔር ለማድረግ የወሰነው ነገር ምን ነበር? በምድር የሚገኙ ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ሁሉ ለማጥፋት ነበር።

6. እግዚአብሔር ሊያመጣ ካለው የዘላለም ቅጣት ይታደገው ዘንድ ኖኅ ይገባው ነበርን? አልነበረም። ኖኅም እራሱ ኃጢአተኛ ነበር። እንደሌሎቹ ሕዝቦች ሊገደል ይገባው ነበር።

7. ታዲያ እግዚአብሔር ኖኅን ለማዳን የወሰነው ለምን ነበር? ኖኅ ኃጢአተኛ እንደሆነ ከእግዚአብሔር ጋር በመስማማቱና በሚመጣው ነፃ አውጪ አማካይነት እግዚአብሔር እንደሚያድነው ስላመነ ነበር።

8. እግዚአብሔር፥ ኖኅን እንዲያደርግ የጠየቀው ምን ነበር? ትልቅ መርከብ እንዲሠራ ነበር።

9. ኖኅ መርከቡን በመሰለው መንገድ እንዲሠራ እግዚአብሔር ፈቀደለትን? አልፈቀደለትም። መርከቡ መሠራት የነበረበት ልክ እግዚአብሔር ባዘዘው መንገድ ነበር።

10. ስለዚህ ትልቅ መርከብ ልናስታውሰው የሚገባ አንድ አስፈላጊ ነገር ምንድን ነው? መርከቡ አንድ በር ብቻ ያለው መሆኑን ልናስታውስ ይገባል። ወደ መርከቡ በመግባት ከእግዚአብሔር ፍርድ ለመዳን የሚቻለው በአንድ መንገድ ብቻ ነበረ።

11. ኖኅ መርከቡን የሠራው እግዚአብሔር በነገረው መንገድ ነበርን? አዎን።

12. ኖኅ ትልቁን መርከብ እየሠራ ሳለ ሌላ ያደረገው ነገር ምን ነበር? ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን መልእክት በመናገር እግዚአብሔር ዝናብን እንደሚያዘንብና በጥፋት ውኃ ዓለምን በሙሉ እንደሚያጠፋ እየገለጸ ያስጠነቅቃቸው ነበር።

13. ሕዝቡ፥ ከዚህ ቀደም ዝናብ አይተው ነበርን? በጭራሽ! ከዚህ ቀደም ዘንቦ አያውቅም ነበር።

14. ሕዝቡ ኖኅ የተናገረውን በማመን ዝንባሌያቸውን ቀየሩን? አልቀየሩም። ከእግዚአብሔር ጋር ለመስማማትና እርሱን ለማመን ሳይፈቅዱ ቀሩ።

ትምህርት 17

የትምህርቱ ክፍል ዘፍጥረት 7-9

አጠቃላይ ርእስ፡- የእግዚአብሔር ፍርድ በዓለም ላይና የእግዚአብሔር ታዳጊነት ለኖኅና በመርከቡ ውስጥ ለነበሩ ሁሉ።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. እግዚአብሔር፥ ለኖኅ፥ ቤተሰቡን፥ እንስሳትንና አዕዋፋትን ወደ መርከቡ እንዲያስገባ ነገረው (7፡1-4)።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ለ. ሁሉም በአንድ በር ገቡ (7፡5-16)።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ሐ. እግዚአብሔር በሩን ከውጭ ዘጋባቸው (7፡16)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

መ. እግዚአብሔር ከመርከቡ ውጭ የነበሩትን ሁሉ አጠፋቸው (7፡17፥ 21-23)።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ሠ. እግዚአብሔር ኖኅንና በመርከቡ የነበሩትን ሁሉ አሰበ (8፡1-4፥ 14-19)።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ረ. እግዚአብሔር የኖኅን መስዋዕት ተቀበለ (8፡20-22)።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ሰ. እግዚአብሔር ትእዛዛቱንና ቃል ኪዳናቸን ለኖኅ ሰጠ (9፡1-7)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ሸ. እግዚአብሔር የቃል ኪዳን ምልክት ይሆን ዘንድ ቀስተ ደመናን ሰጠ (9፡8-17)።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ቀ. ሦስቱ የሰው ልጆች ዝርያ አባቶች (9፡18፥ 19)።

የትምህርት 16 ጥያቄዎችን ከልስ

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

ሀ. እግዚአብሔር፥ ለኖኅ፤ ቤተሰቡን እንስሳትንና አዕዋፋትን ወደ መርከቡ እንዲያስገባ ነገረው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እግዚአብሔር፥ አዳምን «መልካሙንና ክፉውን ከሚያሳውቀው ዛፍ ፍሬ በበላህ ጊዜ ሞትን ትሞታለህ» እንዳለው ታስታውሳላችሁን? አዳምና ሔዋን ፍሬውን በበሉ ጊዜ ሞቱን? እግዚአብሔር የተናገረውን አደረገን?

እግዚአብሔር፥ ለኖኅ ደግሞ እንዲህ አለው። «ከእኔ ጋር በመስማማት ወደ መርከቢቱ ሊገቡ የማይፈቅዱትን ሁሉ ለማጥፋት የጥፋት ውኃን አመጣለሁ»። እግዚአብሔር፥ በዚህም ጊዜ ቢሆን ያለውን እንዳደረገ ተማምናችኋል? እግዚአብሔር ያለውን ነገር ይረሳዋል ብላችሁ አስባችሁ ይሆን?

በከተማችሁ ውስጥ ወይም በአካባቢያችሁ የሚኖር አንድ ሰው ሌላ ሰው ቢያስቀይመው ያስቀየመውን ሰው በማናቸውም መንገድ ይዝትበትና ያስፈራራው ይሆናል። ነገር ግን ያ ቀን አልፎ ማለዳ ሲመጣ ቁጣው ይበርድና ሁሉን ነገር ይረሳዋል።

እግዚአብሔር ግን እንደዚያ አይደለም። እግዚአብሔር፥ ሁልጊዜ የተናገረውን ይፈጽማል። እግዚአብሔር ኃጢአትን በዝምታ አያልፍም፥ አይረሳም። ኃጢአት ዋጋው ሊከፈል ያስፈልጋል። እግዚአብሔር በሚቃወሙት ላይ ያለው ቁጣ አይበርድም። ቁጣው እየበረታ ይሄዳል።

ዘፍጥረት 7፡1-4 አንብብ። በኖኅ ዘመን የነበሩ ሰዎች ኖኅ የነገራቸውን የእግዚአብሔርን ቃል ሳይቀበሉ ቀሩ። መንፈስ ቅዱስ ለአእምሮአቸው ሲናገርና የእግዚአብሔርን ቃል ሲያስታውሳቸው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሳይስማሙ ቀሩ። እንደበደሉና የእርሱ ቅጣት እንደሚገባቸው ባለማመናቸው ከእግዚአብሔር ጋር ሳይስማሙ ቀሩ። እርሱ ነፃ አውጪ እንደሚልክ በገባው ቃል ኪዳን ሳይደገፉ ቀሩ። እግዚአብሔር በጥፋት ውኃ ዓለምን እንደሚያጠፋ ሳያምኑ ቀሩ። እግዚአብሔር ይህን አሳባቸውን እንዲቀይሩ ለ120 ዓመታት በትዕግሥት ጠበቃቸው። ከዚያ በላይ ሊቆያቸው ግን አልቻለም። ይቀጣቸው ዘንድ የእግዚአብሔር ጊዜ ደረሰ።

እግዚአብሔር አሁንም አልተለወጠም። በዓለም የሚኖሩ ሕዝቦች ቃሉን እንዲሰሙ፥ ከእርሱ ጋር እንዲስማሙና በእርሱ እንዲደገፉ በትዕግሥት ይጠብቃቸዋል። ወደፊት አንድ ቀን ግን «አሁን ይበቃል ከዚህ በላይ ልታገሣችሁ አልችልም» ይላል። እግዚአብሔርን ለማመን ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች ሁሉ ወደ ዘላለም ቅጣት ይሄዳሉ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ዝናብ መዝነብ ከመጀመሩ በፊት እግዚአብሔር ኖኅን፥ ቤተሰቦቹንና የተመረጡትን እንስሳት ይዞ ወደ መርከቡ እንዲገባ ነገረው።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ እንዲያሰኝና እንዲድን እምነት ያስፈልገዋል።

ኖኅ፥ እግዚአብሔር እንደተናገረው ዓለምን ሁሉ ያጠፋ ዘንድ አመነ። እርሱና ቤተሰቡ ሊድኑ የሚችሉት በእግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ በማመን እግዚአብሔር ያዘዘውን ነገር ፈጸመ።

እግዚአብሔር፥ ኖኅን ያዳነው መልካም ሕይወት ስለነበረው አይደለም። እግዚአብሔር ኖኅን ያዳነው ከእግዚአብሔር ጋር ስለተስማማና በእርሱ ስለተደገፈ ነው።

ለ. ሁሉም በአንድ በር ገቡ።

ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ዘፍጥረት 7፡5-16 አንብብ። ኖኅና ቤተሰቡ በሙሉ እግዚአብሔር ኖኅን ይሠራ ዘንድ ባዘዘው በአንዱ በር ወደ መርከቡ ገቡ። ማንኛውም ሰው ከጥፋት ውኃና ከእግዚአብሔር ቁጣ ሊድን የሚችልበት አንድ ብቸኛ መንገድ ይህ ነበር።

እንስሳቱም ሁሉ ወደ መርከቢቱ የገቡት በዚሁ አንድ በር ነበር።

ሐ. እግዚአብሔር በሩን ዘጋው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘፍጥረት 7፡16 አንብብ። ሁሉም ወደ መርከቢቱ ከገቡ በኋላ እግዚአብሔር በሩን ዘጋው።

እግዚአብሔር፥ ሌሎች ሰዎች አሳባቸውን ለውጠው ወደ እምነት እንዲመጡ ለማድረግ የሚሰጠው ተጨማሪ ጊዜ አልነበረውም። እግዚአብሔር በሩን ከዘጋው በኋላ የሚመጡ ሰዎች እጅግ የዘገዩ ነበሩ። ከበሩ ውጭ ሆነው እየጮኹ ቢለምኑም እንኳ ወደ ውስጥ ለመግባት አይችሉም ነበር። ኖኅ ሊያስገባቸው ያልቻለው በሩን የዘጋው እግዚአብሔር ራሱ ስለነበረ ነው። የሚድኑበት መንገድ አልነበራቸውም። በመርከቡ ውስጥ የነበሩ ሰዎች ዋስትና አስተማማኝ ነበር፥ ምክንያቱም በሩን የዘጋው እግዚአብሔር ነበር። ከመርከቡ ውጭ የነበሩ ሰዎች ግን የእግዚአብሔርን ቁጣ ሊያመልጡ የሚችሉበት መንገድ አልነበረም፥ ምክንያቱም ውጭ ሆነው ሳሉ እግዚአብሔር በሩን ዘግቶባቸው ነበር።

እግዚአብሔር፥ አዳምና ሔዋንን፥ ከዔድን ገነት ሲያባርራቸውና ከሕይወት ዛፍ ሲያርቅአቸው፥ተመልሰው ወደ ዔድን ገነት ለመግባት ዕድል ነበራቸውን? በፍጹም አልነበራቸውም።

እግዚአብሔር ዓለምን በሙሉ እንደገና ለመቅጣት ሲወስን ከእርሱ ግምለጫ አንዳችም መንገድ አይኖርም።

መ. እግዚአብሔር ከመርከቡ ውጭ የነበሩትን ሁሉ አጠፋቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ዘፍጥረት 7፡17፥ 21-23 አንብብ። እግዚአብሔር የመርከቢቱን በር ከዘጋ በኋላ ዝናብን ላከ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር፤ በምድር፥ በዝናብ፥ በነፋስ፥ በፀሐይ፥ በጨረቃ፥ በከዋክብትና በነገሮች ሁሉ ላይ የበላይ ተቆጣጣሪ ነው። እርሱ ነገሮችን ሁሉ ስለፈጠረ ይቆጣጠራቸዋል።

ይህ ሁሉ ውኃ የመጣው ከየት ነበር? ውኃው ትላልቅ ተራራዎችንና ዓለምን በሙሉ የሸፈነ ነበር። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ዓለምን ሲፈጥር ዓለም ምን ትመስል እንደነበር ታስታውሳለህን? በምድር ላይ ጨለማ ሰፍኖ ነበር፤ ምድርን በሙሉ ውኃ ሸፍኖአት ነበር። በመጀመሪያ ቀን እግዚአብሔር ብርሃንን ፈጠረ፤ በሁለተኛው ቀን አየርንና ሰማይን ፈጠረ፤ በምድር ከነበረው ውኃ አብዛኛውን ሰማይ ላይ አደረገው። እግዚአብሔር ምድርን በጐርፍ የሚመታበት ጊዜ ሲደርስ እግዚአብሔር ሰማይ ላይ ያደረገውን ውኃ እንዲወርድ አደረገ።

መምህር ሆይ፡- እንደ አዳማጮችህ ጠያቂነትና የመመራመር ብቃት አንጻር በመጀመሪያ በምድር የነበሩት ወንዞችና ጅረቶች ከመሬት በታች ከነበረ የውኃ ክምችት የወጡ እንደሆነ መናገር ይቻላል። እግዚአብሔር የምድርን አፍ ከፍቶ ወደላይኛው የምድር ክፍል ታላቅ የውኃ ምንጭ እንዲፈስ ለማድረግ ታላላቅ የመሬት መንቀጥቀጥና የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ ሳያስነሣ አልቀረም (ዘፍጥረት 8፡2)።

እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ ይችላል። ለእግዚአብሔር የሚሣነው ነገር የለም። እርሱ ብቻ ሁሉን ቻይ ነው።

እግዚአብሔር አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በማዝነብ ምድርን በሙሉ፥ ታላላቅ ተራሮችንና ዛፎችን ጭምር በውኃ እንዲሸፍኑ አደረገ።

ከመርከቡ ውጭ የነበሩ ሰዎች በሙሉ በእግዚአብሔር ተደመሰሱ። እግዚአብሔርን አምነው ወደ መርከቡ የገቡት ኖኅና ቤተሰቡ ብቻ ነበሩ። የቀሩት ሰዎች በሙሉ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ።

አብዛኛዎቹ ሕዝቦች ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ይልቅ በሰይጣን ያምናሉ። አብዛኛው ሕዝብ የሚጓዘው ከብዙሃኑ ጋር ነው። ከብዙሃኑ ሕዝብ አመለካከት በተቃራኒ ለመጓዝ አይፈልጉም። አብዛኛው ሕዝብ ኃጢአቱን ስለሚወድ ስሕተት የሠራ መሆኑን ለማመን ከእግዚአብሔር ጋር አይስማማም። እግዚአብሔርን ለማመን ፈቃደኛ ያልሆኑትን ብዙሃን ሰዎች ከተከተላችሁ ወደ ዘላለም ቅጣት ትሄዳላችሁ። እንደ ኖኅ መሆን ግን የተሻለ ነው። እነርሱ ሌሎች ሰዎች ስለሚሉት ነገር አልተጨነቀም። ኖኅ እግዚአብሔርን አመነ።

መምህር ሆይ፡- ስለ ጥፋት ውኃ የሚነገር አፈ ታሪክ ካላቸውና ይህ ታሪካቸው ከኖኅ ታሪክ ጋር የተለየ ቢሆንም፥ አንተ ግን በመጀመሪያ በኖኅና በቤተሰቡ የተነገረው ታሪክ እውነተኛው ታሪክ እንደሆነ አስረዳ። ይህ ታሪክ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ ያለማቋረጥ ተላልፏል። ታሪኩ የሚተላለፈው በአፍ ንግግር ስለነበረ ቀስ በቀስ እየተለወጠ ስለመጣ አሁን የሚነገረው አፈ ታሪክ ትክክል አይደለም። ይህን ታሪኮችና አጋጣሚዎች በቃል በሚተላለፉበት ጊዜ ሰዎች እየጨመሩና እየቀነሱ ስለሚናገሩ እንዴት ሊዛባ እንደሚችል በመናገር አብራራው። ይህን ዓይነቱ ልዩነት በእነርሱም መካከል እንኳ ሊፈጠር እንደሚችል አስረዳቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ ታሪኮችን የያዘ መጽሐፍ መሆኑን በመናገር ላይ አተኩር። ምክንያቱም በእግዚአብሔር የተመረጡ ሰዎች የጻፉት ሊበረዝ ወይም ሊረሳ በማይችል መንገድ በመሆኑ ነው።

ሠ. እግዚአብሔር ኖኅንና በመርከቡ የነበሩትን ሁሉ አሰበ።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘፍጥረት 8፡1-4፥ 14-19 አንብብ። በመርከቡ ውስጥ የነበሩት ኖኅ፥ ቤተሰቡና እንስሳቱ በእግዚአብሔር ደኅንነታቸው ተጠበቀ። አንዳቸውም አልሞቱም።

እግዚአብሔር አሰባቸው፥ ዝናቡም እንዲቆም አደረገ። ውኃውን ለማድረቅ ብርቱ ነፋስ ላከ። ስለዚህ ደረቅ መሬት እንደገና ታየ። እግዚአብሔር ዝናብንና ነፋስን ይቈጣጠራል።

በእነዚህ ነገሮች ላይ ኃይል እንዳላቸው መናፍስት አሳምነውህ ይሆናል፤ ግን ውሸታቸውን ነው። እግዚአብሔር እስካልፈቀደላቸው ድረስ በነፋስ ወይም በዝናብ ላይ አንዳችም ነገር ሊሠሩ አይችሉም።

መምህር ሆይ፡- ለማጣቀሻ ይጠቅም ዘንድ ኢዩ. 1:9-19፤ መዝ. (147)፡18፥ 148፡8 ተመልከት። እግዚአብሔር አይለወጥም። እግዚአብሔር አይረሳም። ኖኅንና አብረውት ወደ መርከብ የገቡትን በሙሉ አልረሳም ነበር። ያለውን ያደርጋል። እንደሚያድናቸው ተናገረ፥ አዳናቸውም። ከመርከቡ ውጭ የነበሩትን በሙሉ እንደሚያጠፋቸው ተናገረ አጠፋቸውም።

መምህር ሆይ፡- ካርታ ላይ የአራራትን ተራራ አመልክታቸው።

ረ. እግዚአብሔር የኖኅን መሥዋዕት ተቀበለ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ዘፍጥረት 8፡20-22። እግዚአብሔር የአቤልን መሥዋዕት እንደተቀበለ የኖኅን መሥዋዕትም ተቀበለ። እግዚአብሔር ኖኅንና ቤተሰቡን የተቀበለው የእግዚአብሔርን መንገድ ስለተከተሉና በእንስሳት ደም አማካይነት ሊቀበላቸው እንደሚችል በማመን በእርሱ ተደግፈው ስለቀረቡ ነው። የእንስሳት ደም የኃጢአታቸውን ዋጋ ሊከፍል አይችልም፤ ነገር ግን ኃጢአት ሞትን እንዳመጣ ያስታውሳቸዋል። እግዚአብሔር የተቀበላቸው በጸጋው ነው።

ሰ. እግዚአብሔር ትእዛዛቱንና ቃል ኪዳኖቹን ለኖኅ ሰጠ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ዘፍጥረት 9፡1-7 አንብብ። እግዚአብሔር፤ ለኖኅና ለልጆቹ ለሴም ለካምና ለያፌት በእንስሳትና በአእዋፋት ደግሞም በባሕር እንስሳት ላይ ገዥ እንዲሆኑ አዳምን በመጀመሪያ በሾመበት መንገድ ሾማቸው። ዓለምና በውስጧ ያሉት ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር ተፈጠሩ። ፍጥረታትን ያስተዳድሩና ይንከባከቡ ዘንድ ግን ለሰው ልጆች ሰጣቸው።

ሸ. እግዚአብሔር ቀስተ ደመናን ምልክቱ አድርጉ ሰጠ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ዘፍጥረት 9፡8-17 አንብብ። እግዚአብሔር፥ ከዚህ በኋላ ምድርን በውኃ እንደማያጠፋት ቃል ኪዳን በመግባት ለዚህ ምልክት ይሆን ዘንድ ቀስተ ደመናን ሰጠ። የጥፋት ውኃ ታሪክ ከተፈጸመ ብዙ ሺህ ዓመታት ያለፉ ሲሆን እግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳን ጠብቋል።

ቀስተ ደመና በምታዩበት ወቅት እግዚአብሔር ዓለምን እንደገና በውኃ እንደማያጠፋ ለገባው ቃል ኪዳን የሰጠው ምልክት መሆኑን አስታውሱ። እግዚአብሔር ሊታመኑበት የሚችል አምላክ ነው።

ቀ. ሦስቱ የሰው ልጆች ዝርያ አባቶች።

ዘፍጥረት 9፡18-19 አንብብ። የሰው ልጆች በሙሉ የተገኙት ከእነዚህ ሦስት ሰዎች ነበር። ከእነዚህ ሦስት ሰዎች አንዱ ምናልባት አባታችሁ የሆነው ካም ይሆናል።

ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር፥ በኖኅ ዘመን የነበሩ ሰዎችን ከእርሱ ጋር እንዲስማሙና ቃሉን እንዲያምኑ የታገሣቸው ምን ያህል ጊዜ ነበር? 120 ዓመታት ነበር።
2. እግዚአብሔር፥ አንድ ነገርን ለማድረግ በዛቻ እንደሚያስፈራራና በኋላ ግን ቀዝቅዞ እንደማያደርግ ሰው ነውን? አይደለም። የእግዚአብሔር የቁጣው ብርታት አይቀነስም። በሚቃወሙት ሁሉ ላይ ብርታቱ እየጨመረ ይሄዳል።
3. ለኖኅ፥ ወደ መርከቡ የሚገባበትን ጊዜ የነገረው ማን ነበር? እግዚአብሔር።
4. ወደ መርከቡ የገቡ ሰዎች የገቡት እንዴት ነበር? እግዚአብሔር ለኖኅ በጐን በኩል እንዲሠራ ባዘዘው በአንዱ በር ብቻ ነበር።
5. በሩን የዘጋው ማን ነበር? እግዚአብሔር።

6. እግዚአብሔር፥ በሩን የዘጋው ለምን ነበር? በመርከቡ ውስጥ ለነበሩት ሰዎች ደኅንነት ዋስትና ለመስጠትና ከመርከቡ ውጭ የነበሩት ሰዎች ወደ ውስጥ ለመግባትና ለመዳን ዕድል እንዳያገኙ ነበር።

7. እግዚአብሔር ኃጢአትን የሚቀጣበትን ጊዜ ከወሰነ እግዚአብሔር ካለው ለማምለጥ የሚችል አለን? የለም።

8. እግዚአብሔር የጥፋት ውኃ ትላልቅ ተራሮችን ጨምሮ ምድርን ሁሉ እንዲሸፍን ያደረገው እንዴት ነበር? እግዚአብሔር ፍጥረታትን በፈጠረበት ሁለተኛ ቀን ከሰማይ በላይ ያሰፈረውን ውኃ በመልቀቅ ነው።

9. ሰዎች ከዚያን በፊት ዝናብ አይተው ያውቁ ነበርን? አያውቁም።

10. ከመርከቡ ውጭ ከነበሩት መካከል ከሞት ያመለጠ ነበረን? አልነበረም፥ ሁሉም ሞተዋል።

11. በመርከቡ ውስጥ ካሉት መካከል የሞተ ነበርን? አልነበረም። እግዚአብሔር ሁሉንም ጠብቋል።

12. እግዚአብሔር፥ ኖኅ ከመርከቡ በወጣ ጊዜ ያቀረበውን መሥዋዕት ለምን ተቀበለ? ኖኅ፥ እግዚአብሔርን ታምኖ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት የእንስሳት መሥዋዕትን ስላቀረበ ነው።

13. የእንስሳት ደም የኖኅን ኃጢአት ሊያስወግድ ይችል ነበርን? አይችልም ነበር። ደሙ የሚያስታውሰው ለኃጢአቱ ሞት እንደሚገባው ብቻ ነበር። እግዚአብሔር የተቀበለው በጸጋው ነው።

14. እግዚአብሔር፥ ለኖኅና ለልጆቹ በእንስሳት፥ በአእዋፋትና በባሕር ዓሦች ላይ የገዥነትን ሥልጣን ሊሰጥ የቻለው እንዴት ነበር? ዓለምና በውስጧ ያሉት ነገሮች ሁሉ የእርሱ የእግዚአብሔር ስለሆኑ ነው።

15. እግዚአብሔር፥ ከዚህ በኋላ ዓለምን በውኃ እንደማያጠፋት ለገባው ቃል ኪዳን የሰጠው ምልክት ምን ነበር? ቀስተ ደመና ነበር።

16. እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ጠብቋልን? አዎ፥ እግዚአብሔር ለቃሉ እውነተኛ ነው። ፈጽሞ አይዋሽም አይለወጥም።

17. የእናንተን ነገድ ጨምሮ የሰው ልጆች ሁሉ አባቶች እነማን ናቸው? የኖኅ ልጆች የሆኑት ሴም፥ ካምና ያፌት ናቸው።

ትምህርት 18

የትምህርት ክፍል፡- ዘፍጥረት 11፡1-9

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር የባቢሎንን ግንብ ለመገንባት የተሰበሰቡ ዓመፀኞችን በተናቸው።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. የሕዝቡ የዓመፀኛነትና የትዕቢተኛነት ዝንባሌ (11፡1-4)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. ሰይጣን፥ ከእግዚአብሔርና ከፈቃዱ ጋር ይዋጋል። እርሱ ውሸታምና አታላይ ነው። ሰውን ይጠላል።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ለ. እግዚአብሔር ተመለከታቸው። (11፡5)

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ሐ. እግዚአብሔር በተናቸው። (11፡6-9)

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

የትምህርት 17 ጥያቄዎችን ከልስ።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ።

ሀ. የሕዝቡ የዓመፀኛነት፥ የትዕቢተኛነት ዝንባሌ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 11፡1-4 አንብብ። እግዚአብሔር፥ ኖኅን፥ ሚስቱን፥ ሦስቱ ልጆቹንና ሚስቶቻቸውን ከታላቁ የጥፋት ውኃ ካዳነ ብዙ ዓመታት አልፏል። በምድር ላይ የሚኖሩት ሕዝቦች እንደገና እጅግ በዙ።

አብዛኛዎቹ የኖኅ ዝርያዎች እግዚአብሔር በምድር ላይ የጥፋት ውኃ በማምጣት የሰጠውን ከባድ ፍርድ ፈጥነው ረሱ። ስለዚህ ሆን ብለው እግዚአብሔርን ተዉ። ለሕይወታቸው ያለውን ፈቃድም ሳይቀበሉ ቀሩ። እንደ አቤል፥ ሴት፥ ሄኖክና ኖኅ አልሆኑም። እግዚአብሔርን ለማወቅና ለማመን አልፈለጉም። በአስተሳሰባቸው

እንደ ሰይጣን ነበሩ። በሰይጣን ቁጥጥር ሥር ነበሩ። የእነርሱ አሳብ እንደ ሰይጣን አሳብ ነበር። ራሳቸውን ከፍ በማድረግ ታላቅ መሆን ይፈልጉ ነበር። እግዚአብሔርን የማወቅ፥ የማምለክ ወይም በእርሱ የመደገፍና ለእርሱ የመታዘዝ ፍላጐት አልነበራቸውም።

እነዚህ ሰዎች የእናንተና የእኛ ቀደምት አባቶቻችን ነበሩ። ስለ ጥሩት ውኃ ሰምተው ነበር፥ ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር እንደሆነም ያውቁ ነበር። በየዕለቱ ቀንና ማታ በሚያደርጋቸው ነገሮች የሚገለጠውን ታላቅ ኃይሉን ማየት ይችሉ ነበር። እግዚአብሔርም ደግሞ ምድርን በውኃ እንደማያጠፋ በቀስተ ደመና ምልክት የገባውን ቃል ኪዳን ለማክበር ታማኝ መሆኑን ማሳየቱን ቀጠለ። እግዚአብሔርን ላለማመናቸው የሚያቀርቡት ምንም ምክንያት አልነበራቸውም። ነገር ግን እግዚአብሔር ሕይወትን፥ ጤናን፥ ፀሐይን ዝናብንና ምግብን በመስጠቱ የሚገባውን ክብር አይሰጡትም ነበር።

ስለ እግዚአብሔር ከሚያውቁት እውነት ሆን ብለው ፊታቸውን አዞሩ። አእምሮአቸው የበለጠ ክፉና የማይረባ ሆነ። የሰዎችን ምስል በመሥራት አመለኳቸው። እንስሳትንና አዕዋፋትን አመለኩ። በመጨረሻ እባቦችንና ሌሎች ተሳቢ እንስሳትን አመለኩ።

መምህር ሆይ፡- ስለዚህ ስፍራ ሰዎች በምትገልጽበት ጊዜ ሮሜ 1፡18-25 በአእምሮህ ይኑር።

ዋና አሳብ፡- ሰይጣን ከእግዚአብሔርና ከፈቃዱ ጋር ይዋጋል። እርሱ ውሸታምና አታላይ ነው። ሰዎችንም ይጠላል።

ሰይጣን፥ የእናንተንና የእኛን ቀደምት አባቶች ከእግዚአብሔርና ከፈቃዱ በተጻራሪ እንዲሄዱ ይመራቸው ነበር። ሰይጣን፥ ሰዎች እንደ ፀሐይ፥ ጨረቃ፥ ከዋክብት፥ አዕዋፍ ወይም እንስሳት የመሰሉትን ፍጡራን ሐሰተኛ አማልክት በማድረግ እንዲያመልኩአቸው ይፈልጋል። እርሱ ብቻ እውነተኛ አምላክ የሆነውን እግዚአብሔርን እስካላመለክን ድረስ፥ሰይጣን ምንም ብናመልክ ግድ የለውም።

እነዚህ የኖኅ ዝርያዎች ከእግዚአብሔር ይልቅ ይመሯቸው ዘንድ ሰዎችን መረጡ። በዚህ ጊዜ ከነበሩት ታላልቅ መሪዎች ወይም አለቆች አንዱ ናምሩድ በመባል ይታወቅ ነበር። ታላቅና ጠንካራ መሪ ነበር። ሕዝቡን በርካታ ከተሞች ይገነቡ ዘንድ ያደራጀ ሰው ነበር። ካስገነባቸው ከተሞች አንዱ ባቢሎን በመባል የሚጠራው ከተማ ነበር።

መምህር ሆይ፡- ዘፍጥረት 10፡8-10 ተመልከት። በካርታ ላይ ባቢሎን በኤፍራጥስና ጤግሮስ ሜዳማ ስፍራ ላይ የተሠራችበትን ቦታ አመልክት።

በጊዜ ቅደም ተከተል ማሳያ ሠንጠረዥ ላይ፡- ባቢሎን የሚለውን ቃል አስፍር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር፥ ለአዳምና ለኖኅ ብዙ ተባዙ በምድር የሚገኙትን እንስሳት፥ አዕዋፍንና የባሕር ዓሦችን ሁሉ ግዙ የሚል ትእዛዝ ሰጥቶአቸው ነበር። እግዚአብሔር፥ ሰዎች በአንድ ቦታ ተከማችተው ራሳቸው ደስ የሚሰኙበትን ነገር ብቻ እንዲያደርጉ አልፈለገም። በአንድነት በዚህ ሁኔታ ከቆዩ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ፈቃዱ ፈጥነው ሊረሱ እንደሚችሉ ያውቅ ነበር። ሰው በእግዚአብሔር የተፈጠረው በምድር ላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያደርግ ዘንድ ነበር። የምንኖረው በየትም ስፍራ ይሁን፥ ምንም ዓይነት መልክ ይኑረን፥ ምንም ዓይነት ቋንቋ እንናገር፥ የእግዚአብሔር ንብረቶች ነን።

እነዚህ ሰዎች ከእግዚአብሔር ከፈጣሪያቸው ለኖኅ የተሰጠውን ትእዛዝ ሆን ብለው ጣሱ። እግዚአብሔር እንዳዘዘው ወደተለያዩ ስፍራዎች ተበትነው ለመኖር አልፈለጉም። በአንድ ስፍራ ተከማችተው ከተማ ከተሙና እጅግ ትልቅ የሆነ ግንብ የመገንባት ሥራ ጀመሩ። እግዚአብሔር ለእነርሱም ሆነ ለዓለም ለነበረው ዕቅድ ግድ አልነበራቸውም። እራሳቸውን ከፍ ከፍ ማድረግ ፈለጉ።

ለ. እግዚአብሔር ተመለከታቸው

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ ይገኛል። ደግሞም ሁሉን አዋቂ ነው።

እግዚአብሔር የተመለከታቸው ይመስልሃልን? ያሰቡትንና ያቀዱትን አውቆ ነበርን? ስለሚያደርጉት ነገር ግድ ነበረውን?

ዘፍጥረት 11፡5 አንብብ። አዎን! እነርሱ ቢዘነጉትም እንኳ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ፍላጐት ነበረው።

እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ ያሉ ሰዎችን ሁሉ ይመለከታል። በሰዎች ሁሉ ላይ ፍላጐት አለው። ደግሞም ስለ እናንተ ሁሉን ነገር ያውቃል። ከእርሱ ልትደብቁት የምትችሉት አንዳችም ነገር የለም። ፈጣሪያችሁ እርሱ ነው። በኃጢአታችሁ ምክንያት ከእርሱ የተለያችሁ

ብትሆኑም እንኳ የእርሱ ናችሁ። ከዚህ ቀደም ያሰባችሁትን፥ የተናገራችሁትንና ያደረጋችሁትን ሁሉ አይቷል፥ ያስታውሳልም።

ሐ. እግዚአብሔር በተናቸው

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ሰይጣን፥ በመንግሥተ ሰማያት በነበረ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ለመዋጋት ሞከረ፥ ነገር ግን ተሸነፈ። ከእግዚአብሔር ጋር ለመዋጋት ከሰይጣን ጋር የተባበሩ ሌሎች መላእክትም ተሸንፉ። አዳምና ሔዋን፤ ቃየንና እንዲሁም ኖኅ በነበረበት ዘመን የኖሩት ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ለመዋጋት ባደረጉት ሙከራ ተሸንፉ። በዚህ ጊዜ ምን የሆነ ይመስልሃል? ሰይጣንና የተከተሉት ሕዝቦች አሸነፉን?

ከእግዚአብሔር ጋር ተዋግቶ በአሸናፊነት ለመወጣት የሚችል የለም። እርሱ ከሁሉ በላይ ነው። አሁን ይህን ጉዳይ እግዚአብሔር እንዴት እንደተቆጣጠረ እናነባለን።

ዘፍጥረት 11፡6-9 አንብብ። እግዚአብሔር የሕዝቡን ቋንቋ ደባለቀው። በቋንቋቸው መደባለቅ ምክንያት ሊግባቡ ስላልቻሉ ሁሉም በየወገኑ በመሆን ወደተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ተበተኑ። ለብዙ ዓመታት ወደተለያዩ የዓለም ክፍሎች በእግር ወይም በጀልባ ተጓዙ።

የተለያዩ ሕዝቦችና ዘሮች መታየት የጀመሩት በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ነበር። የእናንተ ሕዝብም ሕልውና የተጀመረው በዚህ ዓይነት ነበር። የእናንተ ቀደምት አባቶች በባቢሎን ግንብ ግንባታ ላይ ነበሩ። የእናንተ ሕዝቦች ጅማሬ እንዲሁ ነበር።

የእናንተና የእኛ ቀደምት አባቶች የሚያውቁትን የእግዚአብሔርን እውነት በመተው ሰይጣንና መናፍስቱ የሚሰጧቸውን አሳቦች መከተል ጀመሩ።

እውነተኛውንና ሕያው የሆነውን አምላክ ማምለክ የቀጠሉ ጥቂት ሰዎች ብቻ ነበሩ። አብዛኛዎቹ ግን ከእግዚአብሔር ዘወር አሉ።

መምህር ሆይ፡-

ሀ. እዚህ ነጥብ ላይ ቀደምት አባቶቻቸው ሰይጣንን እንደተከተሉ በቀጥታ መናገሩ ብልህነት መሆን አለመሆኑን መወሰን ይኖርብሃል።

ለ. ስለ ቋንቋዎች አጀማመር የሚያውቁት አፈ ታሪክ ይኖር ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቋንቋ አጀማመር እውነተኛውን ታሪክ የሚናገር ብቸኛ መጽሐፍ እንደሆነ ግለጥላቸው።

ጥያቄዎች

1. ከጥፋት ውኃ በኋላ የነበረው ትውልድ ስለ እግዚአብሔር ያውቅ ነበርን? አዎን።

2. እንዴት አወቁ?

   ሀ. ፈጣሪ ስለሆነው እግዚአብሔርና የጥፋትን ውኃ በማምጣት ስለፈጸመው እውነትኛ ፍርድ የሚተርከው ታሪክ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ ይተላለፍ ነበር።

   ለ. እግዚአብሔር በፈጠራቸው ነገሮች ሁሉን ቻይ ፈጣሪ መሆኑን ለማየት ይችሉ ነበር። ፀሐይ፥ ጨረቃ፥ ከዋክብትና በምድር የነበሩ ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ፈጣሪያቸው እንደሆነ ማስረጃዎች ነበሩ።

   ሐ. ቀስተ ደመና እግዚአብሔር በሰማይ ያኖረው ምልክት ነበር።

3. የኖኅ ዝርያዎች በሙሉ እግዚአብሔርን አመለኩን? እግዚአብሔር በተናገረው በመስማማት ነፃ አውጪ እንደሚልክ በሰጠው የተስፋ ቃል ተደገፉን? በጭራሽ! እግዚአብሔርን ያመኑትና ያመለኩት ጥቂቶች ብቻ ነበሩ።

4. ምን አደረጉ?

   ሀ. ከሚያውቁት እውነት ሆን ብለው ዞር በማለት የሰይጣንን ውሸቶች ተከተሉ።

   ለ. በሰዎች፥ በአእዋፍ፥ በእንስሳትና፥ በተሳቢ እንስሳት የተመሰሉ ጣዖታትን አመለኩ። ደግሞም ፀሐይ፥ ጨረቃና ከዋክብትን አመለኩ።

5. እነዚህ ሰዎች እነማን ነበሩ? የአዳምና የኖኅ ልጆች የሴም፥ የካምና የያፌት ዝርያዎች ስለሆኑ የእኛም ቀደምት አባቶች ናቸው።

6. የባቢሎንን ግንብ መገንባት የጀመሩት ለምን ነበር?

   ሀ. እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው ወደተለያዩ ስፍራዎች ተሰራጭተው እንዳይኖሩ ለመከላከል።

   ለ. በምድር ላይ ከፍ ብለው እንዲታዩ።

7. ሊያደርጉ ዐቅደውት የነበረውን ነገር እግዚአብሔር አውቆ ነበርን? አዎን።

8. እግዚአብሔር የሰዎችን ሁሉ ምሥጢር ያውቃልን? አዎን ሁሉንም ያውቃል።

9. ጌታ ምን አደረገ? ለተለያዩ ቤተሰቦች የተለያዩ ቋንቋዎችን በመስጠት ቋንቋቸውን ደባልቆ ወደተለያዩ ስፍራዎች እንዲበተኑ አደረገ።

10. ውጤቱ ምን ነበር? የተለያዩ ቤተሰቦች እርስ በርስ ተለያይተው ወደተለያዩ ስፍራዎች ተጓዙ።

11. የእናንተ ቀደምት አባቶች በመጨረሻ እዚህ ስፍራ የተገኙት እንዴት ነበር? ለብዙ መቶና ሺህ ዓመታት ወደ እዚህ አቅጣጫ በእግርና በጀልባ ተጉዘው ደረሱ።

12. የእናንተና የእኛ ቀደምት አባቶች የሃይማኖት እምነታቸውን ያገኙት ከየት ነበር? ከሰይጣንና ከራሳቸውም አሳብ ጭምር ሲሆን፥ ይኸውም ከእግዚአብሔር እውነት ሆን ብለው ፊታቸውን ባዞሩ ጊዜ ነው።

ትምህርት 19

የትምህርቱ ክፍል፡- ዘፍጥረት 11፡27-32፤ 12፡1-5

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር አብራምን መረጠው፥ ጠራው፥ መራው።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች።

ሀ. አብራም፥ ከሴም የዘር ግንድ የመጣ ሰው ነበር (11፡27-32)።

ለ. እግዚአብሔር አብራምን ጠራውና ትእዛዝን ሰጠው (12፡1)።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ሐ. እግዚአብሔር ለአብራም የገባቸው ቃል ኪዳኖች (12፡2፥ 3)።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ አምላክ ነው።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ አምላክ ነው።

መ. አብራም እግዚአብሔርን አመነና ታዘዘ (12፡4፥5)።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ እንዲያሰኝና እንዲድን እምነት ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

የትምህርት 18 ጥያቄዎችን ከልስ።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

ሀ. አብራም ከሴም የዘር ግንድ የመጣ ሰው ነበር።

ኖኅ ሦስት ልጆች ነበሩት። ስማቸውን ማን ሊነግረኝ ይችላል?

ከእግዚአብሔር መጽሐፍ የምናነበው የሚቀጥለው ታሪክ ከሴም የዘር ግንድ ስለሆነው አንድ ሰው ይነግረናል። የኖረው ሕዝቡ ከዚህ ቀደም የባቢሎን ግንብ ለመገንባት ከሞከረበት ስፍራ አጠገብ ባለ የዓለም ክፍል ነበር። ስሙ አብራም ይባል ነበር፤ አባቱም ታራ በመባል ይጣራ ነበር።

ዘፍጥረት 11:27-30 አንብብ።

የጊዜ ቅደም ተከተል ማሳያ ሠንጠረዥ ላይ «አብርሃም፥ ሣራ፥ ሎጥ የሚሉትን ስሞች አሳይ።» የአብራምና የሦራ ስሞች ለውጥ እንዴት እንደመጣ በታሪኩ የኋለኛ ክፍል እንደሚገለጥ ግለጽ።

አብራምና ሦራ ባልና ሚስት ነበሩ። ነገር ግን ልጅ አልወለዱም ነበር።

ዘፍጥረት 11:31፥ 32 አንብብ። ታራ ከዑር ወጥቶ እስከ ካራን ድረስ ተጓዘ። ታራ፥ አብራምና ሦራን ይዞ ሄደ። ደግሞም አባቱ በዑር ሞቶበት ስለነበር የልጅ ልጁን ሎጥንም ይዞ ሄደ። የታራ ዕቅድ ወደ ከነዓን መጓዝ ቢሆንም እንኳ እስከ ካራን ድረስ ብቻ ተጓዘና በዚያው ሞተ።

መምህር ሆይ፡- ዑርን፥ ካራንና ከነዓንን ካርታ ላይ አመልክት።

ለ. እግዚአብሔር አብራምን ጠራውና ትእዛዝን ሰጠው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ዘፍጥረት 12:1 አንብብ። እግዚአብሔር አብራምን ከአባቱ ጋር ወደ ካራን ከመጓዙ በፊት ወደ ከነዓን እንዲጓዝ ጠራው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

እግዚአብሔር፥ አብራምን የራሱን አገር ትቶ ወደ ከነዓን ምድር እንዲጓዝ ጠራው። እግዚአብሔር አብራምን በቀጥታ በመጥራት ምን ማድረግ እንዳለበት ነገረው። በአብራም ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ገና አልተጻፈም ነበር።

እግዚአብሔር ዛሬ እኛን የሚናገረን በድምፅ ሳይሆን የእርሱ መጽሐፍ በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ነው። ስለ እግዚአብሔርና ለእኛ ስላለው መልእክት ልናውቅ የምንችልበት ብቸኛው መንገድ በዚህ መጽሐፍ ቃሎች ግለትም በመጽሐፍ ቅዱስ ነው።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

የአብራም አገር ሰዎች ጣዖታትን ያመልኩ ነበር። ብቸኛው እውነተኛ ፈጣሪ የሆነውን እግዚአብሔርን አያምኑም፥ አይወዱም ወይም አይታዘዙም ነበር።

መምህር ሆይ፡- ኢያሱ 24፡2 ተመልከት።

አብራም ኃጢአተኛ ነበርን? አዎ። እርሱም የአዳም ዘር ነበር። ነገር ግን ከእግዚአብሔር በተገለጠ መንገድ ወደ እግዚአብሔር መጣ። በእግዚአብሔርና በተሰፋ ቃሎቹ አመነ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር ለአብራም የነበረው ዕቅድ፥ አብራም ጣዖት አምላኪ ከነበሩ የአገሩ ሰዎች ጋር እየኖረ የተሟላ ሰው ለመሆን የማይችል ነበር። አገሩን ትቶ እግዚአብሔር እንደሚመራው ቃል ወደገባለት ምድር ሊጓዝ ያስፈልገው ነበር።

እግዚአብሔር፥ ለአብራም ምን ማድረግ እንዳለበት ሊነግረው መብቱ ነበር። እግዚአብሔር ከሁሉ ይበልጣል። እርሱ ከሁሉ የበላይ ነው።

ሐ. እግዚአብሔር ለአብራም የገባቸው ቃል ኪዳኖች።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።
እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

የኖኅ ልጆች የሆኑት ቀደምት አባቶቻችን ከእግዚአብሔርና ከእውነት እያወቁ ራቁ። ፈጣሪያቸው እግዚአብሔርን በማመን ፈንታ እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ነገሮች አመለኩ። የባቢሎንን ግንብ መገንባት ሲጀምሩ በእግዚአብሔር ላይ ዓመፁ።

ሰዎች በዚህ ሁሉ ኃጢአት ውስጥ ቢኖሩም እንኳ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ከሰይጣን ኃይልና ከዘላለማዊ ቅጣት ለመታደግ ያወጣውን ዕቅድ አልተወም። እግዚአብሔርን ዕቅዱን እንዳይፈጽም ሊያደርገው የሚችል ማንም ደግሞም ምንም የለም። የጀመረውን ሁሉ ወደ ፍጻሜ ያመጣዋል። የእግዚአብሔር ቀጣዩ ዕቅድ አብራምን መጥራት ነበር።

እግዚአብሔር በአብራም ጊዜ እንደነበረው ዛሬም ያው ነው። ዛሬም አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው። ሰዎችን ከዘላለማዊ ቅጣት የማዳን ዕቅዱን አልዘነጋም። እናንተ ሁላችሁ ከሰይጣን ኃይልና ከኃጢአቶቻችሁ እንድትድኑ ይፈልጋል። የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ አድምጡ፥ በዚህ ሁኔታ ልትድኑ የምትችሉበትን ብቸኛ መንገድ ትማራላችሁ።

አሁን እግዚአብሔር ለአብራም የገባቸውን ቃል ኪዳኖች እናነባለን። ዘፍጥረት 12፡2 አንብብ። አብራምና ሦራ ልጅ ያልወለዱ ቢሆንም እንኳ አብራም የታላቅ ሕዝብ አባት እንደሚሆን

እግዚአብሔር ተስፋ ሰጠው። እግዚአብሔር አብራምን እንደሚጠብቀውና እንደሚያበለጽገው ደግሞም እጅግ የከበረ ሰው አድርጉት በእርሱ በኩል ሌሎች ታላቅ ጥቅምና በረከት እንደሚቀበሉ ቃል ኪዳን ገባለት።

ዘፍጥረት 12:3 አንብብ። እግዚአብሔር አብራምን የሚባርኩትን እንደሚባርክ የሚረግሙትን እንደሚረግምም ቃል ገባለት።

እግዚአብሔር ለአብራም ከገባቸው ቃል ኪዳኖች ሁሉ ከፍተኛው በእርሱ አማካይነት የምድር ፍጥረታት ሁሉ እንደሚባረኩ የገባው ቃል ኪዳን ነው። ምክንያቱም ይህ ለአብራም የተገባ ቃል ኪዳን እግዚአብሔር ወደዚች ምድር እንደሚልከው በዔድን ገነት ተስፋ ስለሰጠው አዳኝ የሚናገር ነው። አሁን እግዚአብሔር ሰይጣንን ድል በመንሳት ዓለምን ከእርሱ ኃይል ነፃ የሚያወጣው ከአብራም ዘር የሚመጣ እንደሆነ ተናገረ።

የምድር አሕዛብ በሙሉ ነፃ አውጪ በሆነው ከአብራም ዘር በሚወጣው ይባረካሉ። ይህ እናንተን፥ የእኔን ሕዝቦችና በዓለም የሚገኙ ሌሎች ሕዝቦችን በሙሉ የሚጨምር ነው። እግዚአብሔር ይልከው ዘንድ ተስፋ የሰጠው አዳኝ በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ ሕዝቦች በሙሉ የተሰጠ ነው።

መምህር ሆይ፡- አዳኙ መጥቶ እንደሆነ ከጠየቁህ እንደመጣ አረጋግጥላቸው። ነገር ግን ኃጢአተኛ የመሆናቸው ጉዳይና ለዚህ መፍትሄ እንደሚያስፈልጋቸው በከፍተኛ ደረጃ በሚገባ ሳይረዱ የወንጌልን ታሪክ ለመናገር አትቸኩል። እግዚአብሔር ምን እንድትረዱ እንደሚፈልግ በትክክል ለማወቅ በጥንቃቄ አድምጡ በላቸው። ይህን ሲያደርጉ አዳኙ እንዴትና መቼ እንደሚመጣ ይረዳሉ።

መ. አብራም እግዚአብሔርን አመነና ታዘዘ።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

አብራም እግዚአብሔርን አምኖ ታዘዘን? አዎን

ዘፍጥረት 12:4፥ 5 አንብብ።

መምህር ሆይ፡-

ሀ. አብራም ወደ ከነዓን ሲጓዝ የሄደበትን መንገድ በካርታ ላይ አመልክታቸው።

ለ. አብራምና አብረውት የተጓዙት ሁሉ በድንኳን እንደኖሩ ግለጥላቸው። ድንኳን ስትል ምን ማለትህ እንደሆነ አዳማጮችህ መረዳታቸውን አረጋግጥ።

አብራም በጣም ሃብታም ሰው ስለነበር በርካታ አገልጋዮች ነበሩት። በርካታ የከብት መንጋ፥ በጐችና ፍየሎች ነበሩት። ስለዚህ የነበሩትን ሁሉ ይዞ ተጓዘ።

የአብራም አጐት ልጅ የነበረው ሎጥ ከአብራምና ከሦራ ጋር አብሮ ተጓዘ፤ ሎጥም ደግሞ በእግዚአብሔር አመነ፥ በተስፋ ቃሎቹም ተደገፈ።

አብራምና ሦራ ልጅ አልወለዱም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ከአብራም ዝርያዎች አንዱ የተስፋው አዳኝ በመሆን ሰይጣንን እንደሚያጠፋ ቃል ኪዳንን ሰጥቶ ነበር። አብራምም እግዚአብሔር አዳኝን እንደሚልክ የሚመጣውም ከእርሱ ዘር እንደሆነ አመነ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ጌታ አብራምን በታማኝነት ሊሰጠው ቃል ወደገባለት የከነዓን ምድር መራው።

ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር፥ ነፃ አውጪ እንደሚልክ የገባውን ቃል ኪዳንና ያቀደውን ዕቅድ ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ የባቢሎንን ግንብ በመገንባታቸው ሰረዘን? አልሰረዘም።
2. እግዚአብሔር፥ ይህ ነፃ አውጪ በዚህ ዓለም ተወልዶ የመምጣቱ ጉዳይ እርግጠኛ መሆኑን ለማሳየት ምን አደረገ? አብራምን በመምረጥና በመጥራት የነፃ አውጪው ቀደምት አባት እንደሚሆን ተናገረ።
3. እግዚአብሔር፥ አብራምን ምን እንዲያደርግ ነገረው? አገሩን ትቶ እግዚአብሔር ሊሰጠው ቃል ወደገባለት ምድር እንዲሄድ ነገረው።
4. አብራምና ሦራ እግዚአብሔር ይህን ተስፋ በሰጣቸው ጊዜ ስንት ልጆች ነበራቸው? ምንም ልጅ አልነበራቸውም።
5. እግዚአብሔር ለአብራም የሰጠውን ተስፋዎች ዘርዝር።

ሀ. የአብራም ዝርያዎች ታላቅ ሕዝብ ይሆናሉ።

ለ. እግዚአብሔር አብራምን ጠብቆና አበልጽጐ እጅግ የከበረ ሰው በማድረግ ሌሎች በእርሱ እንዲባረኩ ያደርጋል።

ሐ. እግዚአብሔር አብራምን የባረኩትን እንደሚባርክ የረገሙትን እንደሚረግም ተናገረ።

መ. እግዚአብሔር የዓለም ሕዝብ ሁሉ በእርሱ የሚባርክበት መንገድ እንዳለ ተስፋ ሰጠው።

6. ይህ የዓለም ሕዝብ ሁሉ የሚባረክበት የአብራም ዘር ማን ይሆናል? ነፃ አውጪው ይሆናል። እርሱም ሰይጣንን ድል በመንሳት ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር እንደገና አንድ የሚሆኑበትን መንገድ የሚያዘጋጅ ይሆናል።

7. እግዚአብሔር ለአብራም በቀጥታ ተናገረ። ዛሬ ግን እግዚአብሔር የሚናገረን እንዴት ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባሉት የተስፋ ቃሎቹ ይናገራል።

8. እግዚአብሔር አብራምን የጠራው ኃጢአተኛ ስላልነበረ ነውን? አይደለም። ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ናቸው።

9. አብራም እግዚአብሔርን ያመልክ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር የመጣው እንዴት ነበር? አቤል፥ ሴትና ኖኅ በመጡበት መንገድ ነበር። ይህም ሰዎች ወደ እግዚአብሔር እንዲመጡ እግዚአብሔር የደነገገው መንገድ ነበር።

10. እግዚአብሔር የተስፋ ቃል ኪዳኖችን በሰጠው ጊዜ አብራም ምን አደረገ? በእግዚአብሔር አመነ። አገሩን ትቶ እግዚአብሔር ወደመራው ምድር ሄደ።

ትምህርት 20

የትምህርት ክፍል፡- ዘፍጥረት 13፡5-17፤ 15፡5፥ 6፥ 12-16፥ 17፡1-5፥ 15-19

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር ለሦራ ቃል ኪዳን ገባላት፥ የአብራምን ተስፋም አደሰ።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. በአብራምና በሎጥ የከብት ጠባቂዎች መካከል የተፈጠረ ችግር (13፡5-7)።

ለ. አብራም ለተፈጠረው ችግር የሰጠው መፍትሄ (13፡8፥9)።

ሐ. የሎጥ ምርጫ (13፡10-13)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ሰው ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉ ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

መ. የእግዚአብሔር ቃል ኪዳኖች ለአብራም ታደሱ (እንደገና ተረጋገጡ) (13፡14-17፥ 15፡5፥ 6፥ 12-16፥ 17፡1-5)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉ ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ሠ. እግዚአብሔር ሦራ ወንድ ልጅ እንደምትወልድ ቃል ኪዳን ገባላት (17፡15-17)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

. ሰው እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት እምነት ያስፈልገዋል።

የትምህርት 19 ጥያቄዎችን ከልስ።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ።

ሀ. በአብራምና በሎጥ የከብት ጠባቂዎች መካከል የተፈጠረ ችግር።

ዘፍጥረት 13፡5-7 አንብብ። የአብራም አጐት ልጅ የሆነው ሎጥ እንደ አጐቱ ሃብታም ነበር። ሁለቱም እጅግ ብዙ በጐችና የከብት መንጋ ስለነበራቸው ብዙ ሳይቆዩ በከብት ጠባቂዎቻቸው መካከል ችግር ተፈጠረ።

ለ. አብራም ለተፈጠረው ችግር የሰጠው መፍትሄ

አብራም ለሎጥ ያቀረበው የመፍትሄ አሳብ ነበር። ዘፍጥረት 13፡8÷ 9 አንብብ።

ሐ. የሎጥ ምርጫ

ዘፍጥረት 13፡10÷ 11 አንብብ። ሎጥ÷ አካባቢውን ተመልክቶ ለእንስሳቱ ግጦሽ እጅግ ምቹ ይሆናል ብሎ ያሰበውን ለም ስፍራ መረጠ።

ሎጥ በእግዚአብሔር ያመነና የተደገፈ ሰው ቢሆንም እንኳ ለእርሱና ለቤተሰቡ ከሁሉ የላቀውና የተሻለውን ነገር አላደረገም ነበር። ይኸውም የወሰደው እርምጃ ቤተሰቦቹ ለእግዚአብሔር ያላቸውን እውቀትና እርሱን ደስ የሚያሰኙበትን ችሎታ እንዴት ሊጐዳ እንደሚችል አልተገነዘበም ነበር። ሎጥ ያሰበው እንዴት ብዙ ገንዘብን እንደሚያገኝ ብቻ ነበር። በዚህ ምርጫው ምክንያት አንዳንድ አስጨናቂ ነገሮች በሎጥ ላይ ደረሱ።

ቃየን የእግዚአብሔርን ምክር ቸል በማለቱ የወሰደውን የሞኝነት እርምጃ አስታውሱ። ዝርያዎቹ በሙሉ በጥፋት ውኃ ጠፉ። ሎጥ እግዚአብሔር ማድረግ የሚገባውን ከመጠየቅ ፈንታ ብልጽግናን መረጠ።

ስለምታደርጉት ምርጫ ተጠንቀቁ። የእግዚአብሔርን ቃል ላለመስማት ብትመርጡ እግዚአብሔር ለሰይጣንና ለመናፍስቱ ወዳዘጋጀው የእሳት ቅጣት ስፍራ በምትሄዱበት ጊዜ ለዘላለም ትጸጸታላችሁ። ወደዘላለም የቅጣት ስፍራ የምትሄዱ ከሆነ በዓለም ሁሉ ያለውን ሃብት ብታተርፉ ምን ይረባችኋል?

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

አብራም ወደ ድንጋያማና ብዙ ለም ወዳልሆነው ኮረብታማና ተራራማ ስፍራ ሄደ፤ ሎጥ በምርጫው ወደ ለም ምድር ሄደ።

ዘፍጥረት 13፡12፥ 13 አንብብ። በአገሪቱ ሜዳማ ክፍል ሰዶምና ገሞራ የሚባሉ ሁለት ከተሞች ነበሩ። የእነዚህ ከተሞች ነዋሪዎች ክፉዎችና በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ኃጢአተኞች ነበሩ። እግዚአብሔርን ለማወቅና እግዚአብሔር ምን እንዲያደርጉ እንደሚፈልግ ለመረዳት ግድ አልነበራቸውም። ስለ ራሳቸውና ስለሚያደርጓቸው ክፉ ነገሮች ብቻ ያስቡ ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

እነርሱ ስለ እግዚአብሔር የሚያስቡ ባይሆኑም እንኳ የሚያደርጉትን ነገሮች በሙሉ ተመለከተ። እርሱ ፈጣሪያቸው ነበር። ሰይጣንን በሚከተሉበት ጊዜ እንኳ የእነርሱ ባለመብትና ባለቤት እግዚአብሔር ነበር።

ሕዝቡ እግዚአብሔርን ለመስማት ፈቃደኛ ባለመሆን ቸል ብለው ቢተዉትም እንኳ ስለ እነርሱ ሁሉን ነገር ያውቅ ነበር። እግዚአብሔርን ትተው ሰይጣንን ለመከተል ሊወስኑ ይችላሉ። ቢሆንም ቅሉ የእግዚአብሔር መሆናቸው አይቀርም። አሳባቸውን ለውጠው ከእርሱ ጋር ይስማሙ ዘንድ በቂ ጊዜ እንደሰጣቸው ከአረጋገጠ በኋላ ግን በፍርድ ይቀጣቸዋል።

እነዚህ ክፉና ኃጢአተኛ ሰዎች ምን እንደሚያደርጉ እግዚአብሔር ይመለከታቸው ነበር።

ምን እያደረግን እንደሆነ ለማወቅ እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን ይመለከተናል።

መ. የእግዚአብሔር ቃል ኪዳኖች ለአብራም ታደሱ

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

መጽሐፍ ቅዱስ፥ ሎጥ አብራምን ትቶ ከሄደ በኋላ እግዚአብሔር ለአብራም ተገልጦ የከነዓንን ምድር በሙሉ እንደሚሰጠው እንደገና ቃል እንደገባለት ይነግረናል። ዘፍጥረት 13፡14-17 አንብብ።

መምህር ሆይ፡- እግዚአብሔር ለአብራም ሊሰጠው ቃል ኪዳን የገባለትን ምድር በካርታ ላይ አሳያቸው።

ከደመና በጠራና ኩልል ባለ ሌሊት በሰማይ የምታያቸው ከዋክብት ምን ያህል ናቸው? አንድ ቀን በምሽት እግዚአብሔር አብራምን ከድንኳኑ አውጥቶ ወደ ሰማይ እንዲመለከትና ከዋክብትን ሊቆጥራቸው ይችል እንደሆነ ይጠይቀዋል። ከዚያም አብራም ገና አንድ ልጅ ባልነበረው ወቅት ዘሩን እንደነዚያ የሰማይ ከዋክብት እንደሚያበዛው ይነግረዋል። ዘፍጥረት 15፡5፥ 6 አንብብ።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

አብራም፥ በእግዚአብሔር የተነገረው ነገር የማይቻል ቢመስልም እንኳ እግዚአብሔርን አመነ። አብራምና ሦራ ከተጋቡ ብዙ ዓመታት ስላለፋቸው አሁን አርጅተው ነበር። ልጅ ግን አልነበራቸውም።

አብራም እግዚአብሔር ልጅ እንደሚሰጠውና ነፃ የሚያወጣውን አዳኝ ከእርሱ ዘር እንደሚልክ ስላመነ እግዚአብሔር አብራምን ኃጢአት እንደሌለበት ሰው አድርጐ ተቀበለው። አብራም ኃጢአተኛ ነበር። ነገር ግን በእግዚአብሔር ስላመነ እግዚአብሔር እንደ ፍጹም ሰው ቆጥሮ ተቀበለው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ዘፍጥረት 15፡12-16 አንብብ። እግዚአብሔር የአብራም ዝርያዎች ገና ሳይወለዱ እንኳ ምን እንደሚደርስባቸው ያውቅ ነበር።

በሚቀጥለው ሳምንት፥ በሚቀጥለው ዓመትና ከአሥር ዓመት በኋላ ምን እንደሚሆን ታውቃለህን? ከአንድ ወይም ከሁለት መቶ ዓመታት በኋላ ምን እንደሚሆን ታውቃለህን? ከእግዚአብሔር በስተቀር ማንም አያውቅም። ስለ ወደ ፊት ጉዳያችሁ የሚያውቅ እርሱ ብቻ ነው።

መምህር ሆይ፡- ግብፅን አትጥቀስ። ስለ አብራም ዝርያዎች የሚናገረው ይህ ትንቢት ቦታውን አይገልጥም። በዘጸአት ወደተጻፈው ታሪክ ስንመጣ ወደዚህ ትንቢት ተመልሰን እንመለከታለን።

ዘፍጥረት 17፡1-5 አንብብ። አብራም የ99 ዓመት ሰው ሲሆን እግዚአብሔር እንደገና ተናገረው። ይህን ያህል ዕድሜ የሚኖሩ ሰዎች በአሁን ጊዜ ብዙ አይደሉም። በእነዚያ ዘመናት ግን ሰዎች ለረጅም ጊዜ ይኖሩ ነበር።

እግዚአብሔር የአብራምን ስም ወደ አብርሃም የለወጠው የብዙ ሕዝብ አባት እንደሚሆን ቃል ስለገባለት ነበር። አብርሃም ማለት «የብዙ አሕዛብ አባት» ማለት ነው።

ሠ. እግዚአብሔር ሦራ ወንድ ልጅ እንደምትወልድ ቃል ኪዳን ገባላት።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ዘፍጥረት 17፡15-16 አንብብ። እግዚአብሔር የሦራን ስም ወደ ሣራ ቀየረው። ምክንያቱም ከዚህ በፊት ልጅ ያልወለደች ቢሆንም እንኳ አሁን ወንድ ልጅ እንደምትወልድ እግዚአብሔር ቃል ስለገባላት ነው። የአዲሱ ስሟ ትርጉም «የብዙ አሕዛብ እናት» ማለት ነበር። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዝርያዎች እናት ትሆናለች።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

ሰው እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 17፡17 አንብብ። አብርሃም የ100 ዓመት ሣራ ደግሞ የ90 ዓመት ሰዎች ስለነበሩ ልጅ መውለድ የሚቻላቸው አይመስልም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ኃያል ነው።

እግዚአብሔር የመጀመሪያዎቹን ሰዎች አዳምና ሔዋንን የፈጠራቸው ከምድር አፈር ነበር። የሕይወትን እስትንፋስ እፍ ብሎባቸው ሕይወትን ሰጣቸው። ሕይወት ሁሉ የሚመጣው ከእርሱ ዘንድ ነው። ፍጥረታትን ሁሉ ማለትም ፀሐይ፥ ጨረቃ፥ ከዋክብት ምድርንና በውስጧ ያሉት ነገሮች በሙሉ በእርሱ ቁጥጥር ሥር ናቸው። ለእናንተና ለልጆቻችሁ ሕይወትን የሰጠ ኃያል አምላክ እርሱ ነው። አብርሃምና ሣራ ልጅ ለማግኘት የሚችሉበት ዕድሜያቸው ቢያልፍም እንኳ እግዚአብሔር ልጅ ሊሰጣቸው ይችል ነበር።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት እምነት ሊኖረው ያስፈልጋል።

አብርሃም እግዚአብሔርን ባለማመን ሳይሆን ለሰው የማይቻለውን ይህን አስደናቂ ነገር እግዚአብሔር ሊያደርግ ስለሆነ በመደነቅ ሳቀ። አብርሃም እግዚአብሔር የሚፈልገውን ማንኛውንም ነገር ለማድረግ እንደሚችል ያውቅ ነበር። ስለዚህ በእግዚአብሔር ተደግፎ እምነቱን ገለጠ።

ጥያቄዎች

1. ሎጥ ከአብራም ተለይቶ ከሰዶምና ገሞራ አጠገብ ወዳለው ለም ሜዳማ መሬት የሄደው ለምን ነበር?

ሀ. አብራምና ሎጥ እጅግ ብዙ የእንስሳት መንጋ ስለነበሯቸው በአንድነት ያሰማሯቸው ዘንድ በቂ ሣር የሚገኝበት መሬት አልነበረም።

ለ. ሎጥ ወደመረጠው ስፍራ የሄደው በቂ ውኃና ብዙ ሣር ያለው በዚያ ስለነበር ነው።

2. ሰዎች በሚሞቱበት ጊዜ ወደ ዘላለም ቅጣት የሚሄዱ ከሆነ የዚህ ዓለም ሃብት ምን ያደርግላቸዋል? ምንም አይፈይድላቸውም።

3. የሰዶምና የገሞራ ሰዎች የሚያደርጓቸውን ክፉ ነገሮች ማን ተመለከተ? እግዚአብሔር።

4. ከአስተሳሰባችሁ፥ ከቃላችሁና ከተግባራችሁ ከእግዚአብሔር የሚደበቅ ነገር አለን? የለም።

5. አብራም ሎጥ ትቶት ከሄደ በኋላ እግዚአብሔር ምን ተናገረው?

ሀ. የከነዓንን ምድር በሙሉ እንደሚሰጠው ነገረው።

ለ. ዘሩ ከሰማይ ከዋክብት ሁሉ እንደሚልቅ ቃል ገባለት።

ሐ. የአብራም ዘሮች በሙሉ ወደ ሌላ አገር ለመኖር እንደሚሄዱ፥ በዚያም ለ400 ዓመታት እንደሚሠቃዩ፥ ከዚያን ጊዜ በኋላ ግን እግዚአብሔር ለአብራም ወደ ሰጠው ወደ ከነዓን ምድር እንደሚመለሱ ተናገረ።

6. እግዚአብሔር ለአብራምና ለሦራ የሰጣቸው አዲስ ስሞች የትኞቹ ናቸው?

. አብርሃምና ሣራ ሲሆኑ ምክንያቱም የብዙ ዝርያዎች ወላጆች በመሆናቸው ነው።

7. አብርሃምና ሣራ እግዚአብሔር ተአምራትን ካላደረገ በስተቀር ልጅ ሊኖራቸው ያልቻለው ለምን ነበር?

ሀ. ሣራ መካን ነበረች።

ለ. ሁለቱም አርጅተው ነበር። አብርሃም 100፥ ሣራ ደግሞ 90 ዓመት ነበሩ።

8. የመጀመሪያዎቹን ሰዎች (አዳምና ሔዋንን) የፈጠረና ለሰዎች ሁሉ ሕይወትን የሰጠ ማን ነው? እግዚአብሔር።

9. እግዚአብሔር ሊያደርግ የሚፈልገውና የማይችለው ነገር አለን? የለም። እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ማድረግ ይችላል።

10. የእያንዳንዱን ሰው የወደፊት ጉዳይ ማን ያውቃል? እግዚአብሔር ብቻ።

ትምህርት 21

የትምህርት ክፍል፡- ዘፍጥረት 18፡20፥ 21፥ 19፡1-17፥ 24-26

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር ሰዶምና ገሞራን ደመሰሰ።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. እግዚአብሔር በሰዶምና ገሞራ ላይ የነበረው ዝንባሌ (18፡20፥ 21)

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

ለ. የእግዚአብሔር መላእክት ወደ ሰዶም መጡ (19፡1-3)።

ሐ. የሰዶማውያን ኃጢአተኛነት (19፡4-9)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

መ. ሎጥ ሚስቱና ሴት ልጆቹ ከሰዶም ጥፋት እንዲወጡ ተደረገ (19፡10-17)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ሠ. እግዚአብሔር ሰዶምና ገሞራን ደመሰሰ (19፡24፥ 25)።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ረ. የሎጥ ሚስት ወደኋላዋ ተመለከተች (19:26)።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

የትምህርት 20 ጥያቄዎችን ከልስ።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ።

ሀ. እግዚአብሔር በሰዶምና በገሞራ ላይ የነበረው ዝንባሌ።

ዋና አሳብ:- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ዘፍጥረት 18:20-21 አንብብ። ወደ እነዚህ ሁለት ኃጢአተኛ ከተሞች አካባቢ ለመሄድ የፈለገው ማን እንደነበር የሚያስታውስ አለን? አዎን የአብርሃም የአጐት ልጅ ሎጥ ነበር።

በዚያን ጊዜ በዓለም ላይ ብዙ ሰዎች የነበሩ ቢሆንም እግዚአብሔር በሰዶምና ገሞራ የነበሩ ሰዎችን ተመለከተ። በድፍረት የተናገሩትን እያንዳንዱን ቃል አደመጠ።

እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ይፈልጋል። ዛሬ በብዙ መቶ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በዓለም ላይ ቢኖሩም እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው ያውቃል፥ ደግሞም ይፈልጋል። ለእግዚአብሔር፥ እያንዳንዱ ሰው ደግሞም ማንኛውም ነገር የከበረ ነው። በዓለም ላይ እጅግ ብዙ የሆኑ እንስሳት ቢኖሩም እንኳ እግዚአብሔር እያንዳንዳቸው በሚሞቱበት ጊዜ ያውቃል። እኛ ደግሞ ለእግዚአብሔር ከእንስሳት ይልቅ የከበርን ነን።

እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው መፈለግ ብቻ ሳይሆን ቃሉን ለማመን ባልፈቀዱ ሰዎች በእያንዳንዳቸው ላይ ይፈርዳል።

እግዚአብሔር፥ በእናንተ ሕዝብ ላይ ትኩረት እንደሌለው ታስቡ ይሆናል፤ ምክንያቱም እናንተ ምናልባት በቁጥር ጥቂት ስለሆናችሁ ወይም እያንዳንዳችሁ በግል ስለምታደርጉት ነገር ግድ የሌለው ይመስላችሁ ይሆናል። እንደዚያ ግን አይደለም። እግዚአብሔር በእናንተ ላይ ደግሞ ይፈርዳል።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ሎጥ ወደ ሰዶምና ገሞራ ከመምጣቱ በፊት እንኳ እግዚአብሔር፥ በእነዚህ ኃጢአተኛ ከተሞች ላይ ለረጅም ጊዜ ሲያዝን ቆይቷል። እግዚአብሔር ለረጅም ጊዜ ቢታገሣቸውም እንኳ ከዚህ በኋላ ኃጢአታቸውን ሊታገሥ እንደማይችል ወሰነ። የእግዚአብሔርን ፍርድ ለማምለጥ አይችሉም ነበር።

እግዚአብሔር፥ በኖኅ ዘመን የነበሩ ሰዎች ንስሐ እንዲገቡ ምን ያህል ረጅም ጊዜ እንደታገሣቸው ታስታውሳላችሁን? ነገር ግን እግዚአብሔር እስካሁን የሰጠኋቸው ጊዜ በቂ ነበር ብሎ ያመነበት ወቅት መጣ። ከእግዚአብሔር ጋር ለመስማማት ፈቃደኛ ካልሆኑት ሕዝቦች አንድም ሰው ከቅጣቱ አላመለጠም። እርሱ የሁሉ የበላይ ነው። ምን ማድረግ እንዳለበት ማንንም አያማክርም። ኃጢአተኞችን ለመቅጣት ሲወስን ማንም ሊገታው አይችልም።

እግዚአብሔር፥ ኃጢአትን የሚቀጣው ወዲያውኑ ስላይደለ ኃጢአታችንን እንደ ቀልድ የሚያልፍ ሊመስለን ይችላል። ነገር ግን በመጨረሻ ኃጢአትን በሙሉ ይቀጣል። ሁሉን ቻይ ፈጣሪ ከሆነው ከእግዚአብሔር ሊያመልጥ የሚችል የለም። የእያንዳንዱን ሰው ኃጢአት ይመለከታል። ይቀጣልም።

ለ. የእግዚአብሔር መላእክት ወደ ሰዶም መጡ

ዘፍጥረት 19፡1-3 አንብብ። ሎጥ ቀደም ብሎ የሚኖረው በከተማይቱ አጠገብ ነበር። አሁን ግን ወደ ከተማይቱ ውስጥ በመግባት ከእነዚህ ክፉ ኃጢአተኛ ሰዎች ጋር መኖር ጀምሮ ነበር። አሁን ወደ ከተማይቱ የመጡት መላእክት፥ ሰይጣንን ያልተከተሉ መልካም የእግዚአብሔር መላእክት ነበሩ። እግዚአብሔር ወደ ሰዶም የላካቸው ለልዩ ጉዳይ ነበር።

ሐ. የሰዶማውያን ኃጢአተኛነት።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 19፡4-9 አንብብ

መምህር ሆይ፡- በሰዶምና ገሞራ ሕዝብ ኃጢአትና ይህን ትምህርት በምታስተምራቸው ሰዎች መካከል በሚገኝ ኃጢአት ላይ አተኩር። እንደ ሰዶም ሰዎች ካልሆኑ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ እንደማይፈርድና እንደማይቀጣቸው ያስቡ ይሆናል።

መ. ሎጥ፥ ሚስቱና ሴት ልጆቹ ከሰዶም ጥፋት ሸሽተው እንዲወጡ ተደረገ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 19፡10-17 አንብብ። እግዚአብሔር፥ ሎጥን ሚስቱንና ሴቶች ልጆቹን ያዳነው መልካም ስለነበሩ አይደለም። ሎጥ እንደ ሰዶም ሰዎች የከፋ ኃጢአት ባያደርግም እንኳ እርሱም የተወለደው ኃጢአተኛ ሆኖ ነበር። ሆኖም ግን ሎጥ ኃጢአተኛ እንደሆነ ከእግዚአብሔር ጋር በመስማማት በእግዚአብሔር ምሕረት ተደገፈ።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል። ሎጥ፥ ለአዳምና ለአጐቱ ለአብርሃም ስለሚመጣው አዳኝ የተሰጠውን ተስፋ አመነ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር፥ አፍቃሪ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው። ክፉና ኃጢአተኛ የነበሩት ከተማዎች ከመደምሰሳቸው በፊት የእግዚአብሔር መላእክት ሎጥን ከከተማዎቹ አወጡት።

እግዚአብሔር፥ ከእርሱ ጋር የሚስማሙትንና በእርሱ ላይ የሚደገፉትን ሁልጊዜ ያድናቸዋል። አቤል ከእግዚአብሔር ጋር ተስማማ፥ በእርሱም ተደገፈ፥ እግዚአብሔርም ተቀበለው። ኖኅ ከእግዚአብሔር ጋር ተስማማ፥ በእርሱም ተደገፈ እግዚአብሔርም ከጥፋት ውኃ አዳነው። ሎጥ ከእግዚአብሔር ጋር ተስማማ፥ በእርሱም ተደገፈ፥ ሰዶም ከመደምሰሷ በፊት ከከተማዪቱ በማውጣት እግዚአብሔር ታደገው።

ሠ. እግዚአብሔር ሰዶምና ገሞራን ደመሰሰ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ጻድቅና ቅዱስ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ዘፍጥረት 19፡24-25 አንብብ። ሎጥ ከከተማዪቱ ከወጣ በኋላ እግዚአብሔር በእነዚህ ክፉ ሰዎች ላይ ያደረገው ይህን ነበር። እግዚአብሔር ኃጢአትን ይጠላል። በኖኅ ዘመን ዓለምን በውኃ አጠፋ። አሁን ደግሞ እነዚህን ክፉ ሰዎች በእሳት አጠፋቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እግዚአብሔር አሁንም ያው ነው አልተለወጠም። አሁንም ቢሆን ኃጢአትን ይመለከታል፥ ይጠላልም። ከፍርዱ ሊያመልጥ የሚችል ማንም የለም።

ረ. የሎጥ ሚስት ወደ ኋላዋ ተመለከተች።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ዘፍጥረት 19፡26 አንብብ። መላእክት፥ ሎጥን፥ ሚስቱንና ሴት ልጆቹን ይዘው ከከተማዋ ባወጡአቸው ጊዜ ወደ ተራራዎቹ እንዲሮጡ እንጂ ወደ ኋላ እንዳይመለከቱ ነግረዋቸው ነበር። የሎጥ ሚስት ግን ይህን ትእዛዝ ሳታከብር ቀረች።

እግዚአብሔር በሎጥ ሚስት ልብ ውስጥ የነበረውን ነገር ያውቅ ነበር። የሎጥ ሚስት እንደ ቃየን ነች። በእግዚአብሔር አልታመነችም። ለምን ወደ ኋላ እንደተመለከተች እግዚአብሔር ያውቅ ነበር። ወደ ኋላ የተመለከተችው የሰዶምን ሰዎች ኃጢአታዊ አኗኗር ስለወደደች ነበር። ለመልቀቅ አልፈለገችም ነበር። የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ ቸል በማለቷ ተሞኝታለች። ምክንያቱም ወደ ኋላ በተመለከተች ጊዜ የጨው ዐምድ ሆና ቀረች።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

በአንድ ሰው ላይ በተቆጣን ጊዜ በንዴት እንዝትበት ይሆናል፥ ነገር ግን ከጊዜ በኋላ እንረሳዋለን። እግዚአብሔር ግን፤ እቀጣለሁ ብሎ ያሰበውን የሚረሳ አይደለም። ሁልጊዜ ያው ነው። በምድር ላይ በእርሱ የተደገፉ ሰዎችን እንደሚባርክ የማይታዘዙትን እንደሚቀጣ ለአብርሃም የገባውን ቃል ኪዳኖች ያስታውሳል፥ ይጠብቃልም። እግዚአብሔር ኃጢአት በሙላት እስካልተከፈለ ድረስ ሊረሳ አይችልም። የኃጢአት ቅጣት ሞት ማለትም ከእግዚአብሔር ለዘላለም ተለይቶ በእሳት ባሕር መጣል ነው።

ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር፥ ስለ ሰዶምና ገሞራ ኃጢአት ያውቅ ነበርን? አዎ።
2. እግዚአብሔር፥ ሰዎች ቸል በሚሉትና በሚረሱት ጊዜ ሳይቀጣቸው ዝም ብሎ ያልፋቸዋልን? በጭራሽ! እርሱ ሰዎችን ሁሉ ይመለከታል። በእያንዳንዱ ሰው ላይ ይፈርዳል።

3. እግዚአብሔር የሰዶምና የገሞራን ኃጢአት ወዲያውኑ ያልቀጣው ለምንድን ነው? እግዚአብሔር አሁንም በኃጢአተኞች ላይ ወዲያውኑ የማይፈርደው ለምንድን ነው? እግዚአብሔር፥ አፍቃሪ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ፥ ታጋሽም ነው። ሰዎች አስተሳሰባቸውን ቀይረው በእርሱ ይደገፉ ዘንድ ጊዜ ይሰጣቸዋል።

4. እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን የሚያስፈራራ እንጂ ጨርሶ የማይቀጣ ነውን? አይደለም። እግዚአብሔር ታጋሽ ቢሆንም እንኳ በመጨረሻ ኃጢአተኞችን ይቀጣል።

5. እግዚአብሔር ሰዎች ለንስሐ ጊዜ (አእምሮአቸውን ለመለወጥ) በቂ ጊዜ አግኝተዋል። አሁን ይበቃል ብሎ ከወሰነና ሊቀጣቸው ከተነሣ ሊያግደው የሚችል አለን? በጭራሽ የለም። እግዚአብሔር የሁሉም የበላይ ነው። ማንም ከእርሱ የላቀ የለም።

6. እግዚአብሔር ሎጥን፥ ሚስቱንና ቤተሰቡን ለመታደግ መላእክት የላከው ለምን ነበር? ሎጥ፥ ኃጢአተኛ መሆኑን በማመን ከእግዚአብሔር ጋር ስለተስማማና እግዚአብሔር ነፃ አውጪ እንደሚልክ የሰጠውን የተስፋ ቃል ስላመነ ነበር።

7. እግዚአብሔር የሎጥን ሚስት ወደ ጨው አምድ የቀየራት ለምን ነበር? እግዚአብሔር በእርሱ ፍርድ ወደሚቃጠሉት ከተሞች አትመልከቱ ብሎ የሰጠውን ትእዛዝ ስላጣሰች ነው።